# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# መንግሥት

# የማስፈፀም አቅም ግንባኖ ስትራተጅና ፐሮግራሞች

**በማስኖወቂያ ሚኒስቴር**
**የፕሬስና ኦዲዮቪዥዋል መምሪያ**

*የካቲት 1994 ዓ.ም.*
*አዲስ አበባ*

## ማ ው ጫ

# የኢትዮጵያ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራተጅና ፕሮግራሞች ክፍል አንድ

ገፅ


የማስፈፀም አቅም ግንባታ መርሆዎችና ስትራተጅ ------------1

1. የማስፈፀም አቅም ምንነት ----------------------------------------1
2. የማስፈፀም አቅምና ልማት -----------------------------------7
3. የማስፈፀም አቅም ግንባታና የልማት ስትራተጅዎቻችን ትስስር ---------------------------------- 14
4. የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራተጅያችን ---------------17
   - 4.1. የስትራተጅው ግቦች ------------------------------------17
   - 4.2. ሁሉን አቀፍ የአቅም ግንባታ ስራ መስራት -------18
   - 4.3. የማስፈፀም አቅም ግንባታ አቅሞችን በመገንባት ላይ ያተኮሩ ስትራተጅ ---------------21
   - 4.4. የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራዎችን በአግባቡ ማስተሳሰር -----------------------------------23
   - 4.5. የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራዎችን ከተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር ማጣጣም -------------27

## ክፍል ሁለት
## ትምህርትና ስልጠና


1. መግቢያ --------------------------------------------------------30
2. የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ----------------------------------33
   - 2.1. የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ስርጭት ---------------33
   - 2.2. የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ጥራት -----------------35
   - 2.3. የአንደኛ ደረጃ የመማሪያ ቋንቋ --------------------62
   - 2.4. የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ፋይናንስና አስተዳደር ስርአት ----------------------------------------------70
3. የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ችግሮችን ለመፍታት ልንከተለው የሚገባን አቅጣጫ ------------------------------83
   - 3.1. በአስተማሪዎች ላይ ልዩ ትኩረት ማድረግ ------84
   - 3.2. ለትምህርት ፋይናንስ ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ መሻት -------------------------------94
   - 3.3. የትምህርት አስተዳደር ስርአት ማሻሻል -----------101
4. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ------------------------------107
   - 4.1. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ስርጭትና አወቃቀር --108
   - 4.2. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጥራት -----------------120
   - 4.3. የሁለተኛ ደረጃ ፋይናንስና አስተዳደር ----------123
5. የቴክኒክና ሙያ ስልጠና -------------------------------------125
   - 5.1. የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ስርጭትና አወቃቀር ---125
   - 5.2. የሙያና ቴክኒክ ስልጠና ጥራት ----------------------136
   - 5.3. የሙያና ቴክኒክ ስልጠናና የልማት እንቅስቃሴያችን ----------------------------------------150
   - 5.4. የሙያና ቴክኒክ ስልጠና ፋይናንስና አስተዳደር ---155





6. ከፍተኛ ትምህርት ---------------------------------------------165
   - 6.1. የከፍተኛ ትምህርት ስርጭትና አወቃቀር -------165
   - 6.2 የከፍተኛ ትምህርት ጥራት -------------------------- 173
   - 6.3. የከፍተኛ ትምህርት ፋይናንስና አስተዳደር --------183


## ክፍል ሶስት
## የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራምና ሌሎች የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች


1. መግቢያ ------------------------------------------------------------192
2. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም መሰረታዊ አላማዎች -------------------------------------------196
   - 2.1. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራምና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ አላማችን ----------------------------198
   - 2.2. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራምና የልማት አላማችን ------------------------------------216
3. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ይዘት -----------------222
   - 3.1. የመንግስት ወጭ አስተዳደር ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራም --------------------------------------222
   - 3.2. የሰው ሃይል አስተዳደር ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራም -----------------------------------------227
   - 3.3. የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራም ----229
   - 3.4. የከፍተኛ አመራር ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራም ---------233
   - 3.5. [illegible] ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራም ----------------238

**4. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ቀጣይ ስራዎቻችን --243**

**4.1. ሲቪል ሰርቪሱን ማሻሻያ መሰረታዊ ፖለቲካዊ ስራ መሆኑን መገንዘብ ------------------243**

**4.2. የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ስራ እንዲሰራ ማድረግ -----------------------------------249**

**4.3. ፕሮግራሙን አሳታፊ በሆነ መንገድ መፈፀም -------252**

**4.4. ፕሮግራሙ ረጅም ጊዜ የሚጠይቅ ፕሮግራም መሆኑን የተገነዘበ አፈፃፀም እንዲኖር ማድረግ፣-----255**

**5. የመንግስት ግብር አሰባሰብ ማሻሻያ ፕሮግራም ----------259**

**5.1. የመንግስት ግብር አሰባሰብ ማሻሻያ ፕሮግራም አላማዎች -----------------------------------------------------**

**259**

**5.2. የመንግስት ግብር አሰባሰብና የንብረትና ገቢ ማሳወቅ ስርአት -----------------------------------265**

**5.3. የመንግስት ግብር አሰባሰብ ማሻሻያ ፕሮግራም ይዘት ----------------------------------272**

**5.4. በመንግስት ግብር አሰባሰብማሻሻያ ፕሮግራም አፈፃፀም ላይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች -------------276**

**6. የፍትህ አስተዳደር ስርአት የማሻሻያ ፕሮግራም ----------281**

**6.1. የፍትህ አስተዳደር ስርአት ማሻሻያ ፕሮግራም አላማዎች ------------------------------281**

**6.2. የፍትህ አስተዳደር ስርአት ማሻሻያ ፕሮግራም ይዘት ----------------------------------284**

**7. ማጠቃለያ ------------------------------------------------293**



# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራተጅና ፕሮግራሞች

መግቢያ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት አገራችን የምትገኝበትን የፖለቲካ፣የኢኮኖሚና የማኀበራዊ ሁኔኖ ለመቀየር የሚያስችሉ ፖሊሲ-ችን ቀይሶ በተግባር ላይ ለማዋል በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ ኢትዮጵያን በመሳሰሉ በዕድገት ወደኋላ በቀሩና የዲሞክራሲ ስርዓትን ለመገንባት ዕድሉ ተነፍጓቸው በቆዩ አገሮች ለዕድገትና ለብልፅግናነ ለዲሞክራሲና ለዳበረ መንፈሳዊ ሕይወት መብቃት የሚቻለው ከምንም ነገር በፊት መንግሥት የጠራ ፖሊሲ መንደፍ ሲችልና በሱም ሲመራ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ ከዚህ በመነሳት የኤፌዴሪ መንግሥት ትክክለኛ ፖሊሲ-ች ለመንደፍ መቻሉ አገራችን ከድህነት፣ ከኋላቀርነትና ከፀረ-ዲሞክራሲ ችግሮች ለመላቀቅ የምትችልበትን ወሳኝ መሳሪያ ኖንድንጨብጥ ያስችለናል፡፡

መንግሥት ጥራት ያለው ፖሊሲ ለመንደፍና በሱም ለመመራት መቻሉ የመጀመሪያው ጉዳይ ቢሆንም የተሳካ ውጤት ሊገኝ የሚችለው ደግሞ ፖሊሲውን በሚፈለገው ፍጥነትና የጥራት ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ ስንችል ነው፡፡ በገጠርና ግብርና ልማት፣ በኢንዱስትሪና ከተማ ልማት፣ በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባኖና በዓለም ዓቀፍ ግንኙነት ላይ የምንመራባቸውን ፖሊሲ-ች ተግባራዊ ለማድረግ መቻል የአገራችንን ኖድገት ለማፋጠንና በጽኑ መሠረት ላይ ለመገንባት ያስችለናል፡፡ መንግሥት የነደፋቸውን ፖሊሲ-ች በተግባር ላይ በማዋል የኢኮኖሚና ማኀበራዊ ልማትን በማፋጠን የህዝባችንን ተጠቃሚነት ያረጋግጣል፡፡ ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ኖንድንበቃ በማስቻል የሕዝባችን ቁሳዊ ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ህይወቱ የተስተካከለ ኖንዲሆን ያስችለናል፡፡ ስለሆነም ትክክለኛ ፖሊሲ-ች መንደፍና በነሱ ለመመራት የመቻላችን ጉዳይ ፖሊሲ-ቹን በጥብቅ ተግባራዊ በማድረግ ሲደገፍ ነው የአገራችን ብሔራዊ ጥቅም ማዕከል የሆነው የህዝባችን ተጠቃሚነት ኖውን ሊሆን የሚችለው፡፡

የኢፌዲሪ መንግሥት የሚመራባቸውን ትክክለኛ ፖሊሲ-ች ተግባራዊ የማድረግ ጉዳይ ግን በፍላጐት ላይ ብቻ ሊመሰረት የሚችል አይደለም፡፡

ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችል አቅም ላይ በማተማመን ነው የተነደፋት ፖሊሲ-ቹ በሥራ ላይ ሊውሉ የሚችሉት፡፡ አገራችን የምትገኝበት ሁኔዋ አኳያ ሲመዘን ዝቅተኛ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ቀደምት መንግሥዋት ትኩረዋቸው በልማትና በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባዋ ላይ ስላልነበር ትክክለኛ ፖሊሲ ለመንደፍም ሆነ ይህንኑ በተግባር ላይ ለማዋል የሚያስችል አቅም ፈጥረው አልቆዩም፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ ያለው ክፍተት ዋጅግ በጣም ሰፊ ነው፡፡ መንግሥት ይህን በመገንዘብ የልማትና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባዋ ፖሊሲና ስትራተጅ-ቻችን ተግባራዊ ለማድረግ የማስፈፀም አቅምን መገንባት ወሳኝ ነው ይላል፡፡

አንዳንድ አገሮች ብዙም የተፈጥሮ ፀጋ የለውም በሚባል መሬት ላይ ተቀምጠው አገራቸውን ወደምድራዊ ገነት ለመቀየር የመቻላቸው ምስጢር ያለው የማስፈፀም አቅማቸውን ለመገንባት በመቻላቸው ላይ ነው፡፡ ዋኛ ሰፊ የተፈጥሮ ፀጋና፣ በጥረቱ አሩን ለማልማትና ለመጠቀም የሚችል ብዙ ሕዝብ ዋያለን ለረሃብና ለጉስቁልና የተዳረግነው ያለንን ፀጋ ወደ ተጨባጭ ሃብት ለመቀየር የሚያስችል የማስፈፀም አቅም  ስላላዳበርን ነው፡፡

ከዚህ በመነሳት መንግሥት የማስፈፀም አቅም ግንባዋን የልማት ፖሊሲ-ቻችን ሁሉ ማስፈፀሚያ ቁልፍ አድርጎ መውሰዱ ተገቢና ትክክለኛ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ግንዛቤ የመንግሥት ብቻ በመሆን ሳይወሰን ከአገራችን ልማትና ዕድገት፣ ዋንዲሁም ከዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባዋ ተጠቃሚ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ሁሉ የሚጋሩትና በጥብቅ የሚያምኑበት ሊሆን ይገባዋል፡፡ ኅብረተሰቡ ያላመነበትና ተግባራዊ ሊያደርገው ያልተዘጋጀበት የማስፈፀም አቅም ግንባዋ ፖሊሲ ምንም ያህል ትክክለኛ ይዘት ቢዋረው በሚፈለገው ፍጥነትና የጥራት ደረጃ በተግባር ሊተረጎም አይችልም፡፡ በመሆኑም በዚህ ሰነድ ላይ በቀረቡት የኢፌዲሪ መንግሥት የማስፈፀም አቅም ግንባዋ ስትራተጅና ፕሮግራሞች ላይ  በመወያየት አንድ ዓይነት የጋራ ግንዛቤና ብሔራዊ መግባባት ላይ መድረስ ያስፈልገናል፡፡

የማስዋወቂያ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ከዚህ መሠረዋዊ ግንዛቤና ኅብረተሰቡ የመንግሥትን ልዩ ልዩ ፖሊሲ-ች ዋንዲያውቃቸውና የግልፅነት ባህል ዋንዲዳብር ከማድረግ ተልዕኮ በመነሳት ይህን ሰነድ አሳትሞ ለተጠቃሚው ኅብረተሰብ አቅርቧል፡፡



# ክፍል አንድ

# የማስፈፀም አቅም ግንባታ መርሆዎችና ስትራተጅ

### 1. የማስፈፀም አቅም ምንነት፣

የማስፈፀም አቅም ሲባል አንድ ህብረተሰብ ተፈጥሮንና ማህበራዊ ግንኙነቱን ለህብረተሰቡ አባላት በይበልጥ በሚጠቅምና በሚመች አኳኋን ለመቀየር የሚያስችለው አቅም ማለት ነው፡፡ የማስፈፀም አቅም የተፈጥሮ ሃብትን በመጠቀም፣ የተለያዩ የስራ ማቃለያ፣ ማቀላጠፊያና ጥራት ማሻሻያ መሳሪያዎችን በመስራት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችል ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስፈልገው አቅም ነው፡፡ ማህበራዊ ግንኙነቱ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ አጠቃቀሙን ለማሻሻልና ፍትሃዊ ለማድረግ የሚያስችል እንዲሆን ለማድረግ የሚያስፈልጉ ስራዎችን ለመስራት የሚያስፈልገው አቅም ነው፡፡ የማስፈፀም አቅም ማለት የመሳሪያዎች ጋጋታ ማለት አይደለም፡፡ እነዚህ መሳሪያዎች ስራን ለማቃለል፣ ለማቀላጠፍ ወይም ጥራቱን ለማሻሻል እጅግ ተፈላጊ ቢሆኑም በራሳቸው ግኡዝ ነገሮች እንጂ የማስፈፀም አቅሞች አይደሉም፡፡ የሚሰሩትና የሚፈጠሩት በአንድ በተወሰነ የማስፈፀም አቅም ነው፡፡ በአግባቡ ጥቅም ላይ የሚውሉትም በነሱ ለመጠቀም የሚችል የማስፈፀም አቅም ሲኖር ነው፡፡

የማስፈፀም አቅም የሚባለው ሶስት ነገሮችን አጣምሮ የያዘ ነገር ነው:: የማስፈፀም አቅም የሚባለው የሰው ሃይል፣ አሰራርና አደረጃጀትን ያጣመረ አቅም ነው:: ከዝቅተኛው መሳሪያ ጀምሮ እስከተራቀቀው ድረስ ያሉት ቁሳቁሶች ሰው በአግባቡ ተደራጅቶና የተሻለ አሰራር ተጠቅሞ የፈጠራቸውና የፈለሰፋቸው ነገሮች ናቸው:: በሶስቱ የማስፈፀም አቅም ገፅታዎች በመጠቀም በተሻለ ሁኔታ የሚጠቀምባቸው ናቸው:: ይህም በመሆኑ የስራ መሳሪያዎች በራሳቸው የማስፈፀም አቅም ተደርገው አይወሰዱም:: የማስፈፀም አቅም ተደርጎ የሚወሰደው የሰዎች፣ የአደረጃጀትና የተሻሻለ አሰራር ጥምረት ነው::

የማስፈፀም አቅም መገንባት ማለት የመሳሪያ ጋጋታ ማብዛት ማለት ተደርጎ የሚወስድበት ሁኔታ ያጋጥማል:: በዚህ ጉዳይ ላይ የጠራ ትርጉም ይዞ መነሳት በጣም አስፈላጊ ነው:: በአለም አሉ የሚባሉ ምርጥ መሳሪያዎች ቢሰበሰቡ፣ በነዚህ በአግባቡ ለመጠቀም የሚችል ብቃት ያለው የሰው ሃይል፣ የጠራ አደረጃጀትና አሰራር ከሌለ በስተቀር ፋይዳ ቢስ የመሳሪያ ክምችት ከመሆን አያልፍም:: ብቃት ያለው የሰው ሃይል፣ የጠራ አደረጃጀትና አሰራር ካለ ግን በመጀመሪያ ደረጃ መሳሪያዎች ባይኖሩም መሳሪያዎችን በሂደትና ቀስ በቀስ መስራት ይቻላል:: ቀደምት ትውልዶች ይህን የማስፈፀም አቅም በመጠቀም የፈለሰፉዋቸውና የፈጠሩዋቸው የተሻሻሉ መሳሪያዎች ካሉም በነዚሁ በላቀ ደረጃ ለመጠቀም ይቻላል:: የተሻሻሉ መሳሪያዎች ስራን ለማቃለል፣ ለማቀላጠፍና ጥራቱን ለማሻሻል እጅግ በጣም ጠቃሚ ሊሆኑ ቢችሉም በራሳቸው የማስፈፀም አቅም አይደሉም::



ከዚህ በመነሳት የማስፈፀም አቅም የሰዎች፣ የተስተካከሉ አደረጃጀቶችና አሰራሮች ጥምረት ነው የሚለው ትክክለኛ አባባል በደንብ ሊሰመርበትና ሊጨበጥ የሚገባው ጉዳይ ነው::

የማስፈፀም አቅም ገፅታዎች ተብለው ከተቀመጡት ውስጥ አንዱ የሰው ሃይል ነው:: ህብረተሰብ ተፈጥሮንና ማህበራዊ አካባቢውን ለራሱ በሚመች ሁኔታ በቀጣይነት እያሻሻለ እንዲሄድ ከተፈለገ ይህን ስራ ለመስራት የሚችል ሰው በሚፈለገው መጠን ብቻ ሳይሆን በሚፈለገው አይነትም መኖር አለበት:: በሚፈለገው አይነት ሲባል በቅድሚያ ስራውን ለመስራት የሚያስችል እውቀት ያለው መሆን አለበት ማለት ነው:: እውቀቱ ብቻውን ግን በቂ አይሆንም:: በዚህ እውቀት በመጠቀም አንዳች አይነት የስራ ውጤት ለማስገኘት የሚያስችል የስራ ልምድም ያስፈልገዋል:: ከዚያም በላይ እውቀቱንና የስራ ልምዱን በመጠቀም በታታሪነትና በስራ ወዳድነት፣ በተጨባጭ የስራ መስክ ላይ በመልካም ስነ-ምግባር ለመስማራት የሚያስችለው አመለካከትና ባህል ሊኖረው ይገባል:: የሰው ሃይል በሚፈለገው መጠን በሌለበት፣ በተለይም ከላይ በተገለፀው ደረጃ የሚፈለገውን አይነት በሚያሟላ አኳኋን በሌለበት የሚረባ የማስፈፀም አቅም ሊኖር አይችልም:: ይልቁንም የተስተካከለ አደረጃጀትም ሆነ አሰራር በሰው ሃይል ዙሪያ የሚያጠነጥኑና ከዚሁ ውጭ ህልውና የሌላቸው በመሆኑ የሰው ሃይልን በሚፈለገው መጠን፣ በተለይም በሚፈለገው አይነት መገንባት የማስፈፀም አቅም ግንባታ ቁልፍ ገፅታ ይሆናል::

የሰው ሃይል የማስፈፀም አቅም ዋነኛ ገፅታ ነው:: ይሁንና

የሰው ሃይል ብቻ የማስፈፀም አቅም ሊሆን አይችልም። የሰው ሃይል የማስፈፀም አቅም የሚሆነው በተስተካከለ አሰራርና አደረጃጀት ሲደገፍ፣ በእንደዚህ አይነቱ የአሰራርና የአደረጃጀት ማዕቀፍ ውስጥ ሆኖ ሲሰራ ነው። የሰው ሃይል፣ አሰራርና አደረጃጀት ሲጣመሩ ነው የማስፈፀም ተቋም የሚሆኑት። ከተቋም ውጭ የማስፈፀም አቅም አይኖርም፣ ሌላው ቀርቶ የሰው ሃይል በሚፈለገው መጠንና አይነት ሊገነባ የሚችለው ተቋሞችን በመፍጠርና በማጠናከር ዙሪያ ነው። በመሆኑም ተቋሞችን ከመፍጠር ውጭ አጠቃላይ የማስፈፀም አቅም ግንባታም ሆነ የሰው ሃይል ግንባታ ሊካሄድ አይችልም።

አሰራር ስንል በመሰረቱ ህጎች መመሪያዎች፣ የአሰራር ልምዶች፣ ማንዋሎችና የመሳሰሉትን ያካተተ ነገር ነው። ሰዎች በመሰረቱ ስራቸውን የሚሰሩት በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ ሆነው ነው። ማህበራዊ ግንኙነቱ የሚመሰረትባቸውና የሚገለፅባቸው ህጎች፣ መመሪያዎች፣ ልምዶች ወዘተ. ሰዎችን በላቀ ሁኔታ ለማንቀሳቀስ፣ በሂደት ብቃታቸውን ለመጨመር የሚያስችሉ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ በሚሆንበት ወቅት የህብረተሰቡ የማስፈፀም አቅም ጠንካራ ይሆናል። በሌላ በኩል ደግሞ የህብረተሰቡ አሰራሮች የስራ ትጋትንና ስነ-ምግባርን የሚያላሽቁ፣ ቀልጣፋነቱንና የስራ ጥራቱን የሚያዳክሙ ወዘተ. ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ በሚሆንበት ወቅት የህብረተሰቡ የማስፈፀም አቅም እጅግ በጣም ደካማ ይሆናል።

በመሆኑም የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራ አንዱ ዋነኛ



ገፅታ፣ የህብረተሰቡ ህጎች ፣መመሪያዎች፣ ልምዶች በአጠቃላይም አሰራሮቹ የስራ ቅልጥፍናና ጥራትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ፣ ታታሪነትንና መልካም የስራ ባህልን የሚያጎለብቱ ወዘተ. እንዲሆኑ አድርጎ የማስተካከልና በቀጣይነት የማሻሻል ስራ ነው። በአይነትም በመጠንም ምርጥ የሰው ሃይል ቢሰባሰብ፣ ተብትቦ የሚይዘው ህግና መመሪያ፣ ባህልና ልምድ እስካለ ድረስ የሚረባ የማስፈፀም አቅም ሊኖር አይችልምና።

ሰዎች ተፈጥሮንና ማህበራዊ ግንኙነታቸውን ለራሳቸው በሚመች ሁኔታ የመቀየር ስራ ማለትም የልማት ስራን የሚሰሩት በተናጠል አይደለም። በአንዳች አይነት ማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ ሆነው ነው። ይህ ግንኙነት ልማቱን ለማፋጠን የሚያስችል እንዲሆን ለማድረግ የተስተካከሉ አሰራሮች ሊኖሩ ይገባል። ይህ ብቻውን ግን በቂ አይሆንም። የሰዎች ትስስርና አደረጃጀት የስራ ቅልጥፍናን ለማረጋገጥ የሚያስችልና የጠራም መሆን አለበት። ሰዎችን ተብትቦ የሚይዝ የተንዛዛና ኋላ ቀር አደረጃጀት ባለበት የሚረባ የማስፈፀም አቅም ሊኖር አይችልም። በመሆኑም የማስፈፀም አቅም ግንባታ አንዱ ዋነኛ ገፅታ አደረጃጀቶችን በቀጣይነት የማሻሻል ስራ ይሆናል።

የማስፈፀም አቅም ሰዎች፣ አሰራሮችና አደረጃጀቶች በተናጠል የሚፈጥሩት ሳይሆን የሶስቱም ጥምረት በመሆኑ ይህንኑ አቅም የመገንባት ስራም ሶስቱን በጣምራ በማሻሻልና በተመጋጋቢነት የሚፈፀም መሆን አለበት። የሰው ሃይሉን የማሰልጠንና የማብቃት ስራ፣ አሰራሮችና አደረጃጀቶችን የማስተካከል ስራ ጎን ለጎንና በጣምራ የሚካሄዱና ተነጣጥለው

የማይሰሩ መሆን አለባቸው:: ጎን ለጎንና በጣምራ ብቻ ሳይሆን ተመጋጋቢ በሆነ አኳኋንም መሰራትም አለባቸው:: የሰው ኖይሉ ብቃት ሲሻሻል የተሻሻሉ አሰራሮችን ለመንደፍና ለመተግበር፤ የተሻሻሉ አደረጃጀቶችን ለመቀየስና ለማስፈፀም ይችላል:: ስለሆነም የአደረጃጀትና የአሰራር መሻሻል ከሰው ኖይሉ ብቃት መሻሻል ተነጥሎ የማይኖይ ይሆናል:: በተመሳሳይ መልኩ የተሻሻለ አሰራርና አደረጃጀት ሲኖር የሰለጠነ የሰው ኖይል፣ ዕውቀትና ክህሎቱን በልምድ ለማዳበር ከፍተኛ ዕድል ያገኛል:: የተስተካከለ አሰራርና አደረጃጀት ከሌለ ግን የሰለጠነው የሰው ኖይል በሂደት ዕውቀቱና ክህሎቱ ኖየተረሳና ኖየጠፋ ይሄዳል:: በመሆኑም አደረጃጀትና አሰራርን ማስተካከል የሰለጠነውን የሰው ኖይል ብቃት በቀጣይነት ለማሻሻልና ሙያውን ጠብቆ ኖንዲቀይ በጣም አስፈላጊ ይሆናል:: የማስፈፀም አቅም የሚባለው የሦስቱ ጣምራነት ኖና የሦስቱን መስተጋብር መሰረት ያደረገ አቅም ነው:: በተናጥል ሦስቱም የማስፈፀም አቅም ሊፈጥሩ አይችሉም:: ሦስቱ ተጣምረውና ተመጋጋቢ በሆነ አኳኋን ተቀናጅተው ሲገኝ ብቻ ነው የማስፈፀም አቅምን ሊፈጥሩ የሚችሉት:: በመሆኑም የማስፈፀም አቅም ግንባኖ ስራ የሦስቱን መስተጋብር መሠረት ባደረገ አኳኋን ኖንዲፈፀም በተቋሞች ግንባኖ ማዕቀፍ ውስጥ መፈፀም ይኖርበኖል:: ተቋሞችን ከመፍጠርና ከማሻሻል ውጪ ሦስቱን ማጣመር ስለማይቻል የአቅም ግንባኖ ስራው ተቋሞችን ከመፍጠርና ከማሻሻል ስራ ውጪ በአጥጋቢ ሁኔኖ ሊሰራ አይችልም::

በአጠቃላይ የማስፈፀም አቅም አንድ ህብረተሰብ



ቴፎጥሮንና ማህበራዊ ግንኙነቱን ለራሱ በሚመች ሁኔታ ለመቀየር፣ ወይም በሌላ አገላለፅ የአገሮችን ልማት ለማረጋገጥ የሚያስፈልግ የሰዎች የአሰራርና የአደረጃጀት ጥምረት ነው:: ቁሳቁሶችና መሳሪያዎች በማስፈፀም አቅሙ የሚፈጠሩና የማስፈፀም አቅሙን በላቀ ደረጃ ለመጠቀም የሚያስችሉ ተፈላጊ ነገሮች እንጂ የማስፈፀም አቅሙ ክፍሎች አይደሉም:: አቅም ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ በትክክል ማስቀመጥ ለማስፈፀም አቅም ግንባታ እንቅስቃሴያችንም ሆነ ለአጠቃላይ የልማት እንቅስቃሴያችን መሳካት ከፍተኛ ትርጉም ያለው ነገር ነው::

## 2. የማስፈፀም አቅምና ልማት፣

የማስፈፀም አቅም የልማት ዋነኛ መሳሪያ ነው:: በማስፈፀም አቅምና በልማት መካከል ያለው ትስስር አንድ ዋነኛ ገፅታም ይኸው ነው:: ቀደም ሲል እንደተገለፀው ቁሳቁስና መሳሪያ ስራን ከማቃለል፣ ከማፋጠንና ጥራቱን ከማሻሻል አኳያ ከፍተኛ ትርጉም ያለው ጉዳይ ነው:: ይሁንና እነዚህ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች ሰው በዘመናት ሂደት የሰራቸው በመሆናቸው፣ በአግባቡ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉትም በሰው፣ በአሰራርና አደረጃጀት በመሆኑ በራሳቸው የማስፈፀም አቅም አይደሉም፤ የልማት ዋነኛ መሳሪያም አይደሉም:: የልማቱ ዋነኛ መሳሪያ የማስፈፀም አቅም ነው:: ቁሳቁሶችና መሳሪያዎች በልማት ተግባር ላይ ከፍተኛ ሚና ቢኖራቸውም ዋነኛ የልማት መሳሪያዎችም አይደሉም:: ይህን እጅግ መሰረታዊ የሆነውን ነጥብ በይበልጥ ለመረዳት አንድ ተጨባጭ ምሳሌ መውሰድ ጠቃሚ ነው::

ጀርመን በሁለተኛው የአለም ጦርነት ሂደት በአጠቃላይ

ውድመት ደረጃ ሊመደብ በሚችል አኳኋን ወድሞ ነበር፡፡ የፀረ-ናዚ ሃይሎች ድብደባና የናዚዎች የራሳቸው ከኛ በኋላ ሰርዶ አይብቀል ፈሊጥ ተደማምረው የአገሪቱ የመሰረተ-ልማት አውታሮች፣ ፋብሪካዎች ፣ህንፃዎችና ቤቶች ከሞላ ጎደል በጠቅላላ የወደሙበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት በጦርነቱ መገባደጃ ላይ በርካታ ህዝብ በርዳታና በምፅዋት የሚኖርበት ሁኔታ ላይ ወድቆ ነበር፡፡ በዚህ ሂደት ያልወደመ ነገር ቢኖር የጀርመኖች የጠራ የአደረጃጀትና የአሰራር አቅም ነበር፡፡ በርካታ ሰው ያለቀ ቢሆንም በመጠንም ሆነ በአይነት ከፍተኛ ብቃት የነበረው የሰው ሃይል ነበራቸው፡፡ በሌላ አነጋገር መሳሪያና ቁሳቁሳቸው ከሞላ ጎደል ሲወድም የማስፈፀም አቅማቸው ግን ከሞላ ጎደል እንደተጠበቀ ነበር፡፡ በጣም ከፍተኛም ነበር፡፡

ጦርነቱ ባለቀ በአስር አመት ውስጥ ጀርመን ከነበረችበት ጠቅላላ ውድመት በመላቀቅ ብቻ ሳትወሰን ተመልሳ በአውሮ-ውስጥ ከማንም የተሻለ ኢኮኖሚ ያላት አገር ለመሆን በቅታለች፡፡ በጦርነቱ ያን ያህል ውድመት ካልደረሰባቸው እንደ እንግሊዝ ካሉ አገሮችም የላቀች ሆና ተገኘች፡፡ የወደመውን መሳሪያና ቁሳቁስ በአጭር ጊዜ ውስጥ በተሻለ መሳሪያና ቁሳቁስ ለመተካት ተቻለ፡፡ ይህ የጀርመኖች ተአምር እየተባለ የሚገለፀው ክስተት ሊከሰት የቻለው የጀርመኖች የማስፈፀም አቅም እንደተጠበቀ ስለነበረ ነው፡፡ ብቃት ያለው የሰው ሃይላቸው፣ የተስተካከለ አሰራርና አደረጃጀታቸው፣ ማለትም የማስፈፀም አቅማቸው እንደተጠበቀና በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ስለነበር በጣም በአጭር ጊዜ ውስጥ የወደመውን ከመተካት አልፈው በከፍተኛ ፍጥነት ለመረማመድ ቻሉ፡፡ ዋነኛው የልማት ሃይል የማስፈፀም



አቅም መሆኑን በማያወላዳ ሁኔታ የሚያረጋግጥ አስደናቂ ተግባር ፈፀሙ፡፡ ቁሳቁስና መሳሪያ በልማት ስራ ላይ ከፍተኛ ሚና ቢኖረውም ዋነኛው የልማት መሳሪያ እሱ እንዳልሆነ በተግባር አረጋገጡ፡፡

ዋነኛው የልማት መሳሪያ የማስፈፀም አቅም ነው ሲባል ግን ሌላውን ነገር ሁሉ ትቶ የሰው ሃይል በማሰልጠን፣ አሰራርና አደረጃጀት በማስተካከል ስራ ላይ ብቻ በመረባረብ በአቋራጭ መልማት፣ ጀርመኖች የሰሩትን መድገም ይቻላል ማለት አይደለም፡፡ የማስፈፀም አቅም የልማት ዋነኛ መሳሪያ ብቻ ሳይሆን የልማት ዋነኛ ውጤትም ጭምር ነው፡፡ በመሆኑም ከልማት ውጭ የማስፈፀም አቅምን ያለማቋረጥ ማሳደግ አይቻልም፡፡ የማስፈፀም አቅምን ለማጎልበት፣ ጥራታቸው የተጠበቀ በበቂ መጠን የሚገኙ ልዩ ልዩ የትምህርትና ስልጠና ተቋሞች፣ የጥናትና ምርምር ድርጅቶች ወዘተ. ያስፈልጋሉ፡፡ እነዚህን ለማደራጀትና ለማንቀሳቀስ ከፍተኛ የገንዘብ አቅም፣ ከፍተኛ ልማት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ የማስፈፀም አቅም የልማት ውጤት ነው ሊባል ይችላል፡፡

የማስፈፀም አቅም የልማት ውጤት ነው የምንለው ይህን ለመገንባት የሚያስፈልጉ ድርጅቶችና ተቋሞችን ለመፍጠርና ለማንቀሳቀስ ገንዘብ፣ ልማት ስለሚያስፈልግ ብቻ አይደለም፡፡ አቅሙ ራሱ የሚፈጠረው በነዚህ ተቋሞች ብቻ ስላልሆነም ጭምር ነው፡፡ አንድ የተማረና የሰለጠነ ሰው በሰለጠነበት የስራ መስክ በተግባር ካልተሰማራ እውቀቱን ሊያዳብረውና ሊጠብቀው

አይችልም፡፡ በሂደትም ታጥቦ ጭቃ መሆን የማይቀር ነው፡፡ የማስፈፀም አቅም ግንባታ በተጨባጭ የልማት ተግባር ሂደትና ከዚሁ የልማት ተግባር ጋር ተቀናጅቶ ሲፈፀም ብቻ ነው በርግጥም የማስፈፀም አቅም ሊሆን የሚችለው፡፡ የማስፈፀም አቅም የልማት ውጤት ነው የምንልበት ሶስተኛ ምክንያትም አለ፡፡ የማስፈፀም አቅም የሚገነባው የልማት ስራን ለማከናወን ነው፡፡ መነሻውና መዳረሻው ተፈጥሮንና ማህበራዊ ግንኙነቶችን በይበልጥ ለሰው በሚመች አኳኋን የመቀየር፣ የማልማት ስራ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ የማስፈፀም አቅም ትርጉምም ህልውናም ሊኖረው አይችልም፡፡ ስለሆነም የማስፈፀም አቅም የልማት ዋነኛ መሳሪያ ብቻ ሳይሆን የልማት ዋነኛ ውጤትም ጭምር ነው፡፡

የልማት ተግባር ብዙ ውጤቶች እንደሚኖሩት የታወቀ ነው፡፡ የህብረተሰብ አኗኗር ይሻሻላል መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች በቁጥርም በአይነትም ይጨምራሉ፡፡ የህብረሰቡ የማስፈፀም አቅም፣ ተፈጥሮንና ማህበራዊ ግንኙነትን በቀጣይነት የማሻሻል አቅም ይጎለብታል፣ ወዘተ.. እነዚህና የመሳሰሉት ውጤቶች እጅግ ተፈላጊ ስለሆኑ ነው ልማት እጅግ ተፈላጊ የሚሆነው፡፡ ይሁንና ሁሉም የልማት ውጤቶች እኩል ሚዛን የሚሰጣቸው አይደሉም፡፡ ከነዚህ ሁሉ በዋነኛነት ሊጠቀስ የሚገባው የልማት ውጤት የማስፈፀም አቅም ነው፡፡ የማስፈፀም አቅም የልማት ዋነኛ ውጤት የሚሆነው በልማቱ ሂደት አቅሙ ካልተገነባና በቀጣይነት ካልተሻሻለ በስተቀር ልማቱ ተንገራግጮ የሚቆምና ወደኋላ የሚመለስም ስለሆነ ነው፡፡ የማስፈፀም አቅምን በቀጣይነት የማያጎለብት ልማት ብልጭ ብሎ የሚጠፋ ብርሃን ከመሆን የማይዘል በመሆኑ ነው፡፡



በልማት ሂደት የሚፈጠሩ ቁሳቁሶች መሳሪያዎች ወዘተ. በጦርነት፣ በመሬት መንቀጥቀጥና በመሳሰሉት ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ምክንያቶች በአጭር ጊዜ ውሰጥ ሊወድሙ ይችላሉ፡፡ ሰው እስካለ ድረስ የማይወድመው ዋነኛ ሃብትና የልማት ውጤት የማስፈፀም አቅም ነው፡፡ ይህም የማስፈፀም አቅም ዋነኛ የልማት ውጤት ነው የምንልበት ሌላው ምክንያት ነው፡፡

የማስፈፀም አቅም ዋነኛው የልማት ውጤት ነው ከሚለው አባባል የሚመነጩ በርካታ መሰረታዊ ድምዳሜዎች አሉ፡፡ ህብረተሰቡ በማያቋርጥ የልማት ሂደት ውስጥ የሚገባ እስከሆነ ድረስና የዚሁ የማያቋርጥ የልማት ሂደት ዋነኛው ውጤት የማስፈፀም አቅም መገንባት እስከሆነ ድረስ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራ አንድ ጊዜ ተሰርቶ የሚያበቃ ጉዳይ ሳይሆን ልክ እንደልማቱ ሁሉ የማያቋርጥ የግንባታ ሂደት ነው፡፡ የማስፈፀም አቅምን በማጎልበት ልማት ይፋጠናል፣ ልማትን በማፋጠን የማስፈፀም አቅም በይበልጥ ይጎለብታል፣ የማስፈፀም አቅምን በይበልጥ በማጎልበት ደግሞ የላቀ ልማት ይገኛል፣ ወዘተ. የማስፈፀም አቅም የልማቱ መሳሪያም ውጤትም ሆኖ፣ ከልማት እንቅስቃሴው ጋር በጥብቅ ተሳስሮና ተቆላልፎ በቀጣይነት የሚሰራ ስራ ይሆናል፡፡

የማስፈፀም አቅም ግንባታ ልክ እንደልማት ሁሉ ቀጣይነት ያለውና የማያቋርጥ ብቻ ሳይሆን ከልማት ተግባሩ ጋር በቅርብ ተሳስሮ መፈፀም አለበት ሲባል የማስፈፀም አቅም የመገንባት ስራን በአንድ በኩል፣ የልማት ስራን በሌላ በኩል

አስቀምጦ በመስራት በሂደት ሁለቱ ጎን ለጎን እየተካሄዱ እንዲደጋገፉ የማድረግ ጉዳይ አይደለም:: የማስፈፀም አቅም ግንባታና የልማት ስራ ለትንተና እንዲያመች ተለያይተው የሚተነተኑ ቢሆኑም በተግባር ግን ተነጣጥለው ጎን ለጎን ሊሄዱ የሚችሉ አይደሉም:: የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራው የልማቱ ስራ አንድ ክፍልና አካል ብቻ ሳይሆን የልማቱ ስራ ማዕከል ሆኖ ነው መታየት ያለበት:: ይህንን እጅግ በጣም መሰረታዊ የሆነ ነገር በይበልጥ ለመገንዘብ ቀደም ሲል የተዘጋጀውን የመንግስት የገጠር ልማት ስትራተጅ ስልትና እቅድ በምሳሌነት መውሰድ ይቻላል::

የገጠር ልማት እንቅስቃሴያችን የአገራችን አጠቃላይ ልማት እንቅስቃሴ ወሳኝ ክፍልና መሰረትም ነው:: ይህንን ወሳኝ የልማት ስራ ለመፈፀም እንዲቻል የልማቱ እቅድና አፈፃፀም የማስፈፀም አቅምን በቁልፍ ተግባርነት መውሰድ መቻል አለበት:: ግብርናና ገጠርን ለማልማት አርሶ አደሩ በግብርና ሙያ መሰልጠንና፣ ታታሪነቱ መጠናከር ወዘተ. ይገባዋል:: የምክርና የኤክስቴንሽን አገልግሎት የሚሰጡት ሙያተኞች በሚፈለገው መጠንና አይነት መሰልጠን አለባቸው:: የግብርናና የገጠር ልማት ተመራማሪዎች በሚፈለገው መጠንና አይነት መሰልጠን አለባቸው:: ይህ የትምህርትና ስልጠና ስራ ከገጠርና ግብርና ልማት ስራችን እድገት ጎን ለጎን በመጠንና በአይነት እየተሻሻለ መሄድ አለበት:: በሌላ አገላለፅ በጣም ሰፊና ከልማት ደረጃችን ጋር አብሮ የሚዳብር የሰው ሃይል የማልማት ሰፊ ስራ፣ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራ የገጠር ልማቱ ስራ አንዱና ዋነኛ አካል



መሆን አለበት::

የሰው ሃይል መሰልጠኑ ብቻም አይበቃም፣ የሰው ሃይሉ በአግባቡ መደራጀት አለበት:: ጠንካራ የኤክስቴንሽን፣ የምርምርና የስልጠና ተቋማት ሊደራጁ ይገባል:: የተስተካከለ የግብይት ስርአት የሚፈጥሩ እንደ ህብረት ስራ ማህበራት ያሉ ድርጅቶች፣ የህዝቡን ተሳትፎ የሚያረጋግጡ የብዙሃን ማህበራትና የአስተዳደር አካላት ወዘተ. መደራጀት አለባቸው:: የገጠርና የግብርና ልማትን የሚያፋጥኑ ህጎች መመሪያዎች ልምዶች ወዘተ. በየስራ መስኩና በየተቋሙ መፈጠር አለባቸው:: እነዚህ የድርጅትና የአሰራር ማስተካከል ስራዎች ከገጠር ልማት ደረጃችን እድገት በሚመጣጠን አኳኋን በቀጣይነት መፈፀም አለባቸው:: በሌላ አገላለፅ የገጠር ልማት ስራችን ዋነኛ ክፍል የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራን መፈፀም መሆን ይኖርበታል::

የገጠርና የግብርና ልማት ስራችን ቁልፍ ስራ ከላይ የተጠቀሱትና የመሳሰሉትን የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራዎች መስራት ነው ስንል በዚህ ብቻ ነገሩ ሁሉ ያበቃል ማለት አይደለም:: ይህ ስራ ውሃን ከማቆር፣ ማሳን ከማረስና ከማረም፣ በአጠቃላይ ምርትንና አገልግሎትን ከመጨመር ስራ ሳይነጠል መፈፀም አለበት:: የሚሰለጥነው ሰው፣ የሚስተካከለው አሰራርና አደረጃጀት በተጨባጭ ተግባር የሚፈተሽ ይሆናል:: በዚሁ ተጨባጭ ተግባር ሂደት የሰው ሃይሉ ብቃቱ በይበልጥ እየተረጋገጠ፣ አሰራሩና አደረጃጀቱ በይበልጥ እየጠራና እየተስተካከለ ይሄዳል ማለት ነው:: የማስፈፀም አቅምና ልማት

ጎን ለጎን የሚሄዱ የተለያዩ ነገሮች ሳይሆኑ ተነጣጥለው ሊኖሩ የማይችሉ ነገሮች፣ የአንድ ክስተት የተለያዩ ገፅታዎች ናቸው፡፡ የማስፈፀም አቅም የልማት ዋነኛ መሳሪያና የልማቱ ውጤትም በመሆኑ ከተጨባጭ የልማት ተግባር ውጭ ሊኖርና ሊገነባ የሚችል አይደለም፡፡ በፈንታውም ልማት የማስፈፀም አቅም በሌለበት ሊከናወን የማይችል፣ የማስፈፀም አቅምን የማጎልበት ውጤት ከሌለውም ቀጣይነት ሊኖረው የማይችል ነገር ነው፡፡ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራ የልማቱ ስራ አንዱ ክፍልና ዋነኛውም ክፍል ነው የምንለውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡

### 3. የማስፈፀም አቅም ግንባታና የልማት ስትራተጅዎቻችን ትስስር፣

አገራችን በአሁኑ ወቅት ሁሉን አቀፍ በሆነ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ትገኛለች፡፡ ይህንን የልማት እንቅስቃሴ ለመምራት የሚያስፈልጉና የሚያስችሉ የተለያዩ የልማት ስትራተጅዎችም ተነድፈዋል፡፡ በአገራችን የዳበረ የዴሞክራሲ ስርአት ለመፍጠርና የህዝቦቻችንን ዴሞክራሲያዊ አንድነት ለማጠናከር የሚያስችሉን ስትራተጅዎች ነድፈን በመንቀሳቀስ ላይ ነን፡፡ ገጠርንና ግብርናን ለማልማት፣ ከተማንና ኢንዱስትሪን ለማልማት ተብለው የተነደፉ ስትራተጅዎችም አሉን፡፡ በአንድ ቃል ሁሉን አቀፍ ልማት ለማምጣት ይችላሉ ተብለው የተነደፉ የተለያዩ ስትራተጅዎች አሉ፡፡ ከዚህ ውጭ ራሱን የማስፈፀም አቅምን ለማጎልበት ተብሎ የተነደፈ ስትራተጅም አለን፡፡ በማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራተጅና በሌሎቹ የልማት ስትራተጅዎች መካከል ቀደም ሲል በተቀመጠው መሰረት



ባህሪያዊ ትስስር አለ፣ መኖርም ይገባዋል፡፡

የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራ ራሱን የቻለ አላማ አይደለም፡፡ የማስፈፀም አቅም የምንገነባው ልማታችንን ለማፋጠንና ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ ነው፡፡ በመሆኑም የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራችን ግብ በአገራችን ሁሉን አቀፍ ልማት ማረጋገጥ ነው፡፡ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራተጅያችን ግብ የተቀመጡትን የገጠርና የግብርና ልማት፣ የከተማና ኢንዱስትሪ ልማት፣ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ወዘተ. ስትራተጅዎችን ማስፈፀም ነው፡፡ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራተጅያችን የተቀመጡትን ሌሎች የልማት ስራዎች በላቀ ደረጃ እንዲፈፀሙ ማድረግ በመሆኑ የስትራተጅው መነሻም እነዚህ የልማት ስራዎች ናቸው፡፡ የማስፈፀም አቅምን ለማጎልበት እቅድ በምንነድፍበትና በምናስፈፅምበት ወቅት ከሆነ አጠቃላይ ነገር በመነሳት ሳይሆን ከተጨባጭ የልማት እቅዶቻችን በመነሳትና እነዚህን ተጨባጭ የልማት እቅዶች ለማሳካት የሚያስችል ይዘት እንዲኖረው በማሰብ ነው፡፡ የሰው ሃይል ስናሰለጥን የገጠርና ግብርና ልማትን፣ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታን፣ የከተማና ኢንዱስትሪ ልማትን ወዘተ. ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የሰው ሃይል ለመፍጠር ነው፡፡ በነዚህ ስራዎች ዙሪያ ያለንን የሰው ሃይል ፍላጎት ለማሟላት የሚያስችል በመጠንና በአይነት በቂ ሰው ለማፍራት ነው፡፡ ከዚህ ውጭ የሆነ የትምህርትና ስልጠና ስራ የለም፣ ሊኖርም አይገባም፡፡ ከዚህ ውጭ የሆነ የአሰራርና አደረጃጀት ማስተካከል ስራ የለም፣ ሊኖርም አይገባም፡፡

ሌሎቹ የልማት ስትራተጅዎቻችን የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራተጅያችን ግቦች የመሆናቸው ጉዳይ፣ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራዎቻችን በሙሉ የልማት ስራዎቻችንን ለማስፈፀምና፣ እነዚህን ለማስፈፀም ብቻ ተብለው የሚካሄዱ ከዚህ ውጭ የሆነ ምንም ነገር የማይኖራቸው የመሆኑ ጉዳይ በማስፈፀም አቅም ስትራተጅያችንና በሌሎቹ የልማት ስትራተጅዎቻችን መካከል ያለው ትስስር አንድ ገፅታ ነው:: የትስስሩ ሌላው ገፅታ ደግሞ ሌሎቹ የልማት ስትራተጅዎቻችን ሁሉ በውስጣቸው የማስፈፀም አቅምን የማጎልበት ይዘት ያላቸው፣ ይልቁንም የነዚህ ስትራተጅዎች ማዕከል የማስፈፀም አቅም ግንባታ የመሆኑ ጉዳይ ነው::

ቀደም ሲል እንደተገለፀው የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራችን ግብ የግብርናና የገጠር ልማት ስትራተጅያችን ወዘተ. ማስፈፀም ነው:: ስለሆነም ሁሉም የአቅም ግንባታ ስራዎቻችን የገጠርና የግብርና ልማት ስትራተጅያችንን ወዘተ. ለማስፈፀም፣ ለማፋጠንና ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል ጥራት ያለው የሰው ሃይል፣ አሰራርና አደረጃጀት ለማረጋገጥ ተብለው የሚነደፉና በዚህ ቅኝት ብቻ የሚመሩ ይሆናሉ:: በሌላ በኩል ደግሞ የግብርናና የገጠር ልማት ስትራተጅያችን በማዳበሪያና ምርጥ ዘር፣ በቴክኖሎጅ አቅርቦት ላይ ብቻ የታጠረ አይደለም:: ስትራተጅው እነዚህንና መሰል ጉዳዮችን የሚያካትት ቢሆንም የግብርናና የገጠር ልማትን ለማፋጠንና ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአቅም ግንባታ ስራን ያካተተ ነው:: ይልቁንም ይህ የአቅም ግንባታ ስራ የግብርናና የገጠር ልማት ስትራተጅያችን



ዋነኛ አካል ነው:: ሌሎቹ የልማት ስትራተጅዎችም ተመሳሳይ ናቸው:: በመሆኑም በአንድ በኩል የአቅም ግንባታ ስትራተጅያችን ግቦች የልማት ስትራተጅዎቻችንን ማስፈፀም ይሆናሉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉም የልማት ስትራተጅዎቻችን የማስፈፀም አቅም ግንባታን በውስጣቸው የያዙና ይህንኑ የስትራተጅዎቹ ዋነኛ አካል አድርገው የሚወስዱ ይሆናሉ:: የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራተጅያችንና ሌሎቹ የልማት ስትራተጅዎቻችን በተጠቀሰው መልክ በቅርብ የተሳሰሩ ናቸው::

## 4. የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራተጅያችን፣

### 4.1. የስትራተጅው ግቦች:-

የማንኛውም አገር የማስፈፀም አቅም የመገንባት እንቅስቃሴ ከልማት እንቅስቃሴው ተነጥሎ ሊከናወን የማይችል በመሆኑና ልማት የዚሁ ዋነኛ ማስፈፀሚያ መሳሪያም በመሆኑ የስትራተጅው ግቦች የልማት ስትራተጅዎችን ለማስፈፀም የሚያስችል አቅም መገንባት እንደሚሆን ከላይ ተገልጿል:: በኛም ሁኔታ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራተጅያችን ግቦች የልማት ስትራተጅዎቻችንን ማስፈፀም ይሆናል:: የስትራተጅው ይዘትና አድማስ በግቡ የሚወሰን ይሆናል:: ይዘቱ ከላይ እንደተገለፀው በዝርዝር የተቀመጡትን የልማት ስትራተጅዎችን ለማስፈፀም የሚያስችል ይሆናል:: የስትራተጅው አድማስም በልማት ስትራተጅዎቻችን አድማስ የሚወሰን ይሆናል::

የመንግስታችን የልማት ስትራተጅዎች መንግስት የሁሉንም የልማት ሃይሎች የማምረት አቅም በማጎልበት፣ አቅማቸውን አሟጦ በመጠቀምና በማስተባበር ላይ ያተኮረ ነው። መንግስት በራሱ የተለያዩ የምርትና የአገልግሎት ተቋሞች የሚያቋቁም ቢሆንም ይህንን የሚያደርገው በሌሎች የልማት ሃይሎች ሊሰራ የማይችል ወይም በሚፈለገው መጠን ሊሰራ የማይችል ሲሆን ብቻ ነው። በመሆኑም የመንግስታችን የልማት ስትራተጅ ሁሉንም ነገር ገበያው ይመልሰው ብለው ከሚነሱትም ሆነ ሁሉንም ነገር መንግስት ይስራው ብለው ከሚነሱት መንግስታት የተለየ ነው። በመሆኑም የኛ የማስፈጸም አቅም ግንባታ ስትራተጅ አድማስም ሁሉንም ነገር ለገበያ ከሚተው መንግስታት የተለየ፣ ሁሉም ነገር በመንግስት እንዲሰራ ከሚፈልጉትም የተለየ ይዘትና አድማስ ይኖረዋል።

**4.2. ሁሉን አቀፍ የአቅም ግንባታ ስራ መስራት፣**

በአገራችን የልማት ስትራተጅዎች ውስጥ ዋነኛ ሚና የሚጫወቱ ሶስት የልማት ሃይሎች እንዳሉ ተገልጿል። መንግስት የልማት (የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታም የልማቱ አካል ነው) ስራዎችን የመምራትና የማስተባበር ስራ መስራት ይጠበቅበታል። ህዝቡ በየትኛውም ደረጃ የአጠቃላይ የልማት እንቅስቃሴ ዋነኛ ሃይልና ፈፃሚ ነው። የግል ባለሃብቶች በኢኮኖሚ ልማት እንቅስቃሴያችን ውስጥ ተኪ የሌለው ከፍተኛ ሚና አላቸው። የልማት እንቅስቃሴያችን የተሳካ ፈጣንና ቀጣይነቱ የተረጋገጠ ሊሆን የሚችለው የሁሉም የልማት ሃይሎች አቅም በሚፈለገውና



ሊሆን በሚችለው ደረጃ ሲጎለብትና ይህንኑ አቅም አሟጠው ሊጠቀሙ የሚችሉበት የተመቻቸ ሁኔታ ሲፈጠር ብቻ ነው። የአንደኛው አቅም ተገንብቶ የሌላው በእንጭጩ ቢቀር ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት ማረጋገጥ አይቻልም። በመሆኑም የአቅም ግንባታ ስትራተጅያችን አንድ መሰረኖዊ ይዘት ሁሉንም የልማት ሃይሎች የሚሸፍን መሆኑ ነው። የአቅም ግንባታ ስትራተጅያችን ሁሉን አቀፍ ነው ስንል በተጨማሪ የሰው ሃይል ማልማትን ወይም አሰራርን ወይም አደረጃጀትን ነጥሎ ለማሻሻል የሚሞክር ሳይሆን ሶስቱንም በማጣመር በተቋሞች ግንባታና ማሻሻል ማዕቀፍ ውስጥ የሚፈፀም ያልተነጣጠለ ስትራተጅ ነው ማለታችን ነው።

የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራተጅያችን ሁሉንም የልማት ሃይሎች የሚሸፍን ይሆናል ሲባል ግን ለሁሉም እኩል ትኩረት ይሰጣል ማለት አይደለም። ምንም እንኳን የሁሉንም የልማት ሃይሎች አቅም በሚፈለገውና ሊሆን በሚችለው ደረጃ ለማጎልበት ርብርብ የሚደረግ ቢሆንም የልማት ሃይሎቹ ሚና የተለያየ በመሆኑ ከሚናቸው መለያየት ጋር በተያያዘ መንገድ የሚሰጣቸውም ትኩረት የተለያየ መሆኑ የግድ ነው።

መንግስት የልማት ሃይሎችን በሙሉ የመምራትና የማስተባበር ሃላፊነት አለበት። መንግስት ይህንን ሚና ለመጫወት የሚያስፈልገው የማስፈፀም አቅም ካልተገነባለት በስተቀር ተልእኮውን መወጣት አይችልም። ሌሎቹ የልማት ሃይሎችም ብቃት ያለው አመራር አግኝተው ተልእኮዋቸውን ሊፈፅሙ አይችሉም። መንግስት አስተባባሪና መሪ በመሆኑ ከዚህ የላቀ

ሚናው ጋር አብሮ የሚሄድ የላቀ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል:: መንግስት የራሱን የማስፈፀም አቅም ከመገንባት ባሻገር የሌሎቹንም የልማት ሃይሎች አቅም የመገንባት ሃላፊነት አለበት:: ይልቁንም መንግስት የማስተባበርና የአመራር ሚና መጫወት አለበት የሚባልበት አንዱ ዋነኛ ምክንያትና ይህንኑ የማስተባበርና የመምራት ስራ እንዲሰራ የሚያስችለው ጉዳይ የሌሎቹ የልማት ሃይሎች አቅም ግንባታ ስራም በዋናነት በመንግስት አማካኝነት መሰራት ስላለበት ነው:: ለመንግስት አቅም ግንባታ ስራ የሚሰጠው ትኩረትም ከዚሁ ጋር ተያይዞ የላቀ መሆን ይኖርበታል::

በመሆኑም የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራተጅያችን የሁሉንም የልማት ሃይሎች አቅም የማጎልበት ስራን የሚሸፍን፣ ሁሉም የልማት ሃይሎች በሚፈለገውና ሊሆን በሚችለው ደረጃ አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ለማድረግ የሚያስችል መሆን ቢኖርበትም፣ ይህንኑ ለመስራት የሚቻለው በመንግስት አማካኝነት በመሆኑ የስትራተጅው ትኩረት የመንግስትን የማስፈፀም አቅም በማጎልበት ላይ መሆን ይኖርበታል:: የመንግስትን የማስፈፀም አቅም በማጎልበት ላይ የሚያተኩር ሲሆን ብቻ ነው በዚሁ ላይ ተመስርቶ የሁሉንም የልማት ሃይሎች የማስፈፀም አቅም በሚፈለገው ደረጃ ለማጎልበት የሚያስችል ሁሉን አቀፍ ስትራተጅ ሊሆን የሚችለው::

### 4.3. የማስፈፀም አቅም ግንባታ አቅሞችን በመገንባት ላይ ያተኮረ ስትራተጅ፣



የማስፈፀም አቅም መገንባት ሲባል ብቃት ያለው የሰው ሃይል በቀጣይነት ማፍራት፣ አሰራርና አደረጃጀቶችን በቀጣይነት ማሻሻል ማለት ነው:: የማስፈፀም አቅም መገንባት የሚቻለው ይህንኑ በብቃት ለመስራት የሚያስችሉ በአካባቢ የተደራጁና ብቃት ያላቸው አቅሞች ሲኖሩ ብቻ ነው:: የማስፈፀም አቅም ግንባታ አቅሞች ብለን የምንላቸው፣ የትምህርትና ስልጠና ተቋሞችን፣ የጥናትና ምርምር ድርጅቶችን ኖንዲሁም የምክር አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችንና የመሳሰሉትን ነው::

የሰው ሃይል ብቃትን ለማሳደግ የሚከናወን ስራ ለመስራት ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ እስከ ዩኒቨርስቲ ድረስ የሚዘልቅ የትምህርትና ስልጠና ስርአትና ይህንኑ የሚፈፅሙ ብቃት ያላቸው የትምህርትና ስልጠና ተቋሞች መኖር ይኖርባቸዋል:: አንድ ተጨባጭ ሙያና እውቀት ያለው፣ ጥሩ የስራ ስነ-ምግባርና ታታሪነት የተላበሰ የሰው ሃይል በሚፈለገው መጠን ለማፍራት የሚቻለው ይህንን የመስራት ብቃት ያላቸው በቂ የትምህርትና ስልጠና ተቋሞች፣ የማስፈፀም አቅም ግንባታ አቅሞች ሲፈጠሩና በቀጣይነት እየተጠናከሩና እየተስፋፉ ሲሄዱ ነው:: አደረጃጀቶችንና አሰራሮችን በየጊዜው እየገመገሙ፣ አዳዲስ ሃሳቦችን እያፈለቁ በቀጣይነት ማሻሻል የሚቻለው ይህንኑ ለመስራት የሚችሉ በቂ የጥናትና ምርምር እንዲሁም የምክር አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሲፈጠሩና በቀጣይነት እየተስፋፉና እየተጠናከሩ ሲሄዱ ነው::

እነዚህ የማስፈፀም አቅም ግንባታ አቅሞች በሚስፋፉበትና በሚሻሻሉበት ወቅት በነዚህ ተቋሞች አማካኝነት የሰው ሃይላችንን

በቀጣይነት በማብቃትና በማሻሻል፣ አደረጃጀትና አሰራራችንን በቀጣይነት በማስተካከል ብቃት ያለው የማስፈፀም አቅም የመገንባት ስራ መስራት እንችላለን። እነዚህ አቅሞች በሌሉበት ወይም ባልተጠናከሩበት ግን ጥራትና ቀጣይነት ያለው የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራ መስራት አይቻልም። በመሆኑም ምንም እንኳ የልማት ስትራተጅዎቻችንን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉንን አቅሞች በሙሉ ለመገንባት የምንረባረብ ቢሆንም ዋናው ትኩረታችን ከላይ የተገለፁትን የማስፈፀም አቅም ግንባታ አቅሞች በማጎልበት ላይ መሆን ይገባዋል። ይልቁንም ሁሉንም የልማት ስራዎቻችንን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉንን አቅሞች በሙሉ በብቃት መገንባት የምንችለው በነዚህ የማስፈፀም አቅም ግንባታ አቅሞች ላይ አተኩረን መረባረብ ከቻልን ብቻ ነው።

የማስፈፀም አቅም ስትራተጅያችን ሁሉንም የልማት ሃይሎች የሚዳስስ ነገር ግን በመንግስት የማስፈፀም አቅም ላይ ያተኮረ፣ ሁሉንም የልማት ስራዎቻችንን ለመፈፀም የሚያስችሉንን አቅሞች የሚዳስስ ነገር ግን በማስፈፀም አቅም ግንባታ አቅሞች ላይ ያተኮረ መሆን አለበት ሲባል እርስ-በርስ የሚጋጭ ነገር ሊመስል ይችላል፣ ነገር ግን አይጋጭም። የአቅም ግንባታ አቅሞች በግል ባላሀብቶችና በህዝቡም ሊፈጠሩ ይችላሉ። በሂደትም የግል ባለሀብቶችና የህዝቡ ሚና እየጨመረ ይሄዳል። ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት እነዚህን አቅሞች ከመፍጠር አኳያ ወሳኝ ሚና መጫወት የሚችለውና የሚገባው መንግስት ነው። መንግስት ይህንን ወሳኝ ሚናውን እየተጫወተ የግል ባለሃብቶችና ህዝቡ ከዚህ አኳያ ሊያበረክቱት የሚችሉትን አስተዋፅኦ በቀጣይነት



የማሳደግና ይህንኑ አሚጦ የመጠቀም ስራ መስራት ይችላል፣ ይገባዋልም። በመሆኑም ትኩረታችን የመንግሰትን የማስፈፀም አቅም በማጎልበት ላይ መሆን አለበት የሚለው አገላለፅና፣ ትኩረታችን የማስፈፀም አቅም ግንባታ አቅሞችን በመገንባት ላይ መሆን አለበት የሚለው አገላለፅ አብረው የሚሄዱ እንጂ የሚጋጩ አይሆኑም። ከሁሉም የልማት ሃይሎች በመንግስት የማስፈፀም አቅም ላይ እናተኩራለን፣ ከመንግስት የማስፈፀም አቅሞች ውስጥ ደግሞ በማስፈፀም አቅም ግንባታ አቅሞች ላይ እናተኩራለን ማለት ነው።

### 4.4. የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራዎችን በአግባቡ ማስተባበር፣

የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራ ላይ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ የማይሳተፍ የመንግስት መስሪያ ቤት የለም። ሁሉም የልማት ስራዎቻችን፣ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስራችንም ጭምር ዋነኛ ክፍላቸው የአቅም ግንባታ ስራ ነው። ሌሎች ስራዎች የሚሰሩት የአቅም ግንባታ ስራን መሰረትና ማዕከል በማድረግ ነው። በመሆኑም ሁሉም የመንግስት መስሪያ ቤቶች በልማት ስራ ላይ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ እስከተሳተፉ ድረስ በአቅም ግንባታ ስራ ላይ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ተሳታፊ ከመሆን ውጭ ሊሆኑ አይችሉም። ከዚህም ባሻገር የማስፈፀም አቅም ግንባታ አቅሞች ተብለው የተጠቀሱትና ልዩ ትኩረት ይሰጣቸው የተባሉት ተቋሞችም በአንድ የመንግስት መስሪያ ቤት ስር የሚተዳደሩ አይደሉም። ለአፈፃፀም በሚያመች

አኳኋን በተለያዩ መስሪያ ቤቶች ተደራጅተው የሚገኙና በዚሁ መልክ መደራጀት የሚገባቸው ናቸው:: በአጭሩ በየደረጃው ያሉ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ሁሉ በአቅም ግንባታ ስራ ተሳታፊ ናቸው፣ ተሳታፊ መሆንም ይገባቸዋል:: ከዚህም ባሻገር ህዝቡና የግል ባለሃብቶች በዚሁ ስራ ውስጥ በየጊዜው እያደገ የሚሄድ ሚና አላቸው፣ ሊኖራቸውም ይገባል::

የአቅም ግንባታ ስራው በአንድ በኩል በሁሉም ደረጃ ባሉ፣ የተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በህዝቡና በግል ባለሃብቶች ጭምር መሰራት ያለበት፣ ከዚህ አኳያ ሲታይም የተበታተነ መሆኑ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ የአቅም ግንባታ ስራችን በተለያዩ አካላት የሚሰራ ቢሆንም በአግባቡ የሚቀናጅ ካልሆነ በስተቀር አላስፈላጊ ድግግሞሽ፣ የጊዜና የገንዘብ ብክነት ሊያስከትል የሚችል ነው:: ስራው ወጣ ገባ የመሆን አደጋም ሊያጋጥመው ይችላል:: ስለሆነም በስራው ላይ መሳተፍ የሚችሉና የሚገባቸውን ሁሉ በማሳተፍ ስራዎቹን በአግባቡ የማስተባበርና የማቀናጀት ጉዳይ በስትራተጅው መመለስ ከሚገባቸው ዋነኛ ጉዳዮች አንዱ ይሆናል::

የማስፈፀም አቅም ግንባታው ስራ በተለያዩ አካላት እየተሰራ ባለበት ሁኔታ በአግባቡ እንዲቀናጅ ለማድረግ የሚያስችለው ወሳኝ መሳሪያ በየትኛውም አካል የሚሰራው የአቅም ግንባታ ስራ በአንድ አይነት አመለካከት በአንድ ስትራተጅ የሚመራ እንዲሆን ማድረግ ነው:: በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ በአቅም ግንባታ ስራ ላይ የተሰማራ ተቋም ስራውን በአንድ



ስትራተጅ፣ በአንድ አመለካከት እየተመራ እስከሰራው ድረስ፣ ወጥነት ያለው የአቅም ግንባታ ራዕይ በሁሉም ዘንድ ተጨብጦ ሁሉም የአቅም ግንባታ ስራውን በዚሁ ራዕይ እየተመራ እስከሰራ ድረስ በተለያዩ አካላት የሚሰሩት ስራዎች ከአንድ ምንጭ የሚቀዱ ስለሆነም በባህሪያቸው የተቀናጁ መሆናቸው አይቀርም:: ከዚህ አኳያ ዋናው ስራ የተዘረዘረ የአቅም ግንባታ ስትራተጅና ይህንኑ ለማስፈፀም የተነደፉ ፕሮግራሞችን መቅረፅ፣ ሁሉም ፈፃሚ አካላት ይህንኑ በሚገባ ጨብጠው ስራቸውን በዚሁ መሰረት እንዲያከናውኑ ማድረግ ነው:: ይህ ስራ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራውን በአግባቡ ለማቀናጀትና ለማስተባበር ወሳኝ ቢሆንም ብቻውን ግን በቂ አይደለም::

ሁሉም መስሪያ ቤቶችና አካላት በአቅም ግንባታ ስራው ላይ በሰፊው እንዲሳተፉ የማድረጉ አሰራርና ሁሉም በአንድ ቅኝት እንዲመሩ ለማድረግ የሚያስችል የስትራተጅና የፕሮግራም ቀረፃና ይህንኑ የማስጨበጥ ስራ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንኑ በባለቤትነት የሚያስተባብር አካልም ያስፈልጋል:: በየደረጃው ያሉ መስሪያ ቤቶች በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት እየሄዱ መሆናቸውን ለመቆጣጠርና ለማስተባበር፣ ለመደገፍም የሚችል አካል ያስፈልጋል:: የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራዎች ግልፅ ቅደም ተከተል ወጥቶላቸው በቅደም ተከተሉ መሰረት እየተፈፀሙ መሆናቸውን የሚከታተልና የሚያስተባብር አካል ያስፈልጋል:: በተለይም ልዩ ትኩረት ይሰጣቸዋል ተብለው ተለያይተው የተቀመጡት የማስፈፀም አቅም ግንባታ አቅሞች በጥብቅ ተሳስረውና ተቀናጅተው እየተፈፀሙ መሆናቸውን የሚቆጣጠርና

የሚያስተባብር አካልም ያስፈልጋል፡፡ በየደረጃው የሚካሄዱ የአቅም ግንባታ ስራዎች ድግግሞሽን፣ የጊዜና የገንዘብ ብክነትን በማያስከትል ሁኔታ እንዲፈፀሙ የሚያስተባብር አካል ያስፈልጋል፡፡

አስተባባሪው አካል በእርግጥ አስተባባሪ እንጂ ራሱ ፈፃሚ ሊሆን አይችልም፡፡ ተደጋግሞ እንደተገለፀው የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራ በየደረጃው ባሉ ሁሉም የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በህዝቡና በግል ባለሃብቱ ጭምር የሚፈፀሙ እንጂ በአንድ አካል ሊፈፀሙ የሚችሉ አይደሉም፡፡ በአንድ አካል ይፈፀሙ ቢባሉም ስራው እንዳይሰራ አፍኖ ከመያዝ በስተቀር ሌላ ውጤት ሊያስገኝ አይችልም፡፡ ይሁንና ፈፃሚም ባይሆን አስተባባሪ አካል በሌለበት ስራው በተሳካ ሁኔታ ሊፈፀም አይችልም፡፡

አስተባባሪ አካል እንዲኖር ከማድረግ አኳያ ሁለት አማራጮች አሉ፡፡ አንደኛው አማራጭ በስራው ላይ የላቀ ሚና አላቸው የሚባሉትን መስሪያ ቤቶች የሚያሳትፍ አስተባባሪ ኮሚቴ አቋቁሞ ለማስተባበር መሞከር ነው፡፡ ይህ አሰራር ይህን ያህል ወሳኝ የሆነ ስራ በግልፅ ተለይቶ የተቀመጠ ባለቤት የሌለው የትርፍ ጊዜ ስራ እንዲሆን የሚያደርግ ነው፡፡ ባለፉት አመታት ስራውን በኮሚቴ ለማስተባበር ያደረግነው ሙከራ በግልፅ የሚያሳየው፣ የማስፈፀም አቅም ግንባታን የሚያክል ወሳኝ ስራ በዚህ አኳኋን መምራትና ማስተካከል እንደማይቻል ነው፡፡ ሌላው አማራጭ ይህንኑ ስራ የማስተባበር ሃላፊነት የተሰጠው አንድ መስሪያ ቤት እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡ ይህ መስሪያ ቤት በአንድ



በኩል የማስፈፀም አቅም ግንባታ አቅሞችን የማጎልበት ስራ በቀጥታ የሚመራና የሚያስተባብር በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ ላይ ተመስርቶ ሌሎች የአቅም ግንባታ ስራዎችንም የሚያስተባብር እንደሚሆን አድርጎ ማደራጀት ይቻላል፡፡ በቅርቡ የተጀመረው አደረጃጀትም ይኸው ነው፡፡ ይህ አደረጃጀት ከኮሚቴያዊ አደረጃጀት በጣም የላቀ ውጤት ሊያስገኝ የሚችል ለመሆኑ የእስካሁኑ ውሱን ልምዳችን በተጨባጭ እያረጋገጠው ያለ ጉዳይ ነው፡፡ በአጭሩ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራ በዋነኛነት በአንድ ወጥነት ባለው ስትራተጅና ፕሮግራም እንዲመራ በማድረግ ከዚሁ ጋር ተያይዞም ብቃት ያለው የማስተባበር ሃላፊነት የተሸከመ አደረጃጀት እንዲኖር በማድረግ ማስተባበር መቻል የስትራተጅው ቁልፍ አካል መሆን አለበት፡፡

### 4.5. የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራዎችን ከተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር ማጣጣም

የልማት ስራችን በግልፅ ተለይቶ በተቀመጠ የረጅም ጊዜ ስትራተጅና ማስፈፀምያ ፕሮግራሞች መመራት አለበት፡፡ እንደዚህ አይነት የረጅም ጊዜ ራዕይ የማይመራው የልማት ስራ ወጣ ገባ፣ ድግግሞሽ የበዛበት ከፍተኛ የጊዜና የገንዘብ ብክነት የሚያስከትል መሆኑ አይቀርም፡፡ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራችንም በልማት ስትራተጅያችን ላይ ተመስርቶ በረጅም ጊዜ እቅድ የሚመራ መሆን አለበት፡፡ በየወሩ በየአመቱ የሚገለባበጥ የረጅም ጊዜ እይታ የሌለው የማስፈፀም አቅም ስትራተጅ

የሚያጠግብ ውጤት ሊኖረው አይችልም። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ስትራተጅው በየጊዜው የሚከሰቱትን ለውጦች ለማካተትና በነዚሁ ለመጠቀም የሚችልም መሆን አለበት።

የልማት እንቅስቃሴያችንና ከዚህም ጋር ተያይዞ የሚከናወነው የማስፈፀም አቅም ግንባታ እንቅስቃሴያችን የማያቋርጡ ስራዎች ናቸው። አንዱ ስራ ሲፈፀም በዚሁ ላይ በመመስረት ሌላ ተጨማሪ የአቅም ግንባታ ስራ መስራትን የሚጠይቅ ነው። በዚሁ የአቅም ግንባታ የማያቋርጥ እድገት ሂደት ከእድገቱ ጋር አብረው የሚሄዱ መስተካከሎችና ተጨማሪ ስራዎች መኖራቸው የግድ ነው። የአቅም ግንባታ ስትራተጅያችን ይህንን የእድገትና የለውጥ ሂደት ተከትሎ የሚዳብር እንጂ ደርቆ የሚቀር መሆን የለበትም።

በልማትና በአቅም ግንባታ እንቅስቃሴያችን ሂደት አስቀድመው ያልታዩ ወይም ሊታዩ የማይችሉ ችግ ሮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ። በተመሳሳይ መልኩ አስቀድሞ ያልታዩ ወይም ሊታዩ የማይችሉ መልካም አጋጣሚዎችም ሊኖሩ ይችላሉ። እንደነዚህ አይነቶቹ ችግሮች ወይም መልካም አጋጣሚዎች በሚከሰቱበት ወቅት የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራተጅያችንና ፕሮግራሞቻችን ደርቀው ሊቆሙ አይችሉም፣ አይገባምም። ያልተገመቱትን ችግሮች ለመፍታት፣ በመልካም አጋጣሚዎቹ በላቀ ደረጃ ለመጠቀም በሚያስችል አኳኋን ሊዳብሩና ሊሻሻሉ ይገባል።



የማስፈፀም አቅም ስትራተጅያችን መሰረታዊ ይዘት ከላይ የተቀመጠው ሆኖ ይህንኑ ለማስፈፀም የሚያስችሉ ፕሮግራሞችም ተቀርፀው በመፈፀም ላይ ናቸው። በዚህ ፅሁፍ ፕሮግራሞቹን ዘርዝሮ ማስቀመጥ አይቻልም፣ አያስፈልግምም። በመጀመሪያ ደረጃ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራዎች ከልማት ስትራተጅዎቻችን ጋር በቅርብ የተቀናጁ በመሆናቸው በገጠርና ግብርና ልማት ፅሁፍ ላይ እንደተደረገው አብዛኞቹ ከልማት ስትራተጅዎቹ ጋር ተያይዘው ቢቀርቡ ይመረጣል። በሁለተኛ ደረጃ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራዎችን በሙሉ ለመዘርዘር መሞከር ማለት የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስራዎችን በሙሉ መዘርዘር ማለት ስለሚሆን የሚያስፈልግም የሚጠቅምም አይሆንም። በዚህ ፅሁፍ ላይ የምናተኩረው ቁልፍ በሆኑትና በሌሎች ፅሁፎች በበቂ ሁኔታ በማይሸፈኑት የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራዎች ላይ ይሆናል። በዚህ መሰረት ቀጥለን የምንመለከተው ጉዳይ የትምህርትና ስልጠና ስራችን ይሆናል።

# ክፍል ሁለት
# ትምህርትና ስልጠና

## 1. መግቢያ፣

የማስፈፀም አቅም ዋነኛው የልማት መሳሪያና ውጤት እንደሆነ፣ ከማስፈፀም አቅም ገፅታዎች ውስጥ አንዱ ብቃት ያለው የሰው ሃይል በሚፈለገው መጠን ማፍራት እንደሆነና የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራችን በመንግስት የማስፈፀም አቅም ግንባታ ብሎም እንደ ትምህርትና ስልጠና ባሉ የማስፈፀም አቅም ግንባታ አቅሞች ላይ ማተኮር እንዳለበት ተቀምጧል። በዚሁ መሰረት የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራማችን የማስፈፀም አቅም ግንባታ ፕሮግራማችን ቁልፍ ክፍል ሆኖ ይገኛል።

የማስፈፀም አቅም ዋነኛው የልማት መሳሪያና ውጤት በመሆኑና የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራማችን የማስፈፀም አቅም ግንባታ ቁልፍ ክፍል በመሆኑ ምክንያት ከዚህ የሚከተሉ መሰረታዊ ድምዳሜዎች መኖራቸው የግድ ነው። የያዝነውን የልማት አላማ ለማሳካት የልማት እንቅስቃሴዎቻችን ሁሉ ማዕከልና መሰረት የማስፈፀም አቅም ግንባታ በተለይም የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራማችን መሆን አለበት። በግልባጩ ደግሞ የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራማችን ግብ፣ መነሻና መድረሻ



ለልማት እቅዶቻችን ማስፈፀሚያ የሚሆን ብቃት ያለው የሰው ሃይል በሚፈለገው መጠን ማፍራት ይሆናል። በዚህ መሰረት ለምሳሌ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስራችን መብቱንና ግዴታውን ጠንቅቆ ያወቀ፣ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብና ባህል የተላበሰ የተማረ ዜጋን ኖና የተለያዩ የዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ተቋማትን በብቃት ሊያንቀሳቅስ የሚችል ባለሙያ ይጠይቃል። የገጠርና ግብርና ልማት፣ የከተማና የኢንዱስትሪ ልማት ወዘተ. ስራዎቻችንም በተመሳሳይ መልኩ በተለያየ ደረጃ የሰለጠነ ጠንካራ የስራ መንፈስና ስነ-ምግባር ያለው የሰው ሃይል ይጠይቃሉ። የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራማችን ግብ ይህን ማሟላት ነው። የልማት እንቅስቃሴዎቻችን ማዕከልም እንደዚህ አይነቱን የሰው ሃይል አፍርቶ በተለያዩ የልማት ስራዎች ላይ በብቃት ማሰማራት ነው።

የስልጠናና ትምህርት ፕሮግራማችን የልማት እንቅስቃሴያችን ቁልፍ መሳሪያ ብቻ ሳይሆን የልማቱ ውጤትም ጭምር ነው። በመሆኑም የልማት እንቅስቃሴያችን እየተጠናከረ በሚሄድበት ወቅት ከልማት ደረጃችን ጋር የሚመጥን የሰው ሃይል ለማፍራት የፕሮግራሙ አድማስና ጥራት እየተሻሻለ መሄድ ይኖርበታል። በመሆኑም ፕሮግራሙ በአንድ በኩል የያዝነውን የልማት እንቅስቃሴ ለማሳካት ኖና የሰው ሃይል ለማፍራት የሚያስችል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከልማት አቅዶቻችን መሳካት ጎን ለጎን በይበልጥ እየሰፋና ጥራቱ እየተሻሻለ የሚሄድ ይዘት ሊኖረው ይገባል።

የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራማችን በልማት እንቅስቃሴያችን በአጠቃላይም ሆነ በማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራችን ላይ በተለይ ያለውን ቁልፍ ሚና ሊጫወት የሚችለው ግልፅ የሆኑ አላማዎችና ግቦች ተቀምጠውለት ይህንኑ በአጥጋቢ ደረጃ ማሳካት ሲቻል ነው:: የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራማችን ግብ የልማት እቅዶቻችንን፣ የገጠርና የግብርና ልማት፣ የከተማና የኢንዱስትሪ ልማት፣ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ወዘተ. እቅዶቻችንን ለማሳካት የሚያስችል የሰው ሃይል በሚፈለገው መጠንና አይነት ማፍራት ነው:: እነዚህ እቅዶች በምን ደረጃ የሰለጠነ ምን ያህል የሰው ሃይል እንደሚያስፈልጋቸው መገመት ይቻላል:: የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራማችን ይህን መሰረት በማድረግ ዕቅዶቹ በሚፈልጉት መጠን የሰለጠነ የሰው ሃይል ለማቅረብ የሚችልና ይህንን በማሳካት አላማ የሚመራ መሆን አለበት:: የተቀመጡት እቅዶች ምን አይነት የሰው ሃይል እንደሚጠይቁም ይታወቃል:: ጥሩ የሙያ ችሎታ ያለው፣ በከፍተኛ ታታሪነትና የስራ ስነ-ምግባር የሚሰራና ስራ የሚፈጥር፣ የተሟላ ዴሞክራሲያዊ ስብእና ያለው የሰው ሃይል ነው የሚጠይቁት:: የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራማችን ስራውን ሰርቷል ሊባል የሚቻለው እንዲዚህ አይነቱን የሰው ሃይል በሚፈለገው መጠን ማፍራት ሲችል ነው:: ትምህርትና ስልጠናን በተመለከተ እስካሁን የተፈፀሙትንና ወደፊትም የሚፈፀሙትን ስራዎች ከዚህ በመነሳት ነው ልንቃኛቸው የሚገባን::



## 2. የአንደኛ ደረጃ ትምህርት፣

### 2.1. የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ስርጭት፣

አዲሱ የትምህርት ፖሊሲ ከወጣና ህዝቡም በአንደኛ ደረጃ ትምህርት መስፋፋት ስራ ላይ በሰፊው መሳተፍ ከጀመረ ወዲህ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን በማስፋፋት ረገድ እጅግ አበረታች ውጤት ተገኝቷል:: ባለፈው አመት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ሽፋን 57% መድረሱ አገልግሎቱ በጣም ፈጣን ሊባል በሚችል ደረጃ በመስፋፋት ላይ መሆኑን ያረጋግጣል:: የትምህርት አገልግሎቱ መስፋፋት በዋነኛነት በገጠር ላይ ያተኮረ መሆኑ፣ ለረጅም ጊዜ የትምህርት አገልግሎት ተነፍጎት የነበረው የህብረተሰብ ክፍል ይህንን እድል ማግኘት መጀመሩን የሚያረጋግጥና የስርጭቱን ፍትሃዊነት የሚያጠናክር ነው:: ከዚህ በተጨማሪ በወንዶችና በሴቶች መካከል በአገልግሎት ተጠቃሚነት ረገድ የነበረው ልዩነት እየጠበበ መምጣቱ ለስርጭቱ ፍትሃዊነት መጠናከር ከፍተኛ ትርጉም ይኖረዋል::

ይሁንና የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን በማስፋፋትና በተቻለ መጠን ሁሉም ዜጎች ይህን እድል እንዲያገኙ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው ችግሮች ይታያሉ:: በአርብቶ-አደሩ አካባቢ የትምህርት ስርጭት እድገት ዝቅተኛ ሆኖ ቀጥሏል:: ለዚህም ዋነኛው ምክንያት ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ ለሚኖረው ለዚህ ህዝብ ብቃት ያለው የትምህርት አገልግሎት በተመጣጣኝ ወጪ ለማቅረብ የሚያስችል ስርአት በመዘርጋት ረገድ ያለው ችግር ነው:: ከዚሁ በተጨማሪ በነዚህ አካባቢዎች ጠንካራና

የስራ ቅልጥፍና ያለው አስተዳደር በመመስረት ላይ ያሉ ችግሮችም ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል። እነዚህ ችግሮች በአፋጣኝ ካልተፈቱ በስተቀር በነዚህ አካባቢዎች ሊካሄድ የሚታሰበው የማስፈፀም አቅም ግንባታና የልማት ስራ መሰናከሉና በሁሉም አካባቢዎች ተመጣጣኝ ልማት ለማምጣት የምናደርገው ጥረት ቁልፍ መሳሪያ ከጥቅም ውጪ የመሆኑ አደጋ ጎልቶ መምጣቱ የማይቀር ይሆናል።

በአርብቶ-አደሩ አካባቢ ካለው የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን የማስፋፋት ስራ መጓተት በተጨማሪ በሌሎችም አካባቢዎች ስርጭቱን የሚያጓትቱ በርካታ ችግሮች አሉ። በዚህ ረገድ በዋናነት የሚጠቀሰው ችግር የፋይናንስ ችግር ነው። መንግስት የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ጨምሮ የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራምን ለማስፈፀም የላቀ ሚና መጫወት እንዳለበት ግልፅ ነው። ሌላው ቀርቶ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለመላው ዜጋ ለማዳረስ የሚፈለገው ወጪ እጅግ በጣም ከፍተኛ እንደሚሆን መገመት ያስቸግራል። የህዝቡ ቁጥር እየጨመረ የሚሄድ አገልግሎቱም ከዚሁ ጋር አብሮ መጨመር ያለበት ስለሚሆን ወጪው በዚያው መጠን እየናረ መሄዱ የማይቀር ነው። የአገልግሎቱን ጥራት በየጊዜው ለማሻሻልም ከፍተኛና ተጨማሪ ወጪ መጠየቁ የማይቀር ነው። በአጭሩ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ብቻውን የሚጠይቀው ወጪ በጣም ከፍተኛና በመንግስት አቅም ብቻ በሚፈለገው መጠንና ፍጥነት ሊሟላ የማይችል ስለሆነ፣ ይህንን የፋይናንስ ማነቆ የሚፈታ አማራጭ መሻት እጅግ አንገብጋቢ ሆኗል።



የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ስርጭት በተለይም በገጠሩ አካባቢ የሚገድቡ ሌሎች ችግሮችም አሉ። ህዝቡ ካለበት ድህነት በመነሳት ልጆቹን ለረጅም አመታት ለትምህርት ከመላክ በተለያዩ የቤት፣ የጓሮና የማሳ ስራዎች ላይ ማሰማራትን የሚመርጥበት ሁኔታ አለ። ድህነቱ እየተቀነሰ እስኪሄድ ድረስ አርሶ አደሩ ለራሱና ለልጆቹ የረጅም ጊዜ ጥቅም ቅድሚያ ሰጥቶ ልጆቹን በቀጣይነት ወደትምህርት ቤት የሚልክበትና ከዚህም ጋር ተያይዞ የገጠር የትምህርት ጊዜያት በአርሶ አደሩ የሰራተኛ ጉልበት ፍላጎት ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተፅእኖ በተቻለ መጠን የሚቀነስበት ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር ችግር ሆኖ መቀጠሉ የማይቀር ነው። በተመሳሳይ መልክ አንድ ሰው የሚማረው ተምሮ የመንግስት ተቀጣሪ ለመሆን ተደርጎ ስለሚወሰድና ሁሉም ሰው ተምሮ የመንግስት ተቀጣሪ ለመሆን እንደማይችል የታወቀ በመሆኑ፣ ተምሮ የት ሊቀጠር ነው በሚል ስጋት የሚፈጠር ችግርም አለ። እነዚህ የአመለካከት ችግሮች የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን በማስፋፋት ረገድ ቀላል ግምት የማይሰጣቸው ችግሮች ቢሆኑም ዋነኞቹ ችግሮች አይደሉም። በዋነኛነት ሊጠቀሱ የሚችሉት የፋይናንስ ችግሮችና፣ በአርብቶ አደሩ አካባቢ የሚታዩት ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ናቸው።

## 2.2. የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ጥራት፣

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት እንደሌላው የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራማችን ሁሉ ለልማት እንቅስቃሴያችን ተፈላጊ

የሆነውን የሰው ሃይል በሚፈለገው መጠንና አይነት ለማፍራት ተብሎ የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው፡፡ የትምህርት ስርአቱ በቁጥርም ሆነ በአይነት የሚያፈራቸው ወጣቶች ይህን አላማ ለማሳካት የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡ የትምህርት ስርአቱ ጥራትና ውጤታማነት የሚለካውም ከዚሁ አኳያ መሆን ይኖርበታል፡፡

በዚህ ረገድ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ለሁሉም ዜጎች በነፃ መዳረስ አለበት ብለን እየሰራን ነው፡፡ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ እንቅስቃሴያችንን አስተማማኝ ደረጃ ላይ የሚያደርሰው፣ ህገ-መንግስቱን ጠንቅቆ ያወቀ፣ መብትና ግዴታውን የሚገነዘብ ቢያንስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ያለው ዜጋ ሲኖረን ነው፡፡ ምንም እንኳ ከመሃይምነት ያልተላቀቀ ህዝብም ዴሞክራሲ የሚገባውና የሚፈልግ፣ በዴሞክራሲያዊ መብቶቹ ይብዛም ይነስም መጠቀም የሚችል ቢሆንም የዴሞክራሲ ስርአት በይበልጥ የሚጠናከረውና አስተማማኝ ደረጃ ላይ የሚደርሰው በተማረ ህብረተሰብ ውስጥ እንደሆነ የመላው አለም ልምድ የሚያረጋግጠው ነው፡፡ ስለሆነም የዴሞክራሲ ስርአታችንን በጠንካራ መሰረት ላይ የማኖር አላማችንን እውን ለማድረግ መላው ህዝባችንን የሚሸፍን የአንደኛ ደረጃ ትምህርት አገልግሎት ለማዳረስ ረጅም ርቀት ተጉዘናል፣ ባለን አቅም ሁሉ በመረባረብም ሁሉም ዜጎች ቢያንስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ያጠናቀቁ እንዲሆኑ እናደርጋለን፡፡

የገጠር ልማት እንቅስቃሴያችንን ባለን አርሶ አደር ላይ በመመስረት ልናፋጥነው የምንችልና የሚገባን ቢሆንም ባልተማረ



አርሶ አደር ላይ በመመስረት ሊመጣ የሚችል የገጠር ልማት ግን የራሱ ውሱንነት ያለው መሆኑ ገሃድ ነው፡፡ ቀጣይነት ያለው የቴክኖሎጂ እድገት በገጠርና በግብርና መስክ ለማስፋፋት ቢያንስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ያጠናቀቀ አርሶ አደር መያዝ ይጠይቃል፡፡ የግብርና ግብይት ስርአታችንን ዘመናዊና ቀልጣፋ ለማድረግ ቢያንስ በተመሳሳይ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ሃይል ያስፈልጋል፡፡ በኢንዱስትሪ በንግድ፣ በከተማ ልማትና በመሳሰሉት መስኮች ባልተማረ ሰራተኛ ሊመዘገብ የሚችል እድገት የለም ባይባልም፣ በነዚህ መስኮች በዝቅተኛ ደረጃ የሚሰሩ ስራዎችም ቢሆኑ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን የሚጠይቁ ናቸው፡፡ በሁሉም የኢኮኖሚና የማህበራዊ ልማት መስክ በብቃት ለመሳተፍ ቢያንስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን የሚጠይቅ በመሆኑ ይህንኑ ለሁሉም ዜጎቻችን በተቻለ ፍጥነት ለማዳረስ እየተረባረብን እንገኛለን ፡፡ ይህም ተገቢነቱ አያጠያይቅም፡፡

በኛ ተጨባጭ ሁኔታ የምንፈልገውን የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚና የማህበራዊ እድገት ለማረጋገጥ መላው ዜጋ ቢያንስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ያለው መሆን አለበት ስንል ስርአታችን የሚፈልገውን የሰው ሃይል በሚፈለገው መጠን ለማቅረብ በመቻል ረገድ አንዱ ዋነኛ ግቡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም ማዳረስ መሆን አለበት ማለት ነው፡፡ የትምህርትና ስልጠና ስርአታችን ገና እዚህ ደረጃ ላይ ያልደረሰ መሆኑ ስርአቱ መሰረታዊ ውሱንነት ያለበት እንደሆነ ያረጋግጣል፡፡ ይሁንና ስርአቱ መሆን ከሚገባው አኳያ ብቻ ሳይሆን ከተነሳንበት መሰረት በመነሳትም ጭምር የሚታይ

መሆን ይኖርበታል:: ከ60 ሚሊዮን ህዝብ በላይ ባለበት አገር ከ9 አመታት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ የትምህርት ሽፋናችንን ከነበረበት የ17% ደረጃ ወደ 57% ደረጃ ልናደርስ መቻላችን የሚያበረታታ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል:: በመሆኑም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ስርአታችን የሰው ሃይላችንን በሚፈለገው መጠን በማስተማር ረገድ የሚቀረው ብዙ ነገር ቢኖርም በዚህ ረገድ የተፈፀመው ስራ ከፍተኛና እጅግ የሚያበረታታ ነው::

አንድ ህብረተሰብ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ በብቃት ለመሳተፍ የሚያስፈልገውን ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ የሚወስነው ከልማት ደረጃው ጋር አስተሳስሮ ነው:: በአንዳንድ በከፍተኛ ደረጃ ባደጉ አገሮች እንኳንስና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ያለው፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያለውም ሰው በህብረተሰቡ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ኑሮ ውስጥ በብቃት መሳተፍ አይችልም:: በነዚህ አገሮች እንደግብ የሚወሰደውና መወሰድም ያለበት የአንደኛ ወይም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም ማዳረስ ሳይሆን ከፍተኛ ትምህርትን ለሁሉም ማዳረስ ነው:: በመካከለኛ የእድገት ደረጃ ላይ ያሉ አገሮች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም በማዳረስ ዜጎቻቸውን በብቃት ማሳተፍ ይችላሉ:: እኛ በዝቅተኛ የልማት ደረጃ ላይ የምንገኝ በመሆናችን የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም በማዳረስ ልማታችንን ማፋጠንና ህዝባችንን በብቃት ማሳተፍ እንችላለን:: ስለሆነም የሚፈለገው ዝቅተኛው የትምህርት ደረጃ ከልማት ደረጃው ጋር ተያይዞ መወሰን ይኖርበታል:: ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ሁለት የተሳሳቱ አዝማሚያዎች ይታያሉ::



በአንድ በኩል መላው ዜጋ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ይጨርስ ቢባል ያን ሁሉ ሰው የሚቀጥር ሰው ስለሌለ ተምሮ በከንቱ መቅረትን ያስከትላል በሚል ፈሊጥ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለመላው ዜጋ የማዳረስ አላማን የሚቃወም አዝማሚያ በተለያየ መልክ ይከሰታል:: በርግጥ በአገራችን ዘመናዊ ትምህርት ሲጀመር ለመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚያስፈልግ የሰው ሃይል ለማፍራት ተብሎ ነው የተጀመረው:: ከዚህ ጋር ተያይዞ የተፈጠረው አመለካከት ሰው የሚማረው ተምሮ በመንግስት ለመቀጠር ግፋ ቢል በኩባንያዎች ተቀጥሮ ለመስራት እንደሆነ አድርጎ መመልከት ነው:: ይሁንና በዚህ አመለካከት በመመራት ቀጣይነት ያለው አድገት ያስመዘገበ አገር የለም:: ከሚማረው የሰው ሃይል ውስጥ በመንግስት የሚቀጠረውና ሊቀጠር የሚችለው በጣም አነስተኛው ክፍል ነው:: ሰው የሚማረው ተምሮ በመንግስት ለመቀጠር ብቻ ሳይሆን በዋነኝነት በአገሩ የፖለቲካ ህይወት ላይ በንቃት ተሳታፊ እንዲሆን ነው:: በግብርና በንግድና በሌሎች መስኮች ሁሉ ስራ ፈጥሮ በብቃት ለመስማራትና በነዚህ የስራ መስኮች ምርታማነቱን አሻሽሎ የኑሮ ደረጃውን ከፍ ለማድረግ ነው:: በአጭሩ በአገሪቱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ብቃት ያለው ተሳትፎ ለማድረግ ሲል ነው ቢያንስ በህብረተሰቡ ተፈላጊ የሆነውን ዝቅተኛ ትምህርት ደረጃ ለማግኘት የሚጣጣረው::

ምንም እንኳ በአገራችን በተለያየ ደረጃ ተምረው (እስከ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ ጭምር) በዋነኛነት ሌላ አማራጭ ስራ ባለማግኘታቸው በግብርና ስራ ላይ የተሰማሩ በቀላሉ የማይገመት

ቁጥር ያላቸው ወጣቶች ቢኖሩም፣ ምንም እንኳ ከነዚህ ወጣቶች ውስጥ በርካታዎቹ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች የመቀበል የተሻለ ችሎታ ያላቸው በመሆኑ የኑሮ ደረጃቸው ከሌላው አርሶ አደር የተሻለ ቢሆንም፣ ተምሮ አርሶ አደር መሆን ታጥቦ ጭቃ ተብሎ የሚታይበት ሁኔታ ነው ያለው:: ይህ አመለካከት እስካልተቀየረ ድረስ በዘመናዊ አርሶ አደር የሚንቀሳቀስ ቀጣይነትና ፈጣን እድገት ሊያረጋግጥ የሚችል ግብርና ሊኖረን አይችልም:: በሌሎች የስራ መስኮችም ተመሳሳይ ችግር ማጋጠሙ አይቀርም:: አንድ ሰው ቢያንስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ከተማረ በደረጃው ተቀጥሮ የመስራቱ እድል እንዳለ ሆኖ በዋነኛነት ግን ራሱ ስራ ፈጥሮ በተለያዩ የአነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ ስራዎች፣ በግብርና፣ በተለያዩ የአገልግሎት ስራዎች ላይ በመሰማራት፣ በትምህርቱ ተጠቅሞ ምርታማነቱን አሻሽሎ ካልተማረው ሰው በጣም በላቀ ደረጃ ኑሮውን ለማሻሻል ዕድል እንደሚያገኝ፣ በአገሪቱ የፖለቲካ ህይወት ውስጥ ካልተማረው ሰው በእጅጉ በተሻለ ደረጃ የመሳተፍ ዕድል እንደሚኖረው ሊታመንበትና የትምህርትም አላማ ይህንን ማረጋገጥ እንደሆነ ሊጨበጥ ይገባል::

በሌላ በኩል ደግሞ ማንም ሰው ቢሆን ትምህርቱን በአንደኛ ደረጃ ላይ ማቆም የለበትም፣ እስከሁለተኛ ደረጃ ድረስ፣ ከዚያም ባሻገር መሄድ አለበት ብለው የሚከራከሩ አሉ:: ቀደም ሲል እንደተገለፀው የአቅም ግንባታ የልማት መሳሪያ ብቻ ሳይሆን የልማት ውጤትም ነው:: እንደኛ ያለው አገር ባለው የልማት ደረጃ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትንም ሆነ ከዚያ በላይ ያለውን ትምህርት ለሁሉም ዜጎች ማዳረስ አይችልም:: የአንደኛ ደረጃ



ትምህርትን ለሁሉም ዜጎች ለማዳረስ የሚደረገው ጥረት ብቻ እንኳ ከመንግስት የበጀት አቅም በላይ ነው:: የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በየቀበሌው በተሰራበት ሁኔታ እንኳ ቤተሰቦች በኢኮኖሚያዊ ችግር ምክንያት ልጆቻቸውን በሚፈለገው መጠን ለመላክ ሲቸገሩ ይታያል:: የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ከፍተኛ ትምህርት በየቀበሌው ማቋቋም ሊታሰብ እንደማይችል ገሃድ ነው:: ያለንበት ድህነት ልጆች በየቀበሌያቸው ወደሚገኝ ትምህርት ቤት እንዳይሄዱ እየገደባቸው ባለበት ሁኔታ ሁለተኛ ደረጃንና ከዚያ በላይ ያለውን ትምህርት ለሁሉም ማዳረስ ከመንግስት የበጀት አቅም በላይ ብቻ ሳይሆን ከህብረተሰቡም አቅም በላይ ነው:: ቢፈለግም አሁን ባለንበት የእድገት ደረጃ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል አይደለም::

ሁሉም ዜጋ ከአንደኛ ደረጃ በላይ የሚሄድ የትምህርት አገልግሎት ማግኘት አለበት የሚለው አስተሳሰብ ባለንበት የእድገት ደረጃ ከመንግስትና ከህዝቡ አቅም በላይ የመሆኑ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ ለልማታችን ተፈላጊና ጠቃሚ እንዳልሆነም ሊሰመርበት ይገባል:: ማንኛውም አገር የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ህይወቱን በመምራትና እድገቱን ለማረጋገጥ የሚያካሄደው የአቅም ግንባታ ስራ ከእድገቱ ጋር የሚመጥን መሆን አለበት:: በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በግብርና ዘርፍ ከፍተኛና ቀጣይ እድገት ለማምጣት ከአሁኑ ጀምሮ ምናልባት ለቀጣይ አስር አመታት በተራው አርሶ አደር ደረጃ የሚያስፈልገው የሰው ሃይል የዩኒቨርሲቲ ምሩቅ የሆነ አርሶ አደር ወይም የሁለተኛ ደረጃ ምሩቅ አይደለም:: በዚህ ደረጃ

ላይ የተወሰኑ የግብርና ሙያተኞች ማስፈለጋቸው ባይቀርም ተራው አርሶ አደር የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ያጠናቀቀ ከሆነ የልማት ፍላጎታችንን ለማሳካት በቂ ነው:: በዝቅተኛ የንግድ፣ ኢንዱስትሪና የመሳሰሉት ስራዎች የሚፈለገው የሰው ሃይልም ተመሳሳይ ነው:: ሃቁ ይህ ሆኖ ሳለ ሁሉም ዜጋ ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት በላይ ይሂድ ከተባለ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምሩቅ ሊሰራ የሚችለውን ስራ በዩኒቨርስቲ ምሩቅ ለማሰራት መሞከርን ያስከትላል:: እጅግ በጣም ከፍተኛ የሃብት ብክነትን በማስከተል ልማታችንን ያጓትታል:: በመሆኑም በኛ አገር ሁኔታ ሁሉም ዜጋ ከአንደኛ ደረጃ በላይ የትምህርት አገልግሎት ይድረሰው ሲባል ከመንግስትና ህዝብ አቅም በላይ የሆነ ሊፈፀም የማይችል፣ በሆነ ተአምር ይፈፀም እንኳ ቢባል ልማታችንን ክፉኛ ከማስተጓጎል በስተቀር የሚያስገኘው ጥቅም የሌለ መሆኑ ግሀድ ነው::

በማጠቃለል የትምህርት አገልግሎት ሽፋንን በተመለከተ ትክክለኛው አቅጣጫ ተግባራዊ እያደረግነው ያለነው አቅጣጫ ነው:: የህብረተሰባችንን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ለማፋጠን፣ ከልማት ደረጃችንና ከአቅማችንም ጋር የሚመጥነው የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም ዜጎች በተቻለ ፍጥነትና በነፃ ለማዳረስ መረባረብ ነው:: ይህንን ስናደርግም ይህን የትምህርት አገልግሎት ያገኘ ሰው በአገሪቱ የፖለቲካ ህይወት ላይ በብቃት ለመሳተፍና የዴሞክራሲ ስርአታችንን በጠንካራ መሰረት ላይ ለማኖር፣ በመንግስት ከሚቀጠረው በላይና ከዚሁ በተጨማሪ ይህ የተማረ የሰው ሃይል በግብርናም ሆነ በሌሎች



የልማት መስኮች በራስ ተነሳሽነት ስራ ፈጥሮ ምርታማነቱን አሳድጎ ኑሮውን ለማሻሻል ይችላል በሚል እምነት ላይ በመመስረት መሆን ይኖርበታል::

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ስርአታችን ብቃት የሚመዘነው በሚግረው የሰው ሃይል መጠን ብቻ አይደለም:: የመጠኑ ጉዳይ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ቢሆንም ዋነኛው የብቃቱ መመዘኛ የትምህርቱ ጥራት ነው:: ከትምህርት ጥራት ጉዳዮች ውስጥ አንዱ መሰረታዊ ጉዳይ የቀለም ትምህርቱ ጥራት ጉዳይ ነው:: የሚሰጠው የቀለም ትምህርት ደረጃው የተጠበቀ መሆኑ፣ ተማሪው ይህንኑ የቀለም ትምህርት በሚገባ የጨበጠውና የተረዳው መሆኑ ከዋነኛ የጥራት መመዘኛዎች አንዱ ነው::

የቀለም ትምህርቱን ጥራት ለመጠበቅ የስርአተ-ትምህርቱ ብቃት፣ የመማሪያ መሀፍትና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች መጠንና አይነት፣ የመምህራን መጠንና አይነት፣ ወዘተ… የመሳሰሉ ጉዳዮች ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል:: ከዚህ በመነሳት የቀለም ትምህርቱን ጥራት ለመጠበቅ ባለፉት አመታት ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል::

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት አወቃቀር እንዲቀየር ተደርጓል:: ከዚህ በፊት በአንድ ሳይክል እስከ ስድስተኛ ክፍል ብቻ በማስተማር ይጠናቀቅ የነበረው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በሁለት ሳይክል እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ የሚቀጥል ሆኗል:: በፊት እስከ አስራ ሁለተኛ ድረስ ይጨረስ የነበረው ትምህርት

እስከ አስር አመት ድረስ እንዲጨረስ ተደርጎ ስለተሸጋሸገ በአሁኑ ሰአት የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ይዘውት እንዲወጡ የሚጠበቀው እውቀት ከበፊተኛው የላቀ ነው። በመሆኑም በአሁኑ ሰአት የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ያጠናቀቀ ወጣት በፊት የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ካጠናቀቀው ወጣት የሁለት አመት ተጨማሪ ትምህርት የሚያገኝ ከመሆኑ ባሻገር በተደረገው የክፍሎች መሸጋሸግ ምክንያት የትምህርቱ ደረጃ በፊት የዘጠነኛና አስረኛ ክፍል ተማሪዎች ይሰጣቸው ከነበረው ትምህርት ጋር የሚመጣጠን ነው።

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የሚጠናቀቅበት ጊዜ በሁለት አመት ከፍ ማለቱና በዚሁ ጊዜ የሚሰጠው የትምህርት ደረጃም ላቅ እንዲል መደረጉ ሁለት መሰረታዊ ታሳቢዎችን ግምት ውስጥ ያላስገባ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ለመላው ዜጋ እንደሚዳረስ፣ ይህንን ለማድረግም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በከተማ ብቻ ሳይሆን በገጠርም በየቀበሌውና በየአቅራቢያው እንደሚመሰረቱ በዚህ ምክንያት ቀደም ሲል ኖንደነበረው አብዛኛው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የጀመረ ዜጋ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን ሳይጨርስ የሚወጣበት ሁኔታ እንደሚወገድ፣ ነገር ግን ደግሞ አሁን ባለንበት የእድገት ደረጃ አብዛኛው ተማሪ ከዚያ በላይ ሊቀጥል እንደማይችል ታሳቢ ያደረገ ነው። በሌላ አነጋገር ከዚህ በፊት የነበረውን ሁኔታ በመቀየር የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ለጥቂቶች መዳረሱ ቀርቶ ለሁሉም ዜጎች እንደሚዳረስ፣ አብዛኞቹ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የጀመሩ ተማሪዎች ይህንኑ ሳያጠናቅቁ ትምህርት የሚያቋርጡበት ሁኔታ



ቀርቶ ሁሉም የስምንት አመት ትምህርት እንደሚያገኙ፣ ይሁንና ለወደፊቱ እድገታችን ሲሻሻል ሊሆን ከሚችለው በተለየ ሁኔታ አብዛኛው ተማሪ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ ከዚያ በኋላ በቀጥታ የቀለም ትምህርቱን እንደማይቀጥልበት ተሳቢ ያደረገ ነው።

ብዙ ተማሪ እስከ ስምንተኛ ክፍል ተምሮ ከቀለም ትምህርት ውጪ የሚሆን እስከሆነ ድረስ በቅድሚያ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት አማካኝነት ከአገራችን የእድገት ደረጃና የልማት እንቅስቃሴ አኳያ በብቃት ተሳታፊ ለመሆን የሚያስችለው ትምህርት ሊኖረው ይገባል። በዚህ ላይ በመመስረት አጫጭር የሙያ ስልጠናዎች በማግኘት በተለያዩ የልማት እንቅስቃሴዎች ለመሳተፍ የሚያስችል ሙያ ሊኖረው ይገባል። በቂ የስነ-ዜጋ ትምህርት አግኝቶ፣ የስራ ተነሳሽነቱና ታታሪነቱ ጎልብቶ በአገሪቱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በብቃት መሳተፍ መቻል አለበት። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በሁለት አመት እንዲጨምር ከማድረግ ባሻገር በዚሁ ጊዜ የሚሰጠው ትምህርትም ላቅ ያለ እንዲሆን መደረጉ ተማሪውን ለተቀመጠው ግብ በብቃት ለማዘጋጀት ያስችላል። ጥራቱ የተጠበቀ፣ የአቅም ግንባታና የልማት እቅዶቻችንን ግቦች ለማሳካት የሚያስችል የቀለም ትምህርት ለመስጠት ያስችላል።

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በአንድ ሳይክል መሰጠቱ ቀርቶ በሁለት ሳይክል መሰጠቱም ለቀለም ትምህርቱ ጥራት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታል። በመጀመሪያዎቹ አራት አመታት

የፔዳጎጂ ሳይንስና የሰለጠኑ አገሮች ልምድ በሚጠቁመው መሰረት አንድ አስተማሪ ሁሉንም የትምህርት አይነቶች አጣምሮ ለህፃናቱ የሚያቀርብበትና ከፈተና ይልቅ በተከታታይ ምዘና ላይ ያተኮረ ስርአት እንዲኖር ለማድረግ ያስችላል፡፡ ትምህርት ጀማሪ የሆነውን ህፃን የተለያዩ አስተማሪዎች የተለያየ የትምህርት አይነት ለማስተማር እየገቡ፣ እየወጡ ከሚያስተምሩት ይልቅ አንድ አስተማሪ ሁሉንም የትምህርት አይነቶች እየሸፈነ፣ እያንዳንዱን ህፃን በቅርብ እየተከታተለና እየደገፈ ቢያስተምር እጅግ የላቀ ውጤት እንደሚገኝ የፔዳጎጂ ሳይንስ ያረጋግጣል፡፡ አንድ ህፃን አካባቢውን የሚገነዘበው ሁለገብ በሆነ አኳኋን ኖንደሆነ የማወቅ የመመራመር ባህል የሚያሳድገው በጥናትና ሽምደዳ ሳይሆን በዳሰሳ ኖንደሆነ ስለሆነም በአንድ አስተማሪ ሁለገብ የሆነ ትምህርት መስጠቱ ትክክለኛ ሳይንሳዊ አማራጭ ኖንደሆነ የስነ-ትምህርት ሙያተኞች ሁሉ የሚስማሙበት ነው፡፡ ህፃኑ ነገሮችን ከፋፍሎ ማየት የሚችልበት ደረጃ ላይ ኖስኪደርስ ድረስ በአንድ አስተማሪ ሁለገብ ትምህርት መስጠት፣ በተከኖኖይ ምዘና ኖና በዕለት-ተዕለት ድጋፍ ማብቃት ብቸኛ አማራጭ በመሆኑ ጥራቱ የተጠበቀ የትምህርት ስርዓት ያላቸው አገሮች ሁሉ ይህንን አቅጣጫ ይከተላሉ፡፡ የአገራችን የትምህርት ስርዓት ብቃቱ የተጠበቀ ኖንዲሆን ለማድረግም በስነ-ትምህርት ሳይንስ ከተረጋገጠው ከዚህ አቅጣጫ ውጪ አማራጭ የለንም፡፡ ይሁንና አቅጣጫው በአገራችን አዲስ በመሆኑ በአፈፃፀም ላይ የተለያዩ ችግሮች ማጋጠማቸው አይቀርም፡፡ ምንም ኖንኳን ባለፉት ዓመኖት አስተማሪ-ች ይህንን አቅጣጫ ተግባራዊ ለማድረግ የተወሰነ ስልጠና ኖንዲያገኙ ጥረት የተደረገ ቢሆንም የመምህራን ብቃት በየክፍሉ ያሉ የተማሪ-ች



ብዛት ወዘተ አቅጣጫውን የላቀ ውጤት ለሚያስገኝ አኳኋን ለመተግበር ኖንቅፋት ሆነዋል፡፡ ኖነዚህ ችግሮች የአፈፃፀም ችግሮች ናቸው፡፡ የአቅጣጫውን ሳይንሳዊነት በጥያቄ ምልክት ውስጥ የሚያስገቡ አይደሉም፡፡ መፍትሔው ሊሆን የሚገባው ሳይንሳዊነቱ የተረጋገጠውን አቅጣጫ መቀየር ሳይሆን ይህንኑ ሳይንሳዊ አሰራር በተግባር ላይ ለማዋል በምናደርገው የአፈፃፀም ኖንቅስቃሴ ሂደት የሚያጋጥሙትን ችግሮች ደረጃ በደረጃ ማስወገድ ነው፡፡

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በሁለት ሳይክል እንዲሰጥ፣ በሁለት አመት እንዲጨምርና የሚሰጠው የቀለም ትምህርት ላቅ ያለ እንዲሆን ማድረግ ለቀለም ትምህርቱ ጥራት መጠበቅ እጅግ በጣም አስፈላጊ ቢሆንም ይህ ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ ስርአተ-ትምህርቱ በየጊዜው እየተፈተሸ የተፈለገውን የሰው ሃይል ለማፍራት የሚያስችል መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡ በዚሁ መሰረት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ከላይ እስከታች ተፈትሾ እንደገና እንዲስተካከልና አዳዲስ የመማሪያ መፃህፍት እንዲዘጋጁ ተደርጓል፡፡ በዚህ ረገድ ከፍተኛ መሻሻል መደረጉ የማይታበል ቢሆንም ስርአተ-ትምህርቱ፣ በየጊዜው እየተገመገመ መሻሻል እንዳለበት፣ የመማሪያ መፃህፍት በየጊዜው መሻሻልና መከለስ እንዳለባቸው ሊሰመርበት ይገባል፡፡ አስተማማኝ የትምህርት ስርአት ያላቸው አገሮች ልምድ የሚያረጋግጠው በየጊዜው ስርአተ-ትምህርቱንና የመማሪያ መፃህፍትን እየገመገሙ ከማሻሻል ውጪ የአንድን አገር የትምህርት ስርአት ጥራት ጠብቆ ማቆየት እንደማይቻል ነው፡፡

የቀለም ትምህርቱን ጥራት ለመጠበቅ ሌላው ተፈላጊ ጉዳይ የመማሪያ መፃህፍትና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ተሟልቶ መገኘት ነው። በየትምህርት ቤቱ በቂ የመማሪያ መፃህፍት ለማዳረስ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። የሳይንስ ኪቶችንም ጨምሮ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ለማሟላትም ሰፊ ጥረት ተደርጓል። ከላይ እንደተገለፀው የቀለም ትምህርቱን ጥራት ለማጠናከር ከተሰራው ስራ በተጨማሪ የመምህራንን አቅርቦት በመጠንና በጥራት ለማሻሻል ሰፊ ጥረት በመደረግ ላይ ነው። በብዙ ሺ የሚቆጠሩ መምህራን ሰልጥነው ተመድበዋል፣ በመሰልጠን ላይ ያሉም አሉ። ሰፊ የሙያ ላይ ስልጠና ስራም እየተሰራ ነው። መምህራንን ለማትጋት የአገሪቱ አቅም በሚፈቅደው መጠን ደሞዝ ለማሻሻልና የእድገት ስርአቱን ለማስተካከል ጥረት ተደርጓል።

የቀለም ትምህርቱን ጥራት ለመጠበቅ በርካታ ስራዎች የተሰሩና ከዚህም አኳያ የተገኙ ውጤቶች ቢኖሩም በጥራቱ በኩል አሁንም በጣም ከፍተኛ ችግሮች ይታየሉ። ከዚህ አኳያ በዋነኛነት ሊጠቀስ የሚገባው የመምህራን ብቃት ጉዳይ ነው። የተደረገው ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ አሁንም የሚበዙት መምህራን ለስራቸው የሚመጥን ብቃት ያላቸው አይደሉም። በሚፈለገው መጠን ተሟልተው አለመገኘታቸው አንድ ጉዳይ ሆኖ የሚሰጣቸው ትምህርት ጥራቱ የተጠበቀ ያለመሆኑም ሌላው ጉዳይ ነው። መምህራንን ለማትጋት የተወሰዱ ርምጃዎች ቢኖሩም አሁንም ከአንድ መምህር የሚጠበቅ ስነ-ምግባር፣ አመለካከትና የስራ ተነሳሽነት የሌላቸው በርካታ አስተማሪዎች በስርአቱ ውስጥ አሉ። በእድገት ስርአቱ ከተቀመጠው አቅጣጫ ውጪም እድገት የሚያስገኙ አሉ። ይህም የሌላውን አስተማሪ የስራ ተነሳሽነት



በከፍተኛ ደረጃ እየጎዳው ይገኛል። የመምህራንን ብቃት የማረጋገጥና በሚፈለገው መጠን እንዲገኙ የማድረግ ጉዳይ በቀለም ትምህርት ጥራት ላይ ዋናው ጉዳይ መሆኑ ታውቆ መፍትሄ ሊፈለግለት የሚገባ አንገብጋቢ ጉዳይ ሆኗል።

በስርአተ-ትምህርቱ ላይና ስርአቱ በሁለት ሳይክል እንዲካሄድ የማድረጉ አሰራር ለቀለም ትምህርት ጥራት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው የሚታመንበት ቢሆንም የመምህራን በመጠንና በአይነት ተሟልቶ አለመገኘት ውጤታማነቱን እየተፈታተነው ይገኛል። በመጀመሪያዎቹ አራት አመታት ተማሪውን በአንድ አስተማሪና በተከታታይ ምዘና አማካኝነት የማስተማሩን ስርአት ተግባራዊ ለማድረግ በዚህ ደረጃ የሰለጠነ፣ አካሄዱን በሚገባ የሚያውቅና የሚያምንበት አስተማሪ በተፈለገው መጠንና አይነት ባለመገኘቱ በትክክል ተግባራዊ ሳይሆን ቀርቷል። በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ባለመሆኑና በጉዳዩ ላይ የተሟላ ግንዛቤ በሁሉም ዘንድ እንዲኖር ለማድረግ በቂ ስራ ባለመስራቱ ትልቅ መፍትሄ ይሆናል ተብሎ የታመነበት ጉዳይ እንደመፍትሄ ሳይሆን እንደችግር የሚታይበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። ደረጃው እንዲያድግ የተደረገው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ከዚሁ ጋር የሚመጥን አስተማሪ በሚፈለገው መጠን ባለመገኘቱ ከዚሁ ማግኘት የሚገባን የጥራት መሻሻል በሚፈለገው ደረጃ ሳይገኝ ቀርቷል። ስርአተ-ትምህርቱን በየጊዜው እየገመገሙ፣ የመማሪያ መፃህፍትን በየጊዜው እየፈተሹ በቀጣይነት የማሻሻሉ ጉዳይም በቀጣይነት ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው።

የቀለም ትምህርቱን ጥራት ከመጠበቅ አኳያ ዋነኛው

ችግር መምህራን በሚፈለገው መጠንና ብቃት አለመገኘታቸው ቢሆንም በትምህርት መርጃዎች ደረጃ ያለው ውሱንነትም ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው ጉዳይ ነው:: ሁሉም የመማሪያ መፃህፍት ለተማሪው በሚፈለገው መጠን እንዲዳረሱ፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች (የሳይንስ ኪቶች ወዘተ.) በየትምህርት ቤቱ በሚፈለገው መጠንና አይነት እንዲገኙ ማድረግ አልተቻለም:: ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅዎችን ለዚህ ስራ በሰፊው እየተጠቀምን አይደለንም:: በአንድ ክፍል ብዙ ተማሪዎች የመማራቸውና ትምህርት በፈረቃ የመሆኑ ጉዳይም ጥራቱ ላይ ከፍተኛ ጫና በማሳረፍ ለጥራቱ ማነስ አስተዋፅኦ ማበርከቱ አልቀረም:: እነዚህ ችግሮች በዋነኛነት የፋይናንስ እጥረት ውጤቶች ናቸው:: ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅን ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት በሰፊው የመጠቀሙ ጉዳይ ከፋይናንስ በተጨማሪ የቴሌኮምዩኒኬሽን አገልግሎት በሁሉም አካባቢዎች እንዲዳረስና ዘመናዊነቱን የጠበቀ እንዲሆን ማድረግን የሚጠይቅ ነው::

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ጥራት አንዱ መለያው የቀለም ትምህርቱ ጥራት ቢሆንም ይህ ብቻውን በቂ የጥራት መለኪያ ሊሆን አይችልም:: የትምህርት ስርአታችን በምንገነባው ዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ የነቃ ተሳትፎ ያለው ዜጋ መፍጠር ይኖርበታል:: የዴሞክራሲ አስተሳሰብና ባህል የሰፈነበት አገር ከመፍጠር አኳያ ትምህርት ቤቶች ቁልፍ ሚና መጫወት ይችላሉ፣ ይገባቸዋልም:: ለኛ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ጉዳይ በአገራችን መልካም አስተዳደር የማስፈን፣ ህገ-መንግስታዊ ግዴታ የመወጣት ጉዳይ ብቻ አይደለም:: የህዝቦቻችንን ሰላም፣



አንድነትና ህልውና የማረጋገጥ ጉዳይ ጭምር ነው:: ህዝባችንን እጅግ ዘግናኝ ከሆነ የድህነት አረንቋ የማላቀቅ ጉዳይ ጭምር ነው:: ትምህርት ቤቶቻችን ይህንን አላማ ለማሳካት ካልቻሉ ሌላውን ተልእኮዋቸውን ቢወጡም ዞሮ ዞሮ ግቡን የማይመታ ነገር ሆኖ መቅረቱ የማያጠራጥር ነው:: ዴሞክራሲ ሰላማችንንና ህልውናችንን ለማረጋገጥ፣ የያዝነውን የልማት አላማ ለማሳካት ወሳኝ ጉዳይ በመሆኑ፣ ይህ ባልተሳካበት ሁኔታ አስተማማኝ ሰላምና ቀጣይነት ያለው እድገት ስለማይኖር ይህንኑ የማይ ጨምር የትምህርት ስርአት ዞሮ ዞሮ ግቡን የማይመታ የትምህርት ስርአት መሆኑ የግድ ነው:: የትምህርት ስርአታችን የስነ-ዜጋ ትምህርትን እንደ አንድ ዋነኛ ነጥብ የወሰደ ቢሆንም፣ በዚህ ረገድ የተሰራው ስራ እጅግ በጣም ደካማ ነው::

በስነ-ዜጋ ትምህርት ጉዳይ ላይ የተሰራው ስራ እጅግ በጣም ደካማ የሆነባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ:: በዋነኛነት መጠቀስ የሚገባው ጉዳይ የአመለካከት ጉዳይ ነው:: የስነ-ዜጋ ትምህርትን በሚመለከት ያሉት የአመለካከት ችግሮች በሁለት ተከፍለው የሚታዩ ናቸው:: በመጀመሪያ ደረጃ የአንድ አገር ትምህርት ቤቶች የአገሪቱን ህገ-መንግስት መሰረት በማድረግ ዜጎች በህገ-መንግስቱ መንፈስ እንዲቀረፁ የማድረግ ዋነኛ ተልእኮ እንዳላቸው፣ በኛ አገር ሁኔታም በህገ-መንግስቱ ውስጥ የሰፈሩትን የዴሞክራሲ አስተሳሰቦች ማስረፅ፣ በዚሁ መንፈስ ወጣቶችን መገንባት እንዳለባቸው በሙሉ ልብ በመቀበልና ተግባራዊ ለማድረግ ቁርጠኛ ሆኖ በመነሳት ላይ ከፍተኛ የአመለካከት ችግር አለ:: በተጨማሪም የስነ-ዜጋ ትምህርት ሲባል ምን

እንደሆነ፣ በምን አይነት አኳኋን ቢፈፀም አስተማማኝ ውጤት እንደሚኖረው በመረዳት ላይ ከፍተኛ ችግር አለ።

ብዙ ሰዎች የስነ-ዜጋ ትምህርት መሰጠቱ በመላው አለም የሚሰራበት የተለመደ አሰራር ከመሆኑ ጋር አያይዘው የሚቀበሉት ቢሆኑም ይህ ስራ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መሰረታዊ ስራ እንደሆነ፣ ይህ ስራ በአጥጋቢ ሁኔታ ካልተሰራ በስተቀር ሌላው ሁሉ ከንቱ ሆኖ ሊቀር እንደሚችል ተገንዝበው በቁርጠኝነት ለማስፈፀም አይረባረቡም። ስለሆነም በዚህ ጉዳይ ላይ ለጉዳዩ ያላቸው ድጋፍ ከግብር ይውጣ ያለፈ አይደለም። በሌላ በኩል ደግሞ ለአገራችን ህገ-መንግስት ካላቸው ተቃውሞ በመነሳት ዜጎችን በህገ-መንግስቱ መንፈስ የመገንባቱ ስራ የትምህርት ቤቶች አንዱ ዋነኛ ስራ መሆኑን በጥብቅ የሚቃወሙ፣ ይህንን ማድረግ ትምህርትን የአንድ የፖለቲካ ድርጅት አላማ ማራመጃ መሳሪያ ማድረግ ነው ብለው የሚቃወሙም አሉ።

በመሰረቱ ማንኛውም ስርአትና በየትኛውም አገር ያለ መንግስት ትምህርት ቤቶችን ዜጎችን በአገሪቱ ህገ-መንግስት መንፈስ ለመቅረፅ ይጠቀምባቸዋል። በዚህ ጉዳይ ላይ በአገሮች መካከል ልዩነት የለም። ልዩነቱ የሚታየው በህገ-መንግስቱ ይዘትና በስነ-ዜጋ ትምህርት አሰጣጥ ስርአቱ ላይ ነው። ዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግስት ያላቸው አገሮች ዜጎቻቸውን በዚሁ መንፈስ ለመቅረፅ ይጣጣራሉ። ዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግስት የሌላቸውም ቢሆኑ ዜጎቻቸውን ባላቸው ህገ-መንግስት መንፈስ ለመቅረፅ



ይጣጣራሉ። አንዳንዶች የስነ-ዜጋ ትምህርትን ከሁሉም የትምህርት አይነቶችና የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ጋር አያይዘው እጅግ በጣም ውጤታማ በሆነ አኳኋን ይፈፅሙታል። ሌሎች ደግሞ ጥራትና ብቃት በሌለው አኳኋን ይፈፅሙታል። ትምህርት ቤቶችን ዜጎችን በህገ-መንግስት መንፈስ ለመቅረፅ የማይጠቀም መንግስት ግን በየትኛውም አገር የለም፣ ሊኖርም አይችልም።

የአንድ አገር ህገ-መንግስት የአገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ሁሉ የሚመሩበት መሰረታዊ ሰነድ ነው። የአገሪቱ ህጎች መሰረታዊ ምንጭና የህጎቹ ሁሉ አውራ ነው። ከህጎቹ ውጭና፣ የህጎች ሁሉ ምንጭና አውራ ከሆነው ህገ-መንግስት ውጭ የሚከናወን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እንቅስቃሴ የለም። የትምህርት ስርአቱ አላማ በአንድ አገር ውስጥ ገንቢ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሚና የሚጫወት ዜጋ መፍጠር ነው። ህገ-መንግስቱን ጠንቅቆ ያላወቀ በህገ-መንግስቱ መንፈስ መሰረት ያልተገነባ ዜጋ በህብረተሰቡ ውስጥ የሚፈለገውን ገንቢ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሚና ሊጫወት ከቶ አይችልም። በዚህ ምክንያት ነው ዜጎችን በህገ-መንግስቱ መንፈስ ለመቅረፅ የማያገለግል የትምህርት ስርአት የሌለውና ሊኖርም የማይችለው።

በአገራችንም አገሪቱ የምትመራበት ህገ-መንግስት አለን። ይህ ዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግስት የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ እንቅስቃሴያችን ሁሉ የሚመራበት መሰረታዊ ሰነድ ነው። የሁሉም ህጎቻችን መነሻና አውራ ነው። ይህንኑ ጠንቅቆ

ያላወቀና በዚህ መንፈስ ያልተቀረፀ ሰው በልማትና በዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ እንቅስቃሴው ውስጥ ገንቢና ብቃት ያለው ተሳትፎ ሊኖረው አይችልም፡፡ የትምህርት ስርአታችንም ይህንኑ ተልእኮ በአስተማማኝ መልኩ መፈፀም ካልቻለ መሰረታዊ ተልእኮውን ተወጥቷል ማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም የስነ-ዜጋ ትምህርት ለይስሙላ ወይም በግብር ይውጣ መልኩ ሳይሆን እንደ አንድ መሰረታዊ ተልእኮ ተወስዶ መፈፀም ያለበት ይሆናል፡፡ ይህ ተልእኮ በአስተማማኝ ሁኔታ ካልተፈፀመ የትምህርት ስርአቱ ግቡን እንደማይመታ ታሳቢ በማድረግ በሙሉ ልብና በቁርጠኝነት መፈፀም ያለበት ነው፡፡ በዚህ ረገድ ያለው የግብር ይውጣ አመለካከት አለመወገዱ ለስነ-ዜጋ ትምህርታችን እጅግ ደካማ መሆን ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

ኢትዮጵያውያን ወጣቶችን በአገሪቱ ህገ-መንግስት መንፈስ መገንባት የአንድን ድርጅት የፖለቲካ አላማ ለማራመድ ስለሚያገለግል መሞከር የለበትም በሚል የሚቀርበው የተቃውሞ አስተያየትም እጅጉን የተሳሳተ ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ኢትዮጵያም እንደሌሎቹ አገሮች ዜጎችን በትምህርት ቤት በስነ-ዜጋ ትምህርት መገንባት አለባት፡፡ ከዚህ ውጭ የሆነ ወይም ሊሆን የሚችል አገር የለምና ኢትዮጵያም ከዚህ ውጭ ልትሆን አትችልም፡፡ የስነ-ዜጋ ትምህርት መሰጠት ካለበት ደግሞ አገሪቱ በምትመራበት ህገ-መንግስት መሰረት ካልሆነ በስተቀር በሌላ በማንኛውም ሰነድ ላይ ሊመሰረት አይችልም፡፡ የስነ-ዜጋ ትምህርት ማስተማርና፣ ይህንኑ በአገሪቱ ህገ-መንግስት መንፈስ መፈፀም ምንም አይነት ሌላ አማራጭ የሌላቸው ነገሮች ናቸው፡፡



በአሁኑ ወቅት በስልጣን ላይ ያለው -ርቲ በህገ-መንግስቱ በጥብቅ የሚያምንና፣ ህገ-መንግስቱ በሚፀድቅበት ወቅት ግንባር ቀደም ሚና የተጫወተ መሆኑ ገሀድ ነው፡፡ ይሁንና ህገ-መንግስቱን በሙሉ ልብ ደግፈው እንዲፀድቅ የተንቀሳቀሱ ሌሎች -ርቲዎች እንደነበሩም ገሃድ ነው፡፡ በአንዳንድ የህገ-መንግስቱ ድንጋጌዎች ላይ ተቃውሞ ቢኖራቸውም ህገ-መንግስቱን በአጠቃላይ ደግፈው የተንቀሳቀሱ ሌሎች ድርጅቶች እንደነበሩም የታወቀ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ህገ-መንግስቱ ህዝቡ በዴሞክራሲያዊና ህጋዊ አኳኋን የመረጣቸው ተወካዮች በሰፊው ተከራክረው መንግስት የሚመራበት ሰነድ እንዲሆን ያፀደቁት የኢትዮጵያ ህዝብ ሰነድ ነው፡፡ ከፀደቀበት ከመጀመሪያው ሂደት ጀምሮ የአንድ ድርጅት ሰነድ ሳይሆን የተለያዩ ድርጅቶች የደገፉት የህዝብ ሰነድ ነው፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት እንዲመራበት በህጋዊ መንገድ የተቀመጠ ህጋዊ ሰነድ ነው፡፡ በዚህ ሰነድ መንፈስ ዜጎችን የመቅረፅ ተልእኮ የድርጅት ተልእኮ ሳይሆን የመንግስት ግዴታ ነው፡፡ ማንኛውም ድርጅት የመንግስትን ስልጣን ቢይዝ መፈፀም ያለበት ግዴታ ነው፡፡ አንድ የኢትዮጵያ መንግስት በሆነ ምክንያት ይህንን ሳይፈፅም ቢቀር፣ ወይም በግብር ይውጣ መልክ ቢያሰናክለው፣ የአገሪቱን የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራና ከዚሁም ጋር ተያይዞ የወደፊት ዕድልዋን ከማሰናከሉም ባሻገር ህገ-መንግስታዊ ግዴታውን በአግባቡ ሳይወጣ እንደሚቀር ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ መሆን የሚገባው ይህ ሆኖ ሳለ በመንግስታችን በተለይም በትምህርት ስርአቱ ዋነኛ ተዋናዮች ይህ ግንዛቤ በማያሻማ መልኩ ባለመያዙ የስነ-ዜጋ ትምህርታችን እጅግ በጣም

ደካማ ሆኗል፡፡

የስነ-ዜጋ ትምህርት በብቃት መሰጠት እንዳለበትና በዚህ ጉዳይ ላይ አንዳችም አይነት የማቅማማትና የግብር ይውጣ አዝማሚያ መኖር እንደማይገባው መቀበል ብቻውን የሚፈለገውን ውጤት ሊያስገኝ አይችልም፡፡ ውጤታማ በሆነ አኳኋን የሚፈፀምበት ስርአትም መቀየስ ይኖርበታል፡፡ ይህ ስርአት በየጊዜው እየተገመገመ መዳበርና መስተካከል ይገባዋል፡፡ ከዚህ አኳያ የስነ-ዜጋ ትምህርት ራሱን ችሎ በአንድ የትምህርት አይነት ደረጃ መሰጠቱ ብቻውን በቂ እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ጉዳዩ አመለካከት የመቅረፅ፣ ባህል የመገንባት ጉዳይ ስለሆነ ሁሉን አቀፍ በሆነ መልክ ካልተፈፀመ በስተቀር ሊሳካ እንደማይችል ሊታወቅ ይገባል፡፡ ሁሉም የትምህርት አይነቶች በየፊናቸው አመለካከትን ለመቅረፅ አስተዋፅኦ ማድረግ መቻል አለባቸው፡፡ የትምህርት ቤቱ አሰራር፣ አደረጃጀት፣ ከክፍል ውጪ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ወዘተ. ይህንኑ አመለካከት ለመቅረፅ የሚያስችሉ መሆን ይገባቸዋል፡፡ የስነ-ዜጋ ትምህርት እንቅስቃሴያችን በዚህ መልኩ ሁሉን አቀፍ ይዘት እንዲኖረው ስላልተደረገና አፈፃፀሙ በቀጣይነት እየተፈተሸ እንዲዳብር ባለመደረጉ በጣም ደካማ ሊሆን ችሏል፡፡

የስነ-ዜጋ ትምህርት በሚፈለገው ጥራት እንዳይከናወን ዋነኛ እንቅፋት የሆኑት ከላይ የተገለፁት የአመለካከት ችግሮች ቢሆኑም ይህንን የሚያስፈፅሙ መምህራንና የትምህርት ሃላፊዎች ያላቸው ብቃት ደካማ መሆኑም ከፍተኛ ሚና የነበረው ጉዳይ



ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ሁሉም መምህራንና የትምህርት ሃላፊዎች በጉዳዩ ላይ የተሟላ ግንዛቤና ጠንካራ እምነት እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያስችል በቂ ስራ አልተሰራም፡፡ ይህንኑ ትምህርት በብቃት ለመስጠት የሚያስችላቸው ስልጠና አልተሰጣቸውም፣ ውጤታማ የሆነ የትምህርቱ አሰጣጥ ስርአትም አልተዘረጋም፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ መምህራኑና የትምህርት ሃላፊዎች ትምህርት ቤቶች የስነ-ዜጋ ትምህርት በሚፈለገው መልክ እንዲሰጡ የማድረግ የዜግነትና የሙያ ግዴታ እንዳለባቸው የተገነዘቡበት ሁኔታ የለም፡፡ ተማሪው የተቀመጠለትን የሂሳብ ትምህርት በአግባቡ መማሩን የማረጋገጥ ግዴታ እንዳለባቸው ከሞላ ጎደል ይገነዘባሉ ማለት ይቻላል፡፡ ይህንኑ መፈፀም የማይችል ወይም የማይፈልግ አስተማሪ በአስተማሪነት መቀጠል እንደማይችልና እንደማይገባውም ከሞላ ጎደል ይገነዘባሉ ማለት ይቻላል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የስነ-ዜጋ ትምህርት በብቃት መሰጠቱን የማረጋገጥ ግዴታ እንዳለባቸው፣ ይህንኑ መፈፀም የማይችል ወይም የማይፈልግ አስተማሪ በአስተማሪነት መቀጠል እንደማይችልና እንደማይገባው የሚያውቁ ግን በጣም ጥቂቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም አስተማሪዎችና የትምህርት ሃላፊዎች በጉዳዩ ላይ የተስተካከለ ግንዛቤና የተሟላ እምነት እንዲኖራቸው፣ ትምህርቱን ለመስጠት የሚያስችል እውቀትና ብቃት እንዲያገኙ፣ ይህ ተግባር በጥብቅ የክትትልና አስተዳደራዊ ቁጥጥር ስርአት እንዲደገፍ ለማድረግ የተሰራው ስራ አጥጋቢ ስላልነበረ የስነ-ዜጋ ትምህርታችን እጅግ ደካማ ሆኖ ቆይቷል፡፡

የትምህርት ስርአታችን ከፍተኛ የስራ ተነሳሽነትና

ታታሪነት ያለው፣ ስራን የሚወድና የሚያከብር መልካም ስነ-ምግባር ያለው ዜጋ ማፍራት መቻል አለበት። ይህን የመሰለ ስነ-ምግባርና አመለካከት የሌለው ዜጋ በህብረተሰባችን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ብቃት ያለው ገንቢ ሚና መጫወት አይችልም። የትምህርት ስርአታችን አንድ የጥራት መመዘኛም በዚሁ መልክ ተማሪዎችን በብቃት የመቅረፅ ችሎታው መሆን ይኖርበታል። ይህንን ግብ ለማሳካት የማይችል የትምህርት ስርአት በሌላው መስክ ምንም ስራ ቢሰራ ዞሮ ዞሮ ታጥቦ ጭቃ ከመሆን ያለፈ ስራ ሰርቷል ሊባል አይችልም። ስርአተ-ትምህርታችን ይህንን ተገንዝቦ ከትምህርት መሰረታዊ አላማዎች አንዱ ስራ ወዳድና ጥሩ ስነ-ምግባር ያለው የሰው ሃይል ማፍራት እንደሆነ በግልፅ አስቀምጧል። ይሁንና በተግባር በዚህ ረገድ የተሰራው ስራና የተገኘው ውጤት በጣም አነስተኛ ነው። እዚህም ላይ ዋነኛው ችግር የአመለካከት ነው።

በአገራችን ዘመናዊ ትምህርት የተጀመረው በመመስረት ላይ ለነበረው ቢሮክራሲ የሚሆን የሰለጠነ የሰው ሃይል ለመፍጠር ነው። ከዚህ ባሻገር ሄደ ከተባለም በተወሰኑ ዘመናዊ ተቋሞች ተቀጥሮ የሚሰራ የሰው ሃይል ከማፍራት የሚያልፍ አላማ የነበረው አይደለም። ከአላማው ጋር የትምህርት ስርአቱ ቅኝት ይህን የመሰለውን የሰው ሃይል ለመፍጠር የሚያመች ነው የነበረው። የትምህርት አገልግሎቱ እየተስፋፋ ሲሄድ የተማረው ዜጋ በመንግስት ሊቀጠር ከሚችለው በላይ እየሆነ መጣ። ነገር ግን የትምህርት ስርአቱ ተማሪው ስራ ፈጣሪና ስራ ወዳድ እንዲሆን፣ በማንኛውም የስራ መስክ ስራ ፈጥሮም ሆነ ተቀጥሮ ምርታማነቱን በማሳደግ ኑሮውን ለማሻሻል የሚጣጣርና የሚችል እንዲሆን



ስላላደረገ ገና ትምህርት ለሁሉም ባልተዳረሰበት ሁኔታ ከፍተኛ የተማረ የስራ አጥ ሃይል ተፈጠረ። የተማረው ሰው በምንም አይነት የጉልበት ስራ ለመሰማራት ዝግጁነቱና ሙያው የሚጎድለው ስለነበረ የትምህርት ስርአቱ፣ ስራ ፈጣሪና ታታሪ ሰራተኛ የሰው ሃይል በማፍራት ልማትን ለማፋጠን የሚረዳ ሳይሆን ወጣቱን ከጉልበት ስራና ከስራ ፈጣሪነት እያፈናቀለ ስራ አጥነትን የሚያስፋፋ ስርአት ወደመሆን ተሸጋገረ። የአገራችን የትምህርት ስርአት በዚህ መልክ እጅግ በከፋ ቀውስ ውስጥ ገብቶ በነበረበት ወቅት ነው የፖሊሲ ለውጥ የተደረገው።

በሽግግሩ ዘመን የተደረገው የትምህርት ፖሊሲ ለውጥ ካሉት ዋነኛ ባህሪዎች አንዱ የትምህርት ስርአቱን ከገባበት የከፋ ቀውስ ለማውጣት የሚያስችል የትምህርት አላማ ማስቀመጡ ነው። በአዲሱ ፖሊሲ መሰረት የትምህርት አላማ የመንግስት ተቀጣሪን ማፍራት ብቻ አይደለም። የትምህርቱ ዋነኛ አላማ በተለያዩ ደረጃዎች የተማረና የሰለጠነ የሰው ሃይል በማፍራት በተለያዩ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች በብቃት የሚሳተፍ ዜጋን መፍጠር ነው። ወጣቱ ተምሮና የሙያ ስልጠና አግኝቶ በደረጃው ተቀጥሮም ሆነ ራሱ ስራ ፈጥሮ ምርትና ምርታማነትን በማሻሻል ኑሮውን የሚያሻሽልበት ሁኔታ እንዲፈጠር ማድረግ ነው የአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ አላማ።

በዚህ መሰረት ለምሳሌ ወጣቱ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ተምሮ የግብርና ሙያ ስልጠና አግኝቶ በግብርና ስራ ላይ በዘመናዊ

አርሶ አደርነት ተሰማርቶ ምርትን ከፍ በማድረግ ኑሮውን እንዲያሻሽል ማድረግ የትምህርት አላማ ይሆናል፡፡ ከዚያ የላቀ ትምህርት ያለው ደግሞ በግብርና መለስተኛ ሙያተኛነት ሰልጥኖ በመስኩ ይሰማራል፡፡ በዩኒቨርስቲ ደረጃ የተማረውም በከፍተኛ የግብርና ሙያተኛነትና ተመራማሪነት ይሰማራል፡፡ ከመለስተኛ ግንበኛና አናጢ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ኢንጅነርም በተመሳሳይ ደረጃ ይሰለጥናል፣ ይሰማራል፡፡ በዚህ መልክ በየደረጃው በተሻለ ሁኔታ የማምረት የስራ አቅምና ሙያ ያለው ሰው ተፈጥሮ ራሱ ስራ ፈጣሪ በመሆንና በተቀጣሪነት የሚሰማራ፣ የጉልበት ስራን የሚያከብር፣ ታታሪ፣ ጥሩ ስነ-ምግባር ያለው የሰው ሃይል የማፍራት አላማ ያለው ፖሊሲ አለን፡፡ ፖሊሲው ትምህርት የስራ አጥነት ማራመጃ መሳሪያ ከመሆን ተላቆ በየደረጃው መላውን ህዝብ በሚሸፍንና ስራ አጥነትን በማያስፋፋ መልክ እንዲስተካከል በማድረግ ከገባበት ቀውስ እንዲወጣ ለማድረግ የሚያስችል ነው፡፡

ይሁንና የዚህ ለውጥ መሰረታዊ ትርጉም በውል ተለይቶ ተማሪውና ህብረተሰቡ እንዲያውቀውና እንዲያምንበት አልተደረገም፡፡ በመሆኑም በብዙ አካባቢዎች የመማር አላማ በመንግስት ተቀጣሪ በመሆን የቢሮ ሰራተኛ ለመሆን፣ ግፋ ቢል ደግሞ በታላላቅ ኩባንያዎች ቢሮና መሰል ኩባንያዎች ለመቀጠር ተደርጎ ነው እየተወሰደ ያለው፡፡ የትምህርት ስርአቱ አላማ በፈፃሚውም በተጠቃሚውም ዘንድ በአግባቡ አልተጨበጠም፡፡ የትምህርት ስርአቱ የትምህርት አላማውን ስላልጨበጠውና ተጠቃሚው እንዲጨብጠው ስላደረገም ጥሩ የስራ ተነሳሽነትና



ታታሪነት፣ ስራ አክባሪነትና ወዳድነት፣ መልካም ስነ-ምግባርን በተማሪው ላይ ለመቅረፅ አጥጋቢ ጥረት ሲያደርግ አይታይም፡፡ በዚህ ደረጃ የተማሪውን አስተሳሰብ መቅረፅና የሚፈለገውን ስነ-ምግባር እንዲጨብጥ ማድረግ ለትምህርት ስርአቱ ጥራት መጠበቅና አላማውን እንዲያሳካ ለማድረግ ወሳኝ ሚና ከሚጫወቱ ጉዳዮች አንዱ መሆኑን በቅጡ ባለመገንዘብ ተግባራዊ የሚሆንበት ምቹ ሁኔታ ሳይፈጠር ቆይቷል፡፡

የትምህርት ስርአቱን አላማ በሚገባ ባለመገንዘብ፣ ከዚህ አኳያ በተማሪው ዘንድ መልካም የስራ አመለካከትና ስነ-ምግባር እንዲሰፍን ማድረግ ሊሰጠው የሚገባ ትኩረት ምን እንደሆነ በቅጡ ባለመገንዘብ የተፈጠረው የአመለካከትና ከዚሁ ጋር የተያያዘ የአፈፃፀም መዛባት ዋነኛ ችግር ሲሆን እንደዚህ አይነቱን ባህልና አመለካከት በትምህርት ቤት ውስጥ በምን አይነት መልክ መቅረፅ እንደሚቻል ባለማወቅ የተፈጠረ ችግርም ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው የአመለካከት ችግር ነው፡፡ በነዚህ ሁለት የአመለካከት ችግሮች ምክንያት የትምህርት ስርአታችን የሚፈለገው የስራ አመለካከትና ስነ-ምግባር ያለው ተማሪ በማፍራት ረገድ አጥጋቢ ስራ ለመስራት የማይችል ሆኖ ቆይቷል፡፡

የትምህርት ስርአት ውጤታማነት ሊለካ የሚገባው በስርጭቱ ስፋትና በአገልግሎቱ ጥራት ሲሆን ጥራቱም በቀለም ትምህርቱ ጥራት፣ በስነ-ዜጋ ትምህርት ጥራትና በስራ አመለካከትና ስነ-ምግባር ቀረፃ ትምህርት ጥራት መመዘን ያለበት ይሆናል፡፡ የትምህርት ስርአታችን ጥራት በሶስቱም መመዘኛዎች ሲመዘን በጣም ከፍተኛ ችግር ያለበት ሆኖ ይታያል፡፡ በቀለም

ትምህርቱ ጥራት ረገድ የተሻለ ስራ የተሰራ ቢሆንም በዋነኛነት በመምህራን መጠንና ጥራት ችግር እንደዚሁም በፋይናንስ ችግር ምክንያት የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ አይደለም፡፡ የስነ-ዜጋ፣ የስራ አመላከከትና ስነ-ምግባር ትምህርትን በተመለከተ በተለይም በመምህራንና አስፈፃሚ አካላት ዘንድ ባሉ የአመላከካት ችግሮች፣ ይህን ትምህርት በብቃት ለመስጠት የሚያስችል ስርአትና ጥብቅ የክትትል ስልት ባለመነደፉ ትርጉም ያለው ስራ ተሰርቷል ሊባል የማይችልበት ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ጥራት ችግሮች እስከነምንጫቸው በሚገባ በመረዳት በአፋጣኝ መፍታት በትምህርት ስርአታችን ላይ ከተደቀኑት ዋነኛ ተግባሮች አንዱ ሆኖ ይገኛል፡፡

### 2.3. የአንደኛ ደረጃ የመማሪያ ቋንቋ፣

አዲሱ የትምህርት ፖሊሲ ህፃናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የመማር መብት እንዳላቸው ያረጋግጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎች የፌዴራል መንግስት የስራ ቋንቋ የሆነውን አማርኛ እንዲማሩም ያደርጋል፡፡ በአለም አቀፍ ደረጃ ሰፊ ተቀባይነት ያገኘና በአሁኑ ሰአት የአለም ህብረተሰብ ከሞላ ጎደል እንደ ዋነኛ መግባቢያ ቋንቋ እየወሰደው ያለው እንግሊዘኛም በአንደኛ ደረጃ በተከታታይ ለስምንት አመታት እንደሚሰጥ ይደነግጋል፡፡ በዚህም ረገድ ፖሊሲው በፊት ከነበረው የተለየና በጣም የተሻለ ፖሊሲ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በዚህ ረገድ የአዲሱ ፖሊሲ መለያ ነጥብ ህፃናት በአፍ



መፍቻ ቋንቋቸው የመማር መብት ያላቸው መሆኑን ማስቀመጡና ይኸው መብት በበርካታ አካባቢዎች ተግባራዊ መሆን መጀመሩ ነው፡፡ ህፃናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የመማር መብት ይከበርላቸዋል ተብሎ የተደነገገው በፔዳጎጅካዊና በፖለቲካዊ ምክንያቶች ነው፡፡

ህፃናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በሚማሩበት ወቅት፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ባልሆነ ቋንቋ ከሚመሩበት ወቅት እጅግ በተሻለ አኳኋን ትምህርቱን እንደሚረዱት በፔዳጎጅ ሳይንስ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ አንድ ህፃን የአፍ መፍቻው ባልሆነ ቋንቋ በሚማርበት ወቅት ትምህርቱን ለመረዳት ሁለት መሰናክል ማለፍ አለበት፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የማያውቀውን ቋንቋ የማወቅ መሰናክል ማለፍ አለበት፡፡ ከዚያ ቀጥሎና ከዚሁ በተጨማሪ የሚቀርብለትን አዲስ ትምህርትና እውቀት የመረዳት መሰናክልን ማለፍ አለበት፡፡ በአፍ መፍቻ ቋንቋው በሚማርበት ወቅት ግን አዲሱን እውቀት የመቅሰም መሰናክልን ብቻ ነው የሚያልፈው፡፡ ስለሆነም በአፍ መፍቻ ቋንቋው ሲማር መሰናክሉ ይቀልለታል ትምህርቱን ለመረዳት በጣም የተሻለ ይሆንለታል፡፡ ይህም በመሆኑ የስነ-ትምህርት ጠበብቶች የሚደግፉት ህፃናት በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማራቸውን ነው፡፡ ይህን እንደተባበሩት መንግስት የሳይንስና ትምህርት ተቋምና (ዩኔስኮ)ና እንደ አለም መምህራን ማህበር ድርጅት ያሉ በትምህርት ጉዳይ ላይ ያገባናል የሚሉ አለም አቀፍ ድርጅቶችም በጥብቅ የሚደግፉት ነው፡፡

ህፃናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የመማር መብት

እንዲረጋገጥላቸው የሚፈለግበት ፖለቲካዊ ምክንያትም አለ። ማንም ህዝብ በራሱ ቋንቋ የመጠቀምና ባህሉን የማዳበር መሰረታዊ መብት አለው። እነዚህ መብቶች በህዝቦችና ዜጎች ሰብአዊ መብት ደረጃም እውቅና ያገኙ ናቸው። በአገራችን የዜጎችና የህዝቦች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በአስተማማኝ ሁኔታ ለማስከበር ከፍተኛ ጥረት በሚደረግበት ወቅት የህፃናት በአፍ መፍቻ ቋንቋ የመማር መብት መከበሩም ተገቢ ነው። ይህ መብት እንዲከበር አለማድረግ የአገራችንን ህገ-መንግስትና ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ልዩ ልዩ አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ሰነዶችን መፃረር ይሆናል። እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባ አንድ መሰረታዊ ጉዳይ አለ። -ሊሲው በአፍ መፍቻ ቋንቋ የመማር መብትን ያስከብራል እንጂ ይህንኑ እንደግዴታ አያስቀምጥም። በመሆኑም በአፍ መፍቻ ቋንቋው ለመማር አቅሙ ያነሰው ወይም ፍላጎቱ የሌለው ማንኛውም ህዝብ በመረጠው ቋንቋ መማር ይችላል። በአፍ መፍቻ ቋንቋ ለመማር የፈለገውና የቻለው በዚሁ ይጠቀማል፣ በዚሁ ለመማር ያልቻለ ወይም ያልፈለገ ደግሞ በሌላ በፈለገው ቋንቋ መጠቀም ይችላል። በመሆኑም በአገራችን ካሉት ብሄር/ብሄረሰቦች በአሁኑ ሰአት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሚማሩት ከግማሽ በታች ናቸው። ሌሎቹ መብቱ የተከበረላቸው ቢሆንም በመብቱ ለመጠቀም አቅሙ ስላነሳቸው ወይም ፍላጎት ስለሌላቸው በሌላ በመረጡት ቋንቋ በመማር ላይ ናቸው።

በአንደኛ ደረጃ የትምህርት ቋንቋ ጉዳይ ላይ የተለያዩ ትችቶች ይነሳሉ። የኢትዮጵያን ወጣት በተለያዩ ቋንቋዎች



ማስተማር የህዝቡን አንድነት ያናጋል፣ በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች እንደልቡ ተንቀሳቅሶ እንዳይሰራ የሚያደርግ የመግባቢያ ቋንቋ ችግር ይፈጥራል በሚል የሚቀርብ ትችት ከዋናዎቹ ትችቶች አንዱ ነው። ፖሊሲው ህፃኑ በአፍ መፍቻ ቋንቋው እንዲማር መብት ቢሰጠውም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ አማርኛ ቋንቋን እንዲማር የሚያደርግ ነው። አማርኛ የጋራ መግባቢያ ቋንቋችን እንዲሆን መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በተወካዮቹ አማካይነት የወሰነና በህገ-መንግስታችን ውስጥ እንዲሰፍር ያደረገ በመሆኑ ተማሪው አማርኛን የመማር ግዴታ እንዲኖርበት ማድረግ ትክክለኛ ነው። ለብዙ አመታት አማርኛን በቋንቋነት የተማረ ወጣት በአማርኛ ለመግባባት የሚቸገር አይሆንም። የሚቸገር ከሆነም ይህን ያህል አመት በተማረው ቋንቋ ለመጠቀም ያልቻለበት ምክንያት ቋንቋውን የማስተማርያ ዘዴያችን በጣም ደካማ ከሆነ ብቻ ነው። በአፍ መፍቻ ቋንቋው መማሩ አማርኛን ለበርካታ አመታት ተምሮ እንዳያውቅ የሚያደርገው አይደለም። ስለሆነም ፖሊሲው አንድ የመግባቢያ ቋንቋ እንዲኖረን የሚያደርግ እንጂ የመግባቢያ ቋንቋ እንዳይኖረን የሚያደርግ አይደለም። በተለይም የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥራት ከተጠበቀ በአጭር ጊዜ ውስጥ ቋንቋውን በሚገባ ሊያውቅ የሚችልበትን ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር ነው።

ህዝቦች በራሳቸው ቋንቋ ስለተማሩ፣ ከጋራ መግባቢያ ቋንቋቸው በተጨማሪ የራሳቸውን ቋንቋ በሚገባ ስላወቁ አንድነታቸው የሚላላበት አንድም ምክንያት የለም። ህዝቦችን የሚለያየውና የሚያቃቅረው ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብታቸው

መከበሩ ሳይሆን እነዚህ መብቶች ሳይከበሩ ሲቀሩ ነው፡፡ ስለሆነም ቅሬታና ቅራኔን በመፍጠር ለህዝቦች አንድነት ሳንካ የሚሆነው በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የመማር መብታቸው ሲነፈግ ነው፡፡ ህዝቦች በቋንቋቸው ከተማሩ አንድነታቸው ይላላል የሚለው አመለካከት፣ የተለያዩ ህዝቦች መለያ ባህሪዎችን በማጥፋት ብቻ ነው አንድነት መፍጠር የሚቻለው ከሚል የልዩነት ማጥፋት (አሲሚሌሽኒስት) አመለካከት የሚመነጭ ነው፡፡ የህዝቦችን መለያ ባህሪ በአስተዳደራዊ መንገድ የማጥፋት፣ በዚሁ አማካኝነት "አንድነት" የመፍጠር አመለካከት አገራችንን ጨምሮ በአለማችን በብዙ አገሮች በእብሪተኞች ለረጅም ጊዜ የተሞከረና የከሸፈ ጉዳይ ነው፡፡ አድልዎንና ጭቆናን አስከትሎ የብሄሮች ቅራኔን በከፍተኛ ደረጃ  ከማባባስና ደም መፋሰስን ከማስከተል ውጪ ያረጋገጠው አንድነት የለም፡፡ በመሆኑም የትምህርት ፖሊሲያችን የህዝቦችን መብት በማስከበር ለጠንካራ አንድነታችን መሰረት የሚጥል እንጂ አንድነታችንን የሚያላላ አይደለም፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ የሚቀርበው ሌላው ትችት ተማሪው ለስምንት አመታት በአካባቢ ቋንቋ ተምሮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ላይ በእንግሊዘኛ እንዲማር ሲደረግ ቋንቋውን በሚገባ ሳያውቅ አሁን ባለንበት አለም ንቁ ተሳታፊ ሊሆን የማይችል ይሆናል፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱም በጣም ይከብደዋል የሚል ነው፡፡ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ከሞላ ጎደል የአለም መግባቢያ ቋንቋ በመሆኑ የአገራችን ተማሪዎች ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ እንደቋንቋ እንዲማሩት ተደርጓል፡፡ የእንግሊዝኛ ቋንቋን ውጤታማና ዘመናዊ በሆነ መንገድ ማስተማር በተቻለባቸው አካባቢዎች ከአንድ አመት



ባነሰ ጊዜ ውስጥ በቋንቋው መጠቀም የሚቻልበት ደረጃ ላይ እንደሚደረስ ይታወቃል፡፡ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ቋንቋዎችም ተመሳሳይ ስራ መስራት እንደሚቻል የታወቀ ነው፡፡ ይህ በመሆኑም የከፍተኛ ትምህርትን በራሳቸው ቋንቋ የሚያስተምሩ አገሮች ከውጭ ለከፍተኛ ትምህርት የሚያስገቧቸውን ተማሪዎች ከስድስት ወር እስከ አንድ አመት ድረስ ቋንቋቸውን አስተምረው ከፍተኛ ትምህርት በብቃት እንዲከታተሉ እንደሚያደርጓቸውም ይታወቃል፡፡ እኛ ለስምንት አመታት ቋንቋውን አስተምረን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን በእንግሊዘኛ ቋንቋ ለመከታተል እንዲችል ማድረግ እያቃተን ነው፡፡

የዚህ ችግር መሰረታዊ መነሻ የቋንቋ ትምህርት አሰጣጣችን ያለው ውጤታማነትና ዘመናዊነት ነው፡፡ ሌሎች በስድስት ወራትና በአንድ አመት የሚፈፅሙትን በስምንት አመታት መፈፀም ካቃተን መፈተሽ ያለበት የመማሪያ ቋንቋ እንግሊዘኛ መሆኑ አለመሆኑ አይደለም፡፡ የቋንቋ ትምህርቱ ጥራት ነው መፈተሽ ያለበት፡፡ ቋንቋውን የሚያስተምሩ መምህራን ብቃት አጠያያቂ ነው፡፡ ቋንቋውን በደንብ የማያውቁ መምህራን ቋንቋውን እንዲያስተምሩ የሚመደቡበት አጋጣሚ አለ፡፡ የቋንቋ ትምህርት ስርአቱ እጅግ ኋላ ቀር ነው፡፡ በዚህ ላይ መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት ከተቻለ እንግሊዘኛ የአንደኛ ደረጃ የመማሪያ ቋንቋ ባይሆንም በስምንት አመታት ውስጥ በቋንቋው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን በብቃት ለመከታተል የሚቻልበት ደረጃ ላይ መድረስ የማይቻልበት ምንም ምክንያት ሊኖር አይችልም፡፡

የቋንቋ ትምህርቱ ጥራት ባልተጠበቀበት ሁኔታ እንግሊዝኛን በፊት እንደነበረው ከስምንተኛ ክፍል እንዲጀምር ቢደረግም ችግሩን ሊቀርፈው አይችልም። በአፍ መፍቻ ቋንቋው ሲማር የቆየ ወጣት በእንግሊዘኛ መማር ሲጀምር የቋንቋ ትምህርቱ ጥራት እስከጎደለው ድረስ ትምህርቱን ለመከታተል መቸገሩ አይቀርም። በእንግሊዘኛ መማር የሚጀምረው ሰባተኛ ክፍል ላይ ቢሆንም የሰባተኛ ክፍል ትምህርትን ለመከታተል መቸገሩ አይቀርም። በእንግሊዝኛ መማር የሚጀምረው ዘጠነኛ ክፍል ላይ ከሆነም እዚያ ሲደርስ መቸገሩ አይቀርም። እንግሊዝኛን ለስምንት አመት በቋንቋ ትምህርት መልክ ሲማር ቆይቶ ወደመማሪያ ቋንቋነት ሲያሸጋግረው ለስድስት አመት ተምሮ ከሚሸጋገርበት አካሄድ የተሻለ ጊዜ አግኝቶ ቋንቋውን ለመማር እድል ስለሚያገኝ ሊቀልለት ይችላል፣ ይገባልም። ስለሆነም እንግሊዝኛን በመማሪያ ቋንቋነት የመጠቀሚያ ጊዜን ማዘግየት ከአንድ መማሪያ ቋንቋ ወደሌላ መማሪያ ቋንቋ ሽግግር በሚደረግበት ወቅት የሚፈጠረውን የቋንቋ ችግር ያቃልለዋል። ከዚህ አኳያም ሲታይ ፖሊሲው ችግሩን የሚያቃልል እንጂ የሚያባብስ ሊሆን አይችልም።

ቋንቋው የመማሪያ ቋንቋ በመሆኑ ምክንያት ብቻ ተማሪው ቋንቋውን በይበልጥ የሚያውቅበት ሁኔታ ይፈጠራል ብሎ መገመትም አይቻልም። የሚሰጠው የቋንቋ ትምህርት ደካማ እስከሆነ ድረስ ቋንቋውን የመማሪያ ቋንቋ በማድረግ የሚቀረፍ ችግር የለም። ቀደም ሲል ከሰባተኛ ክፍል ጀምሮ



ተማሪው በእንግሊዘኛ እንዲማር ሲደረግ እንደነበር ይታወቃል። በዚህ መልክ የተማሩ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች እንግሊዝኛን ጠንቅቀው ያወቁበት ሁኔታ ግን ሊፈጥር አልቻለም። ይባስ ብሎ በዚሁ ስርአት ያለፉ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችም ቢሆኑ ቋንቋውን ጠንቅቀው አውቀውታል ሊባል የሚችልበት ሁኔታ ላይ አይደሉም። የመማሪያ ቋንቋው እንግሊዘኛ ነው ሲባልም ተማሪዎቹ ቋንቋውን በሚገባ ካለማወቃቸው የተነሳ አልፎ አልፎም አስተማሪዎቹ ሃሳባቸውን በተሟላ አኳኋን በእንግሊዝኛ መግለፅ ባለመቻላቸው ትምህርቱ በቅይጥ ቋንቋ የሚሰጥበት ሁኔታ ነው የሚታየው። ተማሪውም ባልተቀየደ አኳኋን ሃሳቡን ለመግለፅም ሆነ ለመረዳት የሚቸገርበት ሁኔታ ነው የሚስተዋለው። ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው የቋንቋ ትምህርት ስርአታችን ጥራት ባልተጠበቀበት ሁኔታ አንድን ቋንቋ የማስተማሪያ ቋንቋ በማድረግ ብቻ የሚቀረፍ ችግር እንደሌለ ነው።

የትምህርት -ሊሲያችን በአንድ በኩል የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ እንዲሰጥ በማድረጉ በሌላ በኩል እንግሊዝኛ ማስተማሪያ ቋንቋ የሚሆንበትን ጊዜ በማዘግየት ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ የሚደረገውን ሽግግር ሊያቀል የሚችል የተሻለ ፖሊሲ ነው ሊባል ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ የቋንቋ ትምህርት ጥራት በከፍተኛ ደረጃ ካልተሻሻለ በስተቀር እንግሊዝኛ የመማሪያ ቋንቋ የሚሆንበት ጊዜ ቢቀላጠፍም ቢዘገይም ችግሩን በመፍታት ረገድ መሰረታዊ ለውጥ የማያመጣ ይሆናል። ከዚህ በመነሳት ፖሊሲው ትክክለኛ ቢሆንም ለውጤታማነቱ ወሳኙነት ያለው የቋንቋ ትምህርት ጥራት መሆኑ

ሊታወቅ ይገባል፡፡ በዚህ በኩል ያለብንን እጥረት በተቻለ ፍጥነት ማስወገድ ካልተቻለ ፖሊሲውን በትክክል ተግባራዊ ማድረግ የማይቻል ይሆናል፡፡ በአጠቃላይም የትምህርት ፖሊሲያችን የመማሪያ ቋንቋን በተመለከተ ያስቀመጠው አቅጣጫ ትክክለኛና ዴሞክራሲያዊ ቢሆንም የቋንቋ ትምህርት ስርአታችን እጅግ ኋላ ቀርና ውጤታማ ያልሆነ በመሆኑ የትክክለኛው ፖሊሲ ውጤቶች መሆን በሚገባው ደረጃ አጥጋቢ ሊሆኑ አልቻሉም፡፡

**2.4. የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ፋይናንስና አስተዳደር ስርአት፣**

በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታና የዴሞክራሲ ስርአትን ለመገንባትና ልማታችንን ለማፋጠን ካስቀመጥናቸው እቅዶች አኳያ ሁሉም ዜጎች የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ካላገኙ ብቃት ያለው ገንቢ ተሳትፎ ሊኖራቸው አይችልም፡፡ ዜጎች በአገራቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ብቃት ያለው ገንቢ ተሳትፎ የማድረግ መብት አላቸው፡፡ ይህን መብት ያለአንደኛ ደረጃ ትምህርት በተሟላ ሁኔታ ሊጠቀሙበት እስካልቻሉ ድረስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን የማግኘት መብት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ሁሉም ዜጋ ይህንን የትምህርት ዕድል ማግኘት የሚችለው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በነፃ የሚሰጥ ሲሆን ነው፡፡ በመሆኑም ከትምህርት ፖሊሲያችን የመሰረት ድንጋዮች አንዱ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ነፃ እንዲሆን መደረጉ ነው፡፡

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በነፃ ይሰጣል ሲባል በአንድ በኩል መንግስት ይህንን አገልግሎት ለሁሉም ለማዳረስ ባለው



አቅም ሁሉ መረባረብ አለበት ማለት ነው፡፡ ለመማር የሚፈልግ ሁሉ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን በነፃ የሚያገኝበትን ሁኔታ ማመቻቸት የመንግስት ግዴታ መሆኑ ሊታመንበት ይገባል ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ማንም ዜጋ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ለመማር ራሱ እንዲከፍል የሚገደደው ክፍያ የለም፣ መኖርም የለበትም ማለት ነው፡፡ መክፈል የቻለ የሚማርበት፣ መክፈል ያልቻለ የማይማርበት ሁኔታ መፈጠር የለበትም ማለት ነው፡፡

የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም በነፃ ማዳረስ የመንግስት ግዴታ ነው ሲባል ህዝቡ ከዚህ አኳያ ምንም አይነት አስተዋፅኦ ማበርከት የለበትም ማለት አይደለም፡፡ ህዝቡ ግብር መክፈሉ አልቀረም፣ መንግስት የትምህርት አገልግሎትን የሚያስፋፋው ይህንኑ ግብር በመጠቀም ጭምር ስለሆነ ህዝቡ በተዘዋዋሪ መንገድ አስተዋፅኦ እያበረከተ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ መንግስት የትምህርት አገልግሎትን ማስፋፋት የሚችልበት ምንም አይነት ዕድል የለም፡፡ ከዚህም ባሻገር ህዝቡ ትምህርት ቤቶችን ለማሰራት ገንዘብ፣ ንብረትና ጉልበት ያወጣል፡፡ ትምህርት ቤቶች የተለያዩ ገቢ ማሰባሰቢያ ስልቶችን ተጠቅመው ወጪያቸውን በከፊል ይሸፍናሉ፡፡ ይህም በጣም መሰረታዊና ተገቢ የፋይናንስ ምንጭ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ የትምህርት አገልግሎትን በሚፈለገው መጠን ማስፋፋት የሚቻልም አይሆንም፡፡ ይህ አሰራር ትምህርት በነፃ መስጠት አለበት ከሚለው መርህ ጋር የሚጋጭ አይደለም፡፡ ተማሪው በግል ለመማር ከፈለገህ ክፊል ተብሎ እስካልተጠየቀ ድረስ ህዝቡ በጋራ የሚያደርጋቸው

የፋይናንስ አስተዋፅኦዎች ከፖሊሲው ጋር የሚጋጩ አይደሉም:: በምንም አይነት ሁኔታ መደረግ የሌለበት ጉዳይ ተማሪው ክፍያ እንዲከፍል የማስገደድና ክፍያውን ካልከፈልክ አትማርም ማለት ነው:: ይህን እስካላደረግን ድረስ ህዝቡ በጋራ በጉልበትም ሆነ በገንዘብና በንብረት የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ፖሊሲውን ከማጠናከር አልፎ የሚፃረር አይሆንም::

መንግስት የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም የማዳረስ ግዴታ ያለበት ቢሆንም የግል ባለሃብቶች በዚሁ የስራ መስክ በሰፊው እንዲሰማሩ ያበረታታል:: በግል ባለሃብቶች የሚቋቋሙ ትምህርት ቤቶች ከተማሪው ክፍያ መጠየቃቸው የማይቀርና አግባብም ነው:: ይህም ቢሆን የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በነፃ መሰጠት አለበት ከሚለው መርህ ጋር የሚጋጭ አይደለም:: መንግስት አገልግሎቱን በነፃ በተቻለ መጠን ለሁሉም ማዳረስ መቻል አለበት:: ይህን ግዴታ በፈፀመበት ሁኔታ አንድ ተማሪ በመንግስት ትምህርት ቤት በነፃ የመማር መብቴን ከመጠቀም ገንዘብ ከፍዬ በግል ትምህርት ቤት እማራለሁ ብሎ በነፃ ፍላጎቱ ከወሰነ መብቱ ነው:: የመንግስት ግዴታ አገልግሎቱን ማቅረብ ነው:: መንግስት አገልግሎቱን አቅርቦ ሲያበቃ በተለያየ ምክንያት በዚህ አገልግሎት አልጠቀምም ገንዘብ ከፍዬ እገለገላለሁ የሚል ሲኖር ግን መብቱ ነው:: መንግስት ይህንን ሊቃወም አይችልም፣ አይገባምም:: ይልቁንም ገንዘብ ከፍለው መማር የሚችሉት በግል ቢማሩ የመንግስትን አገልግሎት ከፍሎ ለመማር ለማይችለው ብቻ ለማድረግ ስለሚቻል በመንግስት ላይ ያለውን ጫና የሚቀንስ ይሆናል:: የትምህርት ፋይናንስ ችግርን ለማቃለል የሚረዳ አንድ



አይነተኛ መሳሪያ ይሆናል::

የግል ባለሀብቶችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚያቋቁሟቸው ትምህርት ቤቶች መክፈል የሚችለውንና የሚፈልገውን ተማሪ ቢያስከፍሉም የነፃ ትምህርት ፖሊሲያችንን ሽክም ያቃልላሉ እንጂ ፖሊሲውን አይፃረሩም የሚለው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ሊሰመርበት የሚገባ ሌላ ጉዳይ ግን አለ:: እነዚህም ትምህርት ቤቶች የአቅም ግንባታ እቅዳችን ማስፈፀሚያ መሳሪያዎች ናቸው:: ዜጎችን መንግስት ባስቀመጠው አቅጣጫ በአመለካከት፣ በስነ-ምግባርና በእውቀት ቀርፀው ማውጣት መቻል አለባቸው:: እነዚህን ግቦች ለማሳካት ችሎታው ወይም ፍላጎቱ የሌለው ትምህርት ቤት እንዲሰራ ሊፈቀድለት አይችልም፣ አይገባም:: የትምህርት አገልግሎት በማስፋፋት ረገድ ይረዱናል፣ የፋይናንስ ሸክማችንን ያቃልሉልናል በሚል ብቻ መንግስት ያስቀመጠውን የጥራት መስፈርት የማያሟሉ ትምህርት ቤቶች ሊፈቀዱ አይችሉም:: በመሆኑም መንግስት በአንድ በኩል እነዚህ ትምህርት ቤቶች እንዲበራከቱ እያደፋፈረ በሌላ በኩል የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟሉና በትክክል ተግባራዊ የሚያደርጉ መሆናቸውን የመቆጣጠር ሃላፊነት አለበት::

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት አገልግሎትን ለሁሉም ለማዳረስ እጅግ በጣም ከፍተኛ ወጪ እንደሚጠይቅ ግልፅ ነው:: በአሁኑ ወቅት የትምህርት አገልግሎት ስርጭትን የሚገድበው ዋነኛ ችግር የፋይናንስ ችግር እንደሆነም ግልፅ ነው:: የትምህርትን ጥራት በተለይም የቀለም ትምህርትን ጥራት በማሻሻል ረገድም

ፋይናንስ ከፍተኛ ተፅእኖ እንደሚያሳድር እሙን ነው:: መንግስት ይህንን የፋይንናስ ችግር ለማቃለል የተለያዩ ስልቶችን ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል::

የትምህርት የፋይናንስ ችግርን ለማቃለል አንዱ ትልቅ መሳሪያ መንግስት ለዚሁ ተግባር የሚመድበውን ወጪ መጨመር ነው:: የማስፈፀም አቅም ዋነኛ የልማት መሳርያ ነው:: ትምህርት የማስፈፀም አቅም ግንባታ አንድ ዋነኛ መሳሪያ ነው:: ስለሆነም መንግስት ለትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ቅድሚያ ሰጥቶ ገንዘብ መመደብ ይገባዋል:: ይሁንና መንግስት የሚያሰባስበው ገቢ ለትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ብቻ ሊውል አይችልም:: ሌሎች በመንግስት ወጪ መሸፈን ያለባቸው አስተዳደራዊ የልማት ወጪዎችም አሉና:: ስለሆነም ምንም እንኳ መንግስት ለትምህርት ልዩ ክብደትና ቅድሚያ ሰጥቶ በተቻለ መጠን ከፍተኛ በጀት መመደብ ያለበት ቢሆንም ይህ ያለገደብ ሊለጠጥ የሚችል አማራጭ አይደለም:: የመንግስት ገቢ እየጨመረ ሲሄድ ለትምህርት የሚሰጠው ልዩ ትኩረት እስከቀጠለ ድረስ የሚመደበውም ገንዘብ አብሮ ይጨምራል:: ይሁንና በአሁኑ ወቅት የመንግስት ገቢ ዝቅተኛ ከመሆኑም ባሻገር ለወደፊቱም ያለገደብ ሊለጠጥ የሚችል አይደለም:: በሌላ አነጋገር መንግስት ያለአንዳች ጥርጥር ለትምህርት ፕሮግራም ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እያደገ የሚሄድ በጀት ለአገልግሎቱ መስፋፋት መመደብ አለበት:: ይሁንና የሚመደበው በጀት ካለው ውሱንነት አኳያ ምንም ቢደረግ የትምህርት ወጪ ፍላጎትን በሚፈለገው መጠን ሊያሟላ የሚችል አይሆንም::



የግል ባለሃብቶችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን በማስፋፋት ረገድ ሊጫወቱት የሚችሉትን ሚና በላቀ ደረጃ መጠቀምና ለዚሁ የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው:: ይህን ስራ የትምህርቱን ጥራት ከመጠበቅ ጋር በማይጋጭ መልኩ መፈፀም ይቻላል፣ ይገባልም:: ይሁንና ይህ የፋይናንስ አማራጭም የራሱ ውሱንነት ያለው መሆኑ አይቀርም:: የግል ባለሀብቶች የሚያቋቁሟቸው ትምህርት ቤቶች ሊያገለግሉ የሚችሉት ከፍሎ ለመማር የሚችለውንና የሚፈልገውን ብቻ ነው:: በመሆኑም የአገልግሎት አድማሳቸው የራሱ ገደብ ያለው ነው:: መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም በዚሁ መስክ በሰፊው የሚለጠጥ አቅም ሊኖራቸው አይችልም:: በመሆኑም ይህ የፋይናንስ ምንጭ የማይናቅ አስተዋፅኦ ቢኖረውም የትምህርት ፋይናንስ ክፍተትን በተሟላ አኳኋን ሊሸፍን የሚችል አይደለም::

ህዝቡ በየደረጃው ትምህርት ቤቶችን በመስራትና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በማሟላት ረገድ በገንዘብ፣ በንብረትና በጉልበት አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ ይገኛል:: ህዝቡ በራሱ ጉልበትና ንብረት ላይ ብቻ በመመስረትም ሆነ ከመንግስትና ከሌሎች ወገኖች ጋር በመቀናጀት ትምህርት ቤቶችን በመስራትና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በማሟላት ረገድ እያደረገ ያለው አስተዋፅኦ ይህ ድሃ ህዝብ ለልጆቹ ጥራት ያለው የትምህርት አገልግሎት ለማቅረብ የማያደርገው ነገር እንደሌለ በተጨባጭ እያረጋገጠ ያለ ነው:: የእስካሁኑ ልምድ

ህዝቡ ይህንን የፋይናንስ ክፍተት ለመሸፈን ያለውን ዝግጁነት ከማረጋገጥ ባሻገር የፋይናንስ ክፍተቱን ለመሸፈን መጫወት የሚችለውን ሚና በሙሉ አሟጠን ተጠቅመናል ማለት አይቻልም:: በዚህ ረገድ ህዝቡን በማነሳሳት በከተሞችም ሆነ በገጠሮች ጥራት ያለው የትምህርት አገልግሎት በከፍተኛ ፍጥነት ለማስፋፋት የሚረዳ ከፍተኛ ስራ መስራት ይገባል፣ ይቻላልም::

ትምህርት ቤቶች ራሳቸው ይብዛም ይነስም ወጪያቸውን ለመሸፈን የሚረዳ ልዩ ልዩ የገቢ ማሰባሰቢያ ስልቶችን መቀየስና መተግበር ይችላሉ:: ተማሪውን በሆነ ሽፋን ክፍያ እንዲከፍል ማስገደድ ከፈለጉ ግን የግድ ፖሊሲውን መፃረር ይኖርባቸዋል:: ከዚህ ውጭ ያሉ አማራጮች ሁሉ ክፍት ናቸው:: በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች አካባቢ የሚገኝን መሬትና የተፈጥሮ ሃብትን በገቢ ምንጭነት መጠቀም ይቻላል:: የተማሪዎችን ጉልበት ማህበራዊ ጠቀሜታ ባላቸው መስኮች በማሰማራት የትምህርት ወጭን ለመደጎም የሚያግዝ ገቢ ለማሰባሰብ ከማስቻሉም ባሻገር ይህ ተማሪዎቹ የስራ ክቡርነትን እንዲገነዘቡና ጥሩ የስራ ስነ-ምግባር እንዲያዳብሩ ሊረዳቸው ይችላል:: በነዚህና በመሳሰሉት ስልቶች በመጠቀም ይብዛም ይነስም ገንዘብ የሚያሰባስቡ ትምህርት ቤቶች አሉ:: ይሁንና ይህ አማራጭ የፋይናንስ ክፍተቶችን ከመሸፈን ባሻገር ጥሩ የስራ ስነ-ምግባርና አመለካከትን ከመፍጠር አኳያም ያለውን አስተዋፅኦ ግምት ውስጥ በማስገባት ተገቢው ትኩረት የተሰጠው አይደለም:: በዚህ ረገድ በጣም ሰፊ ተጨማሪ ስራ መስራት ይቻላል፣ ይገባልም::



የአንደኛ ደረጃ የትምህርት ፋይናንስ ችግሮችን ለመፍታት ተግባራዊ በመሆን ላይ ያሉት አራቱም አማራጮች ሊዳብሩና ሊስፋፉ የሚችሉ ናቸው:: ከአራቱም አማራጮች ሊገኝ የሚችለውን የፋይናንስ ምንጭ አሟጦ ከመጠቀም ውጭ ችግሩ ሊቀረፍ የሚችል አይደለም:: ጉዳዩ ግን ከእያንዳንዱ የፋይናንስ ምንጭ ሊገኝ የሚችለወን ገቢ አሟጦ የመጠቀም ጉዳይ ብቻ አይደለም:: የቅንጅት ጉዳይም ጭምር ነው:: የፋይናንስ አሸፋፈንን በተመለከተ በመንግስትና በህዝቡ መካከል ሰፊ ቅንጅት ሊኖር ይችላል:: ለምሳሌ መንግስት ጥራት ያላቸው አስተማሪዎችን አቅርቦ ወጪውን ለመሸፈን፣ ህዝቡ ደግሞ የትምህርት ቤት መስሪያና የትምህርት መርጃ መሳሪያ ወጪን በመሸፈን አንድ አይነት ስምምነት ላይ ቢደረስ ይህን ሊያደርጉ የሚችሉ አካባቢዎች ወረፋ ሳይጠብቁ የትምህርት አገልግሎት በሰፊው እንዲያሰፋፉ ማድረግ ይቻላል:: የወጭ ክፍፍሉን ከዚህ የተለየ በማድረግም ቅንጅት መፍጠር ይቻላል:: በሌሎች የትምህርት ፋይናንስ ምንጮች መካከልም የተሻለ ቅንጅት እንዲኖር ማድረግ ይቻላል:: እንደዚህ አይነት ቅንጅት ሲኖር ከእያንዳንዱ የፋይናንስ ምንጭ የሚገኘውን ገቢ በከፍተኛ ደረጃ ማሻሻል የሚቻል ከመሆኑም በተጨማሪ የፋይናንሱን አጠቃቀም ለማሻሻል ይቻላል::

የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለማስፋፋት የፋይናንስ ምንጮችን ማጠናከር አማራጭ የሌለውና ቁልፍ ጉዳይ ነው:: ከዚሁ ጋር ተደርቦ መታየት ያለበትና ከፍተኛ ግምትም ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ አጠቃቀሙ ቀጣይና ውጤታማ እንዲሆን የማድረግ ጉዳይም ጭምር ነው:: የትምህርት ፋይናንስ አስተዳደር

ቀጣይና ውጤታማ እንዲሆን የማድረጉ ጉዳይ የፋይናንስ ምንጩን ከማበራከት ጉዳይ ያልተለየ ክብደት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው:: ይህን ለማድረግ ወጪውን አገልግሎቱ በሚሰጥበት ዝቅተኛ የአስተዳደር ደረጃ አማካኝነት እንዲፈፀም ማድረግ፣ ከዚሁ ጎን ለጎን የበጀት ስርአቱ በዝርዝር ህግና መመሪያ የሚመራና ጥብቅ ክትትልም የሚደረግበት እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል:: ወጥነት ያለው የትምህርት ወጪ አስተዳደር ህግና መመሪያ አውጥቶ ይህንኑ በጥብቅ ቁጥጥር መደገፍ፣ የወጪ አወጣጡ ግን ያልተማከለና አገልግሎቱን በሚሰጠው ዝቅተኛው ክፍል ደረጃ የሚተዳደር እንዲሆን ማድረግ ተመራጩ አሰራር እንደሆነ የብዙ አገሮች ልምድ ያረጋግጣል::

ያልተማከለ የትምህርት ፋይናንስ አስተዳደር ስርአት ተፈላጊ የሚሆነው ከፋይናንስ ቴክኒክ አኳያ ተመራጩ አሰራር እሱው ስለሆነ ብቻም አይደለም:: በአገራችን የዴሞክራሲ ስርአት ለመገንባትና የህዝቡን ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ ለማጠናከር የተያዘው አላማ ተግባራዊ የሚሆነው ስልጣን ወደዝቅተኛ የአስተዳደር አካላት በበቂ መጠን ሲከፋፈል ጭምር ነው:: በዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች ላይ ያሉ ሃላፊዎችና ህዝቡ እንደትምህርት አገልግሎት በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ የመወሰን ስልጣን ሲኖራቸው ነው የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ግባችን የሚሳካውና በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው:: የትምህርት ፋይናንስ አስተዳደር ያልተማከለ መሆን የሚኖርበት አንዱ መሰረታዊ ምክንያትም የህዝቡን ተሳትፎና የመወሰን ስልጣን ለማጠናከርና ተግባራዊ ለማድረግ ነው::



ከላይ እንደተዘረዘረው የኢትዮጵያ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ፋይናንስ የሚሸፈነው ከአንድ ምንጭ አይደለም:: ሊሸፈን የሚችለው አራት የተለያዩ የፋይናንስ ምንጮችን በመጠቀምና በማቀናጀት ነው:: እነዚህን የተለያዩ የፋይናንስ ምንጮች አሟጦ ለመጠቀምና በላቀ ደረጃ ለማቀናጀት የሚቻለው ያልተማከለ የፋይናንስ ስርአት ሲኖር ነው:: ህዝቡ ሊሳተፍ የሚችለው በየአካባቢውና በየመንደሩ በመሆኑ የተማከለ የፋይናንስ ስርአት ባለበት ሁኔታ የህዝቡን ተሳትፎ አሟጦ መጠቀም አይቻልም:: ከዚሁ ጋር አብሮ የሚሄድ የፋይናንስ ስርአት በሌለበት በዚህ ረገድ የሚደረገው ተሳትፎ ይብዛም ይነስም መገደቡ አይቀርም:: የትምህርት ቤቶች ገቢ የማሰባሰብ ጥረትም የተማከለ የፋይናንስ ስርአት ባለበት ሁኔታ መሆን የሚችልበት ደረጃ ላይ መድረስ አይችልም:: የመንግስትን ፋይናንስ ትምህርት ቤቶች ከሚያሰባስቡት ገቢ፣ ህዝቡ ከሚያበረክተው ፋይናንስ ወዘተ. ጋር ማቀናጀት የሚቻለው ያልተማከለ የፋይናንስ ስርአት ሲኖር ነው::

መንግስት ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የፋይናንስ አስተዳደር ያልተማከለ መሆን እንዳለበት ተገንዝቦ ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል:: የአንደኛ ደረጃ ትምህርት አመራር የክልሎች ስልጣን እንዲሆን በህገ-መንግስቱ ተደንግጓል:: በርካታ ክልሎች በበኩላቸው ይህ ስልጣን ለወረዳ አስተዳደሮችና ለከተማ ማዘጋጃ ቤቶች እንዲከፋፈል አድርገዋል:: የትምህርት ፋይናንስ አስተዳደር

መመሪያዎችን ለማሻሻልና ለማዳበር፣ በዚህ ደረጃ ያለውን ቁጥጥርም ለማጎልበት ጥረት ተደርጓል። ይሁንና በዚህ ረገድ አሁንም ቀላል ያልሆኑ ክፍተቶች ይታያሉ። በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑን ለወረዳዎች የማከፋፈሉ ስራ ገና በመጀመር ላይ ያለ ስራ በመሆኑ የተጠናከረና በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ እየሆነ ያለ አይደለም። ካልተማከለ አሰራሩ ጎን ለጎን መጠናከር ያለበት ወጥነት ያለው የፋይናንስ አስተዳደር መመሪያ የማዘጋጀትና ቁጥጥሩን የማጠናከር ተግባርም ገና ብዙ ስራ የሚቀረው ነው። ፋይናንሱን የማስተዳደር ስራ በወረዳ ብቻ ተገድቦ ሳይቀር ለትምህርት ቤቶችና ለቀበሌዎችም መከፋፈል ይገባዋል። ይህ እስካልሆነ ድረስ ያልተማከለው አሰራር የተሟላ ነው ሊባል አይችልም። በዚህ ረገድ የተኬደው ርቀት እጅግ በጣም ውሱን ነው። በመሆኑም ያልተማከለ የትምህርት ፋይናንስ አስተዳደር ስርአት ለመፍጠር በርካታ ስራዎች የተሰሩ ቢሆኑም ይህንን በተሟላ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ የሚቀር ሰፊ ስራ እንዳለ ሊሰመርበት ይገባል።

የትምህርት ፋይናንስ አስተዳደሩን ያልተማከለ እንዲሆን ከማድረግ ጎን ለጎን መታየት የሚገባው ሌላው ጉዳይ የትምህርቱ አጠቃላይ አስተዳደር ጉዳይ ነው። የትምህርት ፋይናንስ አስተዳደሩ ያልተማከለ እንዲሆን የሚያደርጉት ምክንያቶች በሙሉ አጠቃላይ የትምህርት አስተዳደርም ያልተማከለ እንዲሆን የሚያደርጉ ናቸው። የትምህርት አስተዳደሩ ያልተማከለ ብቻ ሳይሆን የትምህርት ስርአቱ የሚመለከታቸው ወገኖች፣ አስተማሪዎች፣ የትምህርት ሃላፊዎች፣ ተማሪዎች፣ የተማሪዎቹ



ወላጆች በሰፊው የሚሳተፉበትም መሆን ይኖርበታል። ያልተማከለው አሰራር በእንደዚህ አይነቱ ሰፊ ተሳትፎ ሲደገፍ የፋይናንስ ስርአቱን በብቃት ለመምራት፣ ሁሉንም የፋይናንስ ምንጮች አሟጦ ለመጠቀምና በአግባቡ ለማቀናጀት ያስችላል።

ሰፊ ተሳትፎን ለማረጋገጥ የሚያስችል ያልተማከለ አሰራር እጅግ ተፈላጊ የሚሆንበት ሌላው ምክንያት ተማሪውን በሚፈለገው መልክ ለመቅረፅና የትምህርቱን ጥራት ለመጠበቅ አማራጭ የሌለው በመሆኑም ጭምር ነው። የትምህርት ስርአቱ ዜጎች የሚፈለገው እውቀት፣ አስተሳሰብና ስነ-ምግባር እንዲኖራቸው አድርጎ የመቅረፅ ሃላፊነትን የተሸከመ ቁልፍ ተቋም ነው። በዚህ ረገድ የትምህርቱ ስርአት ቁልፍ ሚና መጫወቱ አማራጭ የሌለው ቢሆንም ብቻውን ተፈላጊውን አመለካከትና ስነ-ምግባር በተሟላ ሁኔታ ሊቀርፅ አይችልም። የአካባቢው ህብረተሰብና የተማሪው ወላጆችም በዚህ ረገድ የማይተካ ሚና አላቸው። ተማሪው በሚፈለገው መልክ በተሳካ ሁኔታ ሊቀረፅ የሚችለው በነዚህ አካላት የጋራና የተቀናጀ ጥረት ነው። ትምህርት ቤቶች በዚሁ የተቀናጀ ጥረት ውስጥ ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ በመሆናቸው የሚመለከታቸው ወገኖች በትምህርት አስተዳደሩ ላይ በሰፊውና በቀጥታ መሳተፍ አለባቸው።

የተማሪዎች ወላጆች ልጆቻቸው ተገቢውን እውቀት፣ አመለካከትና ስነ-ምግባር እየቀሰሙ እንደሆነ ማረጋገጥ ይፈልጋሉ። በዚህ ረገድ የላቀ አስተዋፅኦ ለማድረግ ፍላጎቱና

ዝግጅነቱ እንዳላቸውም አያጠራጥርም። ልጆቻቸው የሚማሩባቸው ትምህርት ቤቶች ጥራታቸው የተጠበቀ እንዲሆን፣ በትምህርት ቤት የሚሰጠው ትምህርት በቤትና በአካባቢው እንዲጠናከር ለማድረግ ከምንም በላይ በሙሉ ልብ ሊንቀሳቀሱ ይችላሉ። በመሆኑም በትምህርት አስተዳደር ስርአቱ ውስጥ ለተማሪ ወላጆች ከፍተኛ ቦታ መስጠት የትምህርት ስርአቱ ግቡን እንዲመታ ከማድረግ አኳያ ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል። ተማሪዎችም ትምህርት ቤቶቻቸው የሚፈለገውን ጥራት ያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይሻሉ፣ በዚህም ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረግ ይችላሉ። የትምህርት ቤቱ መምህራንም የላቀ ሚና ሊኖራቸው ይችላል። ተማሪዎችን፣ አስተማሪዎችንና የተማሪዎቹን ወላጆች በትምህርት አስተዳደር በተለይም በትምህርት ቤቶች አመራርና አስተዳደር ረገድ ተገቢ ድርሻቸውን እንዲወጡ ማድረግ የትምህርቱን ጥራት ለመጠበቅ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው።

ህዝቡ፣ በትምህርት አስተዳደር ስራ ላይ በተለይም በትምህርት ቤቶች አመራር ላይ በሰፊው እንዲሳተፍ ባለፉት አመታት ከፍተኛ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል። ይሁንና የትምህርት ፋይናንስ አስተዳደር በሚፈለገው ደረጃ ወደዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች የወረደ ስላልነበረ በፋይናንስ ጉዳይ ላይ ይህ ነው የሚባል የአመራር ሚና ተጫውተዋል ማለት የሚቻል አይደለም። ከዚህ ጋር ተያይዞም ይህንን ተሳትፎ ለማረጋገጥ የሚቋቋሙት ኮሚቴዎች ትምህርት ቤቶችን በመምራት ረገድ ጠንካራ ስልጣን ነበራቸው ማለት አይቻልም። ከዚሁ በተጨማሪ እነዚህ መድረኮች ተጨባጭ ውጤት ያለው ተሳትፎ ማረጋገጥ የሚችሉት አባላቱና



ህዝቡ በአጠቃላይ ስለትምህርት ፖሊሲው የተሟላ ግንዛቤ ሲይዙ፣ ህዝቡና የህዝቡ የተሳትፎ መድረኮች ተልእኮዎቻቸውን በአግባቡ መወጣታቸው ለትምህርት ስርአቱ ውጤታማነት ያለውን ከፍተኛ አስተዋፅኦ በሚገባ ሊገነዘቡ፣ እነዚህ የተሳትፎ መድረኮች ተግባርና ሃላፊነታቸው ምን እንደሆነ በጥልቀት ሲገነዘቡና ሃላፊነታቸውን ለመወጣት የሚረዳቸው የምክርና ስልጠና ድጋፍ ሲያገኙ ነው። ባለፉት አመታት በዚህ ረገድ አጥጋቢ ስራ ተሰርቷል ማለት አይቻልም። በመሆኑም የህዝቡ የተሳትፎ መድረክ ይሆናሉ ተብለው የተቋቋሙት ኮሚቴዎች ተልእኳቸውን በአግባቡ ሳይወጡ ቀርተዋል።

**3. የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ችግሮችን ለመፍታት ልንከተለው የሚገባን አቅጣጫ፣**

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ስርአታችን በሚፈለገው ደረጃ ግቡን እንዳይመታ እንቅፋት እየሆኑ ያሉ ጉዳዮችና እነዚህን ለመፍታት የተደረጉ ሙከራዎች ከላይ ተዘርዝረው ቀርበዋል። ስርጭቱን ማስፋፋት በሚመለከት ዋናው ችግር የፋይናንስ እንደሆነና በአርብቶ አደሩ አካባቢ ለየት ያሉ ተጨማሪ ችግሮች እንዳሉ አስቀምጠናል። የቀለም ትምህርቱ ጥራት ችግር በዋነኛነት የአስተማሪዎች በሚፈለገው መጠንና አይነት ተሟልቶ አለመገኘት፣ ከዚህ በተጨማሪም የፋይናንስ ችግሮች እንዳሉ አስቀምጠናል። የስነ-ዜጋ ትምህርትንና ጥሩ የስራ አመለካከትና ስነ ምግባር በመፍጠር ረገድ ዋናው ችግር የአመለካከትና፣ ትምህርቱ የሚሰጥበት ውጤታማ ስርአት ያለመዘርጋት ጉዳይ

እንደሆነ አስምረንበታል፡፡ ሁሉንም የፋይናንስ ምንጮች አሟጦና አቀናጅቶ በመጠቀም፣ የሚመለከታቸው ክፍሎች በትምህርት አስተዳደሩ ስርአት ውስጥ በብቃት እንዲሳተፉ በማድረግ ረገድ ያልተማከለ አሰራርን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ የማድረግ ችግር እንዳለም አረጋግጠናል፡፡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ችግሮችን ለመፍታት በነዚህ ዋነኛ ችግሮች ላይ ያነጣጠረ ሌሎችንም ችግሮች አብሮ የሚፈታ የመፍትሄ አቅጣጫ ማስቀመጥ ይኖርብናል፡፡

### 3.1. በአስተማሪዎች ላይ ልዩ ትኩረት ማድረግ፣

ፋይናንሱ ተገኝቶ ትምህርትን ለሁሉም ዜጎች ለማዳረስ ጥረት ሲደረግ መምህራን በሚፈለገው መጠንና አይነት ካልተገኙ ችግር እንደሚሆን ግልፅ ነው፡፡ ብቃት ያላቸው መምህራን በሚፈለገው መጠን ካልተገኙ በስተቀር ምንም ቢደረግ በቀለም ትምህርቱ ጥራት ላይ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት አይቻልም፡፡ በስነ-ዜጋና በስነ-ምግባር ጉዳይ ላይም ጠንካራ አመለካከትና በዚህ ረገድ ያለባቸውን ግዴታ ለመወጣት ዝግጁነት ያላቸው አስተማሪዎች ከሌሉ በስተቀር የሚመጣ ዘላቂ መፍትሄ የለም፡፡ በመሆኑም የአስተማሪዎችን መጠንና ብቃት በተቻለ ፍጥነት ማሟላት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ችግሮችን ለመፍታት መወሰድ ካለባቸው ዋነኛ መፍትሄዎች አንዱ ነው፡፡

አስተማሪዎችን በሚፈለገው መጠንና ጥራት ለማግኘት ከሚያስችሉን ዋነኛ መሳሪያዎች አንዱ የአስተማሪዎች ስልጠና



ፕሮግራም ነው፡፡ አስተማሪዎች በሚያስተምሩት ትምህርት ላይ በቂ እውቀት እንዲኖራቸው፣ ከዚህም አኳያ በሌሎች የትምህርት አይነቶች ላይ ካለው የብቃት ችግር ጎን ለጎን የቋንቋ ትምህርት ላይ ያለውን ከፍተኛ ችግር ለመፍታት የሚያስችል እውቀት እንዲኖራቸው ሰፊና ጥራቱ የተጠበቀ የቅድመ-ስራና የስራ ላይ ስልጠና ፕሮግራም ሊኖረን ይገባል፡፡ አስተማሪዎች ስለትምህርት ፖሊሲው፣ ስለግቦቹና አላማዎቹ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው፣ ከዚህም አኳያ በስነ-ዜጋና በስነ-ምግባር ትምህርት ላይ ጠንካራ እምነትና የሙያ ግዴታ ይዘው በብቃት ለመሳተፍ የሚያስችላቸው አመለካከትና እውቀት እንዲያገኙ በተለያዩ ስልጠናዎችና አውደ-ጥናቶች በሰፊው መስራት ያስፈልጋል፡፡

በመምህራን ስልጠና ጉዳይ ላይ ሊተኮርባቸው የሚገቡ በርካታ ጉዳዮች አሉ፡፡ በመጀመሪያ ካለን የመምህራን እጥረትና ለወደፊት ከሚኖረው የመምህራን ፍላጎት አኳያ በጣም ሰፊ የስልጠና ፕሮግራም እንደሚያስፈልገን ነው፡፡ ይህንን ሰፊ የሰው ሃይል ፍላጎት በቅድመ-ስራ ስልጠና ብቻ ልናሟላው አንችልም፡፡ በስራ ላይ ያሉ መምህራንን በተለያዩ አጫጭር የስልጠና ፕሮግራሞች አውደ-ጥናቶችና ሴሚናሮች አማካኝነት በቀጣይነት ማሻሻል እጅግ በጣም ተፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም በአንድ በኩል ያሉንን የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋሞች እያስፋፋንና አዳዲሶችንም እየጨመርን ከመንቀሳቀስ በተጨማሪ በአግባቡ የተደራጀ፣ ቀጣይነት ያለውና በእቅድ የሚፈፀም ሰፊ የስራ ላይ ስልጠና ፕሮግራም መቀየስና መተግበር አለብን፡፡ ሁሉንም አቀናጅተን ጠንካራና የተደራጀ አመራር እንዲኖራቸው አድርገን

ካልተንቀሳቀስን በስተቀር የምንፈልገውን የመምህራን መጠን በምንፈልገው ፍጥነት ልናገኝ አንችልም።

ሰፊ የቅድመ-ስራና የስራ ላይ ስልጠና ፕሮግራም መቀየስና ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ቢሆንም የፕሮግራሙ ጥራት ካልተጠበቀ በስተቀር የምንፈልገውን ውጤት ልናገኝ አንችልም። የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ጥራት ለመጠበቅ የሚያስችለን ዋነኛ ስራ በራሳቸው በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የምናደርገው ጥረት አይደለም። ለውጥ ለማምጣት የሚያስችለን ዋነኛው መሳሪያ በመምህራን ስልጠና ላይ የምናደርገው የጥራት ማሻሻል ስራ ነው። በመሆኑም የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋሞች ከማንኛውም የትምህርት ተቋም የላቀ ትኩረት ተሰጥቷቸው ጥራታቸው በአፋጣኝና በከፍተኛ ደረጃ እንዲሻሻል መደረግ አለበት። በስራ ላይ የሚሰጡት ስልጠናዎች፣ የሚካሄዱት አውደ-ጥናቶችና ሴሚናሮችም የይድረስ ይድረስና የግብር ይውጣ መሆን የለባቸውም። በአስተማሪው ላይ አንድ አይነት የእውቀት፣ የአመለካከት ወይም የአሰራር ለውጥ ለማምጣት ተብለው በብቃት የተዘጋጁ፣ የተደራጁ፣ ቀጣይነትና ተመጋጋቢነት ያላቸውና ግባቸውን ለመምታት በሚያስችላቸው አኳኋን የሚፈፀሙ መሆን አለባቸው።

አስተማሪዎች እንዲያስተምሩ የሚጠበቅባቸው የቀለም ትምህርትን ብቻ አይደለም። ተማሪውን ሁሉን አቀፍ በሆነ መንገድ የመቅረፅ ሃላፊነት ነው የተሰጣቸው። በመሆኑም የሚካሄዱት የቅድመ ስራ ስልጠናዎችም ሆኑ የስራ ላይ



ስልጠናዎች የአስተማሪውን የቀለም ትምህርት እውቀትና የማስተማር ዘዴ በከፍተኛ ደረጃ ከማሻሻል በተጨማሪ አስተማሪው በስነ-ዜጋና በስነ-ምግባር ትምህርት ላይ ያለውን ያልተስተካከለ አመለካከት ለማስተካከል የሚያስችሉ መሆን አለባቸው። በትምህርት ፖሊሲው ላይ በስነ-ምግባርና በስነ-ዜጋ ትምህርት አስፈላጊነት ላይ የተሟላ ግንዛቤ ለመያዝ የሚያስችላቸው ትምህርት፣ የውይይትና ክርክር ዕድል ሊሰጣቸው ይገባል። ይህንን ትምህርት በብቃት ለመስጠት የሚያስችላቸው እውቀትና ትምህርቱን የማስተላለፍ ዘዴ የሚያስጨብጣቸው መሆን ይኖርበታል። እነዚህን ትምህርቶች በብቃት የማስተላለፍ ሙያዊ ግዴታ እንዳለባቸው በማያሻማ አኳኋን፣ የሚያስገነዝብ መሆን ይኖርበታል። ይህንን የማያካትትና በብቃት ለመፈፀም የማያስችል የመምህራን ስልጠና ፕሮግራም ታጥቦ ጭቃ ከመሆን ሊያድነን የሚችል አይደለም።

መምህራንን በሚፈለገው መጠንና አይነት ለማፍራት የሚያስችል የተቀናጀ ጠንካራ አመራር ያለውና ጥብቅ ቁጥጥር የሚደረግበት የመምህራን ስልጠና ስርአት መዘርጋት ዋናው ጉዳይ ሲሆን መምህራን ስራቸውን ለመስራት የሚያስችላቸው ተጨማሪ እገዛም ማግኘት አለባቸው። ከዚህ አኳያ በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችለው የዘመናዊ የቴሌኮምዩኒኬሽን አገልግሎት አበቃቀል ጉዳይ ነው። የሬድዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት መምህራንን በማገዝ የትምህርቱን ጥራቱን ለማሻሻል በሚያስችል አኳኋን እንዲቀረፅና እንዲተገበር ትኩረት ሰጥቶ ማሻሻልና ማስፋፋት ያስፈልጋል። የቴሌኮምዩኒኬሽን አገልግሎት

እየተስፋፋና ጥራቱም እየተሻሻለ ሲሄድ ከዚሁ ጎን ለጎን የኢንቴርኔት አገልግሎትን ለማስፋፋትና በዚሁ አማካኝነት የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማገዝ፣ የመምህራንን እውቀት በስራ ላይ ስልጠና ለማሻሻል በተቻለ መጠን ሁሉ ልንጠቀምበት ይገባል፡፡

መምህራን ስራቸውን በአግባቡ እንዲፈፅሙ ከመደገፍ አኳያ ሌላው ሊተኮርበት የሚገባው ጉዳይ የስነ-ዜጋና የስነ-ምግባር ትምህርት አሰጣጥ ዘዴን የመቀየስና በየጊዜውም እየተሻሻለ እንዲሄድ የማድረግ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ መሰረት የስነ-ዜጋ ትምህርት ራሱን ችሎ በሚሰጥበት ወቅት በውል ተለይተው የተቀመጡ አመለካከቶችንና እምነቶችን ለመፍጠር የሚያስችል ይዘትና አቀራረብ እንዲኖረው መደረግ አለበት፡፡ ሌሎች የትምህርት አይነቶችም ለዚሁ ጉዳይ የየበኩላቸውን አስተዋፅኦ ማድረግ የሚያስችል ይዘት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፡፡ የመማሪያ መፃህፍቱ ከዚህ አኳያ በተከታታይ እየተፈተሹ ሊሻሻሉና ሊዳብሩ ይገባል፡፡ የትምህርት ቤቱ የዕለት ተዕለት አሰራርና ከክፍል ውጭ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ይህንኑ ለመደገፍ በሚያስችል አኳኋን የተቀረፁና የሚፈፀሙ መሆን አለባቸው፡፡ ከትምህርት ቤቱ ውጭ ያሉ በዚህ ጉዳይ ላይ አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ የሚችሉ ወገኖችም በዚሁ ተግባር ላይ በትምህርት ቤቱ ውስጥም ሆነ ከትምህርት ቤቱ ውጭ ድርሻቸውን የሚያበረክቱበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡ እንደዚህ አይነቱ ሁሉን አቀፍ የስነ-ዜጋ የትምህርት ስርአት ከተቀየሰም በኋላ አስተማሪው ስለስርአቱ የተሟላ ግንዛቤ እንዲይዝና በተሟላ ሁኔታ ስራ ላይ እንዲያውለው



ለማድረግ የሚያስችል ተከታታይ ስልጠና ሊሰጠውና እገዛ ሊደረግለት ይገባል፡፡

የስራ አመለካከትና ስነ-ምግባር ትምህርትን በተመለከተም በተመሳሳይ መልኩ ትምህርቱ ሁሉን አቀፍና የተቀናጀ በሆነ አኳኋን ሊሰጥ ይገባል፡፡ በስነ-ዜጋ ትምህርቱ ውስጥ የጉልበት ስራን ጨምሮ ማንኛውም ስራ ክቡር መሆኑን የሚያስጨብጥ፣ ዜጋው በመልካም ስነ-ምግባርና ሞራል እንዲቀረፅ የሚያደርግ ይዘት ሊኖረው ይገባል፡፡ ሌሎች የትምህርት አይነቶችም ይህንን የሚደግፉና የሚያጠናክሩ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ አኳያ ተማሪው እንዲይዛቸው የሚፈለጉ እምነቶችና አመለካከቶች በውል ተለይተው እነዚህን በአስተማማኝ መልክ ለማስጨበጥ የሚያስችል ይዘትና የማስተማር ዘዴ ለመከተል የሚያስችል መሆን አለበት፡፡ የትምህርት ቤቱ አሰራርና ከክፍል ውጭ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች ሆን ተብለው ተለይተው የተቀመጡትን እምነቶችና አመለካከቶች ለማስረፅ የሚያስችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ እያሉና ከአካባቢው ህዝብ ጋር በመቀናጀት በተለያዩ የጉልበት ስራዎች በአቅማቸው እንዲሳተፉ፣ በዚህም የስራ ክቡርነትንና ስራ ፈጥሮ ሰርቶ የመኖር አመለካከትን እንዲለምዱ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በትምህርቱ አላማ ላይ ተማሪዎች፣ አስተማሪዎችና ህብረተሰቡም የተሟላ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ተደርጎ ሁሉም በየበኩላቸው ለዚሁ ትምህርት የየበኩላቸውን አስተዋፅኦ ማበርከት የሚችሉበት ዕድል መፈጠር ይኖርበታል፡፡

አስተማሪው በሚፈለገው መጠንና አይነት ሰልጥኖ፣ ስራውን በተሻለ ደረጃ ለመስራት የሚያስችሉት ከላይ የተዘረዘሩትና ሌሎችም እገዛዎች ተደርገውለት፣ በከፍተኛ የስራ ተነሳሽነትና የሙያ ስነ-ምግባር ካልተንቀሳቀሰ በስተቀር የሚፈለገው ውጤት ሊገኝ አይችልም። የአስተማሪውን የስራ ተነሳሽነትና የሙያ ስነ-ምግባር ለመጠበቅ፣ አመለካከቱን መቅረፅ፣ የተለያዩ የማትጊያ ስልቶችን መጠቀም ያስፈልጋል። ዋናው መሳሪያም ይኸው ነው። ይሁንና ይህ ስራ በአስተዳደራዊ ርምጃ ካልተደገፈ በስተቀር የሚፈለገውን ለውጥ ሊያመጣ አይችልም። ስለሆነም ዋናውን መፍትሄ ለይቶ በማስቀመጥ ሁለቱንም መንገዶች አጣጥሞና አቀናጅቶ መጠቀም አማራጭ የሌለው ጉዳይ ይሆናል።

አስተማሪ አዲሱን ትውልድ ከመቅረፅ አኳያ ቁልፍ ሚና የሚጫወት ሰው ነው። ሁሉም ስራ ክቡር ቢሆንም ከአስተማሪነት በላይ ክቡር የሆነ ስራ የለም። ይህንን የተከበረ ስራ ለመስራት ስነ-ምግባሩና ሞራሉ የተጠበቀ፣ ተማሪዎችን በሚፈልገው መልክ ለመቅረፅ ከፍተኛ ፍላጎትና ተነሳሽነት ያለው ሰው መሆን አለበት። ምግባረ ብልሹ የሆነና በግብር ይውጣ የሚንቀሳቀስ አስተማሪ ምንም አይነት ሌላ ጠንካራ ጎን ቢኖረውም ከጥቅሙ ጉዳቱ ስለሚያመዝን በትምህርት ስርአቱ ውስጥ መቀጠል አይገባውም። ስለሆነም አስተማሪው ስራውን በብቃት ለመፈፀም የሚያስችል እውቀትና ሙያ እንዲኖረው፣ በሙያ ስነ-ምግባሩና ግዴታው ላይ የተሟላ ግንዛቤና ጠንካራ እምነት እንዲኖረው ቀጣይነት ያለው ትምህርት ሊሰጠው፣ የልምድ ልውውጥ መድረኮች



እንዲያገኝ ማድረግ ያስፈልጋል።

አስተማሪው በስራው እንዲለካ ከማድረግና ተነሳሽነቱም እንዲዳብር ከማድረግ አኳያ የላቀ ሚና የሚጫወተውና መጫወትም የሚገባው የስራ ውጤቱ ነው። ተማሪዎቹ ያስተማራቸውን ትምህርት በሚገባ የጨበጡ መልካም ዜጎች እየሆኑ መሄዳቸውን ማየትና ማረጋገጥ ነው ዋነኛው የአስተማሪ የእርካታ ምንጭ። አስተማሪው ይህንን ሊገነዘብና ሊያምንበት ይገባል። ይሁንና ከዚሁ በተጨማሪ የስራ ሁኔታውም በቀጣይነት ሊሻሻልለት ይገባል። ከዚህ በፊትም እንደተደረገው ሁሉ በቀጣይም ጊዜያት ከአገሪቱ ኢኮኖሚ መሻሻል ጎን ለጎን ደሞዙ ሊሻሻል ይገባል። የስራ ሁኔታውን ለማሻሻልና አስተማሪውን ለማትጋት የሚያስችሉ ሌሎች ስልቶችን እየነደፉ በተግባርም ላይ ማዋልም ያስፈልጋል። በስራው ምስጉን የሆነ አስተማሪ ተከታታይ ስልጠና እያገኘ ሙያውንና ኑሮውን የሚያሻሽልበት ወጥ የሆነ በትክክል ስራ ላይ የሚውል የእድገት ስርአት ሊዘጋጅለት ይገባል። አስተማሪው በትምህርት ቤት አመራር ተግባር ላይ በቀጥታና በብቃት ሊሳተፍ የሚችልበት ስርአትም ሊቀመጥ ይገባል። ከዚህም ባሻገር በማህበሩ ተደራጅቶ በትምህርት ስርአቱ ጉዳይ ላይ በቀጣይነት የሚመክርበት፣ አስተያየቱን የሚያቀርብበትና የሚሳተፍበት መድረክ በመንግስት ሊዘጋጅለትና መንግስት ከማህበሩ ጋር በአጋርነት የሚሰራበት ሁኔታ መፈጠር ይኖርበታል።

ከላይ የተዘረዘሩት ስራዎች በትክክል ከተፈፀሙ እጅግ

በጣም አብዛኛው አስተማሪ የሚፈለገው የስራ ተነሳሽነትና ስነ-ምግባር እንደሚኖረው መገመት አያዳግትም። ይሁንና ጥቂትም ቢሆኑ ምግባረ-ብልሹ የሆኑ፣ የስራ ብቃት የሌላቸው አስተማሪዎች መኖራቸው አይቀርም። እነዚህ በስርአቱ ውስጥ እንዲቀጥሉ እስከተደረገ ድረስ ይባስ ብሎም የእድገቱና የጥቅማ ጥቅሙ ተቋዳሽ እስከሆኑ ድረስ የሌላውን አስተማሪ ሞራል መንካቱና የመማር ማስተማሩን ሂደት መጉዳቱ አይቀርም። በመሆኑም እነዚህ ግለሰቦች ጉድለታቸውን እንዲያስተካክሉ በቂ እገዛ ከተደረገላቸው በኋላ የማይስተካከሉ ሆነው ሲገኙ ያለአንዳች ማመንታት ከትምህርት ስርአቱ እንዲወገዱ መደረግ አለበት። ይህንን አስተዳደራዊ መፍትሄ የማይጨምር መፍትሄ ችግሩን በአስተማማኝ መንገድ ሊያስወግድ የሚችል አይሆንም።

ከዚሁ ጎን ለጎን በትምህርት ቤቶች በተለይም በትልልቅ ከተሞች በሚገኙ አንዳንድ ትምህርት ቤቶች የሚታየውን ዋልጌነት ለማስወገድ ጠንካራና የተቀናጀ ስራ መሰራት አለበት። በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች የመምህራንና የትምህርት ሃላፊዎች ቁጥጥር በመላላቱ፣ ህብረተሰቡ የተማሪዎችን ስነ-ምግባር በመጠበቅና በማስተካከል ሊጫወት የሚገባውን ሚና ለመጫወት የሚችልበት በቂ ዕድል ባለመፈጠሩ፣ አልፎ አልፎም የመምህራን ምግባረ-ብልሹነት እየታከለበት ዋልጌነት ተጠናክሮ የሚታይበት ሁኔታ አለ። በመሆኑም እነዚህ ትምህርት ቤቶች ወጣቱን በተስተካከለ አቅጣጫ ከመቅረፅ ይልቅ የዋልጌነት መናኸሪያና ማሰልጠኛ ወደመሆን የሚሸጋገሩበት አደጋ ጎልቶ እየታየ ነው። መምህራን ይህንን ለማስተካከል የመረባረብ ግዴታ ቢኖርባቸውም



በዚህ ረገድ የትምህርት ስርአቱ ሃላፊዎችና ህብረተሰቡ የተሟላ ድጋፍ ካላበረከቱ በስተቀር የሚፈለገው ውጤት ሊገኝ ካለመቻሉም በላይ የመምህራንን የስራ ተነሳሽነትና ስነ-ምግባርም ሊሸረሽር ይችላል። በመሆኑም ሁሉም የሚመለከታቸው ወገኖች የትምህርት ቤቶችን ስነ-ስርአትና ዲሲፕሊን ለማስከበር፣ ጠንካራ የክትትልና ቁጥጥር ስርአት መዘርጋት ይገባቸዋል። ብዙሃኑ ተማሪዎች ይህንን ስርአት አውቀውና አስፈላጊነቱንም አምነውበት እንዲፈፅሙትና በማስፈፀሙ ረገድ ድርሻቸውን እንዲወጡ መደረግ አለበት። ከዚህ ውጭ የሆኑ ዋልጌዎች ከትምህርት ቤቶች ያለማመንታት እንዲባረሩ መደረግ ይኖርበታል።

እነዚህን የመሳሰሉ ርምጃዎችን በመውሰድ የተሟላ እውቀትና የሙያ ስነ-ምግባር ያላቸው፣ ተማሪውን በተቀመጠው አቅጣጫ ለመቅረፅ የሚችሉና የትምህርት ስርአታችንን ችግሮች ከመፍታት አኳያ ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ መምህራንን በሚፈለገው መጠን ማፍራት ይቻላል፣ ይገባልም። በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ጉዳይ ላይ በቀጣይ አመታት ልዩ ትኩረት ሰጥተን ልንረባረብባቸው ከሚገቡት ጉዳዮች አንዱ ይህንኑ ስራ በተሟላ ሁኔታ መተግበርና በየጊዜውም ማሻሻል ሊሆን ይገባል።

### 3.2. ለትምህርት ፋይናንስ ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ መሻት፣

የትምህርት ፋይናንስ ችግሮች የአንደኛ ደረጃ ትምህርት

ስርጭትን የገደበ ዋነኛ ችግር በመሆኑና የትምህርቱን ጥራት በማስጠበቅም ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ የሚያሳድር በመሆኑ መፍትሄ ማግኘት ያለበት አንድ መሰረታዊ ጉዳይ ነው:: የትምህርት ስርጭትን ማሻሻል ሲባል የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ያልደረሳቸው ሁሉ እንዲደርሳቸው ማድረግ ብቻ ሳይሆን በሂደት በሺፍት የመማሩን ሂደት ለማስቀረትና በየክፍሉ የሚማሩት ተማሪዎች ቁጥር ከተቀመጠው መጠን በላይ እንዳይሆን ማድረግንም ያካተተ መሆን ይኖርበታል::

መንግስት የትምህርት ፋይናንስ ዋነኛ ምንጭ ሆኖ መቀጠሉ አይቀርም:: በመሆኑም መንግስት ገቢውን በማሻሻልና ከባጀቱ ውስጥ ለትምህርትና ስልጠና የሚመድበውን መጠን በተቻለ መጠን እንዲሻሻል በማድረግ ለትምህርትና ስልጠና የሚመደበውን የባጀት መጠን መጨመር ይኖርበታል:: ይህ ጉዳይ በፌዴራልም፣ በክልልም፣ በወረዳም ደረጃ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ይሆናል:: መንግስት የግል ባለሃብቶችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም በዚሁ መስክ በሰፊው እንዲሳተፉ ማበረታታቱን መቀጠል አለበት:: ይሁንና በተለይም በአንደኛ ደረጃ ትምህርት አቅርቦት ረገድ የግል ባለሀብቶችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚሸፍኑት ከፍላጎታችን ጋር ሲነፃፀር በጣም ውሱን መሆኑ አይቀርም:: የመንግስት የበጀት ጭማሪም የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም ለማዳረስ፣ በሽፍት ማስተማርን በሂደት ለማስወገድ፣ በየክፍሉ የሚማረው የተማሪ መጠን ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ለማድረግና ጥራቱንም ለማሻሻል ካለን ፍላጎት አኳያ ሲታይ በምንም መንገድ ሊሸፈን የማይችል



ነው የሚሆነው::

መንግስት፣ የግል ባለሀብቶችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሊሸፍኑት የሚችሉት መጠን ከምንጠብቀው ወጪ ጋር በፍፁም የማይመጣጠን ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሲታይ የህዝቡን ተሳትፎ እጅግ ወደላቀ ደረጃ ማድረስና ትምህርት ቤቶች በገቢ ማሰባሰብ ስራ ላይ የተሻለ ስራ እንዲሰሩ ማድረግ በፍፁም አማራጭ የማይገኝለት መፍትሄ ነው:: በርግጥ ህዝቡ አሁንም ቢሆን የትምህርት ፋይናንስ ክፍተትን በመሸፈን ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው:: ይሁንና ያስቀመጥነውን ግብ ለማሳካት የምንችለው በዚህ ረገድ ከነበረውም እጅግ በተሻለ ሁኔታ መንቀሳቀስ ስንችል ነው::

ህዝቡ በዚህ ጉዳይ ላይ በሰፊው እንዲሳተፍ ለማድረግ በተሳትፎው አስፈላጊነት ላይ የተሟላ እምነት መያዝ ይኖርበታል:: በርግጥ ህዝቡ ለልጆቹ ብቃት ያለው የትምህርት አገልግሎት ለማቅረብ ከፍተኛ ፍላጎት እንዳለውና ባለው አቅምም ለመሳተፍ ዝግጁ እንደሆነ እስካሁን ካለው ተግባራዊ እንቅስቃሴም መረዳት ይቻላል:: ይሁንና እስከዛሬ የነበረው ስራ በዋነኛነት መለስተኛ ክፍተቶችን የመሙላትና ተሳትፎውን የማረጋገጥ ባህሪው የጎላ ነበር:: የህዝቡ ተሳትፎ ቁልፍ የፋይናንስ ምንጭ እንደሆነ ግንዛቤ ተወስዶ በአግባቡ በተቀናጀና በተደራጀ አኳኋን ቀጣይነት ባለው መልክ የሚፈፀም አልነበረም:: እጅግ ሰፊ፣ ቀጣይነት ያለውና በአግባቡ የተደራጀ የህዝብ የፋይናንስ አሸፋፈን እንቅስቃሴ ነው የሚያስፈልገን:: ህዝቡ ይህን የመሰለውን ሰፊና

ቀጣይነት ያለው እንቅስቃሴ አስፈላጊነት በሙሉ ልብ አምኖ እንዲሳተፍበት ለማድረግ ሰፊ የማስረዳትና የማነሳሳት ስራ መስራት አለበት፡፡

ህዝቡ የትምህርት ፋይናንስ ወጪን በተለይም የትምህርት ቤት መስሪያ ወጪና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች መግዣ ወጪን በመሸፈን ረገድ በጉልበት፣ በንብረትና በገንዘብ ባለው አቅም ሁሉ መሳተፍ አለበት ሲባል ሁሉም አካባቢዎች እኩል ሊሳተፉ ይችላሉ ማለት አይደለም፡፡ በርግጥ ሁሉም አካባቢዎች እኩል የመሳተፍ ፍላጎት እንዲያድርባቸው ማድረግ ይገባል፡፡ የህዝቡ ገቢና ኢኮኖሚያዊ አቅም ከቦታ ቦታ ስለሚለያይ እኩል አስተዋፅኦ ማድረግ አይችልም፡፡ የተሻለ ገቢና አቅም ያላቸው በተሻለ ፍጥነትና መጠን ትምህርት ቤቶችን መገንባትና መሳሪያዎቹን ማሟላት ይችላሉ፡፡ መንግስት ይህንን ግምት ውስጥ በማስገባት ሁሉም እኩል መራመድ አለባቸው ብሎ ፈጥነው መራመድ የሚችሉትን መግታት የለበትም፡፡ በራሱ ተሳትፎ አስር ትምህርት ቤት መስራት የሚችል አካባቢ ማንንም ሳይጠብቅ ትምህርት ቤቱን ይስራ፡፡ ሌላውም በአቅሙ ይስራ፡፡ በዚህ ምክንያት የሚፈጠር አለመመጣጠን ሲኖር መንግስት አቅሙ ለሌላቸው ተጨማሪ ድጋፍ በመስጠት በሂደት ሊያስተካክለው ይችላል፡፡

የትምህርት ፋይናንስ ችግርን ለመፍታት ሁሉም አካባቢ አቅሙን አሟጦ ይንቀሳቀስ ማለትና ህዝቡን ለዚሁ ተግባር ማነሳሳቱ ብቻ ግን አይበቃም፡፡ መንግስት የራሱን ወጪዎች



ከዚሁ ጋር ማቀናጀት መቻል አለበት፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ መደበኛ ወጪዎች በመንግስት በጀት መሸፈናቸው የተሻለ ይሆናል፡፡ የህዝቡ ተሳትፎ በዋነኛነት በካፒታል ወጪዎች፣ የትምህርት ቤት ህንፃ መስሪያና የትምህርት ቁሳቁሶች ማሟያ ወጪ በመሸፈን ጉዳይ ላይ ቢያተኩር ይመረጣል፡፡ የካፒታል ወጪ በመሸፈን ረገድም የአካባቢው ህዝብ አቅም በጣም አነስተኛ ሆኖ ሲገኝ መንግስት በሙሉ ወይም በከፊል ሊሸፍነው ይችላል፡፡ ዋናው ጉዳይ የመንግስት በጀትና ህዝቡ የሚሸፍነው ወጪ በቅርብ መቀናጀት ያለበት መሆኑ ነው፡፡

በዚሁ መሰረት የተሻለ ገቢ የማሰባሰብ አቅም ባላቸው ከተሞች ዙሪያ መንግስት ትምህርት ቤት ሰርቶ፣ ቁሳቁሱን ለሚያሟላ አካባቢ ሁሉ በቂ መምህራን መድቦ የትምህርት አገልግሎቱን እንደሚሰጥና እንደሚያሻሽል በማሳወቅ በዚህ ደረጃ ለመሳተፍ አቅሙና ፍላጎቱ ካላቸው ቀበሌዎች ከተሞች ወዘተ. ጋር በመሆን የጋራ እቅድ ሊያዘጋጁ ይችላሉ፡፡ መንግስት መምህራንን አቅርቦ የትምህርት አገልግሎቱን የሚረከብበትና የትምህርት ቤቱ ግንባታና የትምህርት ቁሳቁስ የሚሟላበት ጊዜ የተጣጣመ እንዲሆን ለማድረግ የጋራ እቅድ ማዘጋጀት ይቻላል፡፡ ህዝቡ ገንዘቡን፣ ጉልበቱንና ንብረቱን አንቀሳቅሶ የራሱን ድርሻ መፈፀም ከቻለ አስተማማኝ የትምህርት አገልግሎት እንደሚያገኝ በጋራ እቅዱ አማካኝነት ተረጋግጦለት ተሳትፎውን ለማጠናከር ያደፋፍራል፡፡ ቀድሞ የላቀ አስተዋፅኦ ያደረገ ቀድሞ የተሻለ አገልግሎት እንደሚያገኝ ስለሚያውቅ ተሳትፎውን ለማጠናከር ይበረታታል፡፡

ባላቸው አቅም ሁሉ ተንቀሳቅሰው ሲያበቁ አቅማቸው ውሱን በመሆኑ ምክንያት የካፒታል ወጪውን በሚፈለገው ደረጃ መሸፈን የማይችሉ አካባቢዎች፣ ማድረግ የሚችሉትን አስተዋፅኦ ሁሉ እንዳደረጉ እስከተረጋገጠ ድረስ የካፒታል ወጪውን በከፊል አልፎ አልፎም በሙሉ በመሸፈን ረገድ መንግስት አስተዋፅኦ ማበርከት አለበት፡፡ እንደዚህ አይነቱ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ወቅትም ቢሆን ከአካባቢው ህዝብ ጋር የጋራ እቅድ አውጥቶ መስራት ይጠይቃል፡፡ በአሁኑ ሰአት ስልጣን ወደ ወረዳዎችና ወደ ማዘጋጃ ቤቶች በበቂ መጠን እየተከፋፈለ ስለሆነ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት አገልግሎት የመስጠት ሃላፊነት በዋነኛነት የነሱ እየሆነ ስለሚገኝ ከህዝቡ ጋር በቅርብ ተቀናጅቶና የጋራ እቅድ አውጥቶ ለመስራት የተሻለ ዕድል አለ፡፡ ዋናው ነገር ህዝቡ በተለይም የትምህርት የካፒታል ወጪዎችን በመሸፈን ረገድ ከመቼውም ጊዜ የላቀ፣ በአግባቡ የተደራጀ ቀጣይነት ያለውና ከመንግስት እቅድ ጋር በቅርብ የተቀናጀ ተሳትፎ ማድረግ እንደሚገባው አምኖ ለተግባራዊነቱ እንዲረባረብ የማድረግና በየደረጃው ያሉ የአመራር አካላት ለዚሁ ተግባር ብቃት ያለው አመራር እንዲሰጡ የማድረግ ጉዳይ ነው፡፡

ትምህርት ቤቶች፣ በተለይም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሊያሰባስቡት የሚችሉት ገቢ ይህን ያህል ትልቅ ሊሆን እንደማይችልና አንዳንድ የስራ ማስኬጃ ወጪዎችን ከመሸፈን ሊያልፍ እንደማይችል ግልፅ ነው፡፡ ተማሪው በግል የሚከፍለው ክፍያ ሊኖር ስለማይገባና ስለማይችል በየትምህርት ቤቱ



የሚሰበስበው ገቢ በጣም ውሱን ከመሆን አያልፍም፡፡ ይሁንና ትምህርት ቤቶች ማግኘት የሚችሉት እያንዳንዱ ብር በጣም ስለሚጠቅማቸውና አነሰም በዛም በመንግስት ላይ የሚጫነውን የጪ ሸክም ለማቃለል የራሱ ፋይዳ ያለው በመሆኑ ከልዩ ልዩ ምንጮች ገቢ የሚያሰባስቡበት ስልት ተቀይሶ በስራ ላይ እንዲውል መደረግ ይኖርበታል፡፡ በዚህ ረገድ ትምህርት ቤቶች በአካባቢያቸው የሚገኘውን ልዩ ልዩ አመቺ ሁኔታ የተማሪዎቹንና የመምህራኑን አቅም አስተባብረው በማንቀሳቀስ ተጨማሪ ገቢዎችን የሚያገኙበት ሁኔታ ሊፈጠር ይገባዋል፡፡ ይህን የመሰለው አካሄድ በአንድ በኩል ተማሪዎችና የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ የስራ ባህል እንዲዳብር አስተዋፅኦ የሚያደርግ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ከዚሁ በሚገኘው ገቢ ስራቸውን እንዲደጉሙ በማድረግ የመንግስትን ወጪ ለመቀነስ ያስችላል፡፡

ያልተማከለ የትምህርት ፋይናንስ አስተዳደርን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ ከመቼውም ጊዜ የላቀ ተፈላጊነት ያለው ጉዳይ ነው፡፡ የያዝነውን የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም የማዳረስና ጥራቱንም የማሻሻል ስራ፣ በዚህ መስክ የህዝቡን ተሳትፎ ከመቼውም ጊዜ በላቀ ደረጃ ላይ የማድረስ አላማ ሊሳካ የሚችለው ያልተማከለው የትምህርት ፋይናንስ አስተዳደር ስራ ላይ ሲውል ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ስልጣንን ወደወረዳዎችና ማዘጋጃ ቤቶች ለማከፋፈል እየተወሰደ ያለው ርምጃ ረጅም ርቀት እንደሚወስደን እሙን ነው፡፡ ይሁንና ይህ ብቻውን በቂ ስላልሆነ ተጨማሪ ርምጃዎች መወሰድ አለባቸው፡፡

ያልተማከለ የትምህርት ፋይናንስ አስተዳደር ተግባራዊ በሚሆንበት ወቅት አጠቃቀሙ ቆጣቢና ስርአት የተከተለ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህንኑ ለማረጋገጥ ከሚያስችሉት ቁልፍ መሳሪያዎች አንዱ የትምህርት ፋይናንስ ወጪ ስርአትና የክትትልና ቁጥጥሩ ስርአት ወጥነት ባለው መመሪያ እንዲከናወን ማድረግ ነው፡፡ በዚህ መመሪያ ከበላይ አካላት ለበታች አካላት የበጀት ድጋፍ የሚሰጥበት ቀመር ምን እንደሚሆን መወሰን ይኖርበታል፡፡ የበታች አካላት፣ ትምህርት ቤቶቹ ራሳቸውም ጭምር የሚያሰባስቡትን ገቢ በምን መልክ ትምህርትን ፋይናንስ ለማድረግ እንደሚጠቀሙበት የሚወስንም መሆን አለበት፡፡ መመሪያው የመንግስትና የህዝብ የፋይናንስ አስተዋፅኦ ምን መምሰል እንዳለበትና በምን መልክ እንደሚቀናጅም የሚወስን ሊሆን ይገባዋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ወጪ የማውጣት ውሳኔ ማን እንደሚወስን፣ እንዴት እንደሚወስንና በምን መልኩ ቁጥጥር እንደሚደረግበት የሚያስረዳ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከዚህ አኳያ ያሉንን የፋይናንስ መመሪያዎች በመገምገም፣ ያስቀመጥናቸውን አቅጣጫዎችና ግቦች መነሻ በማድረግ የተሟላ የፋይናንስ መመሪያ ማዘጋጀትና ተግባራዊ መሆኑን በጥብቅ መቆጣጠር ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጣቸው ከሚገቡ ጉዳዮች አንዱ ይሆናል፡፡

ያልተማከለ የትምህርት ፋይናንስ አስተዳደር ይኑረን ሲባል በወረዳና በማዘጋጃ ቤቶች ደረጃ ብቻ ተወስኖ መቅረት ያለበት አይደለም፡፡ ይልቁንም ይህ አሰራር ተፈላጊውን ውጤት ማስገኘት የሚችለው ከዚያ አልፎ ወደ ቀበሌዎች በተለይም ወደእያንዳንዱ የትምህርት ተቋም የሚወርድ ሲሆን ነው፡፡



በመሆኑም ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት በአፋጣኝ አሟልቶ፣ የሚዘጋጀው የትምህርት ፋይናንስ መመሪያም ይህንኑ የሚያካትት እንዲሆን በማድረግ ያልተማከለው አሰራር በተቻለ ፍጥነት ወደእያንዳንዱ የትምህርት ተቋም እንዲደርስ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### 3.3. የትምህርት አስተዳደር ስርአትን ማሻሻል፣

ያስቀመጥነው የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን የማስፋፋትና ጥራቱንም የማሻሻል አቅጣጫ፣ የህዝቡንና የተማሪዎች ወላጆችን ተሳትፎ በከፍተኛ ደረጃ የሚጠይቅ ነው፡፡ የትምህርት ቤቶች ማስፋፊያ የካፒታል ወጪ በዋነኛነት ከህዝቡ እንዲመጣ ነው እየታሰበ ያለው፡፡ በዚህ ረገድ የህዝቡ ተሳትፎ በላቀ ደረጃ ላይ ካልደረሰ በስተቀር የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም የማዳረስ ግባችን በሚፈለገው መጠን ሊሳካ አይችልም፡፡ በትምህርት ቤት ውስጥ ስርአትና ዲሲፕሊን በተሟላ ሁኔታ እንዲሰፍን ይፈለጋል፡፡ ይህ ስራ ከህዝቡና ከወላጆች ተሳትፎ ውጪ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም፡፡ በትምህርት ቤት ውስጥ ከሚካሄደው የስነ-ዜጋ ትምህርትና፣ የስራ ስነ-ምግባርና አመለካከት ትምህርት በተጨማሪ ህዝቡም በተማሪዎች ባህሪ ቀረፃ ስራ ላይ በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ በሰፊው መሳተፍ አለበት፡፡ ህዝቡ ከሚጠበቅበት ተሳትፎ ጋር የሚመጥን የአመራር ሚና መጫወት ይገባዋል፡፡ በትምህርት አስተዳደር ስርአት ላይ በቂ ድርሻ ሊኖረው ይገባል፡፡

ህዝቡ በትምህርት አስተዳደሩ ላይ በቂ ተሳትፎ ሊኖረው

ይገባል ሲባል የሚወክሉትን የትምህርት ኮሚቴ አባላት በመምረጥ ላይ የተገደበ ተሳትፎ ማለታችን አይደለም፡፡ በትምህርት ፖሊሲውና እቅድ ላይ የተሟላ ግንዛቤ ጨብጦ፣ በዚህ በኩል የሚጠበቅበትን ድርሻ ለመፈፀም የሚያስፈልጉትን ቋሚና ጊዜያዊ አደረጃጀቶች ተጠቅሞ በሰፊውና በቀጣይነት መሳተፍ አለበት ማለት ነው፡፡ በዚህ መሰረት ለምሳሌ የትምህርት ቤት ግንባታ ስራን የሚመራበት የተለያዩ ኮሚቴዎች ወይም ንኡሳን ኮሚቴዎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡ የተቋቋሙ ትምህርት ቤቶችን በመምራት ስራ ላይ የሚወክሉትን የትምህርት ኮሚቴ አባላት ሊመርጥ ይችላል፡፡ የትምህርት ስርአቱን ችግር ለመቅረፍ በሚል የሚያቋቁማቸው ጊዜያዊ ኮሚቴዎችም ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ የመረጣቸው ኮሚቴዎች ስራቸውን እንዴት እንደፈፀሙ እየገመገመ የማስተካከያ ርምጃዎችን ሊወስድም ይችላል፡፡ ዋናው ነገር ህዝቡ የትምህርት ስርአቱ የልጆቹ ባህሪና ቀረፃ ጉዳይ መሆኑን ተገንዝቦ በልጆቹ ባህሪ ቀረፃ ስራ ላይ በባለቤትነት በሰፊው እንዲሳተፍ የማስቻል ጉዳይ ነው፡፡

በትምህርት አመራር ኮሚቴዎች ውስጥ ህዝቡና የተማሪዎች ወላጆች በቂ ውክልና እንዲኖራቸው ከማድረግ በተጨማሪ አባላቱ ስራቸውን በብቃት እንዲፈፅሙ የሚያስችላቸው አቅም እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የኮሚቴው አባላት የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲውን፣ በአካባቢያቸው ከፖሊሲው አኳያ የተቀመጠውን ግብ፣ ግቡን ከማስፈፀም አኳያ ያሉ ችግሮችና መሰረታዊ የመፍትሄ አቅጣጫዎች ምን እንደሆኑ በጥልቀት እንዲያውቁ መደረግ



አለበት፡፡ በየደረጃው ያሉ የመንግስት የትምህርት አመራር አካላት ይህንን የማረጋገጥ ግዴታ እንዳለባቸው ማወቅ ይገባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የኮሚቴው አባላት ተግባርና ሃላፊነት ምን እንደሆነ በውል ተለይቶ ሊቀመጥና አባላቱም እንዲያውቁት ሊደረግ ይገባል፡፡ በመጨረሻም አባላቱ ስራቸውን በብቃት ለመስራት የሚጎድላቸው ነገር ተለይቶ፣ ይህንኑ ለማስወገድ የሚያስችል አጫጭር ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

የአመራር ኮሚቴዎቹን ውጤታማነት ለማረጋገጥ ኮሚቴዎቹ ፋይዳ ያለው የመወሰን ስልጣን ሊሰጣቸውና፣ ወጥነት ያለው የክትትልና ግምገማ ስርአት ሊኖር ይገባል፡፡ በዚህ መሰረት ኮሚቴዎቹ የትምህርት ቤቱን የስራ እቅድና የትምህርት ቤቱን በጀት በማፅደቅ ላይ ተጨባጭነት ያለው ስልጣን ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ የእቅዱን አፈፃፀም ገምግሞ በማስተካከል፣ የአስተማሪዎችንና የትምህርት ቤት ስራ መሪዎችን የስራ አፈፃፀም በመገምገም ላይና በነዚህ አካላት እድገት ላይ ተጨባጭነት ያለው ሚና ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ሃላፊነታቸውን በሚገባ መወጣታቸውን የአካባቢው አስተዳደር አካላት የሚከታተሉበትና ተፈላጊውን ድጋፍ የሚሰጡበት ስርአትም ሊፈጠር ይገባል፡፡ በመጨረሻም ኮሚቴዎቹ ለመረጣቸው ህዝብ የስራ ዘገባ የሚያቀርቡበት፣ ስራቸውን በአግባቡ ካልፈፀሙ የሚቀየሩበትና የተሻለ ብቃት ያላቸው ሰዎች የሚመረጡበት አሰራር መኖር ይገባዋል፡፡

የትምህርት አመራሩን ስርአት ለማሻሻልና ለማጠናከር

የመምህራን ተሳትፎ በጣም መሰረታዊ ነው፡፡ መምህራን በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ብቻ ሳይሆን በትምህርት አመራር ስራ ላይም መሳተፍ የሚችሉት በግልና በጋራ ማህበራቸው አማካኝነት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የመምህራን ተወካዮች በየትምህርት ቤቱ በሚቋቋመው የአመራር ኮሚቴ ውስጥ በብቃት የሚወከሉበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡ የመምህራን ተወካዮችም እንደህዝቡ ተወካዮች ስራቸውን በብቃት ለመፈፀም የሚያስችላቸው አመለካከትና ብቃት እንዲኖራቸው መደረግ አለበት፡፡

መምህራን በትምህርት አመራሩ ስርአት ውስጥ በግል እየተመረጡ በመሳተፍ ከሚያበረክቱት የማይተናነስ አስተዋፅኦ በማህበራቸው ተደራጅተው ሊያበረክቱ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም በሁሉም ደረጃዎች ያሉ የመንግስት የትምህርት አመራር አካላት በየደረጃው የሚገኙትን የመምህራን ማህበራትን በአጋርነት የማንቀሳቀስና በትምህርት ስርአቱ አመራር ስራ ላይ በቂ ሚና እንዲጫወቱ የማስቻል ሃላፊነት እንዳለባቸው ሊገነዘቡ ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ በቅድሚያ ሊሰሩ ከሚገባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች አንዱ በየደረጃው ያሉ የመንግስት ሃላፊዎች በደረጃቸው ካሉ የመምህራን ማህበራት ጋር በመተባበር በትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ በዚህ ጉዳይ ላይ በተቀመጡት የመፍትሄ አቅጣጫዎችና እቅዶች በአካባቢው ባሉ የትምህርት ስርአቱ ችግሮችና በመምህራን ተሳትፎና መብት አጠባበቅ ጉዳይ ላይ የጋራ መድረክ ፈጥረው ሊወያዩ ሊከራከሩና ሊግባቡ ይገባል፡፡ በነዚህ መድረኮች አማካኝነት በዴሞክራሲያዊ ውይይት በሚደረስባቸው የጋራ ግንዛቤዎች ላይ መንግስትና መምህራን በጋራ ስለሚፈፅሙዋቸው



ስራዎችም በጋራ ማቀድ ይገባል፡፡ ስምምነት ባልተደረሰባቸው ጉዳዮች ላይ ልዩነቶችን እንዴት አቻችሎ መስራት እንደሚቻልም መግባባት ይገባል፡፡

እጅግ በጣም የሚበዙቱ መምህራን እንደዚህ አይነቱ የተደራጀና ቀጣይነት ያለው የተሳትፎ መድረክ ቢከፈትላቸውና በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ በቂ ማብራሪያ ከተሰጣቸው የተቀመጡትን የትምህርትና ስልጠና እቅዶች በከፍተኛ ወኔ ለመተግበር እንደሚነሳሱና በየአካባቢው ካሉት የመንግስት አካላት ጋር ተቀናጅተው ለመስራት ዝግጁ እንደሚሆኑ አያጠራጥርም፡፡ እነዚህ መድረኮች በመምህራን መብትና ጥቅም አጠባበቅ ጉዳይ ላይም ውይይት ሊደረግባቸው የሚችሉ መድረኮች ናቸው፡፡ በዚህ አኳኋን መምህራንና መንግስት በጉዳዩ ላይ አንድ አይነት እውቀትና የጋራ መረጃ ሲኖራቸው፣ ስለሆነም ከመረጃ እጥረትና ከግንዛቤ ጉድለት የሚፈጠሩ ችግሮችን በአጭሩ ለመቅጨት ይችላሉ፡፡ ከዚህ ባሻገር ተጨባጭ ችግሮች ሲኖሩም በመግባባት መንፈስ ለመፍታት ምቹ ሁኔታ ይፈጠርላቸዋል፡፡ መግባባት ያልተቻለባቸው ጉዳዮች ሲያጋጥሙም የመማር ማስተማር ሂደቱን በማይጎዳ አኳኋን በሂደት ሊፈቱ የሚችሉበትን አቅጣጫ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

መምህራንን በተጠቀሰው መልክ በማህበራቸው አማካኝነት በሰፊው በማሳተፍ ጉዳይ ላይ በየደረጃው ባሉ የመንግስት አካላትና በማህበራቱ የሚታዩ አንዳንድ የአመለካከት ችግሮች እንቅፋት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በመንግስት ባለስልጣናት በኩል መምህራን

በማህበራቸው ተደራጅተው በትምህርት አመራር ስራ ላይ የመሳተፍ መብት እንዳለባቸው ከልብ ያለማመን ችግር ያጋጥማል:: ማህበራቱን ከሩቁ በጥርጣሬ አይን የመመልከትና እንደተቀናቃኝ የመፈረጅ ጉዳይም ሊኖር ይችላል:: መምህራን የሚያነሷቸውን የመብትና የጥቅም ጉዳዮችንም በጥሞና የማዳመጥ፣ ባፋጣኝ ሊፈቱ የሚችሉትን ለመፍታት፣ በአፋጣኝ ሊፈቱ የማይችሉትን ምክንያታቸውን አስረድቶ ለወደፊቱ ሊፈቱ የሚችሉበትን አቅጣጫ ለማስቀመጥ ዝግጁ ያለመሆን ያጋጥማል:: በየደረጃው ያሉ የመንግስት አመራር አካላት እነዚህን የተሳሳቱ አመለካከቶች በአፋጣኝ እንዲያስወግዱ ካልተደረገ በስተቀር በመንግስትና በመምህራን መካከል አላማችን በሚጠይቀው ደረጃ ጤናማ ግንኙነትና የአላማ አጋርነት ሊኖር አይችልም::

ማህበራቱ በርግጥ የአባላቱን መብትና ጥቅም የማስከበር ሃላፊነት እንዳለባቸው ተገንዝበው ለዚህ አላማ በቂ ትኩረት ሰጥተው መንቀሳቀስ ይገባቸዋል:: ይሁንና ይህ አላማም በይበልጥ ሊሳካ የሚችለው በጉዳዩ ላይ ቀጣይነት ባለውና ገንቢ በሆነ አኳኋን ከሚመለከታቸው ወገኖች ጋር መወያየት ሲቻልና መፍትሄ ለመሻት በጋራ በመንቀሳቀስ ነው:: ከዚህም ባሻገር መምህራኑ የራሳቸውን መብትና ጥቅም ከማስከበር ጎን ለጎን ለህብረተሰቡ ብቃቱ የተረጋገጠ የትምህርት አገልግሎት የማቅረብ የሙያ ግዴታ እንዳለባቸውና ማህበራቱ ይህንኑ በማረጋገጥ ረገድ ከፍተኛ ስራ መስራት እንዳለባቸው መገንዘብ ይገባቸዋል:: ይህን በተመለከተ በተለያየ ደረጃ ያሉ የተሳሳቱ አመለካከቶች ካልተስተካከሉ በመምህራንና በመንግስት መካከል ጤናማ ግንኙነት



ለመመስረት፣ የመምህራንን መብትና ጥቅም መሆን በሚገባው ደረጃ ለማስጠበቅና የትምህርት አላማችንን በሚፈለገው ደረጃ ለማሳካት አይቻልም:: ማህበራቱ የአባላቱን የሙያ ብቃትና ስነ-ምግባር በማሳደግና በማስከበር፣ ምግባረ-ብልሹ መምህራን ለሙያው ክብርና ለትምህርቱ አላማ መሳካት ሲባል እንዲስተካከሉ የመጣርና መንግስትም በዚህ ጉዳይ ላይ ከሚያደርጋቸው ጥረቶች በጎ አስተዋፅኦ የማበርከት ሃላፊነት እንዳለባቸው መገንዘብ ይገባቸዋል:: መንግስትና መምህራን ከላይ የተጠቀሱትን ጉድለቶች አስተካክለው በቅንጅትና በአጋርነት የሚሰሩበት ሁኔታ መፈጠር የትምህርት አላማችንን ለማሳካትና አስተዳደሩንም ለማሻሻል መከናወን ካለባቸው ወሳኝ ስራዎች አንዱ ነው::

## 4. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት፣

### 4.1. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ስርጭትና አወቃቀር፣

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት አገራችን አሁን ካለችበት የእድገት ደረጃና በሚቀጥሉት 5-10 አመታት ልትደርስበት ትችላለች ተብሎ ከሚገመተው እድገት አኳያ ሲታይ ዜጎች በአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ህይወት ውስጥ በብቃት ለመሳተፍ የግድ የሚያስፈልጋቸው ትምህርት ነው:: ይህም በመሆኑ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማግኘት እንደዜግነት መብት ሊቆጠር ይችላል:: የአንደኛ ደረጃ ትምህርት አላማ ትምህርትን ለሁሉም ዜጎች ማዳረስ በዚህ ላይ ተመስርቶ የተለያዩ አጫጭር የሙያ ስልጠናዎች በመስጠት የአገሪቱን የሰው ሃይል

የልማት አቅም ማጎልበት፣ መለስተኛ ሞያተኛን መፍጠር ነው:: ነገር ግን ለአገሪቱ የሚያስፈልጓት ዝቅተኛ ሞያተኞች ብቻ አይደሉም:: ከኢኮኖሚው እድገት ጋር አብሮ የሚጨምር የመካከለኛና ከፍተኛ ባለሙያ ፍላጎትም አላት:: ስለሆነም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ሰፊውን የአገራችንን ህዝብ ወደ መለስተኛ ሙያተኛ ከማሳደግ ባሻገር መካከለኛና ከፍተኛ ባለሙያዎችን ለመፍጠር የሚያስችል መሸጋገሪያ ድልድይ ሆኖም ያገለግላል::

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አላማ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ውጤትን መሰረት በማድረግ በዋነኛነት አገሪቱ የምትፈልጋቸውን መካከለኛ ሙያተኞች ማፍራት፣ በተጨማሪም ከፍተኛ ሙያተኞችን ለማፍራት ለሚደረገው የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም መሸጋገሪያ ሆኖ ማገልገል ነው:: በአገራችን ተጨባጭ የእድገት ደረጃ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም ዜጎች ማዳረስ የሚቻልም ሆነ የሚያስፈልግ ነገር አይደለም:: ከአገሪቱ እድገትና ከመካከለኛ ሙያተኛ ፍላጎት ጋር በተመጣጠነ አኳኋን እየጨመረ የሚሄድ ነው:: በመሆኑም ምንም እንኳ የአገራችን ልማት እየተፋጠነ ሲሄድ በአንድ ወቅት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለሁሉም ዜጎች ማዳረስ አማራጭ የሌለው የሚሆንበትና ተግባራዊ ለማድረግም የሚቻልበት ደረጃ ላይ እንደምንደርስ ቢገመትም፣ ይህ በአሁኑ ወቅት እንደግብ ሊቀመጥ የሚችል አይደለም:: በአሁኑ ወቅት ሊቀመጥ የሚችለው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ስርጭት ግብ አገሪቱ የምትፈልጋቸውን መካከለኛና ከፍተኛ ሙያተኞች ለማፍራት በሚያስችልና ፍትሃዊነቱ በተረጋገጠ አኳኋን ትምህርቱን ማስፋፋት ነው::



በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ መሰረት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በሁለት ሳይክል እንዲከፈል ተደርጓል:: የመጀመሪያው ሳይክል 9ኛና 10ኛ ክፍልን የሚሸፍን ሲሆን ከዚህ በፊት እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ይሰጥ የነበረውን ትምህርት በሙሉ የሚያካትትና የሚያሻሽል ይዘት ያለው ነው:: ሁለተኛው ሳይክል በዋነኛነት ለዩኒቨርሲቲ ትምህርት መዘጋጃ ሆኖ የሚያገለግልና የ11ኛና 12ኛ ክፍልን ያካተተ ነው:: በዚህ ደረጃ የሚሰጠው ትምህርት ከዚህ በፊት በዩኒቨርሲቲዎች በመጀመሪያው አመት በማዘጋጃነት ይሰጥ የነበረው ትምህርት ነው:: ይህ በዩኒቨርሲቲ በአንድ አመት ይሰጥ የነበረው ትምህርት ተጠናክሮና በሁለት አመት የሚሰጥ እንዲሆን ተደርጎ ነው በሁለተኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል የሚሰጠው::

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በሁለት ሳይክል እንዲከፈል የተደረገው ከትምህርቱ አላማ በመነሳት ነው:: የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ሁለት መሰረታዊ አላማዎች አሉት:: አንዱና ዋነኛ አላማው አገሪቱ የምትፈልጋቸውን መካከለኛ ሙያተኞች ማፍራት ነው:: ሁለተኛው አላማ አገሪቱ የምትፈልጋቸውን ከፍተኛ ሙያተኞች ለማፍራት የሚያስችል ስራ ለመስራት የሚያስችል ዝግጅት ማከናወን ነው:: ሁለቱ ሳይክሎች ከሁለቱ አላማዎች ጋር የተያያዙና ሁለቱን አላማዎች በተሻለ አኳኋን ለመፈፀም ተብለው የታቀዱ ናቸው:: የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የመጀመሪያው ሳይክል ዋነኛ አላማ አገሪቱ የምትፈልጋቸውን መካከለኛ ሙያተኞች ማፍራት ነው:: ይህን ከሙያና ቴክኒክ

ስልጠና ፕሮግራማችን ጋር በማቀናጀት መፈፀም ነው። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ሁለተኛ ሳይክል ዋነኛ አላማ አገሪቱ የምትፈልጋቸውን ከፍተኛ ሙያተኞች ለማፍራት የሚያስችል ቅድመ-ዝግጅት ማጠናቀቅ ነው።

እንደሚታወቀው ሁሉ ከዚህ ቀደም በአገራችን እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ ይሰጥ የነበረው ትምህርት በሌሎች በርካታ አገሮች እስከ 10ኛ ክፍል ባለው ትምህርት የሚጠናቀቅ ነው። በአዲሱ ትምህርት ፖሊሲም ከዚሁ ልምድ በመማር ከዚህ በፊት በ12 አመት ያልቅ የነበረው ትምህርት ስርአተ-ትምህርቱን በማጠናከርና በማሻሻል በ10 አመት እንዲያልቅ ተደርጓል። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ከሚማረው ወጣት መካከል በአሁኑ ወቅት እጅግ የሚበዛው ወደሁለተኛ ደረጃ የሚሸጋገር ሳይሆን ትምህርቱን አጠናቆ የአገሪቱን የመለስተኛ ሙያተኞች ፍላጎት በማርካት ላይ የሚሰማራ እንደሆነው ሁሉ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚማረውም ወጣት እጅግ የሚበዛው ወደዩኒቨርሲቲ የሚገባ ሳይሆን የአገሪቱን የመካከለኛ ሙያተኛ ፍላጎት በማርካት ተግባር ላይ የሚሰማራ ነው። በመሆኑም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን በሁለት ሳይክል ከፍሎ የመጀመሪያው ሳይክል ዋናውን አላማ ማለትም መካከለኛ ሙያተኛ ለማፍራት በሚያስፈልግ ትምህርት ላይ እንዲያተኩር ማድረግ በጣም አስፈላጊና ተገቢም ነው። ከዚህ በፊት በ12 አመት ውስጥ ይሰጥ የነበረው ትምህርት የሌሎች አገሮች ልምድም እንዳረጋገጠው በ10 አመት ሊሰጥ የሚችል በመሆኑ ይህንኑ አጠንክሮ በ10 አመት የቀለም ትምህርት ላይ ተመስርቶ የመካከለኛ ሙያተኛ



ፍላጎትን ማሟላት ተገቢ ነው።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ከሚማረው ተማሪ ውስጥ በጣም የሚበዛው ወደ ዩኒቨርሲቲ የማይቀጥል ነው። በመሆኑም ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚቀጥለውንና የማይቀጥለውን አንድ ላይ አዳምሮ ለከፍተኛ ትምህርት ማዘጋጀት ከፍተኛ የገንዘብና የጊዜ ብክነት የሚያስከትል እንጂ ምንም አይነት ጥቅም ሊሰጥ የሚችል አይሆንም። ስለሆነም ከፍተኛ ትምህርት ለመማር ብቃቱ ያላቸውን ብቻ ለይቶ ለዚሁ ለማዘጋጀት በሚያስችለው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ሁለተኛ ሳይክል ማዘጋጀት በጣም አስፈላጊ ይሆናል። የሁለተኛ ሳይክል መኖር በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ በአንድ አመት ይፈፀም የነበረውን የዝግጅት ምዕራፍ በሁለት አመታት ከፋፍሎና አጠናክሮ በመስጠት የትምህርቱን ጥራት በከፍተኛ ደረጃ ለማሻሻልም ይረዳል። የዝግጅት ምዕራፉ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጥራቱን ይበልጥ ለመጠበቅ የሚያስችል በቂ ጊዜ ተሰጥቶት መጠናቀቁ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የሚደረገውን የአንድ አመት የዝግጅት ስራ በማስቀረት ጥራቱን በማይነካ አኳኋን የትምህርት ጊዜውን ብሎም ወጪውን ለመቀነስም ያስችላል።

የፖሊሲው ጠቀሜታ ይህን ያህል የጎላ ሆኖ ሳለ በጉዳዩ ላይ የተለያዩ ትችቶች መቅረባቸው አልቀረም። ከዚህ አኳያ በዋናነት ሊጠቀስ የሚችለው ትችት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የመጀመሪያ ሳይክልን የሚጨርሱት ወጣቶች በዕድሜ ያልበሰሉ በመሆናቸው ከትምህርት ወጥተው ስራ አያገኙም፣ በአልባሌ

ተግባራት ላይ የሚሰማሩ ይሆናሉ:: ስለሆነም ተጨማሪ ሁለት አመታት እንዲማሩ ሊደረግ ይገባል የሚለው ነው::

በመጀመሪያ ደረጃ ግልፅ መሆን ያለበት የትምህርት ስርአቱ አላማ በመለስተኛ ወጪ ጥራቱ የተጠበቀ የትምህርት አገልግሎት በመስጠት ወጣቶችን ለስራ ማዘጋጀት፣ በህብረተሰቡ ውስጥ ገንቢ ሚና የሚጫወቱ ዜጎች እንዲሆኑ ማብቃት ነው:: ወጣቶች ዕድሜያቸው እስኪደርስ ድረስ ከአልባሌ ቦታ ተከልለው እንዲውሉ ለማድርግ የተቀረፀ መዋያ ስፍራ አይደለም:: ትምህርቱን በብቃት ለመፈፀም በሚያስችል ጊዜ ውስጥ ትምህርታቸውን ጨርሰው የሚሰናበቱበት እንጂ ስራ ስለማያገኙ ወይም ወደአልባሌ ተግባር እንዳይገቡ ተብለው የትምህርት አገልግሎቱን ለመስጠት ከሚፈለገው ጊዜ በላይ መዋያ የሚሆንበት ሁኔታ በፍፁም ሊታሰብ አይገባም::

ትምህርት ቤቶች ወጣቶች ስራ እስካላገኙ ድረስ ከአልባሌ ቦታ ተከልለው የሚውሉባቸው ተቋሞች መሆን ይገባቸዋል የሚል የተሳሳተ አመለካከት ከተያዘም ጉዳዩ በዋነኛነት የ10ኛ ክፍል ትምህርትን ባጠናቀቁ ወጣቶች ላይ መነሳት ያለበት አይደለም:: እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ዕድሜው ለትምህርት ከደረሰው ህፃን በእነዚህ መዋያ መሆን አለባቸው ተብለው በተቀመጡት ትምህርት ቤቶች ለመሳተፍ ዕድሉ የነበረው ከ30 በመቶ በታች ነው:: ከ70% በላይ የሚሆነው እንኳንስ ለ10 አመታት ይቅርና ለአንድ አመትም መዋያ የሚሆን ትምህርት ቤት ያገኝ አልነበረም:: 10ኛ ክፍልን የጨረሰ የ16ና የ17 አመት ወጣት



ሳይሆን በአንደኛ ክፍል ደረጃ የሚመደብ የ6ና የ7 አመት ህፃን ነው በነዚህ መዋያዎች መሳተፍ ተስኖት የቆየው:: የመሳተፍ ዕድል ካገኘውም ከግማሽ በላይ የሚሆነው አራተኛ ክፍል ሳይደርስ ነበር ተንጠባጥቦ የሚቀረው:: በአሁኑ ሰአት ይህን ዕድል የሚያገኘው ህፃን ከ57% በላይ ደርሶ በዚህ ረገድ የነበረው ችግር ተሻሽሏል፣ 8ኛ ክፍልን ሳይጨርስ የሚንጠባጠበውም ቀንሷል:: ይሁንና ዛሬም ቢሆን ገና በህፃንነት ዕድሜው ከትምህርት ውጭ የሚሆነው ኢትዮጵያዊ 10ኛ ክፍልን አጠናቆ ከሚወጣው በጣም በብዙ እጥፍ ይበልጣል::

ትምህርት ቤቶች የመማሪያ ተቋሞች ሳይሆኑ የህፃናትና ወጣቶች መዋያ ተቋሞች ይሁኑ ከተባለም ጥያቄው መነሳት ያለበት በአንድ በኩል በዕድሜ 10ኛ ክፍልን ከጨረሰው በጣም ያነሱት ሆነው በቁጥራቸው ግን እጅግ ከሚበዛውና በተለያዩ ምክንያቶች ከትምህርት ውጭ ሆነው በነበሩት የኢትዮጵያ ህፃናት፣ በሌላ በኩል ደግሞ መሻሻል ቢኖርም አሁንም ወደሁለተኛ ደረጃ ሳይሸጋገሩ በሚቀሩት 70%ና ከዚያ በላይ ከሚሆኑት የኢትዮጵያ ተማሪዎች አኳያ መሆን አለበት:: ጉዳዩን ከዚህ አኳያ ስናየው ትምህርት ቤቶችን የህፃናት መዋያ ስፍራ አድርጎ የሚያየውን ይህንን ጉዳይ የ10ኛ ክፍል ትምህርትን ካጠናቀቁት ወጣቶች አኳያ የሚያየው አመለካከት ምን ያህል የተሳሳተ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል:: የተሳሳተ ብቻ ሳይሆን እጅግ በጣም ኢ-ፍትሃዊ አነሳስ ያለውና እጅግ በጣም የሚበዛውን የኢትዮጵያ ወጣትና ህፃን በፍፁም ግምት ውስጥ የማያስገባ መሆኑን እንገነዘባለን::

ትምህርታቸውን ጨርሰው የሚወጡት ወጣቶች ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ ስራ የማግኘት ዕድል እንዲኖራቸው የማድረጉ ጉዳይ ተገቢና ትኩረት የሚሰጠውም ጉዳይ ነው:: ይሁንና ይህ ከዕድሜ ጋር መያያዙ ትክክል አይደለም:: በአለም አቀፍ መስፈርቶች በስራ ላይ መሰማራት የማይገባው ህፃን ከ14 አመት በታች የሆነው ነው:: በአገራችን ነባራዊ ሁኔታ እንኳንና 10ኛ ክፍልን 8ኛ ክፍልንም የሚጨርሰው ከ14 አመት በላይ ሆኖ ነው:: በተጨባጭ እንደሚታየው ብዙ ተማሪዎች ዕድሜያቸው ከትምህርት ደረጃቸው በላይ ነው:: እድሜያቸውና የትምህርት ደረጃቸው ተቀራራቢ ሆኖ የሚማሩትም ቢሆኑ 10ኛ ክፍልን ሲጨርሱ የ16 ወይም የ17 አመት ወጣቶች ይሆናሉ:: ይህ የተለያዩ የሙያ ስልጠናዎችን ለማግኘት ከሚጠይቀው ጊዜ ጋር ሲዳመር የዜግነት መብትና ግዴታን በተሟላ ሁኔታ ለመፈፀም በሚያስችል የዕድሜ ክልል ውስጥ መግባታቸው አይቀርም:: የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ምሩቃን የሆኑትም በተለይም በገጠሩ አካባቢ በተለያዩ ስራ ሊሰማሩ በሚችሉበት የዕድሜ ክልል ውስጥ ናቸው::

በሌላ በኩል የስራ አጥነት ጉዳይ ተማሪዎችን እስከ 10ኛ ክፍል ወይም እስከ 12ኛ ክፍል በማስተማር የሚወሰን ጉዳይ አይደለም:: የተማሪዎቹ ብቃትና የኢኮኖሚው ሁኔታ ስራ ሊፈጥር የሚችል ካልሆነ እንኳንስና እስከ 12ኛ ድረስ ተምረው ከዚያ በላይ ተምረውም ስራ አጥ መሆናቸው አይቀርም:: ተማሪዎቹን እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ በማስተማር የስራ አጥነቱ ችግር የሚፈታ



ቢሆን ኖሮ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ በነበረው የትምህርት ስርአት እስከ 12ኛ ድረስ ተምረው ስራ አጥ ሆነው የቀሩ በመቶ ሺ የሚቆጠሩ ወጣቶች ባልተፈጠሩ ነበር:: በመሆኑም የትምህርት ፕሮግራሙ ከሚጠይቀው በላይ ተማሪውን ለሁለት አመት ማቆየት የስራ አጥነቱን ችግር በምንም መልኩ አይፈታውም:: የሚያደርገው ነገር ቢኖር ተማሪው ስራ አጥ ተብሎ የሚፈረጅበትን ጊዜ በሁለት አመት ማራዘምና ይህንን ለማድረግም በጣም ከፍተኛ የገንዘብና የጊዜ ወጭን ማውጣት ነው:: የስራ አጥነቱ ችግር የሚፈታው የትምህርት ስርአቱን ለሁለት አመት በማራዘም ወይም በማሳጠር ሳይሆን ከዚያ ውጭ በሚወሰዱና መወሰድም በሚገባቸው ርምጃዎች ነው::

የስራ አጥነትን ችግር ለመቅረፍ በመጀመሪያ ደረጃ የአገራችን ኢኮኖሚ በፍጥነት ማደግ ይኖርበታል:: ልማታችን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችሉ ፖሊሲዎች መቀየስና ተግባራዊ መሆን አለባቸው:: ኢኮኖሚያችን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት የሚያስመዘግብ ካልሆነ የስራ አጥነት ችግር ከአመት አመት እየተባባሰ ከመሄድ ውጭ ሌላ አማራጭ የለም:: የትምህርት ስርአቱ የሚያፈራቸው ወጣቶች ስራ አጥተውና ባክነው መቅረታቸው የማይቀር ይሆናል:: ልማታችን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት ሲኖረው፣ የስራ ዕድል በሰፊው ይፈጠራል፣ የተማረው የሰው ሃይል በተማረበት መስክ ተሰማርቶ ራሱን ጠቅሞ አገሩን ያለማል:: መንግስት ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማረጋገጥ ያስችላሉ ብሎ ያመነባቸውን ስልቶች ቀይሶ ተግባራዊ ለማድረግ እየተረባረበ

ያለው ይህንኑ በመገንዘብ ነው። የማስፈፀም አቅም ግንባታና የዚሁ አካል የሆነው የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ትልቁ የልማት መሳሪያና ውጤትም ነው ብሎ ልማትንና ትምህርትን፣ ትምህርትንና ለተማረው ሰው የስራ ዕድል የሚፈጥረውን ልማት በቅርብ አስተሳስሮ እየፈፀመ ያለው ይህንን በመገንዘብ ነው። የስራ አጥነትን ጉዳይ የትምህርት ስርአቱ በተናጠል ሊፈታው የሚችል ሳይሆን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት ከማረጋገጥ ጋር ተሳስሮ ሲታይና ሲፈፀም የሚፈታ ጉዳይ ነው።

የተማረ ስራ አጥ ችግር የሚፈታው ተማሪው የሚፈለገው እውቀት፣ ባህሪና ስነ-ምግባር ሲኖረውም ጭምር ነው። ወጣቱ ተምሮ በአንድ ተጨባጭ የምርት ወይም የአገልግሎት ተግባር ላይ ለመሰማራት የሚያስችለው፣ እውቀት ክህሎትና ታታሪነት ከሌለው፣ በጉልበት ስራ ላይ ኋላ ቀር አመለካከት የያዘ ከሆነ፣ በመንግስት ወይም በትልልቅ ኩባንያዎች ለመቀጠር ከመጠበቅ ውጭ ስራ በመፍጠር ኑሮውን ለማሻሻል የሚያስችል አመለካከትና ሙያ ከሌለው፣ ልማቱም አይመጣም፣ የስራ ዕድሉም አይፈጠርም። መንግስት ከዚህ በመነሳት ነው የትምህርት ስርአታችን መልካም ስነ-ምግባር ያለው አምራች ዜጋ በመፍጠር፣ የስራ ፈጣሪነትና የስራ፣ የጉልበት ስራም ጭምር አክባሪነት እምነት ያለው ዜጋ መፍጠር አለበት የሚለው። መንግስት ከዚህ በመነሳት ነው የትምህርት ስርአታችን ይህንን ለማድረግ የሚያስችል ይዘትና ብቃት ያለው እንዲሆን እየተረባረበ ያለው።

መንግስት በዚህ ብቻ ሳይወሰን ከቀለም ትምህርቱ ጎን



ለጎን ሰፊ የሙያና የቴክኒክ ስልጠና ስርአት ለመዘርጋት በመንቀሳቀስ ላይ ነው ያለው። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምሩቃንን በመለስተኛና በመካከለኛ ሙያተኛነት በማሰልጠን የራሳቸውን ስራ ፈጥረው ኑሯቸውን ለማሻሻልም ሆነ ተቀጥረው በአንድ ተጨባጭ የምርት ወይም የአገልግሎት ተግባር ላይ ሊሰማሩ የሚያስችላቸው አስተሳሰብና ክህሎት እንዲኖራቸው ጥረት እያደረገ ነው ያለው። በሌላ አነጋገር መንግስት የትምህርትና ስልጠና ስርአቱ ስራ ወዳድና ስራ ፈጣሪ የሆኑ፣ በቂ እውቀትና ክህሎት ያላቸውን ወጣቶች በብቃት በማፍራት፣ ልማቱን በማፋጠንና የስራ ዕድሎችን በመፍጠር ካልሆነ በስተቀር የትምህርቱ ይዘት ከሚጠይቀው በላይ የትምህርት ጊዜን በማራዘም የስራ አጥነትን ችግር ለመፍታት የሚረዳ አስተዋፅኦ ሊያበረክት አይችልም።

የስራ አጥነትን ችግር ለመፍታት የሚቻለው የተማሪው የትምህርት ደረጃ በኢኮኖሚው ውስጥ ከሚኖረው የሙያተኛ ፍላጎት ጋር በቅርብ የተሳሰረ እንዲሆን በማድረግም ጭምር ነው። ለምሳሌ በአሁኑ ሰአት ከህዘባችን ከ85% በላይ የሚሆነው ህዝብ በግብርና መስክ የተሰማራ ነው። በዚሁ ስራ ላይ የሚሰማራው የሰው ሃይል ከእድገታችን ጎን ለጎን እየቀነሰ የሚመጣና እየቀነሰ መምጣት ያለበት ቢሆንም ረዘም ላለ ጊዜ ዋናው የስራ ዕድል በዚህ መስክ መሆኑ አይቀርም። በዚህም መስክ መካከለኛና ከፍተኛ ሙያተኛ የሚያስፈልግ ቢሆንም ዋናው ተፈላጊ ሃይል መለስተኛ ሙያተኛ ነው። በሌሎችም መስኮች ያለው ዋነኛ የስራ ዕድል በመለስተኛ ሙያተኛነት ነው።

በመሆኑም ወጣቱ በዚህ ደረጃ ባሉ የተለያዩ የምርትና የአገልግሎት ስራዎች ላይ (በተለይም በግብርና) ለመሰማራት ፍላጎቱና ችሎታው ሊኖረው ይገባል:: ከዚህም ባሻገር የትምህርት አገልግሎት የሚያገኘው አብዛኛው ወጣት በዚህ ስራ ላይ ለመሰማራት ከሚያስፈልገው በላይ ይማር ቢባል ባለን አቅም በፍፁም የማይቻል ከመሆኑም በላይ ከፍተኛ የገንዘብና የጊዜ ብክነት ያስከትላል እንጂ የሚፈይደው ነገር አይኖርም::

በተመሳሳይ መልኩ መንግስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን የማስፋፋት ፕሮግራም ሲያቅድ አገሪቱ የምትፈልገውን የመካከለኛ ሙያተኛ ቁጥር ግምት ውስጥ በማስገባት መሆን አለበት:: የከፍተኛ ትምህርት መስፋፋት ፕሮግራምም ከአገሪቱ የከፍተኛ ሙያተኛ ፍላጎት ጋር ተያይዞና ተመጣጥኖ መቀየስ አለበት:: ከዚህ ውጭ ከአገሪቱ የሙያተኛ ፍላጎት በላይ የሆነ የሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ ትምህርት ማስፋፋት ስራ ከተከናወነ አንድም ሰው የሚመጥነው ስራ አጥቶ ወይም መፍጠር ተስኖት ስራ አጥ ይሆናል፣ ስራ አጥነት ይባባሳል:: አለያም መለስተኛ ሙያተኛ ሊሰራው በሚችል የስራ መስክ ይሰማራል፣ በመካከለኛና ከፍተኛ ሙያተኛ ደረጃ ለማሰልጠን የወጣው ገንዘብና ጊዜ ባክኖ ይቀራል:: መንግስት ይህንኑ በመገንዘብ ነው የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም ለማዳረስ፣ የሁለተኛ ደረጃና ከፍተኛ ትምህርትን ግን ከአገሪቱ የሙያተኛ ፍላጎት ጋር በማጣጣም መስፋፋት አለበት የሚል ግብ አስቀምጦ በመረባረብ ላይ የሚገኘው::



በአጠቃላይ የተማረ ሃይልን የስራ አጥነት ችግር ለመቅረፍ የሚቻለው በ10ኛ ክፍል ደረጃ እየተሰጠ ያለውን ትምህርት ለሁለት አመት በማራዘም ሳይሆን፣ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት በማረጋገጥ፣ በቂ እውቀት ክህሎት፣ ጥሩ የስራ ስነ-ምግባርና አመለካከት ያለው ስራን ፈጣሪ የሆነ ወጣት በማፍራት፣ የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሙ ከአገሪቱ የሙያተኛ ፍላጎት ጋር ተጣጥሞ እንዲስፋፋ በማድረግ ነው:: መንግስት ይህንን ተገንዝቦ ሶስቱንም የመፍትሄ አካሎች አጣምሮ ተግባራዊ ለማድረግ ሰፊ ጥረት በማድረግ ላይ ነው:: ችግሩን በምንም አይነት መንገድ ሊፈታ የማይችለውን አቅጣጫ ትቶ ችግሩን በትክክል ሊፈታ የሚችል አቅጣጫ ይዞ ነው በመንዝ ላይ ያለው::

በአጠቃላይ አዲሱን የትምህርት ፖሊሲ በሚመለከት የሚቀርበው ዋናው ትችት ትምህርት ቤቶች ትምህርቱን ለመስጠት የሚያስፈልገውን ጊዜ ያህል አስተምረው የሚያሰናብቱ የትምህርት ተቋሞች መሆናቸውን ዘንግቶ፣ ወጣቶች ዕድሜያቸው እስኪደርስ ድረስ የሚቆዩበት ማቆያ ስፍራ አድርጎ የሚመለከት የተሳሳተ ትችት ነው:: ትምህርት ቤቶችን በማቆያነት ከወሰዳቸው አይቀር ደግሞ ይህንን የማቆያ ቦታ የማግኘት ዕድል በተነፈጋቸው ህፃናት ሳይሆን የዜግነት ግዴታቸውን ለመወጣት በተቃረቡት ወጣቶች ላይ ማተኮሩ ኢ-ፍትሃዊ ነው:: ተማሪዎቹ በተጨባጭ የሚመረቁበት ጊዜ ለጋ ዕድሜ ቢሆንም በአለም አቀፍ መስፈርቶች መሰረት በህጋዊ አኳኋን በተለያዩ ስራዎች ሊሳተፉ የሚያስችላቸው ሲሆኑ ትችቱ ይህንን ባለማጤኑም የተሳሳተ

ነው፡፡ የተማረ የስራ አጥነት ችግርን ከላይ በተዘረዘሩት ትክክለኛ አቅጣጫዎች ሳይሆን የ10ኛ ክፍል ትምህርትን ለሁለት አመት በማራዘም ይፈታል ብሎ ማሰቡ የስራ አጥነትን ችግር በከፍተኛ ደረጃ የሚያባብስና ከፍተኛ የጊዜና የገንዘብ ብክነትን የሚያስከትልም ነው፡፡ በመሆኑም በትምህርት ፖሊሲው ላይ የሚቀርበው ትችት በተጠቀሱት አራት ምክንያቶች የተሳሳተና ኢ-ፍትሃዊ ትችት ነው፡፡

## 4.2. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጥራት፣

የትምህርት ፖሊሲያችን በተቀረፀበት ወቅት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ስርጭት እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነበር፡፡ ስለሆነም ፖሊሲው በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ስርጭት ላይና ጥራቱን በማስጠበቅ ላይ በቂ ትኩረት የሰጠ ነበር፡፡ ስርጭትን በተመለከተ በአሁኑ ሰአት ከፍተኛ እድገት ታይቷል፡፡ ምንም እንኳ ከእድገታችን ጋር እየተያያዘ እድገቱ መቀጠል ያለበት ቢሆንም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ረገድ ዋናው ትኩረታችን ስርጭቱን ማስፋፋት ላይ አይሆንም፡፡ የትምህርቱን ጥራት ለማስጠበቅ ስርአተ-ትምህርቱን በማሻሻል፣ አቅም በፈቀደ መጠን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ለማሟላት ከፍተኛ ጥረት በማድረግና በመሳሰሉት መንገዶች ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡ ይሁንና በትምህርት ጥራት ረገድ አሁንም በጣም ከፍተኛ ችግሮች ይታያሉ፡፡ በመሆኑም ስርጭቱን ከኢኮኖሚያዊ እድገታችን ጋር በተቀናጀ አኳኋን የማስፋፋቱ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋናው ስራችን ጥራቱን በማሻሻል ላይ መሆን እንደሚገባው ገሀድ ሆኗል፡፡



የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የጥራት ችግሮችና መፍትሄዎቹ ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት የጥራት ችግሮችና መፍትሄዎች ጋር አንድና ያው ናቸው፡፡ በመሆኑም ከላይ የተዘረዘሩትን እነዚህን ችግሮችና መፍትሄዎቻቸውን እዚህ ላይ ከመድገም እንዳሉ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርትም ይሰራሉ ብሎ ማለፍ ይመረጣል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጥራት ላይ ሊሰመርባቸው የሚገባ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

በሽፍት የመማሩ ሂደትና በአንድ ክፍል ውስጥ መሆን ከሚገባው ተማሪ በላይ የመማሩ ጉዳይ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትንም ክፉኛ የጎዳ ቢሆንም አሉታዊ ተፅእኖው እጅግ የከበደ ሆኖ የሚታየው በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ላይ ነው፡፡ ይህ በትምህርቱ ጥራት ላይ በተለያየ መልኩ ተፅእኖ ያሳድራል፡፡ የትምህርትን ስነ-ስርአትና ዲሲፕሊን በማስጠበቅ ላይም አሉታዊ ተፅእኖ ያሳርፋል፡፡ ዋልጌነት በይበልጥ የሚንፀባረቀው ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መተፋፈግና ከተማሪዎቹ ዕድሜ ጋር ተያይዞ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ላይ ሆኖ ይታያል፡፡ የስነ-ዜጋ ትምህርት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ከሚታየውም ጉድለት በላይ ጎልቶ የሚታየው በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ተጨማሪ ትምህርት ቤቶችንና የትምህርት ክፍሎችን በመስራት መተፋፈጉን ማስቀረትና በሺፍት የሚደረገውን ትምህርት ደረጃ በደረጃ ማስቀረት የተማሪውን ቁጥር ከማበራከቱም በላይ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው፡፡ የስነ-ዜጋ

ትምህርትና የስራ ስነ-ምግባርና አመለካከት ትምህርት በሁሉም የትምህርትና ስልጠና ተቋሞች ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ሲሆን ከወጣቶች ዕድሜ ጋር ተያይዞ የላቀ ውጤት የሚኖረው በአንደኛ ደረጃና በተለይም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ነው፡፡ የትምህርት ዲሲፕሊንና ስነ-ስርአትን በማስከበር ረገድም የላቀ ርብርብ መደረግ ያለበት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ነው፡፡

የትምህርትን ጥራት ለማሻሻል ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅን በአንደኛ ደረጃ ትምህርትም መጠቀም እንደሚያስፈልግ እሙን ነው፡፡ ይሁንና ብዙዎቹ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የቴሌኮምዩኒኬሽን አገልግሎት በሌለበትና በቀላሉ በማይዳረስበት የገጠር ቀበሌዎች ውስጥ ያሉ በመሆናቸው ይህንኑ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ ጊዜ እንደሚጠይቅ እሙን ነው፡፡ በዚህ ደረጃ የሚሰጠው የትምህርት ይዘትና መማሪያ ቋንቋው እንግሊዘኛ መሆኑ ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅን በመጠቀም የትምህርቱን ጥራት ለማስጠበቅ የተሻለ ዕድል ይፈጥራል፡፡ ስለሆነም የትምህርት ጥራቱን ለማሻሻል የሚደረገው ጥረት ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅን ለመጠቀምና ለማስፋፋት ጉዳይ በቂ ትኩረት የሰጠ መሆን ይኖርበታል፡፡

### 4.3. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ፋይናንስና አስተዳደር፣

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የፋይናንስና አስተዳደር ችግሮችና መፍትሄዎቻቸውም ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ፋይናንስና አስተዳደር ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው ጋር አንድና



ያው ናቸው፡፡ ስለሆነም እነዚህን እዚህ ላይ መድገሙ ተፈላጊነት የለውም፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ የትምህርት ደረጃ ለየት ያለ ጫና ሊደረግባቸው በሚያስፈልጉ ጉዳዮች ላይ አንዳንድ ነጥቦችን ማንሳት በቂ ይሆናል፡፡

የግል ባለሀብቶች የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን በማስፋፋት ረገድ በቀላሉ የማይታይ አስተዋፅኦ እያደረጉ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ ይሁንና የእስካሁኑ ልምዳችን የሚያመለክተው በይበልጥ አስተዋፅኦ የሚያደርጉት በሁለተኛ ደረጃና በከፍተኛ ትምህርት ላይ ነው፡፡ የተሻለ ገቢ ሊያገኙበት የሚችሉትም በነዚህ ደረጃዎች ላይ በማተኮር ነው፡፡ መንግስት ይህንኑ ተገንዝቦ የግል ባለሀብቶችን ተሳትፎ ለማበረታታት የሚደረግ ጥረት በነዚህ ደረጃዎች ላይ ያተኮረ እንዲሆን ማድረግ አለበት፡፡

በትምህርት አስተዳደር ረገድ የተማሪዎች ተሳትፎ እጅግ በጣም ጠቃሚና አስፈላጊ የሚሆነው በሁለተኛ ደረጃና ከዚያ በላይ ባሉ የትምህርት እርከኖች ላይ ነው፡፡ የተማሪዎቹ ዕድሜ እንደዚህ አይነቱን ተሳትፎ ተግባራዊ ለማድረግ አመቺ የሚሆነው በዚሁ የትምህርት እርከንና ከዚያ በላይ ባሉ የትምህርት ደረጃዎች ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ወጣቶቹ በየትምህርት ቤታቸውና በማህበራቸው አማካኝነት የላቀ ተሳትፎ እንዲያበረክቱ ጥረት መደረግ አለበት፡፡ ወጣቱን ትውልድ በትምህርትና በመልካም ባህል ለመቅረፅ በየትምህርት ቤቱ የሚኖረው ተሳትፎና የወጣት ማህበራት ሚና ከፍተኛ በመሆኑ በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት ሃላፊዎችና የመንግስት ባለስልጣኖች ልዩ ትኩረት ሊሰጡት

ይገባል።

ተማሪዎች በትምህርት ቤቶቻቸው አስተዳደር ላይ የሚያደርጉት ተሳትፎ፣ የተማሪዎችን መብትና ጥቅም በማስጠበቅና የትምህርት ስርአቱን አላማዎች ከግብ ለማድረስ መሆን አለበት። ተማሪዎች ጥራቱ የተጠበቀ ትምህርት የማግኘት መብትና ፍላጎት አላቸው። አስተዳደሩ ይህንን እንዲያረጋግጥላቸው ለማድረግ በአስተዳደሩ ውስጥ መታገል አለባቸው። የትምህርት ፖሊሲው በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ሆኖ በህብረተሰቡ ውስጥ ገንቢ ሚና ለመጫወት የሚያስችላቸው እውቀትና ባህሪ ይዘው መውጣት መብትና ጥቅማቸውን የሚያስጠብቅላቸው ዋናው ነገር ይሆናል። ስለሆነም ለዚሁ ጉዳይ መረባረብ ይኖርባቸዋል።

በአንዳንድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ዋልጌነት እየተጠናከረ፣ ተማሪዎች ለመማር ማስተማሩ ሂደት የሚሰጡት ትኩረት እየቀነሰ በመምጣት ላይ እንደሚገኝ ግልፅ ነው። ይህንን እጅግ አደገኛ አዝማማያ ለመቋቋም በወላጆች፣ በትምህርቱ ስርአት ሃላፊዎችና በመምህራን ሰፊና የተቀናጀ ስራ መሰራት እንዳለበትም ግልፅ ነው። ተማሪዎችና ማህበሮቻቸውም በዚህ ተግባር ላይ የላቀ አስተዋፅኦ ማበርከት ይገባቸዋል። ተማሪው የዚህን አዝማሚያ አደገኛነት በሚገባ ተገንዝቦ ለማስወገድ መረባረብ እንዳለበት ሊያሳምኑትና ሊያስተባብሩት ይችላሉ። በየትምህርት ቤቱ ያሉ የተማሪዎች ማህበራት ይህንኑ እንደአንድ መሰረታዊ አላማ ይዘው መታገያ ሊያደርጉት ይችላሉ። የዋልጌነት



አራማጅ የሆኑ ወጣቶችን በመምከርም ከዚሁ ተግባራቸው እንዲታቀቡ መርዳት ይችላሉ። ከትምህርት ቤቱ ሃላፊዎች ጋር በመተባበር ወጣቱ ጊዜውን ገንቢ በሆኑ የስፖርትና የመሳሰሉት እንቅስቃሴዎች፣ በጥናትና፣ ለትምህርት ቤታቸው ገቢ ለማስገኘት በሚያስችሉ ስራዎች ላይ እንዲያጠፉ ማስተባበር ይችላሉ። የመማር ማስተማር ሂደቱ በተቀመጠለት አቅጣጫ እንዲሄድ፣ በአስተማሪዎችም ሆነ በትምህርት ሃላፊዎች ዘንድ የሚታዩ ጉድለቶች እንዲታረሙ ሊንቀሳቀሱ ይችላሉ።

ተማሪዎች እንደዚህ አይነቱን ገንቢና የትምህርት ቤቶችን ጥራትና ውጤታማነት በማሻሻል፣ በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚካሄደውን የስነ-ዜጋና የስራ አመለካከትና ስነ-ምግባር ትምህርትን ለማጠናከር የሚያስችል ቁልፍ ስራ መስራት የሚችሉት በአግባቡ ከተደራጁ ነው። ከዚያም ባሻገር በትምህርትና ስልጠና ፖሊሲዎቻችንና ዕቅዶቻችን ላይ በሰፊው ተወያይተው የተሟላ ግንዛቤ ሲያገኙ፣ በዚህ ረገድ ሚናቸው ምን እንደሆነ በሚገባ ሲያውቁና ለተግባራዊነታቸው ብዙሃኑ ተማሪና ማህበራቱ በፅናት የሚቆሙበት ሁኔታ መፈጠር ይኖርበታል። በተጨማሪም ተማሪዎቹ ማህበሮቻቸውና መሪዎቻቸው በትምህርት ቤቶች አስተዳደር፣ በትምህርት ፖሊሲያችንና እቅዶች አፈፃፀም ላይ በየጊዜውና በቀጣይነት የሚወያዩበት መድረክ ሊፈጠርላቸው፣ ይህንን ለማስፈፀም በሚቋቋሙ የትምህርት አስተዳደር አካላት ውስጥ በቂ ውክልናና ተሳትፎ ሊኖራቸው ይገባል።

በየደረጃው ያሉ የመንግስት አካላት ተማሪዎችና

ማህበሮቻቸው ይህን ሚና እንዲጫወቱ በማስቻል ረገድ ልዩና ገንቢ ሚና ሊጫወቱ ይገባል፡፡ ማህበራቱ በየደረጃው በብቃት እንዲደራጁ የተማሪዎቹ ተወካዮች በትምህርት አስተዳደር ኮሚቴዎች ውስጥ በብቃት እንዲወከሉ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው ላይ፣ በአካባቢው የትምህርት ዕቅዶች፣ የትምህርትና ስልጠና ችግሮችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች ላይ ተማሪው በአጠቃላይ፣ የተማሪው ማህበራት መሪዎች ደግሞ በተለይ በቂ መረጃ እንዲኖራቸው፣ በጉዳዩ ላይ ተወያይተው አስተያየታቸውን እንዲሰጡበትና በአፈፃፀሙ ላይ የሚኖራቸውን ድርሻ ለይተው እንዲወስዱ ለማድረግ ተከታታይነት ያላቸው መድረኮች ሊከፈቱላቸው ይገባል፡፡ የተማሪዎቹ ማህበራት ተልእኮቸውን ለመወጣት በሚያካሂዱዋቸው እንቅስቃሴዎች የትምህርት ቤት ሃላፊዎችንና የአካባቢውን አስተዳደር ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ በአጭሩ የተማሪዎች ማህበራትና ተማሪዎቹ ወጣቱን ትውልድ በሚፈለገው መንገድ ለመቅረፅና የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ግቦችን ለማሳካት ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ አጋሮች መሆናቸውን የተገነዘበ እንቅስቃሴ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

**5. የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና፣**

**5.1. የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ስርጭትና አወቃቀር፣**

አንድ የቀለም ትምህርት የተማረ ወጣት በአጫጭር



ስልጠናዎችና በስራ ላይ ስልጠና በተለያዩ ስራዎች ተቀጥሮ ሊሰራ እንደሚችል ይታመናል፡፡ ይሁንና በዚህ መልክ የሚቀሰመው የሙያ ችሎታና አመለካከት አስተማማኝና ጥልቀት ያለው ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳ ብዙ አገሮች ሰፊ የቴክኒክና የሙያ ትምህርት ስልጠና ስርአት ከመዘርጋት የሚቆጠቡ ቢሆኑም በልማቱ ረገድና ሰፊ የሰለጠነ የሰው ሃይል በመፍጠር ረገድ የተዋጣላቸው አገሮች ከቀለም ትምህርቱ ስርአት ጎን ለጎን ሰፊ የቴክኒክና የሙያ ትምህርት ስልጠና ፕሮግራም ይቀርፃሉ፡፡ አዲሱ የትምህርት ፖሊሲያችን ከቀድሞው ፖሊሲ ከሚለይባቸው ዋነኛ ነጥቦች አንዱም ይኸው ነው፡፡ ነባሩ ፖሊሲ የቀለም ትምህርት በማስፋፋት ላይ የታጠረ፣ እጅግ ውሱንና ጥራታቸውም ያልተጠበቀ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋሞችን ከማቋቋም አልፎ፣ ሰፊ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ስርአትን ያልፈጠረና ለመፍጠርም ያልሞከረ ነበር፡፡ አዲሱ ፖሊሲ የቀለም ትምህርትን ከማስፋፋት ጎን ለጎን ሰፊ የሙያና ቴክኒክ ትምህርትና ስልጠና ስርአት መፈጠር እንዳለበት አምኖ ለተግባራዊነቱ ከፍተኛ ርብርብ እንደሚያስፈልግ ያስቀምጣል፡፡

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ለመላው ዜጋ መዳረስ እንዳለበት፣ ይህን ትምህርት ካገኘው ወጣት ውስጥ በርካታው ወደሁለተኛ ደረጃ ሲቀጥል አሁን ባለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ግን በጣም የሚበዛው ከዚህ በላይ ሊቀጥል እንደማይችል ተገልጿል፡፡ በመሆኑም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በአንድ በኩል በአጫጭር ስልጠናዎች ኢኮኖሚው የሚፈልጋቸውን መለስተኛ ሙያተኞች ለመፍጠር የሚያስችል በሌላ በኩል ደግሞ ወደሁለተኛ ደረጃ

የሚቀጥሉትን ለዚሁ የሚያዘጋጅ ይዘት ሊኖረው ይገባል። ለዚህም ሲባል የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ለ8 አመታት የሚሰጥና ከዚህ በፊት በ9ኛና 10 ክፍል ይሰጡ ከነበሩት ትምህርቶች ውስጥ የተወሰኑትን ያካተተ እንዲሆን ተደርጎ ተዘጋጅቷል።

የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን አጠናቆ ወደሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የማይሸጋገረውን ወጣት በአጫጭር ስልጠናዎች የተለያዩ ሙያዎች እንዲያገኝ ለማድረግ ከቀለም ትምህርቱ ጎን ለጎን ሰፊ የመለስተኛ ሙያተኛ ትምህርትና ስልጠና ስርአት መኖር አለበት። መንግስት ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቀጥሎ ለዚሁ የመለስተኛ ሙያተኛ ስልጠና ፕሮግራም ልዩ ግምት ሰጥቶ ስርአቱን ለመፍጠር ከፍተኛ ርብርብ በማድረግ ላይ ይገኛል።

እንደሚታወቀው ሁሉ ከህዝባችን ከ85% በላይ የሚሆነው በገጠር የሚኖርና በግብርና የሚተዳደር ነው። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ለሁሉም ዜጎች በሚዳረስበት ወቅትም፣ እጅግ በጣም የሚበዛው የአንደኛ ደረጃ ተማሪ በገጠር የሚኖር የአርሶ አደር ልጅ መሆኑ አይቀርም። የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን አጠናቆ ወደሁለተኛ ደረጃ ከማይሸጋገረው ወጣትም እጅግ በጣም የሚበዛው ይኸው የገጠር ወጣት መሆኑ አይቀርም። ይህንን ወጣት ለማስተናገድ የሚቀየሰው የመለስተኛ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ይህንኑ ታሳቢ ማድረግ አለበት። ከዚህ በተጨማሪ ከኢኮኖሚ አኳያ ያለውና ወደፊትም ለረጅም ጊዜ የሚቀጥለው ዋነኛ የስራ ዕድል ግብርና ነው። የግብርናው



ዘርፍ ሰፊው አርሶአደር በመለስተኛ የግብርና ሙያተኛ ደረጃ የሰለጠነ በሚሆንበት ወቅት ከፍተኛ እድገት እንደሚያስመዘግብና ለሚሊዮኖች ከፍተኛ የኑሮ መሻሻልን ሊያረጋግጥ እንደሚችል ግልፅ ነው። የሙያና ቴክኒክ ስልጠናው ይህንኑ ታሳቢ ማድረግ አለበት።

ከላይ የተጠቀሱትን ታሳቢዎች መነሻ በማድረግ በመለስተኛ የሙያና ቴክኒክ ደረጃ የሚሰጠው ትምህርትና ስልጠና በተለያዩ የግብርና ዘርፍ ሙያዎችና በገጠሩ አካባቢ መሆን ይኖርበታል። መንግስት ይህንኑ በመገንዘብ በየቀበሌው ተጠናክሮ ከሚቋቋመው የግብርና ኤክስቴንሽን ተቋም ጋር አስተሳስሮ እጅግ በጣም ሰፊ የመለስተኛ የግብርና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስርአት በመዘርጋት ላይ ይገኛል። በዚህ ደረጃ የሚኖረው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና በመሰረቱ የገጠርና የግብርና ሙያ ስልጠና እንዲሆን እየተደረገ ነው። ከዚህ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ስርአት ሰልጥኖ የሚወጣው ወጣትም በቤተሰብና በሂደትም በራሱ መሬት ላይ በግብርና ስራ በመሰማራት በሙያው ሰርቶ የሚተዳደር፣ የራሱን ስራ ፈጥሮ የሚኖር እንደሚሆን ይጠበቃል። በዚህ ደረጃ የሚሰጠው የሙያና ቴክኒክ ስልጠና በመሰረቱ የግብርና ሙያ ስልጠና ቢሆንም በዚህ ብቻ የታጠረ አይሆንም። በአዲሱ ስርአተ-ትምህርት መሰረት እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ የተማረ ወጣት ከግብርና ስራ ውጭ በተለያዩ የምርትና አገልግሎት ስራዎች ውስጥ ከአጫጭር ስልጠናዎች በኋላ ሊሰማራ የሚችል ነው። እንኳንስና በከተማ፣ በገጠርም ይህን የመሰለውን ከግብርና ውጭ የሆኑ የተለያዩ የመለስተኛ

ሙያ ትምህርትና ስልጠናዎች ያገኘ ወጣት የሚያስፈልጋቸው ስራዎች ይኖራሉ። በዚህ ደረጃ ያለው የሙያና ቴክኒክ ስልጠና በዋነኛነት ግብርናን መሰረት ያደረገ ነገር ግን የሁሉም የምርትና አገልግሎት ዘርፎችን የመለስተኛ ሙያተኛ ፍላጎት ለማርካት የሚያስችል ይዘት ያለው ይሆናል።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን የመጀመሪያ ሳይክል ትምህርት ከሚያገኘው ወጣት ውስጥ እጅግ የሚበዛው ወደዩኒቨርስቲ የማይቀጥል ነው። በዚህ ደረጃ የተማረን ወጣት በተለያዩ የሙያና ቴክኒክ ስልጠናዎች አማካኝነት የአገሪቱን የመካከለኛ ሙያተኛ ፍላጎት እንዲያረካ ማድረግ ይቻላል። በመሆኑም የሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል ትምህርት ጨርሶ ወደዩኒቨርሲቲ የማይቀጥለውን ወጣት ሊያስተናግድ የሚችል ሰፊ የሙያና ቴክኒክ ትምህርትና ስልጠና ስርአት በመዘርጋት ላይ ነው። በዚህም መሰረት እንደሁኔታው ከአንድ እስከ ሶስት አመት የሚደርስ ስልጠና በተለያዩ የሙያና ቴክኒክ ትምህርት ቤቶችና መለስተኛ ኮሌጆች ስልጥኖ በሰርቲፊኬትና በዲፕሎማ ደረጃ የሚመረቅ መካከለኛ ሙያተኛ የማፍራት ስራ በስፋት በመከናወን ላይ ይገኛል። በዚህ ደረጃ የሚሰለጥነው ወጣት ከፊሉ በመንግስት፣ ወይም በግል ባለሃብቶች የሚቀጠር ይሆናል ተብሎ ይገመታል። የተቀረው በተለያዩ የምርትና የአገልግሎት ዘርፎች ስራ ፈጥሮ ኑሮውን የሚያሻሽል ይሆናል ተብሎ ይገመታል።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚስፋፋው ለሁሉም



እንዲዳረስ ሳይሆን ኢኮኖሚው በሚጠይቀው መጠን ነው። በዚህ ደረጃ የተማረውን ወጣት በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ለማሰልጠን የሚደረገው እንቅስቃሴም ከኢኮኖሚው ፍላጎት ጋር በቅርብ መቀናጀት አለበት። ከኢኮኖሚው ፍላጎት ጋር በቅርብ መቀናጀት አለበት ሲባል በአጠቃላይ መልኩ ብቻ ሳይሆን በተጨባጭ ሙያ ደረጃም ጭምር ነው። ስለሆነም ፕሮግራሙ ሲታቀድ የአገሪቱ የመካከለኛ ሙያተኛ ፍላጎት ብቻ ሳይሆን፣ የአገሪቱን የመካኒክ፣ የኤሌክትሪሺያን፣ የሂሳብ ሰራተኛ የአስተማሪ ወዘተ. ፍላጎትም ታሳቢ በማድረግ መሆን አለበት። የአገራችን ኢኮኖሚ የእዝ ኢኮኖሚ ባለመሆኑ በዚህ ደረጃ የሚፈለገውን የሰው ሃይል መጠን መቶ በመቶ እርግጠኛ ሆኖ ማስቀመጥ አይችልም። አጠቃላይ ግምት ብቻ ነው ማስቀመጥ የሚቻለው። ከዚያም ባሻገር በነፃ ገበያ ኢኮኖሚ የሚፈለገው የሙያተኛ አይነትና ብዛት በየጊዜው መቀያየሩ የማይቀር ነው። በመሆኑም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስርአታችን የሙያተኛ ፍላጎትን አጠቃላይ ግምት በመውሰድ የሚቀየስ፣ የገበያውን ፍላጎት በመመልከት ከገበያው ፍላጎት ጋር አብሮና በፍጥነት ሊቀያይር የሚችል (ፍሌክሲብል) የሆነ ስርአት መሆን አለበት። እንደቀለም ትምህርቱ በፍጥነት የማይቀያየር ይዘትና አወቃቀር ሊኖረው አይችልም።

የሙያና ቴክኒክ ትምህርት ስልጠና ፕሮግራማችን እንደሌላው የትምህርትና ስልጠና ስርአታችን ሁሉ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ዕቅዳችንን ለማስፈፀም የተቀየሰ ፕሮግራም ነው። የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራተጅያችን የመንግስት፣ የህዝብና

የግል ባለሃብቶችን የማስፈፀም አቅም መገንባት እንደሚያስፈልግ ቢያስቀምጥም ቅድሚያ የሚሰጠው የመንግስትን የማስፈፀም አቅም ለመገንባት መሆን እንዳለበት ነው:: መለስተኛ ሙያተኞችን የማሰልጠን ተግባር በግብርና ላይ ያተኮረ፣ በዋነኛነት ሰልጥነው በራሳቸው ማሳና በራሳቸው መንገድ ስራ ፈጥረው የሚንቀሳቀሱ ሰዎችን ለማሰልጠን የታቀደ ነው:: በዚህም ምክንያት የህዝቡን የማምረት አቅም፣ የማስፈፀም አቅም በመገንባት ላይ ያተኮረ ነው ሊባል ይችላል:: በመንግስትም ሆነ በግል ባለሃብቶች የሚቀጠር መለስተኛ ሙያተኛ ይብዛም ይነስም መኖሩ ስለማይቀር የመንግስትና የግል ባለሃብቶችን የማስፈፀም አቅምም ይገነባል ሊባል ይችላል:: በመካከለኛ ሙያተኛ ደረጃ የሚደረገው ትምህርትና ስልጠና ግን በአሁኑ ወቅት የመንግስትን የማስፈፀም አቅም በመገንባት ላይ ማተኮር ያለበትና የሚያተኩርም ይሆናል::

መንግስት በአሁኑ ወቅት የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ እቅዱን ለማስፈፀም የሚያስችለውን አቅም ለመገንባት ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው መካከለኛ ሙያተኛ ያስፈልገዋል:: የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም ዜጋ ለማዳረስ በጣም ከፍተኛ ቁጥር ያለው በመካከለኛ ሙያተኛ ደረጃ የሚመደብ የአንደኛ ደረጃ አስተማሪ ያስፈልገዋል:: የመሰረተ-ጤና አገልግሎትን ለማስፋፋት ሰፊ የመካከለኛ የጤና ሙያተኛ ሃይል ማሰልጠን አለበት:: የግብርና ልማት ስራም እንደዚሁ ሰፊ የመካከለኛ ሙያተኛ ሃይል የሚጠይቅ ነው:: በገጠር መንገድና መጠጥ ውሃ ስራ፣ በመንግስት ፋይናንስና አስተዳደር ስራ ወዘተም. ሰፊ



የመካከለኛ ሙያተኛ ሃይል የሚጠይቅ ነው:: በአሁኑ ወቅት በሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያው ሳይክል ከተሰማራው የሰው ሃይል ውስጥ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ይህንን የመንግስት የሰለጠነ የሰው ሃይል ፍላጎት ለማሟላት የሚውልና መዋልም ያለበት ነው:: የመካከለኛ ሙያተኛ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም በአሁኑ ሰአት በዋነኛነት የመንግስትን የሰው ሃይል ፍላጎት በማሟላት ላይ ማተኮር አለበት የምንልበት መሰረታዊ ምክንያትም ይኸው ነው::

የግል ባለሃብቱ እየተጠናከረ ሲሄድ ከፍተኛ የመካከለኛ ሙያተኛ ፍላጎት እንደሚኖረው እሙን ነው:: ይህንን ፍላጎት ለመገመት ከግል ባለሃብቶች ጋር ጠንካራ ቅንጅት ማድረግና የሰው ሃይል ቅጥር ገበያ የጥናት አቅምን ማጠናከር ያስፈልጋል:: በመካከለኛ ሙያተኛነት ከሚሰለጥነው ውስጥ በሂደት ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ቁጥር በተናጠልና በጋራ የራሱን ስራ ፈጥሮ በሙያው በመሰማራት ኑሮውን የሚያሻሽል ይሆናል:: ይህንን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ስራን ለመፍጠር ለሚንቀሳቀሱ ወጣቶች ሁሉን አቀፍ እገዛ የሚሰጥ አቅም መገንባት ያስፈልጋል:: በአሁኑ ወቅት እንደዚህ አይነቱ ስርአት በተሟላ አኳኋን ተገንብቷል ማለት አይቻልም:: በመሆኑም በአሁኑ ወቅት የመካከለኛ ሙያተኛ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም የመንግስትን የማስፈፀም አቅም በማጎልበት ላይ እንዲያተኩር ማድረግ ስትራቴጅያችንን ለማስፈፀም በጣም ተፈላጊ ከመሆኑም በሻገር የግል ባለሀብቶችንና የህዝቡን አቅም በማጎልበት ላይ እንዲያተኩር ለማድረግ የሚያስፈልጉ ቅድመ-ዝግጅቶችን ለማሟላት

የሚያስፈልገውን ጊዜም የሚሰጠን ይሆናል፡፡ ፕሮግራሙ በአሁኑ ወቅት በመንግስት አቅም ግንባታ ላይ ማተኮር አለበት የምንልበት ሁለተኛና ተደራቢ ምክንያትም ይኸው ነው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የሁለተኛ ሳይክል ትምህርት ትይዩ ይሁንና የመንግስት የመካከለኛ ሙያተኛ ፍላጎት በአሁኑ ወቅት የሁለተኛ ደረጃ አንደኛ ሳይክል ትምህርትን በመከታተል ላይ ያለውን ወጣት በሙሉ ሊሸፍን የሚችል አይደለም፡፡ ለመንግስት አቅም ግንባታ ቅድሚያ ሰጥተን የመንግስትን ፍላጎት ካሟላን በኋላ የመንግስት የመካከለኛ ሙያተኛ ፍላጎት አሁን ካለው በከፍተኛ ደረጃ እንደሚቀንስም መገመት ይቻላል፡፡ ስለሆነም ከወዲሁ በግል ባለሀብቶች የሚፈለገውንና ራሱ ስራ ፈጥሮ የሚኖረውን መካከለኛ ሙያተኛ መፍጠር መጀመር አለብን፡፡ በሂደትም ዋናው ስራ ይኸው እንደሚሆን ተገንዝበን በዚህ ላይ ያተኮረ የመካከለኛ ሙያተኛ የሙያና ቴክኒክ ስርአት ለመፍጠር መጠናቀቅ የሚገባቸውን ቅድመ-ዝግጅቶች ማጠናቀቅ አለብን፡፡ የመንግስትን ፍላጎት በማርካት ላይ አትኩሮ፣ ነገር ግን የግል ባለሃብቶችንና የህዝቡንም ፍላጎት ካካተተ የሙያና ቴክኒክ ስልጠና ስርአት፣ በዋነኛነት የግል ባለሃብቶችንና የህዝቡን አቅም በመገንባት ስራ ላይ ወደሚያተኩርና ነገር ግን ደግሞ የመንግስትንም የሰው ሃይል ፍላጎት ወደሚሸፍን ስርአት ከፍተኛ ክፍተት በማይፈጥር አኳኋን ለመሸጋገር በጥንቃቄ የታቀደና የተቀናጀ ስራ መስራት አለብን፡፡

የሁለተኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ትምህርት የሚከታተሉ



ወጣቶች በወሳኝ መልኩ ወደዩኒቨርሲቲ የሚገቡ ናቸው፡፡ ዩኒቨርሲቲዎች ከፍተኛ ሙያተኞችን የሚያሰለጥኑ ተቋሞች በመሆናቸው የቀለም ትምህርት ተቋሞችም፣ የሙያና ቴክኒክ ተቋሞችም ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡ የቀለም ትምህርትና የቴክኒክና ሙያ ትምህርት የሚጣመሩባቸውና የሚዋሃዱባቸው ተቋሞች ናቸው፡፡ በመሆኑም የቀለም ትምህርትና የሙያና ቴክኒክ ትምህርት ስርአቶች ጎን ለጎን የሚካሄዱት በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያው ሳይክል ደረጃዎች ብቻ ይሆናል፡፡ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ትይዩ የመለስተኛ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ስርአት ይኖራል፡፡ እንደአንደኛ ደረጃ ትምህርት ሁሉ ከሞላ ጎደል ለመላው ዜጋ የሚዳረስም ይሆናል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ትምህርት ትይዩ የመካከለኛ ሙያተኞች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስርአት ይኖራል፡፡ እንደሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ሁሉ የኢኮኖሚውን የመካከለኛ ሙያተኛ ፍላጎት መሰረት ያደረገ ስፋትና ስርጭት ይኖረዋል፡፡ ከሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያው ሳይክል በኋላ የቀለም ትምህርትና የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ትምህርት በዩኒቨርስቲ ትምህርት አማካኝነት ይዋሃዳሉ፡፡ የሁለተኛ ደረጃን ሁለተኛ ሳይክል ትምህርት ተከታትለው ወደ ዩኒቨርሲቲ የማይገቡ ወጣቶች ካሉ በመካከለኛ ሙያተኛ የሙያና ቴክኒክ ስልጠና ፕሮግራም ውስጥ የሚታቀፉ ይሆናሉ፡፡

### 5.2. የሙያና ቴክኒክ ስልጠና ጥራት፣

የሙያና የቴክኒክ ትምህርትና ስልጠናው ጥራት ሲባል

እንደቀለም ትምህርቱ ሁሉ የተለያዩ ነገሮችን ያካተተ ነው። የሚሰጠውን የሙያና ቴክኒክ ትምህርት በሚገባ የቀሰሙ በሙያቸው በተጨባጭ የምርትና አገልግሎት ስራ በብቃት ለመሳተፍ የሚያስችል ሙያ ያላቸው ወጣቶች የማፍራቱ ጉዳይ አንዱ ገፅታው ነው። የስነ-ዜጋ ትምህርት የተከታተሉ የዜግነት ግዴታዎችን የሚወጡ ወጣቶች የማፍራት ጉዳይም ሌላው ገፅታው ነው። መልካም የስራ አመለካከትና ስነ-ምግባር ያለው ሙያውን የሚያከብርና የሙያ ግዴታውን የሚወጣ ሰው ማፍራትም ሌላ ገፅታው ነው። የስነ-ዜግነት ትምህርትን በተመለከተ ከላይ የተቀመጠው በቴክኒክና ሙያ ትምህርትም የሚሰራ በመሆኑ መድገሙ አስፈላጊ አይሆንም። በዚህ ርዕስ ስር በሙያና ቴክኒክ ትምህርትና ስልጠናውና በሙያ ስነ-ምግባር ጉዳይ ላይ ማተኮሩ በቂ ይሆናል።

የሙያና ቴክኒክ ስልጠና ጥራትን ለማስጠበቅ ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው ከሚገቡ ጉዳዮች አንዱ ስርአተ-ትምህርቱን የመወሰንና መማሪያ መፃህፍትን የማዘጋጀት ጉዳይ ነው። በዚህ ረገድ አገራችን ሰፊ የሙያና ቴክኒክ ስልጠና ፕሮግራም ልምድ የሌላት መሆኑ እንደ ችግር የሚታይ ነው። ይሁንና በዚህ ጉዳይ ላይ ሰፊ ልምድ ያላቸው በርካታ አገሮች በመኖራቸው ከነርሱ ልምድ ተምረን ጥራቱ የተጠበቀ ስርአተ-ትምህርትና ጥሩ የመማሪያ መፃህፍትን ማዘጋጀት እንችላለን። በልማት እንቅስቃሴያችን ሂደት የምንፈልጋቸውን ነገሮች ሁሉ እኛው ራሳችን ማፍለቅ አለብን ማለት አይደለም። ይልቁንም ከሌሎች አገሮች ልምድ በሁሉም የልማት መስኮች በብቃት መማር መቻል ልማታችንን ለማፋጠን እጅግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ



ይኖረዋል። በሙያና ቴክኒክ ስልጠና ረገድም ከሌሎች ልምድ በሰፊው መማር እጅግ ተፈላጊ ጉዳይ ነው። ጥራቱ የተጠበቀ ስርአተ-ትምህርትና ደረጃቸውን የጠበቁ የመማሪያ መፃህፍት በምንፈልገው ፍጥነት ማግኘት የምንችለው ከሌሎች በብቃት በመማር ብቻ ነው።

ከሌሎች በብቃት መማር አለብን ሲባል የሌሎችን ልምድ እንዳለ መቅዳት አለብን ማለት አይደለም። የሌሎችን ልምድ በጥልቀት አጥንተን፣ እንዳለ ሊያገለግለን የሚችለውን በመውሰድ ከኛ ሁኔታ ጋር እንዲጣጣም አድርገን ማስተካከል ያለብንንም አስተካክለን መጠቀም አለብን ማለት ነው። መንግስት ይህንን በመገንዘብ የሙያና ቴክኒክ ስልጠና ስርአተ-ትምህርትና የመማሪያ መፃህፍትን ለማዘጋጀት የሚያስችል ልምድ ለመቅሰም ሰፊ ስራ በመስራት ላይ ይገኛል። ከኛ ፍላጎት ጋር የሚጣጣም ልምድ አላቸው ተብለው ወደሚገመቱ አገሮች የሙያተኛ ቡድኖችን በማሰማራት ልምዱን ለመቅሰም፣ ስርአተ-ትምህርቶችንና የመማሪያ መፃህፍቶችን ለማጥናት ጥረት ተደርጓል። አሁንም በመደረግ ላይ ሲሆን ወደፊትም መቀጠሉ የማይቀር ይሆናል። በዚህ ላይ በመመስረት እንዳሉ ልንጠቀምባቸው የምንችላቸውን እየወረስን፣ መስተካከል የሚገባቸውንም አስተካክለን ጥቅም ላይ እንዲውሉ እያደረግን ነው።

በዚህ ረገድ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናው በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችል ነው። መካከለኛውን

የግብርና ሙያተኛ በብቃት በማሰልጠን ጥሩ ውጤት አስገኝተዋል ተብለው የሚገመቱ የተለያዩ አገሮች ተጎብኝተው ከነሱ ልምድ ተወስዷል፡፡ በዚህ ደረጃ ለኛ የሚሆን ልምድ ይኖራቸዋል ተብለው የተገመቱ እንደቻይናና ህንድ የመሳሰሉ የኢስያ አገሮችና እንደኬንያና ታንዛንያ ያሉ የአፍሪካ አገሮች ትኩረት ተሰጥቷቸው፣ ሌሎች አገሮችንም በሚያካትት አኳኋን ተጠንተዋል፡፡ ከእነዚህ አገሮች ልምድ ይጠቅማል ተብሎ የተገመተው ተመርጧል፡፡ የአንዳንዶቹ ልምድ ይበልጥ ተስማሚ በመሆኑ በሰፊው የተጠቀምንበት ቢሆንም ከሁሉም ትምህርት ወስደናል፡፡ ይህንኑ ከራሳችን ውሱን ልምድና የልማት እቅድ ጋር አስተሳስረን በማየት መስተካከል የሚገባቸውን አስተካክለን አጥጋቢ ሊባል የሚችል ስርአተ-ትምህርት ቀርፀናል፣ የመማሪያ መፃህፍትንም አሰባስበናል፡፡ ለወደፊቱም ይህንኑ አቅጣጫ በመከተል ስርአተ-ትምህርቱንና የመመሪያ መፃህፍቱን እየገመገምን በቀጣይነት እናሻሽላለን፣ ማሻሻልም ይገባናል፡፡

የመለስተኛ የግብርና ሙያተኛ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ያላቸውን አገሮች ልምድም ቀምረናል፡፡ በዚህ ደረጃ ሰፊ ልምድ ያላቸው አገሮች ግን በጣም ጥቂት ናቸው፡፡ ይህንኑ ልምድ ከኛ ሁኔታና ፍላጎት ጋር አስተሳስረን በማየት የኛ ስርአት ምን መምሰል እንዳለበት ወስነናል፡፡ ይህን ስራ ከሁኔታችን ጋር አጣጥሞ ለማስፈፀም በዋነኛነት በኛ ፍላጎትና ሁኔታ ላይ የተመሰረተ የራሳችን ሊባል የሚችል ስርአት መቅረፅን የሚጠይቅ ስለነበረ ከሌሎች ልምድ ብንወስድም በዋነኛነት የተወረሰ ነው የሚባል ስርአት አይደለም፡፡ በዋነኛነት በራሳችን የተቀየሰ ነው ሊባል የሚችል ነው፡፡ ትምህርቱም ከራሳችን የገጠርና የግብርና



ልማት ስትራተጅ ጋር መያያዝ ስላለበት በዚህ ደረጃ ከሌሎች ቴክኖሎጅዎችን የምንዋስ ቢሆንም በዋነኛነት ራሳችን የምናዘጋጀው -ኬጅ ይሆናል፡፡ ከግብርና ሙያ ስልጠና ፕሮግራማችን ልምድ ማየት እንደሚቻለው፣ በዚህ መስክ ከሌሎች ልምድ በሰፊው መማር እንደሚቻልና እንደሚገባ፣ እንደነገሩ ሁኔታ በዋናነት ከውጭ በመዋስ መለስተኛ ማስተካከያዎችን እያደረግን ወይም በዋነኛነት የራሳችን ሆኖ ከሌሎች ልምድ ተምረን በማጠናከር ጥራት ያለው የቴክኒክና ሙያ ስርአተ-ትምህርትና የመማሪያ መፃህፍት ማዘጋጀት ይቻላል፡፡

ከላይ የተጠቀሰውን አቅጣጫ ተከትለን የቴክኒክና ሙያ ስርአተ-ትምህርት በማዘጋጀትና የመመሪያ መፃህፍትን በማሰባሰብ ረገድ ረጅም ርቀት ብንሄድም ገና ሰፊ ተጨማሪ ስራ እንደሚጠይቀን ሊሰመርበት ይገባል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ በዚህ መልክ የተሟላ ስራ ያልተሰራባቸውና ወደፊት በሰፊው ሊሰጡ የሚችሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና መስኮች ስላሉ እነዚህን በአፋጣኝና ጥራቱ በተጠበቀ አኳኋን ማሟላት ይኖርብናል፡፡ ከዚያም ባሻገር ከላይ በተጠቀሰው መልክ ዝግጅታቸው ተጠናቆ ስራው በተጀመረባቸው መስኮችም ላይ ቢሆን በተግባር የምናገኘውን ልምድ ቀምረን ያለማቋረጥ ማሻሻልና ማዳበር አለብን፡፡ በሙያና ቴክኒክ ትምህርትና ስልጠና ረገድ በአሁኑ ወቅት የላቀ ትኩረት ሊሰጣቸው ከሚገቡ ስራዎች አንዱም ይኸው ይሆናል፡፡

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሙን ጥራት ከማረጋገጥ አኳያ ሌላው የላቀ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ

ብቃት ያላቸው መምህራንን በሚፈለገው መጠን የማዘጋጀት ጉዳይ ነው። በዚህ ረገድ በመጠንም ሆነ በአይነት ያለብን ችግር ከቀለም ትምህርቱም በእጅጉ የባሰ ነው። ቀደም ሲል ሰፊ የሙያና ቴክኒክ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራምና በዚህ ደረጃ የሚያስተምሩ መምህራንን የማሰልጠን ስራ የሚሰሩ ጠንካራ ተቋሞች ስላልነበሩን፣ ያሉን አስተማሪዎች ከፍላጎታችን ጋር ሲነፃፀር እጅግ በጣም ውሱን ናቸው። በተጨማሪም እነዚህ አስተማሪዎች በአብዛኛው በንድፈ-ሃሳብ ላይ የተጣራ እውቀት ያላቸው፣ በቂ የተግባር ልምድና የሙያው ችሎታ የሌላቸው ናቸው። ስለሆነም አንድ ተጨባጭ የሙያ ችሎታ ያለው ሙያተኛን ለመፍጠር የሚያስችል የሙያ ብቃት ይጎድላቸዋል። እጅግ በጣም አሳሳቢ የሆነ የሙያና ቴክኒክ መምህራን እጥረት ስላለብን የሙያና ቴክኒክ ትምህርትና ስልጠናውን ፕሮግራም ለማስፋፋት በተለይም ጥራቱ የተጠበቀ እንዲሆን በማድረግ ረገድ ዋነኛ ማነቆ ሆኖ ይገኛል።

መንግስት ይህን ማነቆ በሶስት የተቀናጁ መንገዶች ለመፍታት ነው ጥረት እያደረገ ያለው። በመጀመሪያ ደረጃና ከረጅም ጊዜ አኳያም ወሳኝ የሚሆነው የመካከለኛ ሙያተኞችና የዝቅተኛ ሙያተኞች የስልጠና ፕሮግራምን የሚያስፈፅሙ መምህራንን በሚፈለገው መጠንና ጥራት ለማሰልጠን የሚችሉ የስልጠና ማዕከላትን የማቋቋም ጉዳይ ነው። ይህ የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ ፍላጎታችንን ከማሟላት አኳያ የሚኖረው አስተዋፅኦ ውሱን ቢሆንም ከወዲሁ በሰፊው ካልተገባበት በስተቀር ችግሩ በረጅም ጊዜም የማይፈታ ይሆንና በስርአቱ ላይ የማያላውስ ማነቆ ሆኖ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል። በመሆኑም መንግስት



ለዚሁ ተግባር በመነሻነት ሊያገለግሉ የሚችሉ የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞችን ለማጠናከርና አዳዲሶችንም ለመፍጠር ከፍተኛ ትምህርት ከማስፋፋት ፕሮግራም ጋር የተቀናጀ ስራ ለመስራት የቅድመ-ዝግጅት ስራዎችን በማጠናቀቅ ላይ ይገኛል።

ከዚሁ ስራ ጎን ለጎን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናው ስራ መካሄድ ስላለበት ያሉንን የአገር ውስጥ መምህራን በስራ ላይ ስልጠና ፕሮግራም እንዲታቀፉ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ይገኛል። በዚህም መሰረት ለምሳሌ የግብርና ሞያ አሰልጣኝ መምህራን በሙያው ተግባራዊ ገፅታዎች ላይ ያተኮረ የክረምት ስልጠና በውጭ መምህራን የተሰጣቸው ሲሆን በያዝነው አመትም ይኸው ፕሮግራም የሚቀጥል ይሆናል። በተመሳሳይ መልኩ ሌሎቹ የቴክኒክና ሙያ መምህራን (ከሞላ ጎደል ሁሉም) የሚሳተፉበት በክረምት ወራት የሚሰጥ የአራት ወራት ስልጠና ለማካሄድ ዝግጅት እየተደረገ ነው። ይህ ስልጠናም በሙያዎቹ ተግባራዊ ገፅታዎች ላይ የሚያተኩር ይሆናል። በዚሁ መልክ በተከታታይ ክረምቶች ሰፊና የተጠናከረ የስልጠና ፕሮግራም በውጭ ሙያተኞች አማካኝነት በማካሄድ የቴክኒክና ሙያ መምህራኖቻችንን ብቃት በፍጥነት የሚፈለገው ደረጃ ላይ ማድረስ ይቻላል ተብሎ ይገመታል።

ያሉን የሙያና ቴክኒክ መምህራን በመጠንም በጥራትም የስርአቱን ፍላጎት የሚያሟሉ ሆነው ስላልተገኙ ከፍተኛ እጥረት በሚታይባቸው መስኮች ከውጭ ብቃት ያላቸው መምህራንን ቀጥሮ የማሰማራትን አቅጣጫ እንደአንድ የመፍትሄው አካል

ከመውሰድ በቀር ሌላ አማራጭ የለንም:: ይህ አማራጭ የሚጠይቀው ወጪ በጣም ከፍተኛ እንደሚሆን ቢታወቅም ፕሮግራሙን በሚፈለገው ፍጥነትና ጥራቱ ክፉኛ ሳይጎዳ ለመተግበር ለጊዜው አማራጭ የሌለው መፍትሄ ነው:: በመሆኑም በተለይም በመለስተኛ የግብርና ኮሌጆች የሚያስተምሩ የውጭ መምህራን ተቀጥረው የተሰማሩ ሲሆን በቀጣይ ወራትም ተጨማሪ የውጭ መምህራን ይገባሉ ተብሎ ይገመታል:: ይህ አሰራር በሌሎች የሙያና ቴክኒክ ስልጠና ፕሮግራሞችም አስፈላጊነቱ እየታየ በሚቀጥሉት አመታት የሚቀጥል ይሆናል:: በዚሁ መልኩ የሚቀጠሩት የውጭ መምህራን አብረዋቸው የሚሰሩ ኢትዮ-ጵያውያንን በስራቸው ላይ በማገዝና በአካባቢያቸው አጫጭር ስልጠናዎችን በመስጠት በማጠናከር ስራ ላይ እንደሚሳተፉም ይጠበቃል::

የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ፕሮግራማችን በርግጥም የሙያ ችሎታ ያላቸውን ወጣቶች ማፍራት እንዲችል ለማድረግ ያለብንን የመምህራን እጥረትና የብቃት ጉድለት ለመቅረፍ ከላይ የተዘረዘሩትን ሶስት የመፍትሄ አቅጣጫዎች በማቀናጀት በሰፊው መረባረብ ይጠብቀናል:: በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራማችን አፈፃፀም ላይ ከምንም በላይ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይም ይህ ጉዳይና ከዚሁ ጋር የተያያዘው የስርአተ-ትምህርቱ ቀረፃና የማስተማሪያ መፃህፍት ዝግጅትን በአፋጣኝ ማጠናቀቅና ያለሚቋረጥ ማሻሻል ጉዳይ ነው:: የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናው አካል ተደርጎ ሊወሰድ የማይችል ቢሆንም በጥራቱ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ያለው ሌላው ጉዳይ የሙያ ማረጋገጫ



ስርአቱ ነው::

በአገራችን ወጥነት ያለው የሙያ ማረጋገጫ ስርአት (የሰርቲፌኬሽንና አክሬዲቴሽን ስርአት) የለም:: ሙያተኞቹ አንዳንዶቹ ሙያውን በልምድና በስራ ላይ ስልጠና ያገኙት ሲሆኑ የነዚህ የሙያ ደረጃ ምን እንደሆነ በውል ተለየቶ የሙያ ደረጃ ማረጋገጫ የተሰጣቸው አይደሉም:: ሌሎቹ ካሉት ውሱን የማሰልጠኛ ተቋሞች የተመረቁ በመሆናቸው ከነዚህ ተቋሞች መመረቃቸውን የሚያሳይ የምስክር ወረቀት ሲሰጣቸውም ሙያውን በምን ደረጃ እንደተካኑት ሊያረጋግጥ የሚችል ሆኖ አልተገኘም:: ከዚህም ባሻገር ከማሰልጠኛ ተቋሞቹ የተመረቁ ወጣቶች ሙያቸውን በይበልጥ የሚያዳብሩት በልምድና በስራ ላይ ስልጠና በመሆኑ፣ ይህንኑ ተከታትሎና የእያንዳንዱን ሙያተኛ ብቃት አረጋግጦ ማረጋገጫ ለመስጠት የሚያስችል ስርአት የለም:: ይህም በመሆኑ ምርጥ ሙያተኛውን ከሌላው ለመለየት አልተቻለም:: ሙያተኛ የሚቀጥሩ ሰዎች በግል ትውውቅ ካልሆነ በስተቀር በሌላ መንገድ የሚቀጥሩት ሰው ምን አይነት ሙያ እንዳለው በርግጠኝነት ማወቅ አይችሉም:: በመሆኑም በአንድ በኩል የስራ አጥነት ችግር ያለባቸው ሙያተኞች በሌላ በኩል ደግሞ ሙያተኛ አጥተው የተቸገሩ አሰሪዎች የሚታዩበት ሁኔታ ተፈጥሯል:: ስራና ሰራተኛ በብቃት የሚገናኙበት ስርአት ባለመኖሩ ከፍተኛ ችግር ተፈጥሯል::

የሙያ ማረጋገጫ ስርአት ባለመኖሩ ሃቀኛ ሙያተኛው ከሌላው ተለይቶ የሚቀጠርበትና የስራ ዕድል የሚያገኝበት፣

ወይም በሙያው የስራ ፈቃድ አግኝቶ ራሱ ስራ ፈጥሮ የሚሰራበት ዕድል መጥበቡ፣ የሙያተኛ አገልግሎት የሚፈልጉ ሰዎች በርግጥም የሙያተኛ አገልግሎት ሳያገኙ በከፍተኛ ወጪ ጥራቱ ላልተጠበቀ ምርት ወይም አገልግሎት የሚጋለጡበት ሁኔታ መፈጠሩ አንድ መሰረታዊ ችግር ነው። ይህ ችግር ካልተፈታም በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ስርአቱ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅእኖ እንደሚያሳድር ይታመናል። ይህ ችግር በቴክኒክና ስልጠና ሙያ ጥራትም ላይ በተዘዋዋሪ መንገድ አሉታዊ ተፅእኖ ያሳድራል።

ብቃት ያለው የሙያ ማረጋገጫ ስርአት በሚኖርበት ወቅት እያንዳንዱ ሙያው የሚጠይቀውን እውቀትና ክህሎት ለማግኘት በከፍተኛ ደረጃ መጣጣሩ አይቀርም። በልምድና በስራ ላይ ስልጠና ይህንኑ ለማሻሻል እንደሚፍጨረጨርም እሙን ነው። በዚህ መልኩ የሙያ ችሎታውን ሲያሻሽል የመቀጠርም ሆነ የስራ ፈቃድ የማግኘት ዕድል ይኖረዋል፣ ይህ ካልሆነ ግን እንደሙያተኛ የሚታሰብበት ሁኔታ አይኖርም። በዚህ ምክንያት ሙያው የሚጠይቀውን መስፈርት ለማሟላት በሙያ ሰልጣኞች ዘንድ ሰፊ ጥረት የማድረግ ፍላጎት በመፍጠር ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ጥራት መጠበቅ በተዘዋዋሪ መንገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታል።

በተመሳሳይ መልኩ የሙያና ቴክኒክ ትምህርትና ማሰልጠኛ ተቋሞች ለሰልጣኞች የምስክር ወረቀት ከመስጠታቸውም በፊት እንደተቋም ማሟላት የሚገባቸው ነገር



በውል ተለይቶ፣ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው ሰው ማሟላት የሚገባውን መስፈርት እንደሚያሟላ አድርጎ ለማሰልጠንና ይህንንም በበቂ የምዘና ስርአት ለማረጋገጥ ያላቸው ብቃት ተመዝኖ እውቅና የሚሰጣቸው ከሆነ የሚሰጡት ስልጠና ጥራቱ የተጠበቀ መሆኑን የማረጋገጥ ከፍተኛ ፍላጎት ያድርባቸዋል። ይኸው ስራ በተከታታይ እየተፈፀመ መስፈርቱን የማያሟሉቱ እውቅና ከተነፈጋቸው የስልጠና ጥራታቸውን የማስጠበቅ ተነሳሽነታቸውን ቀጣይነት ያለው ለማድረግ የተሻለ ሙከራ ያደርጋሉ ተብሎ ይታመናል። ስለሆነም ከሙያተኛ የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ ስርአት ጎን ለጎን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ማሰልጠኛ ተቋሞች እውቅና አሰጣጥ ስርአትም ሊኖር ይገባል።

የቴክኒክና የሙያ ስልጠናና ትምህርት ዞሮ ዞሮ አንድ ተጨባጭ ክህሎትን ለማስጨበጥ የሚከናወን ስራ ነው። በትምህርትና ስልጠና ተቋሞች ብቻ ሊጠናቀቅ የማይችል ስራ ነው። በሰለጠነበት የስራ መስክ በስራ ላይ በመሰማራት በተለማማጅ ሰራተኝነት /አፓረንቲስ/ ተመድቦ መሰልጠንንም በማካተት ሊፈፀም የሚገባው ስራ ነው። በቴክኒክና ሙያ ስልጠናና ትምህርት መስክ ኖጅግ የተሳካ ልምድ አላቸው የሚባሉ ሃገሮች ሰፊ የተለማማጅ ሰራተኛ ስርዓት /አፓረንቲስ ሺፕ ሲስተም/ ያላቸው ናቸው። አሰሪ-ች በተለይም የግል ባለሃብቶች ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም የተመረቀውን ወጣት በተለማማጅ ሰራተኛነት ለመቀበል ሙያውን በተሟላ ሁኔኖ ኖንዲካነው ለማድረግ የሚያስችል ሰፊ ስራ ይሰራሉ። በዚህ ሂደት ላለፈው ወጣት ብቻ የሙያ ማረጋገጫ ወረቀት የሚሰጡ

ሃገሮችም አሉ። የሰራተኛው ልምድ ኖየጨመረ በሄደ ቁጥር የሙያ ማረጋገጫ ወረቀቱም በዚያው መጠን ደረጃው ኖየጨመረ ኖንዲሄድ ኖየተደረገ የሰርተፍኬሽን ስርዓቱ አንድ መሰረኖዊ አካል ኖንዲሆን ይደረጋል። በሀገራችንም ሰፊ የተለማማጅ ሰራተኛ ስርዓት መፈጠር ለቴክኒክና ሙያ ስልጠናና ትምህርት መጠበቅ በጣም አስፈላጊ ነው። ይህ ስራ ከምስክር ወረቀትና ዕውቅና አሰጣጥ ስርዓቱ ጋር የግል ባለሃብቶች በቴክኒክና ሙያ ስልጠናና ትምህርት ስርዓቱ ውስጥ መጫወት ከሚገባቸው ሚና ጋር በቀጥና የተያያዘው የተሟላ የህግ ማዕቀፍን የሚጠይቅ በመሆኑ ህጋዊ ማዕቀፉን የመፍጠር ጉዳይም ሊተኮርበት የሚገባ ነው።

መንግስት የዚህን ስርአት አስፈላጊነት በመገንዘብ የሞያ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥና፣ የሙያና ቴክኒክ ትምህርትና ማሰልጠኛ ተቋሞች እውቅና አሰጣጥ ስርአት (የስርቲፊኬሽንና አክሬዲቴሽን ስርአት) ለመዘርጋት ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል። በዚህ ጉዳይ ላይ በጣም ውጤታማ የሆነ ልምድ አላቸው ከሚባሉ አገሮች በተለይም በዚህ ረገድ በምሳሌነት ከምትጠቀሰው ጀርመን ልምድ በመማር ይህንኑ ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ስርአቱ የሚቀየስበትና ተግባራዊ የሚሆንበት ቅድመ-ዝግጅት በመከናወን ላይ ነው። ይህ ስራ ሰራተኛንና ስራን የማገናኘቱን ሂደት በማቅለልና ቀልጣፋ እንዲሆን በማድረግ፣ በርግጥም ሙያው ያላቸው ሰዎች ብቻ የሙያ ስራ እንዲሰሩ በማድረግ የምርትና አገልግሎቶቻችንን ጥራት በማሻሻል፣ የሙያተኛ የሰው ሃይል ገበያን ቅልጥፍና በማረጋገጥ ለአጠቃላይ ልማታችን ከሚያበረክተው ከፍተኛ



አስተዋፅኦ በተጨማሪ የሙያና ቴክኒክ ትምህርትና ስልጠና ስርአታችንን ጥራትም ለማረጋገጥ ከፍተኛ እገዛ ስለሚያደርግ በቂ ትኩረት ተሰጥቶት በተቻለ ፍጥነት ተግባራዊ ሊሆንና በየጊዜውም እየተገመገመ ሊዳብር የሚገባው ነው።

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሙን ጥራት ለመጠበቅ ከፍተኛ ሚና የሚጫወተው ሌላው ጉዳይ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች አቅርቦት ጉዳይ ነው። ይህ ስልጠና ተጨባጭ ክህሎትን የመፍጠር ስልጠና በመሆኑና ሰፊ የተግባር ልምምድን የሚጠይቅ በመሆኑ ከቀለም ትምህርቱም እጅግ በላቀ ደረጃ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች በቂ አቅርቦትን የሚጠይቅ ነው። በርግጥ በዚህ ደረጃ የሚጠየቀው ወጭ እንደየትምህርት አይነቱ ይለያያል። በዚህ መሰረት ለምሳሌ የሂሳብ ሰራተኞችን ለማሰልጠን የሚያስፈልጉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች የሚጠይቁት ወጭ መካከለኛ ሜካኒኮችና ኤሌክትሪሺያኖችን ለማሰልጠን የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች ከሚጠይቁት ወጭ በጣም ያነሰ እንደሚሆን መገመት ይቻላል። ይሁንና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና በዚህ ረገድ የሚጠይቀው ወጭ ከፍተኛና የቀለም ትምህርቱ ከሚጠይቀውም የላቀ ነው። በመሆኑም በዚህ ረገድ ያለው ከፍተኛ የፋይናንስ እጥረት ከፍተኛ ማነቆ መሆኑ ባይቀርም ወጪውን ለመቀነስ የሚያስችሉ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም አቅርቦቱን ለማሟላት ከፍተኛ ጥረት በመደረግ ላይ ነው።

የቴክኒክና ሙያ ሰልጣኝም እንደሌላው ዜጋ ሁሉ የስነ-ዜጋ ትምህርት ማግኘት ይገባዋል። በአንደኛ ደረጃ ትምህርት

ላይ የስነ-ዜጋ ትምህርትን በተመለከተ ያስቀመጥነው አቅጣጫ እዚህም ላይ ይሰራል። የቴክኒክና ሙያ ሰልጣኝም መልካም የስራ ስነ-ምግባርና አመለካከት ሊኖረው ይገባል። ይህንኑ በተመለከተ በቀለም ትምህርቱ ስርአት ከሚሰጠው ትምህርት በተጨማሪ የቴክኒክና ሙያ ሰልጣኝ ሙያውን የማክበርና የማፍቀር፣ የሙያ ግዴታውንና ስነ-ምግባሩን ጠንቅቆ የማወቅና ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጁ የመሆን፣ እንደዚሁም ስራ ፈጥሮ በሙያው የመተዳደር አመለካከት ሊያዳብር ይገባል። የሙያና ቴክኒክ ትምህርትና ስልጠና ስርአታችን ጥራት የሚለካበት አንዱ መሰረታዊ መመዘኛም ይኸው ይሆናል። ፕሮግራማችን በዚህም ጉዳይ ላይ ጥራቱ የተጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ የተለያዩ ጥረቶች እየተደረጉ ነው። መደረግም ይገባቸዋል።

የሙያና ቴክኒክ ትምህርት በባህሪው ሰፊ ተግባራዊ ልምምድን የሚጠይቅ መሆኑ የስራ ፍቅርንና ክብርን ለማስረፅ የተሻለ ዕድል ይሰጣል። ይሁንና ዕድሉን በብቃት ለመጠቀም የተግባር ልምምዱን በሰፊው ማስኬድ ያስፈልጋል። በዚሁ ሂደት የስራ ክቡርነትን በሚመለከት ቀጣይ ትምህርትና ቅስቀሳ መስጠት ያስፈልጋል። ዋናው መመዘኛው የተግባራዊ ልምምዱ ውጤት የሆነው ነገር እንዲሆን በማድረግ ጥሩ ውጤት ያገኘው በስራው ማለትም በሙያው የሚኮራበት ሁኔታ መፈጠር ይኖርበታል። በሙያ እውቀታቸውና ክህሎታቸው የታወቁ ሰዎችን ታሪክ እንዲገነዘብና ከነሱ እንዲማር መደረግ ይኖርበታል።

በሙያና ቴክኒክ ሰልጥኖ የሚወጣው ወጣት በመንግስት



ወይም በግል ባለሃብቶች የሚቀጠር ብቻ ሳይሆን የራሱን ስራ ፈጥሮ በሙያው የሚተዳደርም ስለሚሆን፣ ስራን ለመፍጠር የሚያስችለው እውቀትና አመለካከትም ሊኖረው ይገባል። በመሆኑም በፕሮግራሙ ሂደት የሚሰለጥነው ተቀጣሪ ለመሆን ብቻ እንዳልሆነ በሰፊው ሊገለፅለትና እንዲያምንበት ሊደረግ ይገባል። የራሳቸውን ስራ ፈጥረው በሙያቸው በመተዳደር ጥሩ ውጤት ያስገኙ ሰዎች ልምድ ሊገለፅለትና ከዚሁ እንዲማር ሊደረግ ይገባል። ስራ ለመፍጠር እውቀት እንዲኖረው የሚያስችል ትምህርት (የኢንተርፕረነርሺፕ ዴቨሎፕመንት ትምህርት) ሊሰጠው ይገባል። በአጠቃላይ ክህሎቱ ብቻ ሳይሆን የስራ ፈጠራ ችሎታውና የሙያ ስነ-ምግባር እንዲኖረው መደረግ ይኖርበታል። ከዚህ አኳያ የስራ ፈጠራ እውቀትን ለማስጨበጥ በስርአተ-ትምህርቱ ውስጥ እንዲካተቱ የተደረጉ ነገሮች ቢኖሩም ጥራቱን ለመጠበቅ መደረግ የሚገባቸው ነገሮች ሁሉ እየተሰሩ ነው ለማለት አይቻልም። በመሆኑም በቀጣዩ እንቅስቃሴያችን ለዚሁ ስራ በቂ ትኩረት መስጠት በጣም አስፈላጊ ይሆናል።

**5.3. የልማት ኖንቅስቃሴ-ችንና የሙያና ቴክኒክ ትምህርትና ስልጠና**

የሙያና ቴክኒክ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራማችንና የልማት እንቅስቃሴያችን ተቀናጅተው መፈፀም እንዳለባቸው ገሀድ ነው። በዚህ መሰረት ለምሳሌ የሙያና ቴክኒክ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራማችን ከመንግስትና ከግል ባለሀብቶች የሰው ሃይል ፍላጎት ጋር በቅርብ መተሳሰር ያለበት ይሆናል። ከሚሰለጥነው ሙያተኛ ውስጥ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው በተናጠል ወይም በግል የራሱን ስራ ፈጥሮ በሙያው የሚተዳደር

በመሆኑ ይኸው ክፍል በሙያው እንዲተዳደር ለማስቻል በመንግስት በኩል የተሟላና ሁሉን አቀፍ እገዛ ሊደረግለት ይገባዋል:: ይህ ስራ ከመንግስት የልማት አቅድ አፈፃፀም ጋር በቅርብ ተቀናጅቶ ሊሄድ ይገባዋል:: በዚህ ረገድ በመንግስት ምን ሊሰራ እንደሚገባው ሁለት ምሳሌዎችን በመውሰድ መገንዘብ ይቻላል::

በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ከሚታቀፈው ወጣት ውስጥ እጅግ በጣም የሚበዛው በመለስተኛ ሙያተኛነት የሚሰለጥን እንደሆነ፣ ከዚህም ውስጥ እጅግ የሚበዛው በተለያዩ የግብርና ሙያዎች እንደሚሰለጥንና በራሱ ስራ ፈጥሮ በሙያው እንደሚተዳደር ተገልጿል:: በዚህ ደረጃ የሚሰለጥነው በሙያው እየተዳደረ ኑሮውን እንዲያሻሽል በመንግስት ሁሉን አቀፍ እገዛ ሊደረግለት ይገባዋል:: ሙያተኛው አምርቶ ለመጠቀም ከሙያው በተጨማሪ እንደግብርና ስራው ባህሪ የሚለያይ መሬትና መነሻ ካፒታል ያስፈልገዋል:: መሬቱን ከቤተሰቡ ወይም በአካባቢው ጥቅም ላይ ያልዋለ መሬት ካለ ከዚሁ በመጠቀም ለማግኘት እንዲችል የአካባቢው የመንግስት አካላት ከወጣቶች ቤተሰቦች ጋር በመተባበር ማረጋገጥ አለባቸው:: ለስራ መነሻ የሚሆናቸው ካፒታል እንዲያገኙ በገጠር የፋይናንስ አገልግሎት ስርአት አማካኝነት ጥረት ሊደረግና ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ማድረግ ያስፈልጋል:: በዚህ ደረጃ ሰልጥነው የሚሰማሩት ዘመናዊ አርሶ አደሮች ምርታቸውን በዋነኛነት ለገበያ የሚያቀርቡ መሆናቸው ስለማይቀር የገጠር የግብይት ስርአቱ አሁን ካለው በእጅጉ ሊሻሻልና ገበሬዎችን በብቃት



ሊያስተናግድ የሚችልበት ደረጃ ላይ መድረስ ይኖርበታል:: እነዚህን መሰል ተግባራት ከተፈፀሙ በሙያና ቴክኒክ ፕሮግራም ውስጥ ከሚታቀፈው ሃይል እጅግ በጣም የሚበዛው ስራ ፈጥሮ በራሱ ሙያ እየተዳደረ ኑሮውን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያሻሽል ምንም አያጠራጥርም::

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በየትኛውም አገር ቢሆን ከፍተኛ የሰው ሃይል የሚቀጥር ኢንዱስትሪ ነው:: ከግንባታ ስራ በስተጀርባ ከኢንዱስትሪው ጋር የተሳሰሩ እንደብረታ ብረትና እንጨት ስራ ያሉ ለግንባታው ለራሱ የሚያስፈልጉና ከግንባታው በኋላ የቤት ቁሳቁሶችን (አልጋ ወንበር ወዘተ.) በመስራት በሰፊው የሚሳተፉ ዘርፎችም ይኖራሉ:: በዚህ ስራ ትልልቅ ኩባንያዎች የላቀ ሚና እንደሚጫወቱ ቢታወቅም ትናንሽ ተቋሞች ከዚያም አልፎ ተናጠል ሙያተኞች ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ:: የአገራችን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ይህንኑ በመገንዘብ ከመለስተኛ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ሙያተኛ ጀምሮ እስከ ከፍተኛው ሙያተኛ ድረስ በሚፈለገው መጠን ማሰልጠኑ አይቀርም:: በዚህ ደረጃ ያለንን ውሱን ልምድ መነሻ በማድረግ መንግስት እንዴት እነዚህ ሙያተኞች በተናጠልና በጋራ ስራ ፈጥረው በሙያቸው መተዳደር እንዲችሉ ማድረግ እንደሚገባው ማየት ይቻላል::

መንግስት የተለያዩ ፕሮግራሞችን ለማስፈፀም ሰፊ የኮንስትራክሽን አገልግሎት እንደሚጠይቅና በተለይም በክልልና ከዚያ በታች ባሉ እርከኖች የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶቹ

በአብዛኛው በትናንሽ ተቋሞች ሊፈፀሙ የሚችሉ እንደሆኑ ይታወቃል። በዚህ ረገድ ከፍተኛ ጥረት በመኖሩ የመንግስት የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች በከፍተኛ ደረጃ ከመጓተታቸውም ባሻገር ጥራታቸው ብዙውን ጊዜ አጥጋቢ ሳይሆን ይቀራል። መንግስት ይህንን የኮንስትራክሽን አገልግሎት ፍላጎቱንና ለዚሁ የመደበውን ባጀት በመጠቀም በሙያው የሰለጠኑ ወጣቶች የራሳቸው ድርጅት ፈጥረው እንዲተዳደሩ ማድረግ ይችላል።

በመጀመሪያ ደረጃ መሰራት የሚኖርበት ጉዳይ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶቹን ለመስራት የሚችሉ መካከለኛና መለስተኛ ሙያተኞች በቡድን በቡድን እንዲሰባሰቡና የራሳቸው ድርጅት እንዲያቋቁሙ ማድረግ ነው። ይህ በወጣቶቹ በራሳቸው ፍላጎት የሚፈጠር እንጅ መንግስት በምደባ ሊፈጥረው የሚችል አይደለም። በዚህ ደረጃ የሚሰባሰቡት ወጣቶች የኮንስትራክሽን ስራ የተለያየ ክህሎት ያላቸውና የስራ ፈጠራና የድርጅት መምራት ስልጠናም ያላቸው ይሆናሉ ብሎ መገመት ይቻላል። እነዚህ ሰዎች ከሙያቸው በስተቀር ምንም ነገር እንደማይኖራቸው ታሳቢ በማድረግ መንግስት የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶችን በገበያ ዋጋ ለነዚህ ድርጅቶች መስጠት ይገባዋል። ከዚሁ ለፕሮጀክቱ ከተመደበው ገንዘብ ለመሳሪያ መግዣ እንዲውል በማድረግ በወጣቶች የሚቋቋሙት ድርጅቶች በሂደት በቂ መሳሪያ እንዲኖራቸው ማድረግ ይገባል። የተቀረው የፕሮጀክት ማስፈፀምያ ገንዘብ በተሰራው ስራ መጠን በወጣቶቹ ለተቋቋመው ድርጅት ይሰጣል። በዚህ መልኩ የተወሰኑ ፕሮጀክቶች ከሰሩ በኋላ በቂ መሳሪያና ፕሮጀክት የማስፈፀም ልምድ ያላቸው



በርካታ የኮንስትራክሽን ድርጅቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ። መንግስት የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶቹን በሚፈለገው ፍጥነትና ጥራት ያስፈፅማል፣ ያለተጨማሪ ወጪ በርካታ አነስተኛ የኮንስትራክሽን ድርጅቶች ተቋቁመው በገበያ ተወዳድረው መኖር የሚችሉበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ።

በእንጨትና ብረታ ብረት ስራ የሰለጠኑ ወጣቶችንም በተመሳሳይ መልኩ ማስተናገድ ይቻላል፣ ይገባልም። በቡድን ተደራጅተው ከኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶቹ ጋር የተያያዙ የእንጨትና ብረታ ብረት ስራዎችን ለማሰራት የሚያስችል ኮንትራት ሊሰጣቸው ይችላል። መንግስት በሚገዛቸው የፅህፈት ቤት ቁሳቁሶች ስራ (ወንበር፣ ጠረጴዛ ወዘተ.) መስራት ፕሮጀክቶች ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ ይቻላል። እነዚህም ሆኑ የግንባታ ቡድኖች ከፍተኛ ሙያ በሚጠይቁ አንዳንድ የክትትልና ቁጥጥር ስራዎች ላይ የሚያግዛቸው ሰው ሊያስፈልጋቸው ይችላል። የመንግስት መስሪያ ቤቶች ይህንኑ የክትትልና ቁጥጥር ስራ እንዲሰሩ በማድረግ ማገዝ ይቻላል። ፈቃደኝነቱ ያላቸው ትልልቅ ኩባንያዎች ሲገኙም እነዚህ ኩባንያዎች ኮንትራቶቹን ወስደው ተመልሰው ለቡድኖቹ እንዲሰጡ (ሳብ-ኮንትራት እንዲያደርጉ) በማድረግ በመንግስት ይሰራሉ የተባሉት ስራዎች ሁሉ በግል ኩባንያዎች እንዲሰሩ ማድረግ ይቻላል። በዚህ ተግባር ላይ ለሚሰማሩ የግል ኩባንያዎች የተለያዩ የማትጊያ ስልቶችን በመንደፍ ማደፋፈርና ማጠናከርም ይቻላል።

የዚህ ፅሁፍ አላማ በዚህ ረገድ ሊሰሩ የሚችሉ ስራዎችን

በሙሉ መዘርዘር አይደለም። ስራዎቹን በየአካባቢው ያሉ የመንግስት ሃላፊዎች የፈጠራ ችሎታቸውን በመጠቀምና ከልምዶቻቸው በመማር ሊዘረዝሯቸው የሚገባ እንጂ እንደዚህ ባለ ፅሁፍ ተዘርዝረው ሊያልቁ የሚችሉ አይደሉም። የዚህ ፅሁፍ አላማ ከዚህ አኳያ ሊሰሩ የሚችሉ የተወሰኑ አብነቶችን በማቅረብ መሰረታዊ አቅጣጫውን ለማብራራት ነው። መሰረታዊ አቅጣጫው በገጠር የሚካሄደው የልማት እንቅስቃሴ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናው ጋር በቅርብ የተቀናጀና ስልጠናውን ያጠናቀቁ ወጣቶች በሙያቸው ስራ ፈጥረው የሚተዳደሩበት የተመቻቸ ሁኔታ ለመፍጠር ሁሉን አቀፍ እገዛ ለማድረግ የሚያስችል መሆን እንዳለበት ነው። በከተማም ጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች የማስፋፋት ስትራተጅያችን በሙያና ቴክኒክ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራማችን ዙሪያ የሚያጠነጥንና የስልጠና ተቋሞቹ ምሩቃን ጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶችን በማስፋፋት ረገድ ግንባር ቀደም ሚና እንዲጫወቱ ለማድረግ የሚያስችል ሁሉን አቀፍ እገዛ የሚሰጥ መሆን አለበት። በዚህ ተግባር ላይ የክልልና የየአካባቢው የመንግስት አካላት ግንባር ቀደም ሚና መጫወት ይገባቸዋል፣ በሳብ ኮንትራት አሰራር በዚህ ተግባር ለመተባበር የሚችሉና የሚፈልጉ የግል ኩባንያዎችንም የሚያሳትፍ መሆን ይኖርበታል።

## 5.4. የሙያና ቴክኒክ ትምህርትና ስልጠና ፋይናንስና አስተዳደር፣

በሙያና ቴክኒክ ትምህርትና ስልጠና ፋይናንስ ጉዳይ ላይ ከቀለም ትምህርቱ ፕሮግራም ለየት ያሉ ሁለት መሰረታዊ



ጉዳዮች አሉ። የዚህ ስልጠና ፕሮግራም ወጪ በአጠቃላይ ሲታይ ከቀለም ትምህርቱም በጣም የሚበልጥ መሆኑና የማሰልጠኛ ተቋሞቹ ገቢ የማሰባሰብ አቅማቸው ከቀለም ትምህርቱም የተሻለ መሆኑ አንደኛው ጉዳይ ነው። የግል ባለሃብቶች ተሳትፎ ከማንኛውም የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም በጣም ልቆ የሚገኘውና መገኘትም የሚገባው በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ መሆኑ ሌላው ጉዳይ ነው።

ጥራቱ የተጠበቀ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራምን ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ ወጭ እንደሚጠይቅና በመንግስት ባጀት ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ እንደሚያሳድር እሙን ነው። ይህ በመሆኑና መንግስት በነፃ ትምህርቱን ማዳረስ የሚገባው እስከሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያው ሳይክል ድረስ በመሆኑ በፖሊሲ ደረጃ የመካከለኛ ሙያተኛ ስልጠና ተሳታፊ የሆነው ወጣት ወጭን በመጋራት ላይ ተሳታፊ መሆን እንዳለበት ተቀምጧል። ይህን የወጭ መጋራት ፖሊሲ የተማሪውን የመማር ዕድል በማያደናቅፍ መንገድ ለመፈፀም የሚያስችል ስርአት ለመቀየስ የተለያዩ ችግሮች በመኖራቸው ፖሊሲውን ተግባራዊ ማድረግ የሚገባቸው ክልሎች እስካሁን ድረስ ተግባራዊ አላደረጉትም። ለወደፊቱ ሙያተኛው በመጠነኛ ደሞዝ የተወሰነ ጊዜ መንግስትን እንዲያገለግል በማድረግም ሆነ ስራ ከያዘ በኋላ ከገቢው የተወሰነ ክፍያ እንዲከፍል በማድረግ የወጭ መጋራቱን ተግባር በከፊል መፈፀም ይቻል ይሆናል። ይሁንና በዚህ ደረጃ ሊኖር የሚችለው ገቢ ይህን ያህል ከፍተኛ ባለመሆኑ ተማሪው ወጭውን በመጋራት መልኩ ሊሸፍን የሚችለው የወጭ መጠን በጣም ዝቅተኛ

እንደሚሆን አያጠራጥርም፡፡ ስለሆነም ምንም እንኳ የወጭ መጋራቱ ፖሊሲ መቀጠሉ ትክክለኛ ቢሆንም በዚሁ አማካኝነት ሊሸፈን የሚችለው በጣም ዝቅተኛ እንደሚሆን የተገነዘበ የወጭ አሸፋፈን ስርአት ሊኖር ይገባል፡፡

ይህንኑ ችግር በማካካስ ረገድ ትምህርት ቤቶቹ ራሳቸው ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማበርከት ይችላሉ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎቹ በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚሰሩዋቸው ስራዎች በገበያ ተሸጠው ዋጋ ሊያስገኙ የሚችሉ እንዲሆኑ ማድረግ ይቻላል፣ ይገባልም፡፡ ከዚህ የሚገኘው ገቢ ወጭ በመሸፈን ረገድ የማይናቅ አስተዋፅኦ ሊያበረክት ይችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተቋሞቹ ክፍያ ከማይጠይቁበት መደበኛ ስልጠና ጎን ለጎን በክፍያ የሚሰጡ የተለያዩ ስልጠናዎችን ማካሄድ ይችላሉ፣ ይገባቸዋልም፡፡ በዚህ ረገድ ልዩ ግምት ሊሰጠው የሚገባው የተለያዩ ኩባንያዎች ሰራተኞችን ብቃት በአጫጭር ስልጠናዎች ለማሻሻል የሚሰጥ ስልጠና ነው፡፡ የስልጠና ተቋሞቹ ጥራታቸው አስተማማኝ ከሆነ የተለያዩ ድርጅቶች ለሰራተኞቻቸው አጫጭር የስልጠና ፕሮግራም አዘጋጅተው እንዲሰጡላቸው ኮንትራት ሊሰጧቸው ይችላሉ፡፡ በዚህ መልክ የሚካሄዱ ስልጠናዎች የስልጠናውን ወጭ በመሸፈን ረገድ ከሚያበረክቱት አስተዋፅኦ በተጨማሪ ከዋና ዋና አላማዎቻቸው አንዱ የሆነውን የግል ባለሃብቱን አቅም የማጠናከር ስራ ለመስራት ያስችላቸዋል፡፡

ተቋሞቹ በዚህ መልኩ ገቢ ለማሰባሰብና የግል ባለሃብቱን ለመደገፍ የሚችሉት ይህን ለማድረግ የሚያስችል ብቃትና አመለካከት ሲኖራቸው ነው፡፡ ተቋሞቹ የተለያዩ የግል ኩባንያዎች



ሰራተኞች ያሉባቸውን የሙያ እጥረቶች አጥንተው ይህንኑ በአስተማማኝ መንገድ ለመቅረፍ የሚያስችል ፕሮግራም ለመቅረፅና ለመተግበር የሚያስችል ብቃት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የሙያ እጥረቶችን ለይቶ ለመወጣት፣ ይህንን ለመቅረፍ የሚያስችል የስልጠና ፕሮግራም የማዘጋጀት ወይም በስልጠናው አማካኝነት የሙያ እጥረቱን በብቃት ለመቅረፍ የሚያስችል ብቃት ካልገነቡ የስልጠና ኮንትራት የሚሰጣቸው ኩባንያ አይኖርም፣ ስለሆነም ገቢውንም አያገኙትም፣ የግል ባለሃብቱን አቅም በማጠናከር ረገድ ሊጫወቱት የሚገባቸውን ሚናም መጫወት አይችሉም፡፡

የስልጠና ፕሮግራም ከመቅረፅና ከማስፈፀም ብቃት በተጨማሪ ተቋሞቹ ከዋና ዋና ተግባሮቻቸው አንዱ የግል ባለሃብቱን አቅም ማጠናከር እንደሆነ፣ ከዚህም የተነሳ ተቋሞቹ የመንግስትና የህዝብ ብቻ ሳይሆን የግል ባለሃብቱ አገልጋዮችም እንደሆኑ በሚገባ ማወቅና ማመን አለባቸው፡፡ የግል ባለሀብቶችን የሰለጠነ የሰው ሃይል ችግር ለመቅረፍና የስልጠና ፍላጎትን ለማርካት ምን ጊዜም ዝግጁ መሆን አለባቸው፡፡ የግል ባለሃብቶች ከተቋሞቹ እንደዚህ አይነት እገዛ በሚጠይቁበት ወቅት ባላቸው አቅም ሁሉ የግሉን ባለሃብት ጥያቄና ፍላጎት ለማሟላት ለመረባረብ የሚያስችላቸው አመለካከት ሊይዙ ይገባል፡፡ ከዚህም በላይ ሄደው በአካባቢያቸው ካሉ የግል ኩባንያዎች ጋር እየተገናኙ ምን አይነት አገልግሎትና ድጋፍ ሊሰጡ እንደሚችሉ እያስረዱ የግል ባለሃብቶቹ በተቋሞቹ በሰፊው እንዲጠቀሙና አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ማደፋፈርና መቀስቀስ አለባቸው፡፡ አገልግሎታቸውን ለነዚህ ተጠቃሚዎች "ለመሸጥ" አበክረው

መስራት አለባቸው፡፡ እንደዚህ አይነቱ የገበያ ቅኝትና የግል ባለሃብቱን በብቃት የሚያገለግል ዝግጁነት ከሌላቸው ወጭያቸውን በመሸፈን ረገድ ሊጫወቱት የሚችሉትን ሚና በብቃት አይጫወቱም፡፡

በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ረገድ የግል ባለሃብቶችም ሰፊና ቀጥተኛ ሚና መጫወት ይኖርባቸዋል፡፡ በቀለም ትምህርቱም እንደሚያደርጉት የሙያና ቴክኒክ ትምህርት ቤቶችን አቋቁመው ከፍሎ ለመማር የሚፈልገውንና የሚችለውን በማሰልጠን ስራ ላይ መሳተፍ ይገባቸዋል፡፡ የተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም በክፍያም ሆነ በነፃ ይህንኑ አገልግሎት መስጠት ይችላሉ፡፡ መንግስት የግል ባለሀብቶችንና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በዚህ ተግባር በሰፊው እንዲሳተፉ ማበረታታት ይጠበቅበታል፡፡

የግል ባለሃብቶች በተለይም ተለቅ ተለቅ ያሉቱ የራሳቸውን ሰራተኞች ለማሰልጠን የሚያስችሉዋቸው የስልጠና ተቋሞች ማደራጀት ይችላሉ፡፡ በሌላው አለም ታላላቅ ኩባንያዎች የራሳቸው ሰራተኞች ለማሰልጠን ብለው ታላላቅ ዩኒቨርሲቲዎች እስከማቋቋም ድረስ ይሄዳሉ፡፡ በኛ ሁኔታ መለስተኛ የስልጠና ተቋሞች እስከማደራጀት ከሄዱም ትልቅ ጉዳይ ነው፡፡ ቋሚ የስልጠና ተቋም መፍጠር የማይችሉትም፣ አልፎ አልፎ የሚከናወኑ የስልጠና ፕሮግራሞች በማዘጋጀት የራሳቸውን ሙያተኞች በመጠቀምም ሆነ ጊዜያዊ አሰልጣኞችን በመቅጠር፣ ከስልጠና ተቋሞች ጋር በመተባበር ወዘተ. ሰራተኞቻቸውን



ማሰልጠን ይችላሉ፡፡ የሰራተኛን የሙያ ብቃት ማሻሻል ማለት የምርታማነትና የምርት ወይም አገልግሎት ጥራትን ማሻሻል ማለት በመሆኑ ለስልጠና ከሚያወጡት ወጭ ኩባንያዎቹ ከፍተኛ ጥቅም ያገኛሉ፡፡ ሰራተኞቹም ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስት ኩባንያዎች ሰራተኞቻቸውን ለማሰልጠን የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ለማበረታታት መጣር አለበት፡፡ ከዚህ አኳያ ለምሳሌ ኩባንያዎች ለሰራተኛ ስልጠና የሚያወጡት ወጭ በሙሉ ግብር የማይከፈልበት እንዲሆን ማድረግና ይህ አሰራር በጥብቅ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል፡፡

የግል ባለሃብቶች ከዚህም በላይ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ወጭን ለመሸፈን በጋራና በተናጠል ሊንቀሳቀሱ ይችላሉ፡፡ በሌላው አለምም እንደሚደረገው የግል ባለሀብቶች ለሙያና ቴክኒክ ትምህርትና ስልጠና በአጠቃላይም ሆነ በተሰማሩበት የስራ ዘርፍ የሚካሄደውን ስልጠና ለመሸፈን ከገቢያቸው የተወሰነ መጠን እንዲከፍሉ ሊደረግ ይችላል፡፡ ሰራተኞቻቸውን ከላይ በተጠቀሰው የአጫጭር ስልጠናዎች ፕሮግራም አማካኝነት ብቻ ሳይሆን በመደበኛ ፕሮግራሞችም ክፍያ ከፍለው ሊያሰለጥኑ ይችላሉ፡፡ የማሰልጠኛ ተቋሞችም በዚሁ መልኩ ከፍለው ለሚማሩ የኩባንያዎች ሰራተኞች በመደበኛ የስልጠና ፕሮግራም ጭምር ለማስተናገድ የሚያስችል ዝግጁነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረውና በዚህ ጉዳይ ላይ የተሳካ

ስራ ሰርተዋል የሚባሉ አገሮች ልምድም እንደሚያረጋግጠው የግል ባለሃብቶች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ወጭን በመሸፈን ረገድ በተለያዩ ስልቶች የላቀ ሚና መጫወት ይገባቸዋል፡፡ መንግስት ይህን ተገንዝቦ የግል ባለሃብቶቹ የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲጫወቱ ማበረታታት አለበት፡፡ ይሁንና የአገራችን ባለሃብቶች በሰራተኛ ስልጠና አስፈላጊነት ላይ ያላቸው አመለካከት በጣም ደካማ በመሆኑ በዚህ ረገድ ያላቸውን የተሳሳተ አመለካከት ለማሻሻል አስቀድሞ መስራት እንደሚያስፈልግ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የፋይናንስ አቅማቸው ደካማ በመሆኑ የስልጠና ፕሮግራሙን ወጭ በመሸፈን ረገድ የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ከግል ባለሃብቶች መጠናከር ጋር አብሮ እያደገ የሚሄድ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ገና ከመጀመሪያው በሌላው አገር በሚደረገው መጠን ወጭውን ይሸፍኑ ቢባል የፋይናንስ አቅማቸውም፣ በጉዳዩ ላይ ያላቸው አመለካከትም ከሚፈቅደው በላይ ሆኖ ጥረቱ በእንጭጩ ሊቀጭ ይችላል፡፡

የትምህርት ፋይናንስ አስተዳደር ያልተማከለ መሆን እንዳለበትና አሰራሩ የትምህርት ተቋሞቹ በዚህ ረገድ በቂ ስልጣን እንዲኖራቸው የሚያደርግ መሆን እንዳለበት ተቀምጧል፡፡ ያልተማከለው የትምህርትና ስልጠና ፋይናንስ አስተዳደር ስራ ከምንም በላይ ተፈላጊ የሚሆነው በቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋሞች ውስጥ ነው፡፡ ተቋሞቹ በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚያመርቷቸውን ምርቶችና አገልግሎቶች ሸጠው ለራሳቸው መጠቀም ካልቻሉ በዚሁ ስልት አማካኝነት ሊያሰባስቡ የሚችሉት



ገቢ በከፍተኛ ደረጃ እንደሚቀንስ አያጠራጥርም፡፡ ተቋሞቹ አገልግሎታቸውን ለግል ባለሀብቶች በማስተዋወቅና "በመሸጥ" ገቢ ለማሰባሰብ የሚደፋፈሩት የገቢው ተጠቃሚዎች ራሳቸው ሲሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ተቋሞች ገቢ የማሰባሰብና በገቢያቸው የመጠቀም ሰፊ ስልጣን ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ይህንኑ ለማድረግ የሚያስችል ወጥነት ያለው የፋይናንስ መመሪያ፣ የክትትልና የቁጥጥር ስርአት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡ ተቋሞቹ ገቢ ለማሰባሰብና ወጭያቸውን በብቃት ለማስተዳደር የሚያስችላቸው የተጠናከረ የፋይናንስ መዋቅርና የሰው ሃይል እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የሙያና ቴክኒክ ስልጠና አስተዳደርም እንደሌላው የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ሁሉ ከስልጠናው ሃላፊዎች በተጨማሪ መምህራኑና አስተማሪዎቹ ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱበት የሚገባ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የተቀመጠው አቅጣጫ እዚህም ላይ ሊሰራ የሚችልና የሚገባው ነው፡፡ በሙያና ቴክኒክ ትምህርትና ስልጠና አስተዳደር ረገድ ለየት ባለ መልኩ መታየት የሚገባው የግል ባለሃብቶች ሚና ነው፡፡ የግል ባለሃብቶች በወላጅነታቸው ከሚጫወቱት ሚና ባሻገር እንደ ባለሃብት በትምህርትና ስልጠና አስተዳደር ረገድ የላቀ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉትና የሚገባቸውም በሙያና ቴክኒክ ስልጠና ላይ ነው፡፡

የግል ባለሃብቶች የቴክኒክና ሙያ ሰልጣኞችን በመቅጠር ረገድ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ ናቸው፡፡ ለጊዜው በዚህ ረገድ መንግስት የላቀ ሚና በመጫወት ላይ ያለ ቢሆንም በሂደት ስራ

ፈጥሮ በሙያው ከሚተዳደረው ሙያተኛ ውጭ ያለውን የሰው ሃይል መቅጠር ያለበት የግል ባለሃብቱ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ምን አይነት ሙያተኛ በምን አይነት ደረጃ እንደሚሰለጥን ለመወሰን የግል ባለሃብቶቹ ፍላጎትና የሚያቀርቡት መረጃ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ አጠቃላይ የገበያ ቅኝት በማድረግ የሚፈለገውን የሰው ሃይል አይነትና መጠን መገመት የሚቻልና የሚገባ ቢሆንም፣ በእንደዚህ አይነቱ ጥናት የግል ባለሀብቶች መረጃ ወሳኝነት ያለው ነው፡፡ የስልጠና ፕሮግራሙ ራሱ በገበያው ፍላጎት መሰረት የሚታቀድና የሚፈፀም በመሆኑ፣ የገበያው መረጃ በዋነኛነት በግል ባለሃብቶች የሰው ሃይል ፍላጎትና እነሱ በሚያቀርቡት መረጃ ላይ የሚመሰረት በመሆኑ የግል ባለሃብቶች ምን አይነት ሙያተኛ በምን አይነት ደረጃ መሰልጠን እንዳለበት በመወሰን ረገድ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ፣ መጫወትም ይገባቸዋል፡፡

በግል ስራ ከሚተዳደረው ሙያተኛ ውጭ ያለው ባለሙያ በሂደት በዋነኛነት በግል ባለሀብቱ የሚቀጠር መሆኑ አይቀርም፡፡ በመሆኑም ማሰልጠኛ ተቋሞቹ የስልጠና ስራቸውን በብቃት እየፈፀሙ መሄዳቸውን በሚገባ በመረዳት በኩል የግል ባለሃብቱ የላቀ ሚና ሊጫወት ይችላል፡፡ ሰልጥነው የወጡ ሰዎችን ቀጥሮ የሚያሰራ በመሆኑ ምርታማነታቸውንና የምርት ወይም አገልግሎት ጥራቱን በቅርብ በመከታተል የሚጎድላቸው ነገር ምን እንደሆነ በአፋጣኝ ሊገነዘብ ይችላል፡፡ የማሰልጠኛ ተቋሞቹ እንደዚህ አይነቱ መረጃ ሲደርሳቸው ጉድለታቸውን ለማስተካከል ሰፊ ዕድል ያገኛሉ፡፡ የግል ባለሃብቱ በዚህ መልኩ የቴክኒክና



ሙያ ስልጠና ስርአቱ ጥራት እየተሻሻለ እንዲሄድ ማድረግ ይችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የግል ባለሃብቱ እላይ እንደተዘረዘረው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናን ፋይናንስ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ የግል ባለሃብቱ ከላይ የተጠቀሱትን ስራዎች በብቃት መፈፀም የሚችለው በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ስርአት አመራር ውስጥ በየደረጃው ሰፊ ተሳትፎ እንዲኖረው ከተደረገ ብቻ ነው፡፡

የግል ባለሀብቱ በስልጠናው አስተዳደር ረገድ በተለያዩ ደረጃዎች መሳተፍ ይችላል፣ ይገባዋልም፡፡ በአገር አቀፍ ደረጃና በተለይም በክልል ደረጃ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሙን ለመምራትና ለማስተባበር የተለያዩ አካላትን ያሳተፈ ጉባኤ ወይም ኮሚቴ በሚቋቋምበት ወቅት የግል ባለሃብቶች ተወካዮች በነዚህ ኮሚቴዎችና ጉባኤዎች በብቃት የሚወከሉበት ሁኔታ ሊፈጠር ይገባል፡፡ እንደነዚህ አይነቶቹ ኮሚቴዎችና ጉባኤዎች ስራቸውን በብቃት ለመስራት ይችሉ ዘንድ ምን መደረግ እንዳለበት ከአንደኛ ደረጃና ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጋር በማያያዝ የቀረበው ሃሳብ እዚህም ላይ ሊሰራ ይችላል፡፡

የግል ባለሃብቶች አጠቃላይ አመራር በሚሰጡ ኮሚቴዎችና ጉባኤዎች ከመሳተፍ በተጨማሪ በተቋሞቹ በራሳቸው አመራር ኮሚቴዎች ውስጥ በስፋት ሊሳተፉ ይገባል፡፡ በዚህ መሰረት እንደነገሩ ሁኔታ ተቋሙ በሚገኝበት አካባቢ የሚገኙ ባለሀብቶች በተቋሞቹ አመራር ኮሚቴዎች ውስጥ እንዲወከሉ በማድረግ፣ ወይም በማሰልጠኛ ተቋሙ የሚሰልጥኑ ሰዎችን በመቅጠር ረገድ ተሳታፊ የሚሆኑ ባለሃብቶች ተወካዮቻቸውን

እንዲመርጡ በማድረግ፣ ወይም ሁለቱን አማራጮች በማቀናጀት በተቋሞቹ አመራር ኮሚቴዎች ውስጥ በብቃት እንዲወከሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

መንግስት እጅግ በጣም ሰፊ የሙያና ቴክኒክ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ነድፎ ተግባራዊ ለማድረግ በመረባረብ ላይ ነው፡፡ አገራችን የእንደዚህ አይነት የስልጠና ስርአት ልምድ ስለሌላት በአፈፃፀሙ ላይ የተለያዩ ችግሮች ማጋጠማቸው የማይቀር ነው፡፡ ፕሮግራሙ በአሁኑ ወቅት በተለይም በመካከለኛ ሙያተኛ ደረጃ የመንግስትን የሰው ሃይል ፍላጎት በማርካት ላይ እንዲያተኩር መደረጉ ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮችን ለማስወገድ ተጨማሪ ዕድልና ጊዜ የሚሰጠን ነው፡፡ ይሁንና ከላይ በተዘረዘረው አኳኋን መሰራት የሚገባቸውን ስራዎች ለመፈፀም ከወዲሁ ከፍተኛ ርብርብ ካልተደረገ በስተቀር ለተወሳሰቡና በጣም ጎጂ ለሆኑ ችግሮች እንደምንጋለጥ ሊሰመርበት ይገባል፡፡

## 6. ከፍተኛ ትምህርት፣

### 6.1. የከፍተኛ ትምህርት ስርጭትና አወቃቀር፣

በተለምዶ ከፍተኛ ትምህርት የሚባለው በዲፕሎማ ደረጃ የሚሰጠውን ትምህርት ጨምሮ፣ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት



በኋላ ያለው ትምህርት በሙሉ ነው፡፡ የቴክኒክና ሙያ ስልጠናችን መካከለኛ ሙያተኛ ለማሰልጠን ከሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ውስጥ በርካታዎች በሙያና ቴክኒክ ማሰልጠኛ መለስተኛ ኮሌጆች በዲፕሎማ ደረጃ የሚሰጡ ይሆናሉ፡፡ በመሆኑም እነዚህ ፕሮግራሞችም የከፍተኛ ትምህርት አካል ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡ የተለመደው አሰራር ይኸው ሆኖ ሳለ በዚህ ፅሁፍ ከፍተኛ ትምህርት ስንል በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የሚሰጠውን እንጂ በመለስተኛ ኮሌጆች የሚሰጠውን የሚጨምር አይሆንም፡፡ በመለስተኛ ኮሌጆች ደረጃ የሚሰጠው ስልጠና በሙያና ቴክኒክ ስልጠና ፕሮግራም ውስጥ ከላይ የተዘረዘረ በመሆኑ በዚህ ክፍል በዩኒቨርሲቲ ትምህርት ላይ ማተኮሩ የሚመረጥና ተገቢም ነው፡፡

በአገራችን የከፍተኛ ትምህርት ስርጭት እጅግ በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነበር፡፡ አንድ የተሟላ ዩኒቨርሲቲ፣ አንድ የግብርና ዩኒቨርሲቲና የተለያዩ ኮሌጆችን በመያዝ በአመት ከስድስት ሺ የማይበልጥ ተማሪ የመቀበል አቅም ይዘን ነበር የጀመርነው፡፡ ባለፉት አስር አመታት፣ በተለይም ባለፉት አምስት አመታት ስርጭቱን ለማስፋፋት የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ በሚቀጥሉት ሶስት አመታትም ከመቼውም የላቀ ጥረት በማድረግ ስምንት የተሟሉ ዩኒቨርሲቲዎች እንዲኖሩንና በአመት ከ30ሺ የማያንሱ ተማሪዎችን ለመቀበል የሚያስችለን አቅም እንፈጥራለን ተብሎ ይገመታል፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ስርጭት አንዱ ዋነኛ ችግር የዩኒቨርሲቲዎች ቁጥር ማነስና በዲግሪ ደረጃ የሚማሩ ተማሪዎችን የመቀበል አቅም ማነስ የነበረ በመሆኑ በተያዘው ፕሮግራም በዚህ ረገድ የነበረብን ችግር በከፍተኛ ደረጃ ይቀረፋል

ተብሎ ይገመታል፡፡

ከፍተኛ ትምህርት በተለያዩ የስራ መስኮች የአመራር ሚና የሚጫወቱና አዳዲስ ሃሳቦች የሚያመነጩ ተመራማሪዎችን በማፍራት የአገሪቱን የከፍተኛ ሙያተኛና ተመራማሪ ፍላጎት የማርካት አላማ ያለው የትምህርት ደረጃ ነው፡፡ ከፍተኛ ትምህርት በትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ላይ ብቻ ሳይታጠር ለአገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት፣ ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ የሚበጁ አዳዲስ ሃሳቦችን የማፍለቅ፣ በነዚህ መስኮች የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ አማራጭ መፍትሄዎችን የማቅረብ አላማ ያለው ተቋምም ነው፡፡ በሌላ አነጋገር የትምህርትና ስልጠና ብቻ ሳይሆን የምርምር ተቋምም ጭምር ነው፣ መሆንም አለበት፡፡ በዚህም ምክንያት ቁልፍ የማስፈፀም አቅም ግንባታ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታው ስራ በዋና ከተማችን ብቻ ሳይሆን በየክልሉ የሚካሄድ፣ በዋነኛነትም በየክልሉ የሚካሄድ ነው፡፡ በየክልሉ የሚካሄደውን ዋናውን የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ በምርምር የሚደግፉ ዩኒቨርሲቲዎች በአቅራቢያው ካላገኘ በስተቀር በሚፈለገው መጠን በምርምር የተደገፈ ስራ ሊሰራ አይችልም፡፡ ስለሆነም በከፍተኛ ትምህርት ስርጭት ረገድ ሊተኮርባቸው ከሚገቡ ጉዳዮች አንዱ የክልላዊ ስርጭት ጉዳይ ነው፡፡ ባለፉት አመታት የተካሄደውና በመካሄድ ላይ ያለው የዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ስራ በአብዛኛው ከአዲስ አበባ ውጭ የተካሄደ በመሆኑ በዚህ ረገድ የነበረብንን ትልቅ ችግር ለመቅረፍ አስችሎናል፡፡ ለወደፊቱም ይህንኑ አቅጣጫ ተከትለን መሄድ



ይኖርብናል፡፡

የዩኒቨርሲቲዎችን ክልላዊ ስርጭት ማስተካከልን በሚመለከት ሊሰመርባቸው የሚገቡ የተለያዩ ነጥቦች አሉ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ በፌዴራል መንግስት የሚቋቋሙት ዩኒቨርሲቲዎች የፌዴራል መንግስት ተቋሞች በመሆናቸው የሚመሩት በአገር አቀፍ የፌዴራል መንግሰት እቅድና አገሪቱን በሞላ ለማገልገል በሚያስችል አኳኋን ነው፡፡ የየክልሉን ተማሪዎች ለማስተማር ወይም የክልሎችን የምርምር ፍላጎት ብቻ ለማርካት ተብለው የተቋቋሙ አይደሉም፡፡ ይህ መሰረታዊ መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ዩኒቨርሲቲዎቹ ከአካባቢያቸው ህዝብና የመንግሰት አካላት ጋር የቅርብ ትስስር ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በየአካባቢያቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የማታ ትምህርት፣ የክረምት ትምህርትና የመላላክ ትምህርት ፕሮግራሞችን ቀይሰው ተግባራዊ ማድረግ ይችላሉ፡፡ ይህንኑ ስራ ከአገራዊ ተልእኳቸው ጋር በማይጋጭ ይልቁንም አገር አቀፍ ተልእኳቸውን በሚያጠናክር አኳኋን ሊፈፅሙት ይችላሉ፡፡ በየአካባቢያቸው የሚያጋጥሙ የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ የምርምር ስራዎችን አገራዊ ተልእኳቸውን በሚደግፍ አኳኋን ማካሄድ ይችላሉ፡፡ የፌዴራል መንግስት ተቋማት የመሆናቸው ባህሪ እንደተጠበቀ ሆኖ በአቅራቢያቸው የሚገኘውን ህዝብና መስተዳድር መደገፍ ይችላሉ፣ ይገባቸዋልም፡፡ የዩኒቨርሲቲዎችን ክልላዊ ስርጭት የማስተካከል ጉዳይ በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ ሲታይ ነው ጠቃሚነታቸው አስፈላጊነቱ ጎልቶ የሚታየው፡፡

በየክልሉ የሚቋቋሙት ዩኒቨርስቲ-ች አገራዊ ተልዕኮ ባህሪይ ኖንደተጠበቀ ሆኖ በአቅራቢያቸው ያሉ ክልሎችንም ለመርዳት የሚያስችላቸው ዝግጁነት ኖንዲኖራቸው ማድረጉ ተፈላጊ ቢሆንም ይህ ብቻውን ክልሎች በዩኒቨርስቲ-ች በላቀ ደረጃ ኖንዲጠቀሙ ሊያደርጋቸው አይችልም፡፡ ክልሎቹ ራሣቸውን ይህንን ትልቅ አቅም የመጠቀም አስፈላጊነት ተገንዝበው ከዩኒቨርስቲ-ቹ ጋር ተቀራርበው፣ በሚቻላቸው መንገድ ሁሉ ኖየደገፉ፣ በአገልግሎቱ ለመጠቀም ፍላጐቱና ዝግጁነቱ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ክልሎቹ ተቋሞቹን ኖንደትልቅ ፀጋ በማየት ሊደግፏቸውና ሊጠቀሙባቸው ኖንደሚገባ መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡

በዚህ መሰፈርት የዩኒቨርሲቲዎችን ክልላዊ ስርጭት ማስተካከል ተገቢ መሆኑ የሚታመንበት ቢሆንም ዩኒቨርሲቲዎች የሚቋቋሙባቸው ቦታዎች ማሟላት የሚገባቸው መስፈርት ይኖራል፡፡ ዩኒቨርሲቲዎች ስራቸውን በብቃት መፈፀም የሚችሉት የተሟላ የመሰረተ-ልማት አገልግሎት በሚገኙባቸው ከተሞች ሲቋቋሙ ነው፡፡ በዩኒቨርሲቲው የሚካሄደውን የትምህርትና ምርምር ስራ ለማከናወን የሚቻለው በዚሁ ተግባር ተሳታፊ የሚሆኑ ከፍተኛ ሙያተኞችን ለመሳብ የሚችል አገልግሎት ባላቸው ትልልቅ ከተማዎች ዙሪያ የተቋቋሙ እንደሆነ ነው፡፡ በነዚህና በመሳሰሉት ምክንያቶች ዩኒቨርሲቲዎች መቋቋም የሚችሉት በዋነኛነት ባሉት ትልልቅ ከተሞች ዙሪያ ነው፡፡ የዩኒቨርሲቲዎቹን ስርጭት ለማሻሻል ሲባል ከዚህ ውጭ ዩኒቨርሲቲዎችን መስርቶ ስራቸውን በአግባቡ ሳይሰሩ የሚቀሩበት ሁኔታ መፈጠር የለበትም፡፡



ከክልላዊ ስርጭት ማስተካከል ሌላ በከፍተኛ ትምህርት በቂ ተሳትፎ የሌላቸውን የአንዳንድ ክልል ተወላጆችና ሴቶችን ተሳትፎአቸውን ለማጠናከር ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡ ምንም አይነት ብቃት የሌላቸውን ተማሪ-ች ወደ ዩኒቨርሲቲ ማስገባት የማይቻልና የማይገባ ቢሆንም ለሴቶችና በቂ ተሳትፎ ለሌላቸው ክልሎች ወደ ዩኒቨርስቲ መግቢያ መመዘኛውን በመጠኑ ዝቅ በማድረግና በመሳሰሉት መንገዶች ተሳትፏቸውን ማጠናከር ይገባል፡፡ በዚሁ መልኩ ወደ ዩኒቨርሲቲ-ች ከገቡ በኋላም ልዩ ድጋፍ ስለሚያስፈልጋቸው ዩኒቨርሲቲ-ቹ ይህንኑ ልዩ ድጋፍ መፍጠር መቻል አለባቸው፡፡ የዩኒቨርሲቲ-ቹ የብቃት መለኪያ ደከም ያሉትን ተማሪ-ች መጣልና ማስወጣት አይደለም፡፡ የብቃኖቸው ማረጋገጫ ጐበዝ ተማሪውን ብቻ ሳይሆን ደከም ያለውንም በልዩ ሁኔኖ በመደገፍና በማብቃት፣ ተማሪው ሳይንጠባጠብ ትምህርቱን ኖንዲያጠናቅቅ ማድረግ መቻላቸው ነው፡፡ ይህ መቶ-ችንና በቂ ተሳትፎ የሌላቸውን ክልሎች በቅድሚያ የሚመለከት ቢሆንም ሌላው ተማሪም ቢሆን የሚመለከተው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ዩኒቨርሲቲ-ቹ በዚህ ገረድ ያለባቸውን የባህልና የአሠራር ጉድለት ኖንዲያስተካክሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በአገራችን የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ከተጀመረ ብዙ አመታትን ያስቆጠረ ቢሆንም የድህረ-ምረቃ ፕሮግራሞች እጅግ ዘግይተው የጀመሩና በጣም አነስተኛ በሆነ ቁጥርና የትምህርት መስክ ብቻ የሚካሄዱ ነበሩ፡፡ ይህም በመሆኑ አገሪቱ ከፍተኛ

ተመራማሪዎችን በሚፈለገው መጠንና አይነት የማፍራት አቅሟ ተገድቦ ቆይቷል፡፡ በራሳቸው በከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች የሚፈለገውን አስተማሪ በሚፈለገው መጠንና አይነት ለማፍራት ሳይቻልም ቀርቷል፡፡ በመሆኑም የትምህርትና ስልጠና ስርአታችን የተሟላ እንዲሆን ለማድረግና በላቀ ደረጃ የሰለጠኑ ፕሮፌሽናሎችን በሚፈለገው መጠንና አይነት ለማፍራት ዩኒቨርሲቲዎች እንዲበራከቱና የመቀበል አቅማቸው እንዲጨምር ብቻ ሳይሆን የድህረ-ምረቃ ትምህርት እንዲስፋፋ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በዚህም ጉዳይ ላይ ባለፉት አመታት ሰፋ ያለ ጥረት ተደርጓል፡፡ በሚቀጥሉት አመታትም ጥረቱ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡ የድህረ-ምረቃው ትምህርት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ላይ እንዲያተኩር በማድረግ በዚህ ደረጃ የቅበላ አቅማችንን በከፍተኛ ደረጃ ለመጨመርና የሚሰጡትን የትምህርት አይነቶችም ለማብዛት ርብርብ በማድረግ በሂደትም ከአዲስ አበባ ውጭ ያሉ ዩኒቨርሲቲዎች በዚሁ ፕሮግራም ተሳታፊ የሚሆኑበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

በአንድ አገር ውስጥ የተሟላ ስርጭት ያለው የዩኒቨርሲቲ የትምህርት ስርአት ሊኖር የሚችለው ሁለገብ የትምህርትና ምርምር አገልግሎት የሚሰጡ ዩኒቨርሲቲዎች በመበራከታቸው ብቻ አይደለም፡፡ ዩኒቨርሲቲዎቹ በተለያየ መስክ ከሚሰጡት የትምህርትና የምርምር አገልግሎት በተጨማሪ በተወሰኑ መስኮች የላቀ አቅም ገንብተው ምርጥ የብቃት ማዕከሎች (የኤክስለንስ ሴንተርስ) ሲሆኑም ጭምር ነው፡፡ በአገራችን የነበረው ሁለገብ ዩኒቨርሲቲ አንድ ብቻ በመሆኑ ምንም አንኳ በተወሰነ መስክ



የትምህርት አገልግሎት የሚሰጡ ኮሌጆች ተቋቁመው የነበሩ ቢሆኑም በተወሰኑ መስኮች ምርጥ የብቃት ማዕከሎች የሆኑ ሁለገብ ዩኒቨርሲቲዎች ነበሩን ማለት አይቻልም፡፡ ከዚህም አኳያ ሲታይ የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ስርጭት የተዛባ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ተጨማሪ ሁለገብ ዩኒቨርሲቲዎችን የማቋቋም ፕሮግራማችን በዚሁ ሂደት ዩኒቨርሲቲዎቹ በተወሰኑ መስኮች ምርጥ የብቃት ማዕከሎችም እንዲሆኑ ለማስቻል የታቀደ በመሆኑ በዚህ ረገድ የነበረውን የስርጭት መዛባት ችግር ለመቅረፍ ያስችላል ተብሎ ይታመናል፡፡

የከፍተኛ ትምህርት አገልግሎት ሁለገብ ዩኒቨርሲቲዎች በማቋቋም ብቻ የሚሟላ አይደለም፡፡ የተለየ ትኩረት በሚያስፈልጋቸው መስኮች የትምህርትና ምርምር አገልግሎት የሚሰጡ ከፍተኛ ኢንስቲትዩቶች ማቋቋምም ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ረገድ የአገራችን የከፍተኛ ትምህርት ስርአት ከፍተኛ የስርጭት መዛባት እንደነበረበት መገንዘብ ይቻላል፡፡ መንግስት ይህን ችግር ለማስወገድ የተለያዩ ጥረቶችን አድርጓል፡፡ ከአጠቃላይ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ፕሮግራሙ ጋር በማያያዝ ልዩ ልዩ ከፍተኛ ኢንስቲትዩቶችን አቋቁሟል፣ በማቋቋምም ላይ ነው፡፡ በዚህ መሰረት የሲቪል ሰርቪሱን የከፍተኛ ሙያተኛና የምርምር አገልግሎት ፍላጎቶች በማሟላትና በተለይም የክልሎችን የሰው ሃይል ችግር በተቻለ ፍጥነት በመቅረፍ ላይ ያተኮረ የሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ተቋቁሟል፡፡ በምርምር አገልግሎትና ከፍተኛ የሲቪል ሰርቪስ ሙያተኛ በማሰልጠን ረገድ ያበረከተው አስተዋፅኦ ውሱን ቢሆንም የክልሎችን የሰው ሃይል እጥረት በመቅረፍ

ረገድ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው አስተዋፅኦ አበርክቷል። የመከላከያ ሃይላችን የሚፈልገውን የከፍተኛ ፕሮፌሽናል ፍላጎት ለማሟላት ተብሎ የተቋቋመውና በመጠናከር ላይ የሚገኘው የመከላከያ ዩኒቨርሲቲም በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችል ነው። የግል ባለሃብቱን አቅም ለማጎልበት ቅድሚያ በተሰጣቸው የኢንዱስትሪ መስኮች የትምህርትና ምርምር አገልግሎት እንዲሰጥ የተቋቋሙትና በመጠናከር ላይ ያሉት የጨርቃ ጨርቅ ኢንስቲትዩትና የቆዳ ኢንስቲትዩትም በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው።

በአጠቃላይ የአገራችን የከፍተኛ ትምህርት ስርአት የተለያዩና ከፍተኛ የስርጭት ችግሮች የነበሩበት ስርአት ነው። ተማሪዎችን የመቀበል አቅሙ በጣም ውሱንና ክልላዊ ስርጭቱም በጣም የተዛባ ስለነበር የመቀበል አቅሙን በከፍተኛ ደረጃ ለማሻሻልና ክልላዊ ስርጭቱንም ለማስተካከል ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። የድህረ-ምረቃ ፕሮግራምን በተገቢው መጠን ያላካተተና በተወሰኑ መስኮች ምርጥ የብቃት ማዕከሎች ሊሆኑ የሚችሉ ሁለገብ ዩኒቨርሲቲዎችን ያልፈጠረ ስለነበር፣ ይህንኑ ለማስተካከል ሰፊ ስራ ተሰርቷል። በመሰራትም ላይ ነው። ከሁለገብ ዩኒቨርሲቲዎች በተጨማሪ ልዩ ትኩረት በሚያሻቸው መስኮች ከፍተኛ የትምህርትና ምርምር ኢንስቲትዩቶችንና ተቋሞችን ለመፍጠር ስራ በቂ ትኩረት ሳይሰጥ የቆየ  በመሆኑ ይህንኑም ለማስተካከል ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። በአጠቃላይ በከፍተኛ ትምህርት ዙሪያ የነበሩብንን ከፍተኛ የስርጭትና የአወቃቀር ችግሮች ለመፍታት ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፣ ተስፋ ሰጪ



ውጤቶችም ተገኝተዋል። ከዚሁ አኳያ በመጭውም ጊዜ ዋናው ትኩረት የተያዙትን ዕቅዶች ተረባርቦ ዳር ማድረስና የከፍተኛ ትምህርት አገልግሎትን የማስፋፋት ስራችን በዚሁ አቅጣጫ የሚመራ እንዲሆን ማድረግ ነው።

## 6.2. የከፍተኛ ትምህርት ጥራት፣

የከፍተኛ ትምህርት ጥራት እንደሌላው የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራማችን ሁሉ በቀለም ወይም በሙያ ትምህርቱ ጥራት፣ በስነ-ዜጋ ትምህርቱ ብቃትና በስራ ስነ-ምግባርና አመለካከቱ ጥራት ይመዘናል። የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ከርሱ በታች ካሉት የትምህርትና ስልጠና ማዕከላት የሚመጡለትን ተማሪዎች ተቀብሎ የማሰልጠን ሃላፊነት ያለበት በመሆኑ የሚቀበላቸው ተማሪዎች ጥራት ያለው ትምህርትና ስልጠና ሳያገኙ የሚመጡ ይሆኑና የዩኒቨርሲቲውንም የጥራት ደረጃ ያወርዱታል። በዚህ ረገድ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጥራትን ለማሻሻል እየተደረገ ያለው ጥረት፣ በተለይም የዩኒቨርሲቲ ማዘጋጃ ትምህርት በሁለት አመታት ተጠናክሮ እንዲሰጥ መደረጉ የዩኒቨርሲቲ ትምህርትን ጥራት ለማስጠበቅ የበኩሉን እገዛ እንደሚያደርግ ይገመታል።

ይሁንና የዩኒቨርስቲ ትምህርትን ጥራት ከማስጠበቅ አኳያ ወሳኝ የሚሆነው በውስጡ የሚሰራው ስራ መሆኑ አይቀርም። በዚህም ረገድ በርካታ ችግሮች ይታያሉ። በመጀመሪያ ደረጃ መፈተሽ ያለበት የስርአተ-ትምህርቱ ጉዳይ ነው። በዩኒቨርሲተዎች

ደረጃ የሚሰጠው ትምህርትና ስልጠና አገሪቱ የምትፈልገውን ከፍተኛ ሙያተኛ ለማፍራት የሚያስችልና ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የሚቀርቡት የመማሪያ መፃህፍትም በዚሁ ደረጃ መሆናቸው ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የዩኒቨርሲቲዎቻችን ስርአተ-ትምህርት ከአገራችን የሙያተኛ ፍላጎት ጋር በሚገባ ያልተሳሰረና ደረጃውንም ያልጠበቀ መሆኑ በጥናትና ግምገማ የተረጋገጠ ነው፡፡ ይህንኑ ለማሻሻል የሚያስችሉ የተለያዩ ጥናቶችም ሲካሄዱ ቆይተዋል፡፡ ከዚህ አኳያ ከተመረጡ የውጭ ዩኒቨርሲቲዎች ልምድ በመማር ስርአተ-ትምህርቱን የማሻሻል ስራን ማቀላጠፍ እንደሚቻል በመገመቱ ይህንኑ ለማድረግ የሚያስችል ስራም ተጀምሯል፡፡ የራሳችንን ጥናትና የውጭ ልምድ በመቀመር ስርአተ-ትምህርቱን በአፋጣኝ ማስተካከልና የመማሪያ መፃህፍቱንም ጥራት ማስጠበቅ ለነገ የማይባል ጉዳይ በመሆኑ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

የዩኒቨርሲቲ ትምህርትን ጥራት ለመጠበቅ ሌላው ቁልፍ ጉዳይ የመምህራን ጥራትና መጠን ነው፡፡ በመምህራን መጠን ጉዳይ ላይ ዩኒቨርሲቲዎች ከመጨመራቸው ጋር ተያይዞ የሚፈጠር ችግር ቢኖርም ከፍተኛ ችግር ያለበት ጉዳይ አይደለም፡፡ ዋናው ችግር ያለው ጥራት ላይ ነው፡፡ በአገራችን የድህረ-ምርቃ ትምህርት በጣም ደካማ በመሆኑ በሚፈለገው ደረጃ የሰለጠኑ መምህራን መመደብ አልተቻለም፡፡ ይህንን ከውጭ በሚቀጠሩ መምህራን ለማካካስ ጥረት የተደረገ ቢሆንም ይህም በሚፈለገው መጠን የተሄደበት አይደለም፡፡ በዩኒቨርሲቲ መምህርነት ለመቀጠል ብቃቱ ወይም የስራ ተነሳሽነቱና ስነ-ምግባሩ



የሚጎድላቸው ሰዎች ጉድለታቸውን እንዲያሻሽሉ ወይም ከስርአቱ እንዲወገዱ ለማድረግ ብቃት ያለው አሰራር ተግባራዊ አልሆነም፡፡ በመሆኑም ምንም ብቃት የሌላቸው፣ የስራ ስነ-ምግባርና ተነሳሽነት የሚጎድላቸው ቁጥራቸው አነስተኛ ያልሆኑ መምህራን በስርአቱ ላይ ተጭነው ጥራቱን ክፉኛ እየጎዱት ይገኛሉ፡፡

የዩኒቨርሲቲ ትምህርትን ጥራት ለመጠበቅ በመምህራን በኩል ያለውን ችግር ቁርጠኛ በሆነ አኳኋን በአፋጣኝ እንዲፈታ ማድረግ አማራጭ የሌለው ነው፡፡ በዚህም መሰረት በሚፈለገው ደረጃ የተማሩ መምህራንን ለማሰልጠን የተጀመረውን የድህረ-ምረቃ ትምህርት በከፍተኛ ደረጃ የማሻሻል ስራ ጥራቱ ተጠብቆ በአፋጣኝ ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን የመምህራን ጥራት ጉድለትን ለማካካስ በሁሉም የዩኒቨርሲቲ ደረጃዎች ብቃት ያላቸው የውጭ መምህራን ተቀጥረው እንዲሰሩ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ይህ በተለይም በድህረ-ምረቃ ፕሮግራሙ ልዩ ክብደት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ይሆናል፡፡ በዚህ ላይ የዩኒቨርሲቲ መምህራንን ብቃት ለማስጠበቅ ብቃቱ የሚጎድላቸውንና በትምህርትና ስልጠና ማሻሻል የሚችሉትን በመለየት የማሻሻያ ድጋፍና ዕድል ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ መምህራን ሊያሟሉ የሚገባቸው የብቃት፣ የስራ ተነሳሽነትና ስነ-ምግባር፣ የስራ ውጤታማነት መመዘኛ ተቀምጦ የዩኒቨርሲቲ ሃላፊዎች መምህራኑና ተማሪዎች በሚሳተፉበት አኳኋን አስተማሪዎች የሚገመገሙበትና ሸክም የሆኑቱ ከስርአቱ የሚወገዱበት ስርአት በጥብቅ ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል፡፡ በዚህ ረገድ ከዚህ በፊት የነበረው ስርአት ብቃት ያላቸውንና የሌላቸውን አስተማሪዎች

በማንገዋለል ረገድ ለምን ውጤታማ ሊሆን እንዳልቻለ ተገምግሞ የሚስተካከልበት መንገድ መፈለግ ይኖርበታል።

እንደሌላው የትምህርት ስርአቱ እርከኖች ሁሉ የስርአተ-ትምህርትና የመማሪያ መፃህፍት ብቃት፣ የመምህራን በሚፈለገው መጠንና አይነት ተሟልቶ መገኘት ጉዳይ የትምህርቱን ጥራት ከመጠበቅ አኳያ ወሳኝ ሚና አለው። ይሁንና በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በሌሎች ደረጃዎች የሌለ ተጨማሪ የጥራት መስፈርትም ይኖራል። ዩኒቨርሲቲ የትምህርትና ስልጠና ተቋም ብቻ ሳይሆን ተመራማሪዎችን የሚያፈራ የምርምር ተቋምም ጭምር ነው። ተቋሙ የህብረተሰቡን ልዩ ልዩ ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉ አዳዲስ ሃሳቦችና መፍትሄዎችን የማፍለቅ ተልእኮ አለው። ይህንን ስራ በብቃት መፈፀም ከቻለ በርግጥም ጥራቱ የተጠበቀ ይሆናል። የመፍትሄ ሃሳቦችን የማፍለቅ ተልእኮውን በአግባቡ ከመፈፀም ባሻገር ተማሪዎቹ ትምህርታቸውን ተጨባጭ የምርምር ውጤት ባስገኙ የላቁ ሙያተኞች የሚማሩበትና በምርምሩ ተግባር በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ የሚሳተፉበት ዕድል ስለሚከፍትላቸው የመማር ማስተማሩ ሂደት ጥራትም ይበልጥ የተጠበቀ ይሆናል። ብቃት ያለው የምርምር ስራ በዩኒቨርሲቲዎች መካሄዱ ራሱን የቻለ አላማ ያለው ከመሆኑ በተጨማሪ የትምህርቱን ጥራት ለማስጠበቅም ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል።

ከዚህ አኳያ ሲታይ በዩኒቪርሲቲዎቻችን ከፍተኛ ትርጉም ያለውና ጥራቱ የተጠበቀ የምርምር ጥናት ስራ ይካሄዳል ማለት



አይቻልም። መምህራኑ አስተማሪም ተመራማሪም ናቸው። የመምህራኑ የብቃት ደረጃ ዝቅተኛ መሆን ለመማር ማስተማሩ ሂደት ከሚፈጥረው ችግር ባሻገር ብቃት ያለው ተመራማሪ ሃይል ያላቸው ዩኒቨርሲቲዎች እንዳይሆኑም ያደርጋል።

መንግስትና የግል ባለሃብቶች የሚያስፈልጉዋቸውን የጥናትና ምርምር ስራዎች በዩኒቨርሲቲዎች እንዲካሄዱ ስለማያደርጉም በተቋሞቹ የሚካሄደውን የምርምር ስራ ክፉኛ ጎድቶታል። ለዚህ በምክንያትነት የሚቀርበው ተቋሞቹ ተጨባጭነት ያለውና ችግር ፈቺ የሆነ የጥናትና የምርምር ስራ ለማካሄድ አቅሙ ስለሌላቸው ነው የሚል ነው። በርግጥ ይህ አንድ ምክንያት ቢሆንም ብቸኛ ምክንያት ግን አይደለም። የመንግስትና የግል ባለሀብቶች በነዚህ ተቋሞች የምርምር አቅም የመጠቀም ፍላጎትና አመለካከት ደካማ መሆንም ትልቅ ምክንያት ነው። በመሆኑም በዚህ በኩል ያለው የመንግስትና የግል ባለሃብቶች የተሳሳተ አመለካከት ካልተስተካከለ በስተቀር በተቋሞቹ ውስጥ የሚካሄድ የምርምርና ጥናት ስራ ሊጠናከር አይችልም። መንግስትና ህብረተሰቡ በምርምር አገልግሎት ረገድ ከተቋሞቹ ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅምም አያገኙም።

የምርምር ስራውን አዳክመውታል ተብለው ከሚጠቀሱት ችግሮች አንዱ የፋይናንስ ችግር ነው። በርግጥ የፋይናንስ አጠቃቀምን በማሻሻልና አላስፈላጊ ወጭዎችን በማስወገድ ለምርምር ስራ ሊውል የሚችል መጠነኛም ቢሆን ገንዘብ ማግኘት የሚቻል ነው። መንግስትና የግል ባለሃብቶች ከሚመድቡት

የምርምር ወጭ ውስጥ ዩኒቨርሲቲዎች አገልግሎቱን በመስጠት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ቢደረግ ችግሩን በመጠኑም ቢሆን ሊቀርፍ እንደሚችል መገመት ይቻላል። ይሁንና በአሁኑ ወቅት የፋይናንስ ችግር በተቋሞቹ የሚካሄደውን የምርምር ስራ እንደጎዳው አያጠያይቅም።

ዩኒቨርሲቲዎች መምህራን በምርምር ስራ ላይ እንዲሳተፉ በማበረታታት ረገድ የሚከተሉት አሰራር የተዋጣለት አለመሆኑም በችግርነት ይጠቀሳል። መምህራን በአንዳች አይነት የምርምርና ጥናት ስራ ላይ ተሳትፈው ተጨባጭ ውጤት ማስገኘታቸው በአስተማሪነት ለመቀጠልም እንደቅድመ ሁኔታ መወሰድ የሚገባውና፣ ለቀጣይ እድገታቸውም መሰረታዊ መነሻ መሆን ሲችል ይህ አሰራር በጥብቅ ስራ ላይ አለመዋሉ የምርምር ስራውን እንደጎዳው ያመለከታል። በምርምር ስራ ሊገኝ የሚችለው ገቢ በተመራማሪዎቹና በተቋሞቹ መካከል የሚከፋፈልበት ወጥነት ያለውና የሁሉንም ወገኖች ጥቅም የሚያስጠብቅ ስርአት አለመኖሩም በምክንያትነት ይጠቀሳል።

በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲዎቻችን ይህ ነው የሚባል ጥራቱ የተጠበቀ የምርምርና ጥናት ስራ የማያካሂዱ መሆናቸው ህብረተሰቡን በምርምር ውጤቶቻቸው የመደገፍ መሰረታዊ ተልእኳቸውን ለመፈፀም እንዲሳናቸውና የመማር ማስተማሩ ሂደት ጥራትም ደካማ እንዲሆን አድርጓል። ለዚህ የሚቀርቡ



የተለያዩ ምክንያቶች ያሉ ሲሆን የዩኒቨርሲቲዎቻችንን ጥራትና ውጤታማነት ለማረጋገጥ በዚህም ረገድ ሰፊ ስራ መሰራት አለበት። የመምህራንን ጥራት ለመጠበቅ የሚሰራው ስራ የተቋሞችን የጥናትና ምርምር አቅም ከማጠናከር ጋር በቅርብ የተሳሰረ እንዲሆን መደረግ አለበት። የዩኒቨርሲቲዎቹ አሰራር የምርምርና ጥናት ስራዎችን ለማጠናከር፣ ተመራማሪዎችን የሚያደፋፍርና የሚያነቃ እንዲሆን ተደርጎ መቀረፅ አለበት። የግል ባለሃብቶችና መንግስት የተቋማቱን ፋይናንሳዊ አቅም ለማጠናከር ጥረት ማድረግ አለባቸው። በተለይም መንግስት ከተቋሞቹ ምርምርና ጥናት አቅም መጠናከር ጋር ተያይዞ ለዚሁ ተግባር የሚመድበውን በጀት መጨመርና ከዚሁ በጀት ዩኒቨርሲቲዎቹ በሚፈለገው መጠን ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረግ አለበት።

በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የሚሰጠው ትምህርት አዳዲስ ሃሳቦችን ለማፍለቅ የሚችሉ ከፍተኛ ሙያተኞችን ለማፍራት ተብሎ የሚካሄድ ነው። ስለሆነም በዚህ ደረጃ የሚካሄደው ትምህርት በአስተማሪዎች ድጋፍ በዋነኛነት ደግሞ በራሳቸው በተማሪዎቹ ጥረት የሚፈፀም ነው። የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ወደሚፈለገው ደረጃ ሊደርስ የሚችለው የቤተ-ሙከራዎችና የመሳሰሉት አገልግሎቶች በሚፈለገው መጠን ተሟልተው ሲገኙ ነው። በዚህ ደረጃ ዩኒቨርሲቲዎቻችን ከፍተኛ ችግር ስላለባቸውና የሚሰጡት ትምህርት አጠቃላይ ጥራቱ በጣም ደካማ ስለሆነ ስርአቱ ከሁለተኛ ደረጃ ብዙም ባልተለየ አኳኋን መምህሩ በሚሰራው ስራ ላይ የተንጠለጠለና ችግር ፈቺና ህሳብ አፍላቂ የሆነ የሰው ሃይል

ለመፍጠር የማይችልና ጥራቱ ያልተጠበቀ ሆኖ ይገኛል። ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ማስፋፋት ይህንን ችግር በዝቅተኛ ወጭ በከፍተኛ ደረጃ ለመቅረፍ የሚቻልበት ሁኔታ ቢፈጥርም፣ ይኸው ቴክኖሎጅ በዩኒቨርሲቲዎቻችን በሚፈገለው መጠን ባለመስፋፋቱ ችግሩ ሊቀረፍ አልቻለም።

የዩኒቨርሲቲዎቻችንን የጥራት ደረጃ ለማሻሻል ትኩረት ከሚሰጣቸው ጉዳዮች አንዱ ይኸው የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን እጥረት የመቅረፍ ጉዳይ ነው። ይህን በሚመለከት ተጨማሪ ፋይናንስ የማሟላት ጉዳይ አንድ መሰረታዊ ጉዳይ ሲሆን ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ አጠቃቀምን የማሻሻል ጉዳይም ልዩ ግምት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው። በዚህ ረገድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጀመረው ስራ አበረታች በመሆኑ ተጠናክሮ እንዲቀጥልና ወደሌሎች ዩኒቨርሲቲዎችም እንዲስፋፋ መደረግ አለበት።

በከፍተኛ ትምህርት ደረጃ ጥራትን ለማስጠበቅ የሚካሄድው ስራ የስነ-ዜጋ ትምህርትንና የስራ ስነ-ምግባርና አመለካከት ትምህርትንም ማካተት ይኖርበታል። በርግጥ በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ከዚህ አኳያ የሚሰራው ስራ ብቃቱ የተረጋገጠ ከሆነ ወጣቱ ወደዩኒቨርሲቲ በሚገባበት ወቅት የተስተካከለ ባህሪና አመለካከት ይዞ ስለሚገባ በዚህ ረገድ የሚሰራውን ስራ በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያቀለው አያጠራጥርም። ከዚህ በተጨማሪ ዩኒቨርሲቲ አዳዲስ ሃሳቦች የሚፈልቁበት፣



የተለያዩ ሃሳቦች በሰፊው የሚንሸራሸሩበት ስለሆነና መሆንም ስለሚገባው በዚህ ደረጃ ከስነ-ዜጋና ስነ-ምግባር አኳያ የሚሰጠው ትምህርት ከተቋሙ ባህሪ ጋር የተጣጣመ መሆን ይኖርበታል። እነዚህ ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆነው በከፍተኛ ትምህርት ደረጃ የስነ-ዜጋና የስነ-ምግባር ትምህርት መስጠት የለበትም ማለት አይደለም። ይዘቱና አቀራረቡ ከተቋሙ ባህሪ ጋር እንዲጣጣም ይደረጋል እንጅ መልካም ዜጋን በማፍራት ስራ ላይ የማይሳተፍ የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ሊኖር አይችልም፣ አይገባምም።

በተቋሞቹ የሚሰጡት ትምህርቶች ከአገሪቱ ተጨባጭ ችግሮች፣ ፖሊሲዎችና የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስራዎች ጋር በቅርብ የተሳሰሩ እንዲሆኑ ማድረግ አንዱ መሰረታዊ አቅጣጫ ነው። ትምህርቱ የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት ያደረገ፣ ያሉ ችግሮችን በትክክል ተንትኖ የሚያሳይና የተቀመጡትን የመፍትሄ አቅጣጫዎች የሚያስረዳ ሲሆን፣ ተማሪው በዚህ ላይ ተመስርቶ የራሱን ጥናትና ምርምር ጨምሮ ትክክለኛ የመሰለውን ሃሳብ ሊይዝ ይችላል። በተቋሞቹ የሚካሄዱ የምርምር ስራዎችም በተመሳሳይ መልክ የተቃኙ ሲሆኑ ተማሪው የአገሩን ተጨባጭ ሁኔታ ጠንቅቆ የሚያውቅ አገሪቱን በማልማትና የዴሞክራሲ ስርአትን ለመገንባት የተቀመጡ ፖሊሲዎችን በዝርዝር የሚረዳ፣ በተጨባጭ ጥናትና ምርምር እነዚህን በይበልጥ ተግባራዊ ለማድረግም ሆነ ለመቀየርና ለማሻሻል የሚያስችል ሃሳብ የሚያመነጭ፣ አገሩን የሚያውቅና ለህዝቡ የሚቆረቆር ዜጋ ይሆናል።

በአሁኑ ወቅት በተቋሞቹ ውስጥ ያለው ሁኔታ ከዚህ በእጅጉ የተለየ ነው:: የትምህርት ስርአቱ ከአገሪቱ ሁኔታ ጋር በቅርብ ያልተሳሰረ፣ የአገሪቱን ሁኔታና ፖሊሲዎች የሚያሳውቅ፣ የህዝብን ችግር ለመፍታት በሚያስችል ምርምርና ጥናት ላይ ያልተመሰረተ የትምህርት ስራ ነው የሚሰራው:: በስርአቱ ጥራት መጓደል ምክንያት የተማሪውን የፖለቲካ አመለካከት ብስለት ችግሮችን በመጠቀም የተለያዩ ሃይሎች በወሬ እንዲናጥ ለማድረግ የሚችሉበትን ነው ያለው:: ከዚህም የተነሳ የዴሞክራሲያዊ ባህልና አስተሳሰብ፣ የህዝብ ዴሞክራሲያዊ አንድነትና እኩልነት አመለካከት በከፍተኛ ደረጃ የሚሸረሸሩባቸው ተቋሞች ናቸው:: በመሆኑም የዩኒቨርሲቲውን ጥራት ለመጠበቅ የስነ-ዜጋና የስነ-ምግባር ትምህርት ከተቋሞቹ ባህሪ ጋር ተጣጥሞና ከላይ የተቀመጠውን አቅጣጫ መሰረት አድርጎ በተጠናከረ ሁኔታ ሊሰጥ ይገባል::

ከፍተኛ ትምህርትን በተመለከተ ከፍተኛ የስርጭት ችግር እንዳለብንና ይህንኑ ችግር ለመፍታት እየተከተልነው ያለነው አቅጣጫ ምን እንደሆነ ተዘርዝሯል:: ምንም እንኳ የተቀመጠውን አቅጣጫና ማስፈፀሚያ እቅዶቹን ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ ርብርብና ትኩረት የሚጠይቅ ቢሆንም በከፍተኛ ትምህርት ደረጃ የሚኖርብን ዋነኛ ችግር የመጠንና የስርጭት ችግር እንደማይሆን መገመት ይቻላል:: በዚህ ደረጃ የሚኖርብን ዋነኛ ችግር የጥራት ማረጋገጥ ችግር እንደሆነ ግልፅ ነው:: የጥራቱ



ችግር የተወሳሰበና በአጭር ጊዜ ለማስወገድም የሚከብድ ነው:: በስርአቱ ውስጥ ያለውን ከፍተኛ የጥራት ችግር ካላስወገድን ስርጭቱ ምንም ያህል ቢሻሻል የምንፈልገውን የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራ ለማሳካት የሚያስችለን አይሆንም:: በመሆኑም የከፍተኛ ትምህርት ፕሮግራማችንን በተመለከተ ከምንም ነገር በላይ ትኩረት ሰጥተን ልንረባረብበት የሚገባን ጉዳይ ከላይ የተዘረዘሩትን አቅጣጫዎች መሰረት በማድረግ የስርአቱን ጥራት ለማረጋገጥ ነው::

### 6.3. የከፍተኛ ትምህርት ፋይናንስና አስተዳደር፣

የከፍተኛ ትምህርት ወጭ እጅግ በጣም ከፍተኛ እንደሆነ ይታወቃል:: አንድን ተማሪ በከፍተኛ ትምህርት ለማስተማር በመንግስት በየአመቱ የሚወጣው ወጭ በሺ-ች የሚቆጠሩ የማያንሱ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን ማስተማር ይችላል:: ሰፊው ህዝብ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ባልተዳረሰለት አገር ይህን በሚያህል ወጭ የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎችን በነፃ ማስተማር ከፍትሃዊነት አኳያ ሲታይ እጅግ በጣም አጠያያቂ ነው:: የከፍተኛ ትምህርት ምሩቃን ትምህርታቸውን ሲጨርሱ የሚያገኙት ገቢ ከህብረተሰቡ አጠቃላይ ገቢ ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ሊባል የሚችል መሆኑ ተማሪውን በነፃ ማስተማርን ኢ-ፍትሃዊ የሚያደርገው ሁለተኛ ምክንያት ነው:: መንግስት ከዚህ በመነሳት ተማሪው የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ወጭን መጋራት እንዳለበት የፖሊሲ ውሳኔ ወስኗል:: ፖሊሲው ፍትሃዊና ትክክለኛም ነው::

ይሁንና የፖሊሲው አፈፃፀም የአገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል:: ተማሪው የከፍተኛ ትምህርት ወጭውን በጠቅላላ ይሸፍን ቢባል ተማሪው ከተመረቀም በኋላ ለመክፈል በጣም የሚቸግረው ዕዳ ለመሸከም ይገደዳል:: ስለሆነም ያለው አማራጭ ተማሪው ወጭውን በሙሉ እንዲሸፍን ሳይሆን ከወጭው ውስጥ የተወሰነውን ክፍል ብቻ እንዲሸፍንና ወጭውን ከመንግስት ጋር እንዲጋራ ማድረግ ነው:: መንግስት በከፍተኛ ትምህርት ደረጃ የሙሉ ክፍያ ፖሊሲ ሳይሆን የወጭ መጋራት ፖሊሲን የመረጠው ለዚህ ነው::

የአከፋፈሉ ስርአት ተማሪው በገንዘብ እጦት ምክንያት ብቻ ሳይማር እንዳይቀር ለመከላከል የሚያስችል መሆን አለበት:: ይህንን ለማስፈፀም ይረዳል ተብሎ የሚቀርበው አንዱ አማራጭ ገንዘብ ያላቸው የወጭ መጋራት ክፍያውን ከፍለው እንዲማሩ፣ ገንዘብ የሌላቸው ደግሞ በብድር መልክ መንግስት የወጭ መጋራቱን ክፍያ ከፍሎላቸው ተመርቀው ስራ ከያዙ በኋላ ብድሩን በተራዘመ ጊዜ እንዲከፍሉ ማድረግ ነው:: ይህ አሰራር ገንዘብ የሌለው ተማሪም እንዲማር የሚያስችል ቢሆንም የብድር አሰባሰቡ ስርአት እንኳንስና በኛ አገር በበለፀጉ አገሮችም አስቸጋሪ ስለሚሆን ተመራጭ አይደለም:: ሌላው አማራጭ ከፍለው ለመማር የማይችሉ ወይም የማይፈልጉ ተማሪዎች የወጭ መጋራት ክፍያውን ሳይከፍሉ እንዲማሩ ከተደረገ በኋላ ተመርቀው ስራ ሲይዙ የከፍተኛ ትምህርት ምሩቃን ግብር ተጥሎ ከደሞዛቸው እየተቆረጠ እንዲከፈል በማድረግ፣ ይህም የወጭ መጋራቱ ክፍያ



እስኪጠናቀቅ የሚቀጥል እንዲሆን ማድረግ ነው:: ይህ አሰራር ማንም ሰው በገንዘብ እጦት ምክንያት ሳይማር እንዳይቀር የሚከላከል፣ ስራ ያላገኘ ምሩቅ በዕዳ እንዳይቸገር የሚከላከልና ከሌሎች አገሮች ልምድም እንደታየው ለአሰባሰቡ የቀለለ ነው:: ስለሆነም ተመራጭ ስልት ተደርጎ የተወሰደውና ተግባራዊ ለማድረግ የዝግጅት ማጠናቀቅያ ስራ እየተሰራበት ያለው ስልት ይኸው ነው::

ምንም እንኳ የወጭ መጋራቱን ፖሊሲ ተግባራዊ ማድረግ የከፍተኛ ትምህርትን የፋይናንስ ችግር ለማቃለል የሚረዳ በመሆኑ ተግባራዊ ማድረጉ አማራጭ ባይኖረውም በዚሁ መልክ በጣም ውሱን የሆነውን የወጭውን ክፍል ብቻ ነው መሸፈን የሚቻለው:: ስለሆነም የከፍተኛ ትምህርት ፋይናንስ ችግርን ለመፍታት ሌሎች ተጨማሪ መፍትሄዎች መፈለግ አለባቸው:: የሌሎች አገሮች ልምድ እንደሚያመለክተው ዩኒቨርሲቲዎች የራሳቸውን ወጭ በመሸፈን ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረግ ይችላሉ:: ለምሳሌ በአሜሪካን አገር መሬት ተሰጥቷቸው ከመሬቱ በሚያገኙት ገቢ እንዲተዳደሩ ተደርገው የተቋቋሙና በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ታዋቂነት ያተረፉ ዩኒቨርሲቲዎች እንዳሉ ይታወቃል:: በየክልሉ ያሉ ዩኒቨርሲቲዎች በዚሁ መልክ በደን ልማት መልክም ሆነ በሌላ አኳኋን አልምተው የሚጠቀሙበት መሬት ሊሰጣቸው ይቻላል:: ይህ አሰራር በቀላሉ ሊፈፀም የሚችል ሆኖ ሳለ እስካሁን ድረስ ያልተሞከረና በሰፊው ተግባራዊ ሊሆን የሚገባው አሰራር ነው::

ዩኒቨርሲቲዎች ከመደበኛ የትምህርት ፕሮግራማቸው በተጨማሪ የማታ፣ የክረምትና የመላላክ ትምህርት ፕሮግራሞችን በማዘጋጀትና በክፍያ እንዲሰጥ በማድረግ ወጭያቸውን ለመሸፈን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ፡፡ መንግስትና የግል ባለሃብቶች ጥናትና ምርምር እንዲካሄድባቸው በሚፈልጉዋቸው ስራዎች ላይ ክፍያ እያስከፈሉ በመስማራት ገቢ ሊያሰባስቡ ይችላሉ፡፡ መፃህፍት በማሳተምና በሌሎች ተግባሮችም ገቢ መሰብሰብ ይችላሉ፡፡ በየክልሉ ያሉ ዩኒቨርሲቲዎች በእንደዚህ አይነቶቹ ተግባራት በሰፊው ቢሰማሩ በአንድ በኩል ገቢያቸውን በማጠናከር ራሳቸውን ይጠቅማሉ፣ የመንግስትን የፋይናንስ ችግርም ያቃልላሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ክልሎች በክፍያም ቢሆን የትምህርትና ስልጠና፣ የምርምርና ጥናት ስራ የሚሰራላቸው ብቃት ያለው ሃይል አግኝተው ይጠቀማሉ፡፡

ምንም ያህል ገንዘብ ቢሰበሰብ ቆጣቢና ውጤታማ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ካልዋለ ዞሮ ዞሮ ቀዳዳ በርሜልን ከመሙላት የተለየ አይሆንም፡፡ በዚህ ረገድ በዩኒቨርሲቲዎች መካከል አንድ አይነት ትምህርት ለማስተማር የሚወጣው መደበኛ ወጭ በጣም ይለያያል፡፡ የአንዳንዶቹ ከሌሎች ከእጥፍ በላይ የሚሆንበት ሁኔታ አለ፡፡ ለዚሁ ዋነኛው ምክንያት አንዳንዶቹ እጅግ በጣም ሰፊ የአስተዳደርና አገልግሎት መዋቅር ዘርግተው ወጭያቸውን በከፍተኛ ደረጃ ስለሚያንሩና ቆጣቢ የሆነ የገንዘብ አወጣጥ ስርአት ስለሚጎድላቸው ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ተማሪው ከወጭው ይህን ያህል በመቶ ተጋራ ቢባል በፋይናንስ አስተዳደር ድክመት



ምክንያት የናረውን ወጭ ተሸከም ማለት ሆናል፡፡ ይህ በመንግስትም በተማሪዎችም ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም፡፡ ስለሆነም እያንዳንዱ ዩኒቨርሲቲ የወጭ አርእስቶቹን እንደገና መርምሮ የመማር ማስተማሩን ሂደት ሳይነካ ወጭዎችን ለመቀነስ የሚያስችለው እቅድ ሊያወጣና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ መንግስትም ከዚህ አኳያ አንድ መስፈርት አስቀምጦ በልዩ ልዩ ስልቶች በመታገዝ ሁሉም ወደተፈለገው ደረጃ እንዲደርሱ ማድረግ አለበት፡፡

ዩኒቨርሲቲዎች ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ገንዘብ የሚያንቀሳቅሱ ተቋሞች ናቸው፡፡ በጀታቸውን በብቃት ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር እጅግ የተጠናከረና ዘመናዊ የፋይናንስ አስተዳደር ስርአት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲዎች አሰራራቸውን ቀይረው ከፍተኛ ገቢ የማሰባሰብ ሰራ መስራት የሚጠበቅባቸው ድርጅቶች ናቸው፡፡ አገልግሎታቸውን ለተጠቃሚ በመሸጥ፣ ንብረታቸውን በማንቀሳቀስ ከፍተኛ ገንዘብ ማሰባሰብ የሚችሉና የሚገባቸው ተቋሞች ናቸው፡፡ ከዚህ አኳያ ከአገልግሎት አቅራቢ ኩባንያ ጋር የሚያመሳስላቸው ባህሪም ይኖራቸዋል፡፡ ይህ ስራ ሙያተኛን የሚጠይቅ የሙሉ ጊዜ ስራ እንጅ በተደራቢነት ሊከናወን የሚችል አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት ዩኒቨርሲቱዎች ጠንካራ የገቢ ማፈላለግና ማሰባሰብ ስርአት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

የወጭ መጋራት ስርአቱና፣ በዩኒቨርስቲዎች በራሳቸው

የሚካሄድ የገቢ ማሰባሰብ ስርአት በከፍተኛ ደረጃ ከተጠናከረ፣ ዩኒቨርሲዎች ስራቸውን ቆጣቢ በሆነ መንገድ ከሰሩ በሂደት የዩኒቨርሲቲዎች የመደበኛ ወጭ ከነዚህ ከሁለት ምንጮች ሊሸፈን ይችላል:: መንግስት የካፒታል ውጭውን በመሸፈን ሊያተኩር ይችላል:: ይህ በከፍተኛ ትምህርት ደረጃ የመንግስትን የፋይናንስ ጫና በመቀነስ ረገድ መከናወን አለበት ተብሎ ከሚታመነውና በብዙ አገሮች ተግባራዊ ከሆነው ጋር ሲያያዝ የመንግስትን የፋይናንስ ችግር በበቂ ደረጃ የማያቃልል ቢሆንም አሁን ካለንበት መንግስት መደበኛውንም የካፒታል ወጭውን ከሞላ ጎደል ሙሉ በሙሉ ከሚሸፍንበት አሰራር በጣም የተሻለ ይሆናል::

የግል ባለሀብቶች የከፍተኛ ትምህርት ወጭን በመሸፈንም ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማበርከት ይችላሉ:: በመጀመሪያ ደረጃ በክፍያ የዩኒቨርሲቲዎችን የጥናትና ምርምር አቅም ቢጠቀሙ ራሳቸውን ጠቅመው ዩኒቨርሲቲዎችን ይጠቅማሉ:: ከዚህ ባሻገር በሰለጠኑት አገሮች እንደሚታየው የግል ባለሃብቶች ለመረጡዋቸው ወይም ለተማሩባቸው ትምህርት ቤቶች የተለያዩ የገንዘብና የማቴሪያል ስጦታ፣ የነፃ ትምህርት ዕድል ወዘተ. ሊሰጡ ይችላሉ:: ከዚያም ባሻገር በአገራችን በተግባር በመታየት ላይ እንዳለው ዩኒቨርስቲዎችን አቋቁመው ከፍሎ ለመማር የሚችለውንና የሚፈልገውን በክፍያ ማስተማር ይችላሉ:: መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም በተመሳሳይ መልኩ ዩኒቨርሲቲዎችንና ሌሎች የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞችን መመስረት ይችላሉ:: መንግስት እነዚህ ወገኖች የከፍተኛ



ትምህርትን ለማስፋፋትና በመንግስት ላይ የሚያስከትለውን የፋይናንስ ጫና ለመቀነስ የሚጫወቱትን ሚና ግምት ውስጥ በማስገባት ሊያበረታታቸው ይገባል::

ዩኒቨርሲቲዎች በብዙ ሺ የሚቆጠር ተማሪ አስተማሪና ሰራተኛ የያዙ፣ በብዙ ሚሊዮኖች የሚመነት ገንዘብ በየአመቱ የሚያንቀሳቅሱ ከፍተኛ ጥናትና ምርምር የሚካሄድባቸው ተቋሞች ስለሆኑ የራሳቸውን የውስጥ ጉዳይ በራሳቸው የሚወስኑበት ስልጣን ሊኖራቸው ይገባል:: በአገራችን በዚህ ረገድ ሁለት ችግሮች ይታያሉ:: በአንድ በኩል መንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የራሳቸው ቻርተር ኖሯቸው የሚተዳደሩበት ስርአት በመፍጠር ረገድ መወሰድ የሚገባቸውን ርምጃዎች ሳይወስድ ቀርቷል:: በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ የዩኒቨርስቲ ማህበረተሰብ አባላት በመንግስትና ህዝብ ገንዘብ የሚንቀሳቀሱ ዩኒቨርሲቲዎች ለመንግስትና ህዝብ አንዳችም አይነት ተጠሪነት ሳይኖራቸው እንዳሻቸው ሊሆኑ እንደሚችሉ አድርገው ይቆጥራሉ::

እነዚህ ሁለት አመለካከቶች የተሳሳቱ በመሆናቸው በአፋጣኝ መስተካከል ይኖርባቸዋል:: በአንድ በኩል መንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የራሳቸውን የውስጥ ጉዳይ በራሳቸው የሚወስኑበትና የአካዳሚ ነፃነታቸው የሚረጋገጥበት ሁኔታ ለመፍጠር የዩኒቨርሲቲዎች ቻርተሮች እንዲፀድቁና ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ አለበት:: በሌላ በኩል በህዝብ ገንዘብ

የሚተዳደሩ ተቋሞች እንደመሆናቸው መጠን፣ ይህ ገንዘብ ለህክምና፣ ለመንገድ ስራ ወዘተ. ሊውል ሲችል ልማቱን በይበልጥ የሚፋጥንልኝ የከፍተኛ ትምህርት ነው ብሎ ህዝቡ ካለችው ውሱን ገቢ ቆንጥሮ በመደበው ገንዘብ የሚተዳደሩ ተቋሞች በመሆናቸው ለህዝቡ ብቃት ያለው አገልግሎት እያቀረቡ መሆናቸው፣ የሚፈለገውን የሰው ሃይል በሚፈለገው አይነት እያፈሩ፣ የሚፈለገውን የጥናትና ምርምር ስራ እየሰሩ መሆን አለመሆናቸውን በተመለከተ ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል፡፡ ከዚያ ውጭ ሆነው ሲገኙም በቂ የማስተካከያ ርምጃ የሚወሰድበት ስርአት መኖር ይገባዋል፡፡ የውስጥ ነፃነትን ከህዝብና መንግስት ተጠሪነት ጋር ያጣጠመ የአስተዳደር ስርአት ሊፈጠር ይገባል፡፡ ይህ አሰራር በብዙ አገሮች የተለመደ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከሌሎች ልምድም በመማር በአፋጣኝ ተግባራዊ መሆን ይችላል፡፡

በዩኒቨርስቲው የተቋሙ መሪዎች፣ ተማሪዎችና መምህራን በብቃት የሚሳተፉበት የአመራር ስርአት መፍጠር ይቻላል፡፡ እነዚህ በአመራሩ ላይ ተሳታፊ የሚሆኑ አካላት ሃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲውን፣ የተቋሙን ችግሮችና ችግሮቹን ለመፍታት የተቀመጡ መሰረታዊ አቅጣጫዎችን በሚገባ እንዲያውቋቸውና እንዲያምኑባቸው ሊደረግ ይገባል፡፡ የአመራር አካላቱ በአንድ በኩል የዩኒቨርስቲዎችን ማህበረሰብ አባላት መብትና ጥቅም ለማስከበር፣ በሌላ በኩል ደግሞ ተቋሞቹ የተቋቋሙበት



የትምህርትና ምርምር መሰረታዊ አላማ የሚሳካበት፣ ሁኔታ የመፍጠር ግዴታ እንዳለባቸው የሚያውቁና ግዴታቸውን በአግባቡ መወጣት ሲያቅታቸው የሚተኩ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ለዩኒቨርሲቲዎች አጠቃላይ አመራር የሚሰጡ የበላይ አካላት እንዲኖሩና በነዚህ አካላት ውስጥ የመንግሰት ተወካዮች በብቃት እንዲሳተፉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በየክልሉ የተቋቋሙት የኒቨርሲቲዎች ከአካባቢው ህዝብና የመንግስት አካላት በቂ ውክልና ያሏቸው የበላይ አካላት ሊቋቋሙላቸው ይገባል፡፡

ፌዴራል መንግስት ለተቋቋሙትና በመቋቋም ላይ ላሉት ዩኒቨርሲቲዎች አጠቃላይ አመራር መስጠት አለበት፡፡ የከፍተኛ ትምህርት የጥራት ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የዩኒቨርሲቲዎችን የጥራት ሁኔታ በየጊዜው የሚከታተልና የሚገመግም የመፍትሄ ሃሳቦችን የሚያመነጭ አቅም ሊፈጠርና በዚህ ደረጃም አመራር ሊሰጥ ይገባል፡፡ የአገራችንን የከፍተኛ ትምህርት እንቅስቃሴ እየተከታተለ መሰረታዊ የእድገት አቅጣጫዎችን የሚቀይስ አቅም ሊኖር ይገባል፡፡ በአጠቃላይ የከፍተኛ ትምህርት ስትራተጅያዊ አመራር ሊፈጠርና ስራውን በብቃት ሊፈፅም ይገባል፡፡

# ክፍል ሦስት

# የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራምና ሌሎች የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች

## 1. መግቢያ

የማስፈፀም አቅም ለመገንባት የሰው ሃይልን በሚፈለገው መጠንና አይነት ማሰልጠን ያስፈልጋል፡፡ የትምህርትና ስልጠና ስርአቱ ይህን መሰረታዊ ተልእኮ በማሟላት በማስፈፀም አቅም ግንባታ እንቅስቃሴያችን ውስጥ የላቀ ሚና ይጫወታል፡፡ ይሁንና የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራዎች በትምህርትና ስልጠና ብቻ የሚፈፀሙ አይደሉም፡፡ የማስፈፀም አቅም የሚፈጠረው በሰለጠነ የሰው ሃይል ላይ ብቃት ያለው አሰራርና አደረጃጀት ሲጨመርበት ነው፡፡ ለዚህም ነው የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራችን በተቋሞች ዙሪያ፣ ተቋሞችን በመፍጠርና በማሻሻል ዙሪያ መፈፀም ያለበት ነው የምንለው፡፡ ለዚህ ነው ከትምህርትና ስልጠና ፕሮግራማችን ጎን ለጎን ተቋሞችን በመፍጠር ወይ በማሻሻል ዙሪያ በጣም ሰፊ የአቅም ግንባታ ስራ እየተካሄደ ያለውና መካሄድም ያለበት፡፡



የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራውን አንድን ተጨባጭ ተቋም በመፍጠር ወይ በማሻሻል ዙሪያ ስንፈፅመው የሰለጠነ የሰው ሃይልን ብቃት ካለው አሰራርና አደረጃጀት ጋር በማስተሳሰር የልማትና የዴሞክራሲ ግንባታ እቅዳችንን ከዳር ለማድረስ የሚችል አንድ ተጨባጭ ሃይል እንፈጥራለን፡፡ ይህ አሰራር ስልጠናው በተጨባጭ ልምድ እንዲዳብር በማድረግ ውጤታማነቱን ያሻሽለዋል፡፡ ከስልጠናና ትምህርት ተቋም የወጣው ሰው ብቃት ያለው አደረጃጀትና አሰራር ወዳለው ተቋም በሚገባበት ወቅት በዕለት-ተዕለት ስራው ሂደት በአፋጣኝ ልምድ እያካበተ፣ እውቀቱን በራሱ ጥረትና በተቋሙ ውስጥ በሚሰጠው ቀጣይ ትምህርትና ስልጠና እያሻሻለ ይሄዳል፡፡ በሌላ አነጋገር በትምህርትና ስልጠና ስርአቱ የተፈጠረው የስራ ችሎታ ይበልጥ እየተጠናከረና እየበሰለ ይሄዳል፡፡ የሰለጠነው ሰው በእንደዚህ አይነቱ ብቃት ያለው ተቋም ካልተመደበ ግን እንኳንስ ተጨማሪ እውቀትና ክህሎት ሊያገኝ፣ የነበረውንም የሚረሳበትና የሚያጣበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ስለሆነም የማስፈፀም አቅም ግንባታው ስራ በተቋሞች ዙሪያ በሚፈፀምበት ወቅት የሰለጠነውን የሰው ሃይል አንድ ተጨባጭ የለውጥ ሃይል እንዲሆን ከማስቻሉም በላይ የስልጠናና ትምህርት ተግባሩ በሌላ መልክ ቀጥሎ የሰው ሃይሉን በቀጣይነት በተሻለ ለማብቃት የሚያስችል ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራው በተቋሞች ዙሪያ ሊፈፀም የሚችለው በአንድ በኩል የሰለጠነ የሰው ሃይል የሚያፈራ

ብቃት ያለው የትምህርትና ስልጠና ስርአት ሲኖር በሌላ በኩል ደግሞ አደረጃጀትና አሰራሮችን በማሻሻል ስራ ላይ የሚሳተፍ፣ የምርምርና የምክር አገልግሎት የሚሰጥ ስርአት ሲኖር ነው:: ዩኒቨርሲቲዎች የምርምርና የምክር አገልግሎት ለመንግስት፣ ለህዝብና ለግል ባለሃብቶች መስጠት እንዳለባቸው፣ አጠቃላይ ቅኝታቸው ከዕለት-ተለት የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ እንቅስቃሴ የተነጠለ የትምህርት ገዳም መፍጠር ሳይሆን በግንባታው ሂደት የሚፈጠሩ ችግሮችን የመፍታትና ለሁሉም የልማት ሃይሎች ብቃት ያለው የምክርና የምርምር አገልግሎት በመስጠት ላይ ያተኮረ መሆን እንዳለበት፣ ይህንን የማድረግ አቅምም መገንባት እንዳለባቸው ተቀምጧል:: በዚህ ደረጃ ዩኒቨርሲቲዎቻችን መሆን በሚገባቸው ደረጃ ላይ የሚገኙ ስላልሆኑ በአጭር ጊዜ ውስጥ የምክርና የምርምር አገልግሎት ፍላጎታችንን በብቃት ሊያሟሉ የሚችሉ አይደሉም::

የምክርና የምርምር አገልግሎት በዩኒቨርሲቲዎች በሰፊው መካሄድ ያለበት ቢሆንም፣ በዚህ ብቻ የታጠረ ሊሆን አይችልም:: የተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ይህንን ስራ የመስራት አቅም ሊኖራቸው ይገባል:: የተለያዩ የምክርና ምርምር አገልግሎት የሚሰጡ የግል ተቋሞችም መደራጀት ይኖርባቸዋል:: ይሁንና እነኚህ ተቋሞችም በአሁኑ ወቅት በሚፈለገው ደረጃ ላይ የሚገኙ ስላልሆኑ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራችን ከነዚህ በሚገኘው አገልግሎት ላይ ብቻ ሊታጠር የሚችል አይሆንም:: እነዚህን የአገር ውስጥ የምክርና የምርምር ተቋሞች በአፋጣኝ ለማጠናከር የምንችለውን ያህል እየተረባረብን፣ ማበርከት



የሚችሉትን አስተዋፅኦ አሟጠን እየተጠቀምን ለጊዜው የውጭ ተቋሞችና ግለሰቦችን የምክር አገልግሎት በሰፊው ከመጠቀም ውጭ አማራጭ የለንም:: ከዚህም አኳያ ዋናው ጉዳይ ከውጭ የምናገኘውን የምክርና የልምድ ልውውጥ አገልግሎት በላቀ ደረጃ ተጠቅመን የማስፈፀም አቅማችንን በአፋጣኝ ማሻሻል፣ የምክርና ምርምር አቅማችንንም ከዚሁ ጎን ለጎን ማጠናከር ነው::

በመሆኑም በአሁኑ ወቅት በተቋሞች ዙሪያ የሚፈፀመውን ዋነኛ የአቅም ግንባታ ስራ በዋናነት በራሳችን የትምህርትና ስልጠና ስርአት የሰለጠነውን የሰው ሃይልና፣ የራሳችንን የምርምርና የምክር አቅምም እያጠናከርንና አሟጠን እየተጠቀምን በቁልፍ ጉዳዮችና የራሳችን አቅም ተሟልቶ በማይገኝበት ላይ ግን በዋነኛነት የውጭ አማካሪዎችንና ሙያተኞችን ተፈላጊ ሆኖ በተገኘው መጠን እየተጠቀምን የምናስፈፀመው ይሆናል::

የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራችን በሁሉም የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ እንቅስቃሴያችን ውስጥ ተካቶ የሚፈፀም ነው:: እያንዳንዱ የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስራ፣ ስራውን ለመፈፀም የሚያስችሉ ተቋሞችን የመፍጠር ወይም የማሻሻልን ስራ እንደዋና ተግባሩ አድርጎ በመውሰድ፣ የማስፈፀም አቅምን በተቋሞች ዙሪያ በማጎልበት ብቻ ነው በተሳካ ሁኔታ ሊፈፀም የሚችለው:: የእያንዳንዱ የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ እንቅስቃሴ ማዕከል የማስፈፀም አቅም ማጎልበት እንደሆነም በተደጋጋሚ የተገለፀ ጉዳይ ነው:: ስለሆነም በተቋሞች ዙሪያ የሚካሄደውን የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራ በዚህ ፅሁፍ

ውስጥ ለመዘርዘር ቢሞከር ሁሉንም የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስራዎች መዘርዘር የሚያስከትል ይሆናል፡፡ በመሆኑም በዚህ ክፍል ውስጥ የሚቀርቡት በምሳሌነት ሊወሰዱ የሚችሉትና በሌሎች ፅሁፎች ያልተዘረዘሩት ወይም የማይዘረዘሩት ብቻ ናቸው፡፡ በዚሁ መልክ በምሳሌነት ሊቀርቡ ከሚችሉት የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራዎች ዋነኛው የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ነው፡፡

**2. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም መሰረታዊ አላማዎች፣**

ሁሉም መንግስታት ይብዛም ይነስም በሌላ ማንኛውም አካል ሊከናወን የማይችል የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የፖለቲካ አገልግሎት ያቀርባሉ፡፡ ይህንን ተኪ የሌለውን ስራ ለማስፈፀም የሚችሉት ይህንኑ ለማድረግ የሚችል ብቃት ያለው ሲቪል ሰርቪስ በመፍጠር ነው፡፡ የመንግስት መሰረታዊ ተልዕኮዎች ማስፈፀሚያ ቁልፍ መሳሪያ ሲቪል ሰርቪሱ መሆኑን ተገንዝበው ለዘመናት ባለማቋረጥ ሲቪል ሰርቪሳቸውን ይገነባሉ፣ ያሻሽላሉ፡፡ የዳበረ ዴሞክራሲያዊ ስርአትና ኢኮኖሚ ያላቸው፣ ስለሆነም መንግስት በዚህ ረገድ የሚጫወተው ሚና ይህን ያህል ከፍተኛ ባልሆነባቸው አገሮችም ቢሆን ብቃት ያለው ሲቪል ሰርቪስ ሳይፈጥር ተኪ የሌለውን ተልዕኮውን ለመፈፀም የሚችል መንግስት የለም፡፡

በኛ አገር ሁኔታ መንግስት ያለው ተልእኮ አስቀድሞ የዳበረና ስር የሰደደን የዴሞክራሲ ስርአት የማስቀጠልና የመጠበቅ



ተልእኮ አይደለም፡፡ በኛ ሁኔታ መንግስት እንደዚህ አይነቱን ስርአት የመፍጠር፣ በአገራችን ለዘመናት ተንሰራፍቶ የቆየውን ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አገዛዝና ባህል በዴሞክራሲያዊ ባህልና አስተዳደር የመተካት እጅግ ወሳኝና ውስብስብ የሆነ ተልዕኮ ነው ያለው፡፡ መንግስት በኛ አገር ሁኔታ የበለፀገ ኢኮኖሚን የመንከባከብ ተልእኮ አይደለም ያለው፡፡ በልማት ከአለም አገሮች ሁሉ የመጨረሻ ከሚባሉት አንዷ የሆነችውን አገራችንን ከድህነትና ኋላቀርነት አላቆ የበለፀገች አገር እንድትሆን የማድረግ እጅግ ውስብስብና ከባድ የሆነ ተልእኮ ነው የተሸከመው፡፡ የኛ ሲቪል ሰርቪስ አስቀድሞ የተገነባን የዴሞክራሲ ስርአት፣ አስቀድሞ የነበረን የዳበረ ኢኮኖሚና ዴሞክራሲያዊ ስርአት የመንከባከብና የማስቀጠል ስራ ሳይሆን ይህንኑ ስርአት የመፍጠር ተልዕኮ ያለው ነው፡፡ አስቀድሞ የተገነባን ስርአት ለማስቀጠልና ለመንከባከብ ከፍተኛ ብቃት ያለው ሲቪል ሰርቪስ እንደሚያስፈልግ አምነው የዳበሩት አገሮች ሲቪል ሰርቪሳቸውን ለማሻሻል ሌት-ተቀን ይጣጣራሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት አዲስ ስርአት የመገንባት ተልዕኮ የተሸከመው መንግስት ይህን እጅግ አስቸጋሪና ውስብስብ የሆነውን ተልዕኮ ለመፈፀም በዳበሩ አገሮችም ከሚሰራው የላቀ ትኩረት የሚሰጠው የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም መንደፍና ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባው ለመገንዘብ የሚያዳግት አይሆንም፡፡ በያዝነው የአገር ልማትና ግንባታ ስራ ላይ መንግስት የላቀ የአመራር ሚና አለው፡፡ ይህንኑ ለማሳካት መንግስት እጅግ ከፍተኛ ብቃት ያለው የማስፈፀም አቅም ያስፈልገዋል፡፡ የመንግስት ዋነኛ የማስፈፀም አቅም ሲቪል ሰርቪሱ ነው፡፡ ስለሆነም ሲቪል ሰርቪሱን የማብቃትና የማሻሻል ስራ

መንግስት ተልእኮውን እንዲፈፅም ከማስቻልና ያስቀመጥናቸውን የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስራዎች ከማሳካት አኳያ ቁልፍ ሚና ያለው ስራ ይሆናል።

**2.1. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራምና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ አላማችን፣**

የሲቪል ሰርቪሳችንን የምናሻሽለውና የምንገነባው ያስቀመጥናቸውን የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ እቅዶች ለማስፈፀም የሚያስችለን ብቃት ያለው መሳሪያ ለማግኘት ነው። በመሆኑም ግንባታው ላስቀመጥነው ግብ የሚመጥን፣ ግባችንን ሊያሳካ የሚያስችል ባህሪና ይዘት ያለው ሲቪል ሰርቪስ ለመፍጠር የሚያስችለን መሆን አለበት። በዚህ መሰረት ለምሳሌ እኛ የምንሰራው የዴሞክራሲ ስርአትን፣ ፌዴራላዊ የሆነና በህዝብ ሁለገብና የነቃ ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ የዴሞክራሲ ስርአትን ለመገንባት ነው። ሲቪል ሰርቪሳችንም ለዚሁ አላማ አገልጋይ የሆነ፣ ይህንኑ ስርአት ለመገንባት የሚያስችለን ብቃት ያለው መሆን አለበት። ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አገዛዝን ለማገልገል የተቀረፀ ሲቪል ሰርቪስ ምንም ለውጥ ሳይደረግበት ዴሞክራሲያዊ ስርአትን የሚያገለግል ሊሆን አይችልምና።

በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ የአገሪቱ ፖሊሲዎችና መሰረታዊ አቅጣጫዎች የሚወሰኑትና መወሰንም ያለባቸው በህዝቡና በህዝቡ በተመረጡ ወኪሎች ነው። ህዝቡ የተለያዩ ሃይሎች ከሚያቀርቧቸው አማራጭ አቅጣጫዎችና ፖሊሲዎች



ይጠቅመኛል የሚለውን ይመርጣል። ይህንን ፖሊሲና አቅጣጫ የሚከተለውን ድርጅት መርጦ ለስልጣን ያበቃል። የህዝቡን ይሁንታና ድጋፍ ያገኘው ይኸው ፖሊሲ የአገሪቱ መመሪያ ሆኖ ያገለግላል፣ በሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ተፈፃሚ ይሆናል። ሰዎች ይህንን የብዙሃኑን ውሳኔ ሂስ የማድረግ፣ የመቃወም መብት አላቸው። በዴሞክራሲያዊ አኳኋን እንዲቀየር የመታገል መብትም አላቸው። የብዙሃኑን ምርጫና ውሳኔ ተግባራዊ እንዳይሆን የማሰናከልና የማደናቀፍ መብት ግን የላቸውም። ይህ የብዙሃኑን የዴሞክራሲ መብት የሚጋፋ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ተግባር ይሆናል።

ስለሆነም በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ ሲቪል ሰርቪሱ ፖሊሲ አውጪ አካል አይደለም፣ ሊሆንም አይገባውም። በህዝቡና በህዝቡ ቀጥተኛ ተወካዮች የወጡትንና የብዙሃኑን ድጋፍ አግኝተው የተቀረፁትን ፖሊሲዎች የማስፈፀም ተልእኮ ነው ያለው። የሲቪል ሰርቪሱ አባላት ፖሊሲውን ሊያምኑበት ወይም ላያምኑበት ይችላሉ። የብዙሃኑ ድጋፍ ያለውን ፖሊሲ አፈፃፀም ሊያደናቅፉ ግን አይችሉም። ይህ ፍፁም ፀረ-ዴሞክራሲ ተግባር ይሆናልና። ግፋ ቢል ፖሊሲው አገሪቱን ለጥፋት ይዳርጋል ብለው ካመኑ ራሳቸውን ከሲቪል ሰርቪሱ ማግለልና ስራቸውን መልቀቅ ይችላሉ እንጅ የብዙሃኑን ውሳኔ ለማስፈፀም ተብሎ በተቋቋመ ሲቪል ሰርቪስ ውስጥ ሆነው ሊያሰናክሉት፣ ሊያደናቅፉት አይችሉም። የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ እንደዚህ አይነት እምነትና አመለካከት ያለው ሲቪል ሰርቪስ ይጠይቃል። የመንግስትን ፖሊሲ ለማስፈፀም ባለው አቅም ሁሉ የሚጣጣር፣ የመጀመሪያም

የመጨረሻም መመዘኛው የመንግስትን ፖሊሲ ምን ያህል በብቃት ማስፈፀሙ እንደሆነ ተገንዝቦ የሚረባረብ ሲቪል ሰርቪል ያስፈልጋል፡፡

ሲቪል ሰርቪሱ የፖሊሲ አስፈፃሚ እንጂ ፖሊሲ አውጪ አይደለም ሲባል በፖሊሲ አወጣጥ ሂደት ውስጥ ምንም ሚና አይጫወትም ማለት አይደለም፡፡ የሚያስፈፅማቸውን ፖሊሲዎች ገምግሞ፣ ለወደፊት ሊሻሻሉ የሚገባቸውን ነጥቦች የመጠቆምና አማራጭ የፖሊሲ ሃሳቦችን በህዝብ ለተመረጡት የፖለቲካ ሃላፊዎች የማቅረብ መብትና ግዴታ አለው፡፡ የፖለቲካ ሃላፊዎቹ ይህንን ምክር ግምት ውስጥ አስገብተው፣ የሚቀበሉትን ተቀብለው፣ የሚሻሻሉትን አሻሽለው፣ ራሳቸው የሚያመጡትንም አካተው ፖሊሲውን የዴሞክራሲ ስርአቱ በሚያዘው መሰረት ይቀርፃሉ፡፡ በዚሁ መልክ ሲቪል ሰርቪሱ ፖሊሲን ከማስፈፀም ዋና ተልእኮው ጎን ለጎን በፖሊሲ ቀረፃ ሂደት ሙያዊ ድጋፍና ምክር በመስጠት ተሳታፊ ይሆናል፣ መሆንም ይገባዋል፡፡

ሲቪል ሰርቪሱ በፖሊሲ አስፈፃሚነቱ የተቀረፀውን ፖሊሲ ገንዘብና ጊዜን በሚቆጥብ የላቀ ውጤታማነት ባለው አኳኋን ለመፈፀም የሚያስችሉ እቅዶች በማዘጋጀትና በፖለቲካ ሃላፊዎች ተቀባይነት ሲያገኙ የማስፈፀም፣ አዳዲስ ፖሊሲዎች በመቅረፅ ረገድ ሙያዊ ምክርና ድጋፍ የመስጠት ስራ ለመስራት የሚችለው ፖሊሲዎቹን በጥልቀት ሲያውቃቸው ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ሲቪል ሰርቪሱ ፖሊሲዎችን በጥልቀት እንዲገነዘብ የማድረግ ስራ የሲቪል ሰርቪሱን ብቃት ለማረጋገጥ ከሚያስችሉ ዋነኛ



ስራዎች አንዱ ይሆናል፡፡ በእርግጥ ሲቪል ሰርቪሱ ፖሊሲዎችን ለማስፈፀም፣ ፖሊሲዎችን በጥልቀት ከማወቅ ባሻገር በፖሊሲዎቹ ላይ ጠንካራ እምነት እንዲኖረው ማድረግ የግድ አይደለም፡፡ በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ አንድ የሲቪል ሰርቪል አባል ፖሊሲዎቹን ቢያምንባቸውም ባያምንባቸውም በሙሉ ልብ የማስፈፀም ግዴታ አለበት፡፡ ፖሊሲዎቹን በሙሉ ልብ ማስፈፀም ከራሱ እምነት ጋር በፍፁም ሊሄድ የማይችል ሆኖ ካገኘው ያለው ብቸኛ አማራጭ የሲቪል ሰርቪስ ስራውን መልቀቅ ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ፖሊሲዎችን ቢያምንባቸው ለአፈፃፀም እጅግ የተመቸ ይሆናል እንጂ በማንም ላይ የሚያስከትለው ጉዳት የለም፣ ሊኖርም አይችልም፡፡ ስለሆነም መንግስት ፖሊሲውን ለማስፈፀም ሲቪል ሰርቪሱ ፖሊሲዎችን ጥልቀት ባለው አኳኋን እንዲያውቃቸው ብቻ ሳይሆን በተቻለ መጠንም እንዲያምንባቸው በከፍተኛ ደረጃ መረባረብ አለበት፡፡

ሲቪል ሰርቪሱ በፖሊሲዎቹ ላይ እምነት ቢኖረውም ባይኖረውም ባለው አቅም ሁሉ ለማስፈፀም መረባረብ አለበት ሲባል ሊሆን የማይችል ነገር ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በርግጥም አንድ ሰው የማያምንበትን ፖሊሲ በተመለከተ ከግብር ይውጣ ባሻገር የሆነ የማስፈፀም ርብርብ ሊያደርግ መቻሉ በጣም አጠያያቂ ነው፡፡ አንድ ሰው ይህን ማድረግ የሚችለው የተወሰኑ ፖሊሲዎችን ባይቀበልም አጠቃላይ የግንባታ ስራውን በጥብቅ የሚያምንበት፣ ሲቪል ሰርቪሱ በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ መጫወት የሚገባውን ሚና በሚገባ የተገነዘበና የሚያምንበት እስከሆነ ድረስ ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ጠንካራ እምነት ያለው

ሰው የማያምንባቸውን ፖሊሲዎች በሙሉ ልብ ለማስፈፀም የሚረባረበው በዋናው ተልዕኮው ላይና በዋናው የግንባታ አቅጣጫ ላይ ጠንካራ እምነት ስላለው ነው። ምርጥ ዕጌረዳን ለመቅጠፍ አንዳንድ እሾሆችን ማለፍ እንደሚያስፈልግ ሁሉ፣ ይህን በጥብቅ የሚያምንበትን መሰረታዊ አቅጣጫ ለማስፈፀምና ይህንኑ አሳክቶ የመንፈስ እርካታ ለማግኘት በእሾህነት የሚያያቸውንና የማይስማማባቸውን ፖሊሲዎችም አብሮ ማስፈፀም እንዳለበት ያምናል።

በመሆኑም በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ የመንግስትን ፖሊሲ በብቃት ለማስፈፀም ፖሊሲዎቹን በተናጠል ማስጨበጥ፣ በተቻለ መጠንም ማሳመን ብቻ በቂ አይሆንም። በመሰረታዊ አቅጣጫዎች ላይ የጋራ እምነት ለመፍጠር (ናሽናል ኮንሰንስስ ለመፍጠር) ሰፊ ርብርብ ሊደረግ ይገባል። በዚሁ ሂደት ሲቪል ሰርቪሱም የጋራ እምነቶቹን የሚጋራና አጠናክሮ የያዛቸው እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል። ከዚህ በተጨማሪ ሲቪል ሰርቪሱ ህብረተሰብ የማገልገሉን ሃላፊነት የሚገነዘብና የሚያምንበት፣ በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ የህዝቡን ውሳኔዎች መተግበር ከአንድ ጠንካራ ዜጋ የሚጠበቅ የዴሞክራሲ አስተሳሰብ መገለጫ መሆኑን የሚያምን ሊሆን ይገባል። በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ እንደዚህ አይነቱ የጋራ ብሄራዊ እምነትና ተልዕኮውን የማወቅና ለመወጣት ዝግጁ የመሆን አመለካከት ከሌለ እንኳንስና ዴሞክራሲያዊ ስርአትን በብቃት የሚያገለግል ሲቪል ሰርቪስ፣ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ስርአትን በብቃት የሚያገለግል ሲቪል ሰርቪስም መፍጠር አይቻልም።



የምንገነባውን ዴሞክራሲያዊ ስርአት የሚያገለግል ጠንካራና ብቃት ያለው ሲቪል ሰርቪስ ለመፍጠር ሰፊ የፖለቲካ ስራ ይጠይቃል። የሲቪል ሰርቪሱ አባላት ፖሊሲዎቹን በጥልቀት እንዲያውቋቸው፣ በተቻለ መጠንም እንዲያምኑባቸው ለማድረግ ሰፊ የማብራራትና በዴሞክራሲያዊ አኳኋን የማሳመን ስራ መሰራት አለበት። ከዚህም ባሻገር በአገሪቱ መሰረታዊ የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ አቅጣጫዎች ላይ አንድ የጋራ ብሄራዊ እምነት እንዲያዝ፣ ሲቪል ሰርቪሱም ይህንኑ እንዲጋራ ለማድረግ ሰፊ የማብራራትና በዴሞክራሲያዊ አኳኋን የማሳመን ስራ መሰራት አለበት። ሲቪል ሰርቪሱ በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ ህብረተሰብን ስለሚያገለግልበት አላማ አፈፃፀም የተሟላ እውቀትና እምነት ሊኖረው ይገባል። እነዚህ የማሳመንና የማስረዳት ስራዎች በመሰረታዊ ይዘታቸው የፖለቲካ ስራዎች ናቸው። ይህ ስራ በብቃት ካልተሰራ በስተቀር ብቃት ያለው ሲቪል ሰርቪስ ሊፈጠር አይችልም።

ያለቀጣይና ሰፊ የፖለቲካ ስራ ሲቪል ሰርቪሱ ዴሞክራሲያዊ ስርአትን እንዲያገለግል አድርጎ መቅረፅ አይቻልም ሲባል ሲቪል ሰርቪሱ የፖለቲካ ድርጅት አባል መሆን አለበት ማለት አይደለም። የተባሉትን አመለካከቶች ለመጨበጥ የአንድ የፖለቲካ -ርቲ አባል መሆንን አይጠይቅም። እነዚህን አመለካከቶች እስከጨበጠ ድረስ የሲቪል ሰርቪሱ አባል የማንኛውም ድርጅት አባል ቢሆን ወይም የድርጅት አባል ሳይሆን ቢቀር የሚያመጣው ለውጥ የለም። ከዚህ በመነሳትም

በርካታ አገሮች የሲቪል ሰርቪስ አባላት የፖለቲካ ድርጅቶች አባላት እንዳይሆኑ ይከላከላሉ። በአገራችን ይህ ክልከላ የለም። ይህ መንግስት በመንግስትነቱ የሚሰራው የፖለቲካ ስራ ዴሞክራሲያዊ ስርአትን ለማገልገል የሚያስችል እምነትና አመላከከት ያለው ሲቪል ሰርቪስ ለመፍጠር እንጂ የገዥው -ርቲ አካላትን ለመመልመል መሆን የለበትም። የአባላት ምልመላ ስራ የፖለቲካ ድርጅቶች እንጅ የመንግስት አይደለም፣ ሊሆንም አይገባም።

የምንገነባው የዴሞክራሲ ስርአት ፌዴራሊዝምን መሰረት ያደረገና ስልጣንን ለዝቅተኛ የአስተዳደር አካላት በበቂ መጠን የሚያከፋፍል፣ የህዝቡን ቀጥተኛ ተሳትፎ የሚጋብዝ ስርአት መሆን እንዳለበት በህገ-መንግስቱ በግልፅ የተደነገገ ጉዳይ ነው። ማዕከላዊነትን ከሚያጠብቅ ዴሞክራሲያዊ ስርአት በብዙ መልኩ የተለየ ስርአት ነው። የኛን የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስራ የሚፈፅም ሲቪል ሰርቪስ በዚህ መልክ የተቃኘና የኛን የዴሞክራሲ ስርአት ሊያገለግል የሚችል መሆን አለበት። በዚህ መሰረት ለምሳሌ ሁሉንም ክልሎች በብቃትና በእኩልነት የሚያገለግል ሲቪል ሰርቪስ በፌዴራል ደረጃ መፈጠር ሲኖርበት፣ ከቀበሌ ጀምሮ እስከ ክልል ድረስ ያለውን የመንግስት ስራ በብቃት የሚፈፅም የራሱ ህልውናና ባህሪ ያለው የየክልሉ ሲቪል ሰርቪስም መኖር አለበት። በአንድ አገር ሁለት የየራሳቸው ህልውና ያላቸው ሲቪል ሰርቪሶችን ነው እየፈጠርን ያለነው።

የፌዴራል ሲቪል ሰርቪሱ የአገሪቱን የጋራ እቅዶች



በብቃት የማስፈፀምና ይህንኑ መላውን የአገሪቱን ህዝቦች በሚጠቅም አኳኋን ለመፈፀም የሚያስችል እምነትና አመለካከት ሊኖረው ይገባል። ይህንን በማድረግ ሁሉንም የአገሪቱን ክልሎች በተዘዋዋሪ መንገድ ያገልግላል። ነገር ግን የፌዴራል ሲቪል ሰርቪሱ በዚህ ብቻ ሳይታጠር ክልሎችን በቀጥታም ማገልገል አለበት። የፌዴራል ስርአት በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው በተለያየ የስርአቱ አካላት መካከል የየራሳቸውን ስልጣን በማይጋፋ መልኩ ጠንካራ ትስስርና መደጋገፍ ሲኖር ነው። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ከየክልሉ ሲቪል ሰርቪሶች ጋር በቅርብ በመደጋገፍና በቅንጅት የሚሰራ ፌዴራል ሰርቪስ ያስፈልጋል። የየክልሉን ሲቪል ሰርቪሶች በአቅም ግንባታ ረገድ የሚደግፍ ብቃት ያለው ሲቪል ሰርቪስ ያስፈልጋል። ይህንን ለማድረግ የሚያስችል ሙያዊ ብቃት የሌለው፣ ወይም አመለካከቱና እምነቱ የሌለው ሲቪል ሰርቪስ የምንገነባውን ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመፍጠር የሚያስችል መሳሪያ ሆኖ ሊያገለግለን አይችልም።

በተመሳሳይ መልኩ ከቀበሌ ጀምሮ እስከ ክልል ድረስ የተዋቀረውና በመዋቀር ላይ ያለው ሲቪል ሰርቪስ በየደረጃው የተሰጠውን ሃላፊነት በብቃት ከመወጣት ባሻገር ከበላይ ወይም ከበታች አካላት ጋር በቅርብ ተቀናጅቶ ለመስራት የሚያስችል፣ የተሻለ አቅም ያለው ደከም ያለውን በአቅም ግንባታ ረገድ ለመደገፍ የሚያስችለው ብቃት፣ አመላከከትና እምነት ሊኖረው ይገባል። ይህ በተለያዩ የየክልሉ የሲቪል ሰርቪስ አካላት መካከል ብቻ ሳይሆን በክልልና በፌዴራል ሲቪል ሰርቪሶች መካከል

ያለውን ግንኙነት የሚመለከትም መሆን ይገባዋል። ሁሉም የየራሳቸው ስራ ዘላቂ ውጤት የሚኖረው የሌላውም በብቃት ሲፈፀም ብቻ መሆኑን የሚገነዘቡበት፣ የየክልሉ ልማትና ጥቅም የሚጠበቀው አገራዊ ልማትና ጥቅም ሲጠበቅ መሆኑን፣ አገራዊ ልማትና ጥቅምም የሚጠበቀው የክልሉ ልማትና ጥቅም ተጠብቆ ሲደመር ብቻ መሆኑን የሚገነዘቡ መሆን አለባቸው። በተመሳሳይ መልኩ የየቀበሌውና ወረዳው ልማትና ጥቅም የሚረጋገጠው የክልል ልማትና ጥቅም ሲጠበቅ መሆኑን፣ የክልሉ ልማትና ጥቅምም የሚጠበቀው የየቀበሌውና ወረዳው ልማት ሲጠበቅና ሲደመር መሆኑን ማመን አለባቸው።

በሌላ አገላለፅ እያዋቀርን ያለነው ሁለት የተለያዩ ሲቪል ሰርቪሶችንና በእያንዳንዱ ሲቪል ሰርቪስ ውስጥ የተለያዩ እርከኖችን የሚጠይቅ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ስርአትን ነው። የዚህን ስርአት እቅዶች ለማስፈፀም የሚቻለው በአንድ በኩል ሁሉም በየፊናው የየራሱን ስራ በብቃት ለመፈፀም የሚፍጨረጨርበት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉም በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ልማትን ለማረጋገጥ የተፈጠረ አንድ ሰራዊት የተለያዩ ክፍሎች አባላት መሆናቸውን አምነው እንደአንድ ሰራዊት አቅማቸውን ከየአቅጣጫው አቀናጅተውና አስተባብረው ዋናውን የጋራ ግብ ለማሳካት መዝመት እንዳለባቸው አምነው የሚንቀሳቀሱ ሊሆኑ ይገባል። እንደዚህ አይነቱን ሲቪል ሰርቭስ ለመፍጠር ወጥነት ያለው የሲቪል ሰርቪስ አሰራርና አደረጃጀት፣ የትብብርና የቅንጅት ስርአቶች ወዘተ. መፍጠር ያስፈልጋል። በዚህ ብቻ ሊፈፀም የሚችል ግን አይደለም። ጉዳዩ የእምነትና



የአመለካከት ጉዳይም ጭምር ስለሆነ ይህንን ለመፍጠር የሚያስችል ተከታታይና ብቃት ያለው የፖለቲካ ስራ መስራትም ይጠይቃል።

የምንገነባው የዴሞክራሲ ስርአት በህዝብ ሰፊና የነቃ ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ እስከሆነ ድረስ ይህንኑ በብቃት ሊያስፈፅም የሚችል ሲቪል ሰርቪስም ያስፈልገናል። ሙያተኛው እኔ ነኝ መሃይም ህዝብ በማያውቀው ጉዳይ ላይ ገብቶ መፈትፈት የለበትም ብሎ የሚያስብ ሲቪል ሰርቪስ፣ ህዝብን ማሳተፍ ብሎ ነገር አላስፈላጊ የጊዜ መጓተትን የሚያስከትል ነገር አድርጎ የሚወስድ ሲቪል ሰርቪስ፣ እራሱን እንደህዝብ ተቀጣሪና አገልጋይ ሳይሆን እንደ የበላይ ተቆጣጣሪና ተገልጋይ አድርጎ የሚወስድ ሲቪል ሰርቪስ የመንግስትን ዴሞክራሲያዊ ስርአት የመገንባት ፖሊሲዎች ለማስፈፀም በፍፁም አይችልም። የመንግስትን የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ፖሊሲዎች ለማስፈፀም የሚያስችል ሲቪል ሰርቪስ ህዝቡ በመሰረታዊ ፖሊሲዎች ላይ ተወያይቶ የድጋፍ አቋም ካልያዘ በስተቀር የሚፈፀም የረባ የልማትም ሆነ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስራ እንደማይኖር ተገንዝቦ ይህንኑ በጥብቅ የሚያምን፣ ህዝቡ ከልምዱ የሚያገኛቸው ለፖሊሲ ቀረፃም ሆነ አፈፃፀም ከፍተኛ ትርጉም ያላቸው እውቀቶች እንዳሉና እነዚህን አፈላልጎ ጥቅም ላይ ማዋል ለእቅዶቻችን መሳካት ልዩ ትርጉም እንዳለው በጥልቀት የተገነዘበና የሚያምን፣ የሲቪል ሰርቪሱ አላማ ህዝቡን ማገልገል እንደሆነና ይህም ህዝቡንና መብቶቹን በማክበር እንደሚጀምር በጥብቅ የሚያምን መሆን አለበት። እንደዚህ አይነቱን ሲቪል ሰርቪስ መፍጠር የሚቻለው

በህዝቡና በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ ተከታታይነት ያለውና ውጤታማ የፖለቲካ ስራ ሲሰራ ብቻ ነው።

ከላይ ከተዘረዘሩት ነጥቦች መረዳት የሚቻለው አንድ መሰረታዊ ቁምነገር አገራችን የምትፈልገውን ሲቪል ሰርቪስ ለመፍጠር፣ በህብረተሰቡ ውስጥ አንድ አጠቃላይ የጋራ አገራዊ አመላከከት የሚፈጥር፣ ሲቪል ሰርቪሱ የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ቁልፍ አስፈፃሚ ሃይል እንዲሆን የሚያስችሉት ጠንካራ አመለካከቶችና እምነቶች እንዲኖሩት የሚያደርግ ሰፊና ተከታታይ የማብራራት፣ የማስረዳትና የማሳመን ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስራ በመንግስት መሰራት ሲችል ብቻ ነው። ይህን የመሰለ ብቃት ያለው የፖለቲካ ስራ ሰርቶ የሲቪል ሰርቪሱን እምነትና የፖለቲካ አመለካከት ከመቅረፅ ውጭ ፋይዳ ያለው ሲቪል ሰርቪሱን የማሻሻልና ብቃት ያለው የመንግስት ፖሊሲ አስፈፃሚ አካል እንዲሆን የማድረግ ስራ ሊሰራ አይችልም። ስለዚህም ነው የሲቪል ሰርቪሱ ማሻሻያ ፕሮግራም ቴክኒካዊ ፕሮግራም ብቻ ሳይሆን በዋናነት ፖለቲካዊ ስራ ነው የምንለው። ይሁንና ከዚህ በመነሳት ሲቪል ሰርቪሱ የአንድ ድርጅት የፖለቲካ መሳሪያ መሆን አለበት፣ ወይም በዋነኛነት በፖለቲካዊ አቋሙ ምክንያት የሚመመለመል መሆን አለበት ማለት አይደለም።

ሲቪል ሰርቪስ የሚፈለገው የአንድ ድርጅት የካድሬ መዋቅር እንዲሆን አይደለም። ይህ እያንዳንዱ ድርጅት በየራሱ መንገድና በድርጅታዊ መዋቅሩ የሚፈጥረው እንጂ የመንግስትን መዋቅር ወደ ድርጅት መዋቅር በመቀየር አይደለም፣ ይህ በፍፁም



መሆን የማይገባው ነው። ሲቪል ሰርቪስ የሚፈለገው በመጀመሪያ ደረጃ የመንግስት ፖሊሲዎችን በብቃት ለመፈፀም፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በፖሊሲ ቀረፃ ሂደት የሙያ ምክርና ድጋፍ እንዲሰጥ ነው። ብቃት ያለው ሙያተኛ የተሰበሰበበት ሲቪል ሰርቪስ ብቻ ነው ይህንን ማድረግ የሚችለው። በመሆኑም የሲቪል ሰርቪሱ የምልመላና የእድገት መመዘኛው ሊሆን የሚገባው አንድ ነገር ነው። ይኸውም የግለሰቡ ሙያዊ ብቃትና ፖሊሲዎችን በብቃት የማስፈፀም ችሎታ ነው። ከዚህ ውጭ የሆነና ይህንኑ የሚፃረር የምልመላና እድገት መመዘኛ በፍፁም መኖር የለበትም። ከዚህ ውጭ የሆነ መመዘኛ ከተቀመጠ ብቃት ያለው አስፈፃሚ አካል አይኖርም። መንግስት ያስቀመጠው ፖሊሲም የሰማይ ላይ ዳመና ሆኖ ይቀራል። ምንም አይነት ጠንካራ የካድሬ መዋቅር ያለው ድርጅት ስልጣን ቢይዝ ያስቀመጠውን ፖሊሲ ሊያስፈፀም የማይችል ይሆናል። ሲቪል ሰርቪሱ ፖሊሲ ለማስፈፀም ብቃቱና የሙያ ችሎታው እየተመዘነ በሚመለመልበትና በሚያድግበት በዚህ ስርአት ውስጥ የዚህን ሙያተኛ አመለካከትና እምነት ለመቅረፅ ነው የፖለቲካ ስራ የሚሰራው እንጂ፣ ሲቪል ሰርቪሱን ወደ የፖለቲካ ካድሬ መዋቅር ለመቀየር አይደለም፣ ሊሆንም አይገባውም።

ከዚህ አኳያ ሊታዩ የሚገባቸውና ባለፉት አመታት የተለያየ ብዥታ የተፈጠረባቸው የሲቪል ሰርቪሱ የብሄራዊ ተዋፅኦና የብቃት መመዘኛ ጉዳዮች ናቸው። የተመጣጠነ ብሄራዊ ተዋፅኦ ያለው ሲቪል ሰርቪስ በፌዴራል ደረጃ የመፍጠሩ ግብ አንድ መሰረታዊ ህገ-መንግሰታዊ ግብ ነው። ይህን ግብ የማስፈፀም

ተግባርና የሲቪል ሰርቪሱን ፖሊሲ የማስፈፀም ብቃት ማረጋገጥ መሰረታዊ ተልእኮ ሊጋጩ ይችላሉ፡፡ እነዚህን አጣጥሞ የማስኬድ ጉዳይ በሲቪል ሰርቪሱ ግንባታ ሂደት ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ የብሄራዊ ተዋፅኦ ጉዳይ በክልል ሲቪል ሰርቪሶችም ደረጃ በተለየ መልኩ እንደ አንድ ትልቅ ጉዳይ ሊነሳ የሚችል ጉዳይ ነው፡፡

የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ የሚፈለገው የመንግስትን ፖሊሲዎች በብቃት በማስፈፀም መላውን የአገሪቱን ህዝብ በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ ለማገልገል ነው፡፡ ሲቪል ሰርቪሱ መላውን የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያገለግል ስለሆነ ብሄራዊ ስብጥሩም በተቻለ መጠን ህዝቡን መምሰል አለበት፡፡ በመሆኑም ሲቪል ሰርቪሱ የተመጣጠነ ብሄራዊ ተዋፅኦ እንዲኖረው ሰፊ ጥረት መደረግ ይኖርበታል፡፡ ፌዴራል ሲቪል ሰርቪሱ መላውን ህዝብ ሊያገለግል የሚችለው የመንግስትን ፖሊሲ በብቃት ማስፈፀም ሲችል ነው፡፡ የመንግስትን ፖሊሲ በብቃት ማስፈፀም የማይችል ሲቪል ሰርቪስ ብሄራዊ ተዋፅኦው ምንም ቢሆን ማንኛውንም ህዝብ ሊጠቅም አይችልም፡፡ በመሆኑም ሁሉንም የኢትዮጵያ ህዝቦችና ክልሎች በላቀ ደረጃ የሚያገለግል ሲቪል ሰርቪስ ለመፍጠር ከሁሉም በፊትና ከሁሉም በላይ መረጋገጥ የሚገባው ጉዳይ የሲቪል ሰርቪሱ ብቃት ጉዳይ ነው፡፡ ብቃቱ ከተረጋገጠ በኋላ ይኸው ብቃቱ የተረጋገጠ ሲቪል ሰርቪስ የተመጣጠነ ብሄራዊ ተዋፅኦ፣ የፆታ ተዋፅኦ ወዘተ. እንዲኖረው ማድረግ ይቻላል፣ ይገባልም፡፡



በአፈፃፀም ደረጃ በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ የሚኖር የምልመላና የእድገት ስራ በግለሰቡ ብቃት ላይና በዚሁ ላይ ብቻ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ወሳኝ የሆነውን የብቃት ጉዳይ ለማረጋገጥ ያስችላል፡፡ ይህ መሰረታዊ መርሆ እንደተጠበቀ ሆኖ ብሄራዊ ተዋፅኦውን ለማመጣጠን፣ የፆታ ተዋፅኦውን ለማመጣጠን ወዘተ. በቂ ተሳትፎ የሌላቸው ብሄሮች፣ ሴቶች በትምህርትና ስልጠና ረገድ ልዩ ድጋፍና ማበረታቻ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ በዚሁ መልክ ብቃታቸውን አረጋግጠው በምልመላ ውድድር ላይ ከተቻለ ከሌላው የላቁ በመሆናቸው፣ ቢያንስ ቢያንስ ግን ከሌላው ጋር እኩል በመሆናቸው ቅድሚያ አግኝተው ሊመለመሉ የሚችሉበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡ ስለዚህ የሲቪል ሰርቪሱን ብሄራዊ ተዋፅኦ ለማመጣጠን በመጀመሪያ በትምህርትና ስልጠና ረገድ ልዩ ድጋፍ መስጠት፣ ከዚያ በኋላ ደግሞ የተሻለ ውጤት ስላገኙ ወይም ከሌላው ጋር እኩል የሆነ ውጤት ስላገኙ በቂ ተሳትፎ ለሌላቸው ቅድሚያ በመስጠት የሚፈፀም ይሆናል፡፡ ከሌላው ጋር ቢያንስ እኩል የሆነ ውጤት ያላገኙት በምንም አይነት መልክ የብሄር ወይም የፆታ ቅንብር ለማመጣጠን ሲባል መመልመል ወይም እድገት ማግኘት የለባቸውም፡፡

ይህ አሰራር በክልሎችም ውስጥ ተግባራዊ መሆን ያለበት ነው፡፡ ብዙዎቹ ክልሎች ከአንድ በላይ ብሄር/ብሄረሰብ ያላቸው በመሆኑ የብሄር ተዋፅኦ ማመጣጠን እንደ አጀንዳ የሚነሳባቸው ናቸው፡፡ የአንድ ብሄር የተለያዩ አካባቢዎች የተመጣጠነ ተዋፅኦ የሚነሳበት አጋጣሚም ሊኖር ይችላል፡፡ በአካባቢው ብቃት

ያላቸው በቂ ሙያተኞች በማይገኙበት አጋጣሚም ከክልሉ ውጭ ሙያተኞች የመቅጠር ጉዳይ ሊነሳ ይችላል። የፆታ ስብጥር ማመጣጠን በሁሉም አካባቢዎች የሚነሳና መነሳትም ያለበት ጉዳይ ነው። በየትኛውም መልክ ቢሆን ተዋፅኦን የማመጣጠን ስራ በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ የሚፈፀምበት መርህ አንድና ያው ነው መሆን ያለበት። ብቃቱ የሌለው ሰው ተዋፅኦ ለማመጣጠን ሲባል በምንም መልኩ መመልመል ወይም እድገት ማግኘት የለበትም። ተዋፅኦ የሚመጣጠነው በትምህርትና ስልጠና ልዩ ድጋፍ በመስጠትና በዚሁ አማካኝነት ብቃታቸውን አዳብረው ከሌላው ጋር ተወዳድረው ቢያንስ እኩል ውጤት ያመጡትን ቅድሚያ በመስጠት ነው። ከዚህ ውጭ በክልልም ሆነ በፌዴራል ደረጃ ተዋፅኦ ለማመጣጠን የሚቀርብ መፍትሄ የለም።

በተለይም በክልሎች አካባቢ ከክልሉ ውጪ የመጡ ሙያተኞችን በሲቪል ሰርቪስ ውስጥ በመቅጠር ዙሪያ የሚነሱ ጥያቄዎች ይኖራሉ። የክልሉ ህዝብ የራሱን ጉዳይ በራሱ የመወሰን ህገ-መንግስታዊ መብቱ ተከብሮለት ሲያበቃ፣ በአካባቢው ብቃቱ ያላቸው ሙያተኞች ከሌሉ ከሌላ አካባቢ መቅጠር ሳይሆን በአካባቢው ካሉትና ብቃቱ ከሌላቸው ሰዎች ውስጥ የተሻለውን መርጦ መመደብ ካልቻለ መብቱ ይሸረሸራል የሚሉ አሉ። በመሰረቱ ህዝቡ የራሱን ጉዳይ በራሱ የመወሰን ፖለቲካዊ መብት ተረጋግጦለታል፣ ይህ በምንም መልኩ መሸርሸር የለበትም። ስለሆነም የአካባቢውን ፖሊሲ የሚያወጣውና የሚያፀድቀው፣ የፖለቲካ አመራር የሚሰጠው አካል የአካባቢው ህዝብ ይሆነኛል ብሎ የሚመርጠው መሆን አለበት። ይህ እስከተረጋገጠ ድረስ



የአካባቢው ህዝብ የራሱን ጉዳይ በራሱ የመወሰን መብት መቶ በመቶ ተግባራዊ ሆኗል ማለት ይቻላል።

ሲቪል ሰርቪስ የሚፈለገው ፖሊሲ ለማውጣት ወይም ለማፅደቅ፣ ወይም የፖለቲካ አመራር ለመስጠት አይደለም። ህዝቡ ይጠቅመኛል ብሎ የወሰነውን ነገር በብቃት ለማስፈፀም ነው። የህዝቡ የመወሰን ስልጣን በርግጥ ተግባራዊ የሚሆነው፣ የህዝቡ የፖለቲካ ውሳኔ መብት በርግጥም የበላይ የሚሆነው መርጦ የወሰነው ውሳኔ በላቀ ደረጃ ተግባራዊ ሲሆን ነው። ይህንኑ ለማድረግ ብቃቱና ዝግጁነቱ ያለው ሲቪል ሰርቪስ ሲኖር ነው። እንደዚህ አይነቱ ሲቪል ሰርቪስ ከሌለ ህዝቡ ውሳኔዎችን ይወስናል፣ ውሳኔዎቹ ግን ተፈፃሚ አይሆኑም፣ ስለዚህ የህዝቡ መብት ተጨባጭነት ያለው መብት ሳይሆን በወረቀት ላይ ብቻ ሰፍሮ የቀረ መብት ይሆናል። ህዝቡ ከልማት ተጠቃሚ የሚሆነው ያስቀመጠው የልማት እቅድ በተሟላ መልኩ ተፈፃሚ ሲሆንለት ነው። ያለበለዚያ የበይ ተመልካች ሆኖ ይቀራል። የልማት እቅድ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው ይህንን ለማድረግ ብቃቱ ያለው ሲቪል ሰርቪስ ሲኖር ነው።

ስለሆነም የህዝቦች የራሳቸውን ጉዳይ በራሳቸው የመወሰን መብትና ስልጣን፣ የልማትና ከልማቱ ተጠቃሚ የመሆን መብት የሚረጋገጠው ብሄራዊና የፆታ ስብጥሩ ምንም ይሁን ምን ብቃቱ የተረጋገጠ ሲቪል ሰርቪስ ሲፈጠር ነው። ተዋፅኦ በማመጣጠን ሽፋን ብቃት የሌለው ሲቪል ሰርቪስ መፍጠር የአካባቢውን ህዝብ ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ክፉኛ የሚሸረሽር፣ የአካባቢውን ልማት የሚያቀረቅዝና የአካባቢውን ህዝብ በከፍተኛ

ደረጃ የሚጎዳ ነው። እንደዚህ አይነቱ አሰራር የሚጠቀመው ክፍል ቢኖር ምንም ችሎታና ብቃት ሳይኖረው የፆታ ወይም የብሄር ካርዱን አንጠልጥሎ፣ ይህችን ካርድ አውለብልቦና "ሽጦ" በመንግስት ስራ ላይ ተኮፍሶ ብቃት ያለው ስራ ሳይሰራ ለመጠቀም የሚፈልገውን ነው። በጥገኝነት መኖር የሚሻውን ነው። ይህ በስመ ተዋፅኦ ማመጣጠን የህዝብ ሳይሆን የጥገኝነት አጀንዳ ማራመድ ነው የምንለውም በዚህ ምክንያት ነው።

በርግጥ አንዳንድ ጊዜ የቋንቋ ችግር በመኖሩ ከሌሎች ክልሎች ሙያተኞች የመቅጠሩ ጉዳይ ሊያስቸግር ይችላል። ይሁንና በየክልሉ የሚሰሩት ስራዎች ሁሉ የአካባቢውን የስራ ቋንቋ ማወቅ የሚጠይቁ አይደሉም። ስለዚህ ይህ ችግር የማይታለፍ ችግር አይደለም። ከሁሉም አካባቢ ሙያተኛ ተፈልጎ የሚታጣበት ሁኔታም ያጋጥማል። በእንደዚህ አይነቱ ወቅት የተገኙትን አወዳድሮ የተሻሉት በጊዜያዊነትና ከሙያቸው ጋር የሚመጥን ደሞዝ እየተሰጣቸው እንዲሰሩ በሂደት አንድም ብቃቱ ያለው ሰው ሲገኝ የሚተኩበት፣ አለያም በጊዜያዊነት የተመደበው ሰው በቀጣይ ትምህርትና ስልጠና ልምድና ብቃቱን አግኝቶ በቋሚነት ተመድቦ የሚሰራበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። ዞሮ ዞሮ በፌዴራልም ሆነ በክልል ሲቪል ሰርቪስ ወሳኙ ነገር ምልመላና እድገት በብቃትና በብቃት ላይ ብቻ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ፣ የብሄርና የፆታ ስብጥር የማመጣጠን ጉዳይ ደግሞ ይህንኑ መርህ በማይፃረር መልክ ብቻ የሚፈፀም መሆን እንዳለበት ነው።

የሲቪል ሰርቪሱን ብቃት ለማረጋገጥ የምልመላና



የእድገት መመዘኛው ብቃትና ብቃት ብቻ መሆን አለበት ብሎ በጥብቅ ለማስፈፀም መንቀሳቀስ ብቻውን በቂ አይደለም። የብቃት መመዘኛውን በትክክል ማስቀመጥ በጣም አስፈላጊ ነው። ብዙውን ጊዜ የብቃት መመዘኛ ተደርገው የሚወሰዱት የትምህርት ደረጃና የስራ ልምድ ናቸው። ምን አይነት የትምህርትና ስልጠና ምስክር ወረቀት እንዳለውና ምን ያህል እንደሰራ ማየት እንደብቃት መመዘኛ መወሰዳቸው ተገቢ ነው። አንድን ስራ ለመስራት ትምህርቱና የሙያ ስልጠናው ስለሚያስፈግና በስራ ልምድ የሚገኝ እውቀትም ስላለ ሁለቱም እንደስራ መመዘኛ ሊወሰዱ ይችላሉ። ይሁንና የትምህርት ማረጋገጫ ወረቀትና ረጅም የስራ ልምድም ኖሮት የሚፈይድ ስራ ለመስራት የሚችል ወይም የማይፈልግ ሰው ሊኖር ይችላል። በመሆኑም የመጨረሻው ማረጋገጫ መሆን ያለበት የስራ ውጤቱ ነው። በሲቪል ሰርቪሳችን ውስጥ የስራ ውጤት መመዘኛ ተብሎ የሚሞላ ፎርም አለ። ይሁንና ይህ አሰራር ብዙ ጉድለቶች ያሉት ነው። ከሁሉም በላይ የስራ ውጤትን ለመመዘን ምንም አይነት የረባ ሚና የሚጫወት አይደለም። በመሆኑም ሲቪል ሰርቪሳችን በመሰረቱ ሰውን በስራ ውጤቱ በትክክለኛ መንገድ ለመመዘን የሚያስችል አስተማማኝ ስርአት የሌለው ነው።

እንደዚህ አይነት አስተማማኝ ስርአት በሌለበት ሁኔታ ታታሪና ትጉህ ሰራተኛውም አልምጡም አብረው የሚኳትኑበት፣ ለአድልዎ በር የሚከፈትበት፣ የሲቪል ሰርቪሱ ብቃት ለአደጋ የሚጋለጥበትና የታታሪና ትጉህ ሰራተኞች የስራ ተነሳሽነትና ሞራል የሚነካበት ሁኔታ ይፈጠራል። ተሽፋፍኖና ተከናንቦ አንዳች

አጥጋቢ ስራ ሳይሰራ የሚኖር የወደቀ ግንድ በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ እየተከማቸ፣ በፍጥነት ሊያድጉ የሚችሉና የሚገባቸው ታታሪ ሰራተኞች ዕድሉ ተነፍጓቸው ማበርከት የሚችሉትን አስተዋፅኦ በሙሉ ሳያበረክቱ የሚቀሩበት ሁኔታ ይፈጠራል:: ሲቪል ሰርቪሳችን ይህንን ችግር በአስተማማኝ መልክ የሚያስወግድበት ስርአት ካልተበጀ በስተቀር የምንፈልገውን ብቃት ያለው ሲቪል ሰርቪስ መፍጠር በፍፁም የሚቻል አይሆንም::

**2.2. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራምና የልማት አላማችን፣**

የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራማችን እንደሌሎቹ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ፕሮግራሞቻችን ሁሉ የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ አላማችንን ብቻ ሳይሆን የልማት አላማችንንም ለማሳካት የሚያገለግልና በዚሁ የተቃኘ መሆን ይኖርበታል:: የልማት አላማችንን ለማሳካት መንግስት የራሱ የሆነ የማይተካ ሚና አለው:: መንግስት በህዝብ ወይም በግል ባለሃብቶች ሊሰሩ የማይችሉትን ወይም በሚፈለገው ደረጃ ሊሰሩ የማይችሉትን ስራዎች በራሱ መስራት አለበት:: ይህ በተለምዶ የመንግስት ስራ ተብለው የሚታወቁ ህግና ስርአት የማስጠበቅ፣ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መሰረተ-ልማት አገልግሎቶችን መስጠት የሚመለከት ይሆናል:: ነገር ግን በዚህ ብቻ ሳይታጠር በህዝብ ወይም በግል ባለሀብቶች በብቃት ሊሰሩ ያልቻሉ ክፍተቶችን የሚሞሉ የልማት ድርጅቶችን ማቋቋምንም ይጨምራል:: ይህ በጣም ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው የመንግስት



ስራ ቢሆንም ዋናው ጉዳይ ዋናው የልማት ሃይል የሆነውን ህዝብና የግል ባለሃብቶች የልማት አቅማቸውን አሟጠው እንዲጠቀሙ ማስቻል፣ ማገዝና ማስተባበር ነው የመንግስት ዋናው ልማታዊ ስራ::

በዚህ መሰረት መንግስት የህዝቡንና የልማታዊ ባለሃብቶችን የማስፈፀም አቅም ለማጎልበት በሰፊው መስራት ይኖርበታል:: ህዝቡና የግል ባለሀብቶች በልማት መስክ በሚሰማሩበት ወቅት የሚያጋጥሟቸውንና ባላቸው አቅም ሊያስወግዷቸው የማይችሉትን ችግሮች እየጠራረገ በሙሉ አቅማቸው ለልማት ሊሰማሩ የሚችሉበት የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር አለበት:: በአጋርነት፣ በችግር ፈችነትና በአስተባባሪነት መሰለፍ ይኖርበታል:: ሲቪል ሰርቪሳችን መንግስት የልማት አላማችንን ለማሳካት እፈፅማቸዋለሁ ብሎ ያስቀመጣቸውን ከፍ ሲል የተገለፁትን ሁለት መሰረታዊ ስራዎች በብቃት ለመፈፀም የሚችል መሆን አለበት::

ሲቪል ሰርቪሱ ይህንን ስራ በሚፈለገው ደረጃ ሊፈፅም የሚችለው መንግስት የአገራችንን የልማት አላማዎች ከማሳካት አኳያ ምን መስራት እንዳለበት፣ የሁሉም የልማት ሃይሎች ሚና ምን እንደሆነ፣ በነሱ መካከል ያለው ቅንጅትና ትብብር ምን መምሰል እንዳለበት ጠንቅቆ ማወቅ ይኖርበታል:: የተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎችን ለማልማት የተቀመጡ አቅጣጫዎች ምን እንደሆኑ በጥልቀት ማወቅ አለበት:: አገራችንን ለማልማት የተቀመጡትን ፖሊሲዎችና አቅጣጫዎች ለማስፈፀም በቁርጠኝነት

ለመረባረብ የሚያስችለው እምነትና አመለካከት መያዝ አለበት፡፡ አገሪቱን ከድህነትና ኋላ ቀርነት ለማላቀቅ በሚደረግ የተከበረ ትግል ውስጥ ለመሳተፍና ድርሻውን ለማበርከት ዝግጁ የሆነ መሆን አለበት፡፡ በሌላ አነጋገር ስራውን ለመስራት የሚያስችለው መሰረታዊ ፖለቲካዊ እምነትና አመለካከት ያለው፣ የልማት ፖሊሲዎቹንና አቅጣጫዎቹን ጠንቅቆ ያወቀ መሆን አለበት፡፡ በአሁኑ ወቅት እንደዚህ አይነት አመለካከት፣ እምነትና እውቀት ያለው ሲቪል ሰርቪስ እንደሌለን ግልፅ ነው፡፡

የልማት አላማችንን ለማሳካት፣ የግል ባለሀብቶችና ህዝቡ የልማት አቅማቸውን አሟጠው የሚጠቀሙበት ሁኔታ ለመፍጠር እጅግ በጣም ቀልጣፋ የሆነ ሲቪል ሰርቪስ ያስፈልገናል፡፡ በገበያ፣ በተለይም በአለም ገበያ የሚቃኝ ልማት ለማምጣት በምንጣጣርበት በአሁኑ ወቅት በገበያ ተወዳድሮ ለማሸነፍ፣ ጊዜን በቀናት ወይም በሳምንታት ሳይሆን በሰአታትና በደቂቃዎች ቆጥቦ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ጊዜ ወርቅ ነው የሚባለው አባባል ከመቼውም ጊዜ በላይ ተጨባጭነት ያለው ሆኗል፡፡ የግል ባለሃብቶችና ህዝቡ ከሲቪል ሰርቪሱ የሚፈልጉትን አገልግሎት በጣም ቀልጣፋ በሆነ መንገድ ማግኘት ካልቻሉ በጊዜ ተበልጠው በገበያ ተወዳድረው ማሸነፍ አይችሉም፡፡ ያስቀመጥነው የልማት ስትራተጅ ቀርፋፋና የተንዛዛ ቢሮክራሲያዊ አሰራር ባለበት ሁኔታ በምንም አይነት መንገድ ሊሳካ አይችልም፡፡

ሲቪል ሰርቪሳችን የልማት ሃይሎች የሚፈልጉትን አገልግሎት እጅግ ቀልጣፋ በሆነ አኳኋን ካልፈፀመ፣ የድህነትና



ኋላቀርነት አጋር በመሆን በኢትዮጵያ ህዝብ የልማት አላማና ተስፋ ላይ የተሰለፈ ከፍተኛ እንቅፋት እንደሚሆን በቅጡ የሚገነዘብ አይደለም፡፡ ነገሮችን በይደር ማጓተት በህዝቡ የልማት አላማ ላይ ደባ መፈፀም ማለት እንደሆነ የሚገነዘብ አይደለም፡፡ ይልቁንም የተንዛዛ አሰራሩን ቃል በቃል መፈፀም የጥሩ ሲቪል ሰርቪስ ሰራተኛ መለያ ባህሪ አድርጎ የሚመለከትበት፣ የባለስልጣንነቱና ውሳኔ የመወሰን ስልጣን ያለው ለመሆኑ ማረጋገጫ አድርጎ የሚመለከትበት፣ አጋጣሚም አለ፡፡ ችግሩ የሲቪል ሰርቪሱ አመለካከት ብቻም አይደለም፡፡ አሰራሩና አደረጃጀቱ ራሱ ለተገልጋይ ቀልጣፋ አገልግሎትን መስጠት መሰረት በማድረግ የተቃኘ ሳይሆን ቁጥጥርን መሰረትና ማዕከል ያደረገ ነው፡፡ በመሆኑም የሲቪል ሰርቪሱ አመለካከት፣ አደረጃጀቱና አሰራሩ ተመጋግበው የቅልጥፍና ፀር የሆነ፣ እጅግ በተንዛዛ አሰራር የተተበተበ የልማት አላማችንን ለማሳካት በፍፁም የማይቻለው ሲቪል ሰርቪስ እንዲሆን አድርገውታል፡፡

ሲቪል ሰርቪስ የሚለው የእንግሊዘኛ ቃል፣ ትርጉሙ የህዝብ አገልጋይ ማለት ነው፡፡ በአገራችን የተለመደው ቃል የመንግስት ሰራተኛ የሚል ነው፡፡ በአገራችን የነበሩት መንግስታት ለህዝብ ተጠሪና የህዝብ አገልጋይ የነበሩ መንግስታት አልነበሩም፡፡ የህዝብ የበላይ፣ በህዝብ ጫንቃ ላይ ተቀምጠው በህዝብ የሚገለገሉ ነበሩ፡፡ የመንግስት ሰራተኛ የሚባለውም የእንደዚህ አይነቶቹ መንግስታት ስራ አስፈፃሚ፣ በህዝብ ተገልጋይ፣ የህዝብ ተቆጣጣሪ የሆነ አካል ነው የነበረው፡፡ የመንግስት ሰራተኛው የሚመራበት አሰራርና አደረጃጀትም ሆነ የመንግስት ሰራተኛው አመለካከት

ራሱን የህዝቡ ተቀጣሪና አገልጋይ አድርጎ እንዲቆጥር ሳይሆን የህዝብ የበላይ ተቆጣጣሪና ተገልጋይ አድርጎ እንዲቆጥር የሚያደርገው ነበር:: ህዝቡን በአግባቡና በትህትና ማስተናገድ ራሱን ማዋረድና ዝቅ ማድረግ የሚመስለው ሰራተኛ ነው የተፈጠረው::

በአሁኑ ወቅት እየተረባረብን ያለነው የህዝብ ተጠሪና አገልጋይ የሆነ፣ ህዝብ ሲፈልግ የሚሾመውና የሚሽረው ዴሞክራሲያዊ መንግስትና ስርአት ለመፍጠር ነው:: በአሁኑ ወቅት እየተረባረብን ያለነው ህዝቡና የግል ባለሃብቶች ከመንግስት የሚያስፈልጋቸው አገልግሎትና ድጋፍ በተሟላ መልክ አግኝተው የልማት አቅማቸውን አሟጠው እንዲጠቀሙ ለማድረግ የሚችል የህልውናው አንዱ መሰረታዊ ምክንያት ይህ እንደሆነ የሚገነዘብ ልማታዊ መንግስት እንዲፈጠር ነው:: ህዝቡን በብቃትና በትህትና ማስተናገድ አላማውን በብቃት ማሳካት ማለት እንደሆነ፣ የሲቪል ሰርቪሱ የኩራት ምንጭ ይህ እንደሆነ የሚገንዘብ ሲቪል ሰርቪስ ለመፍጠር ነው ጥረት እያደረግን ያለነው:: ይህንኑ በብቃት ለመፈፀም የሚያስችል አሰራርና አደረጃጀት ያለው ሲቪል ሰርቪስ፣ ይህንኑ አሰራርና አደረጃጀት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል አመለካከት ያለው ሰራተኛ ከሌለ በስተቀር የልማት አላማዎቻችን በፍፁም እንደማይሳኩ ተገንዝበን ነው እየተንቀሳቀስን ያለነው:: እንደዚህ አይነቱ ሲቪል ሰርቪስ በአሁኑ ሰአት እንደሌለን ግልፅ ነው::

የአገራችን ሲቪል ሰርቪስ የድሃ አገር ሲቪል ሰርቪስ



ነው:: እያንዳንዷ ሳንቲም በቁጠባ ጥቅም ላይ ካልዋለች በስተቀር ልማታችን ሊፋጠን እንደማይችል የተገነዘበ ሲቪል ሰርቪስ መሆን አለበት:: መሰራት ያለባቸው ስራዎች እጅግ ብዙ የሆኑበት፣ እነዚህን ስራዎች ለመስራት ያለን ገንዘብና የሰው ሃይል እጅግ ውሱን የሆነበት አገርን የሚያገለግል ሲቪል ሰርቪስ ነው:: በዚሁ ሁኔታ ውስጥ የሚሰጥ ሲቪል ሰርቪስ እያንዳንዱን ስራ ካለው ልማታዊ አስተዋፅኦ አኳያ መድቦ ቅደም ተከተል በማውጣት ቅድሚያ ሊሰጣቸው በሚገባ ጉዳዮች ላይ አተኩሮ የሚረባረብ መሆን አለበት:: እንኳንና እንደኛ ባለ ድሃ አገር በበለፀጉት አገሮችም ቢሆን የመንግስት ገንዘብ መመዝበር፣ ሙስና የመንግስትን ልማታዊ አስተዋፅኦ ክፉኛ የሚያቀጭጭ፣ የህዝቡንና የልማታዊ ባለሃብቶችን ጥረት አስተጓጎሎ ጥግኝነትን የሚያስፋፋ የልማት ነቀርሳ እንደሆነ የታወቀ ነው:: ስለሆነም ሲቪል ሰርቪሳችን የመንግሰትን ገቢ በጥንቃቄ ሰብስቦ፣ እያንዳንዷን ሳንቲም ቆጥቦና የላቀ ልማታዊ አስተዋፅኦ ላላቸው ስራዎች ቅድሚያ ሰጥቶ የሚረባረብ ከሙስና የፀዳ የሰው ሃይል ያለው፣ ይህንን ለማድረግ የሚያስችል አሰራርና አደረጃጀት ያለው ሲቪል ሰርቪስ መሆን ይገባዋል:: በአሁኑ ወቅት እንደዚህ አይነቱ ሲቪል ሰርቪስ እንደሌለን ግልፅ ነው:: የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ያስቀመጥነውን የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታና የልማት አላማ ለማሳካት የሚያስችል የሰው ሃይል፣ አሰራርና አደረጃጀት ለመፍጠር ያግዛል ተብሎ የተቀረፀ ፕሮግራም ነው::

**3. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ይዘት፣**

የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም የአገራችን ሲቪል ሰርቪስ የልማትና የዴሞክራሲያዊ ስርአት አላማዎቻችንን በብቃት ለመፈፀም የሚችልና ያሉበትን መሰረታዊ ችግሮች ያስወገደ ሲቪል ሰርቪስ እንዲሆን ለማድረግ የታቀደና ይህንኑ ለማድረግ ያስችላሉ ተብለው የተገመቱ ንኡስ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን ያቀፈ ፕሮግራም ነው፡፡ ፕሮግራሙ በማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራተጂያችን ውስጥ የተቀመጡትን የአቅም ግንባታ ገፅታዎች ማለትም የአሰራርና አደረጃጀት ማስተካከልን፣ የሰው ሃይል በሚፈለገው መጠንና አይነት በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ እንዲገኝ ማድረግንና እነዚህን አቀናጅቶ ማስፈፀምን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ፕሮግራሙ እነዚህን መርሆዎች መሰረት በማድረግ በአምስት ንኡስ ፕሮግራሞች ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ነው፡፡ የመንግስት ወጭ አስተዳደር ንኡስ ፕሮግራም፣ የሰው ሃይል አስተዳደር ንኡስ ፕሮግራም፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራም፣ የስነ-ምግባር ንኡስ ፕሮግራምና የከፍተኛ አመራር ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራም ናቸው፡፡

### 3.1. የመንግስት ወጭ አስተዳደር ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራም፣

መንግስት ወጭውን የላቀ ልማታዊ አስተዋፅኦ ባላቸው ጉዳዮች ላይ በማተኮርና እያንዳንዷን ሳንቲም በቁጠባ ጥቅም ላይ ለማዋል በሚያስችል አኳኋን ማስተዳደር መቻል አለበት፡፡ የየዕለት ስራና ውጤት ብቻ ሳይሆን የመካከለኛና የረዥም ጊዜ እይታ ባለውና ቀጣይነት ያለውን ልማት ለማረጋገጥ በሚያስችል አኳኋን ማስተዳደር አለበት፡፡ ወጭውን በዚሁ መልኩ ለማስተዳደር



የሚያስችል የሰው ሃይል፣ የጠራ ቀልጣፋ አሰራርና አደረጃጀት ያለው ሲቪል ሰርቪስ ያስፈልገዋል፡፡ የመንግስት ወጭ አስተዳደር ንኡስ ፕሮግራም ሁሉንም የማስፈፀም አቅም ግንባታ ገፅታዎች አጣምሮ በመጠቀም አሁን ያለውን ሲቪል ሰርቪስ አሻሽሎ ከላይ የተጠቀሱትን ስራዎች ሊሰራ የሚችል ሲቪል ሰርቪስ እንዲሆን የማድረግ ግብ ያለው ንኡስ ፕሮግራም ነው፡፡

የመንግስት ወጭ ከላይ በተቀመጠው መልኩ በተግባር ላይ እንዲውል ይህንን ለማድረግ የሚያስችል ቀልጣፋ፣ የግልፅነትና የተጠያቂነትን መርሆ በተሟላ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል አሰራር መቀመጥ ይኖርበታል፡፡ የረጅምና የመካከለኛ ጊዜ ዕቅድን በማዘጋጀትና በዚሁ እቅድ መሰረት መፈፀም ያለባቸውን ስራዎች ቅደም ተከተል በመስጠት፣ የላቀ አስተዋፅኦ ላላቸው በበጀት አመዳደብ ረገድ ቅድሚያ በመስጠት ለመስራት የሚያስችል የበጀት አወጣጥ አሰራር መኖር አለበት፡፡ እያንዳንዱ የበጀት እቅድ የዛሬውን ውጤት ብቻ በማየት የሚፈፀም ሳይሆን የረጅምና መካከለኛ ጊዜ እይታ ባለው አኳኋን የሚታቀድና የሚፈፀም እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል አሰራር መኖር አለበት፡፡ እያንዳንዷ ሳንቲም በተቀመጠው እቅድና በጀት በትክክል በስራ ላይ መዋሏን ለማረጋገጥና ለመቆጣጠር በሚያስችል አኳኋን የተቀረፀ አሰራር መኖር አለበት፡፡ ይህ አሰራር በአንድ በኩል የተጠያቂነትና የግልፅነት መርህን ተግባራዊ ለማድረግ በሌላ በኩል ደግሞ የስራ ቅልጥፍናን ለማረጋገጥ የሚያስችል እንዲሆን ማድረግ አለበት፡፡

አሰራራችንን በዚሁ መልኩ ለማስተካከል የበጀት አስተዳደር ስርአቱን የሚገዙ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በዚሁ መልክ መቀረፅ ነበረባቸው፡፡ የበጀት እቅድ አዘገጃጀት ስርአቱ የተጠቀሰውን አላማ ለማሳካት የሚያስችል እንዲሆን ተደርጎ መቀረፅ ነበረበት፡፡ እነዚህን የህግና የመመሪያ ለውጦች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ብቃት ያለው ማንዋልም መዘጋጀት ነበረበት፡፡ የስራ ቅልጥፍናን በሂደት በይበልጥ በማረጋገጥ ስርአቱ በዘመናዊ የኮምፒውተር አገልግሎት የሚደገፍ መሆን ነበረበት፡፡ ተጠያቂነትና ግልፅነትን ለማስፈን የውስጥና የውጭ ኦዲት ስርአትን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል፣ በየደረጃው ያሉ በጀቱን የማፅደቅ ስልጣን ያላቸው ምክር ቤቶች በቁጥጥሩ ስራ ላይ በብቃት ሊሳተፉ የሚችሉበት ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስችል ሆኖ መዘጋጀት ነበረበት፡፡

ይህን የአሰራር ለውጥ ለማምጣት፣ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች ማንዋሎች ወዘተ. ለማዘጋጀት በውጭ ሙያተኞች በሰፊው የታገዘና በርካታ አመታትን የጠየቀ ስራ ተሰርቷል፡፡ ወሳኝ የሚባሉት የአሰራር ለውጦች አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ማንዋሎች ተዘጋጅተው በአብዛኛው ተግባራዊ መሆን ጀምረዋል፡፡ የአሰራር ለውጥን በተመለከተ የቀሩ ጉዳዮች ቢኖሩም ዋናው ስራ የተሻሻሉ አሰራሮችን የመቀየስ ጉዳይ አይደለም፡፡ የቀሩትን የማጠናቀቁ ስራ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋናው ስራ የተዘጋጁትን አሰራሮች በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ፣ በተግባር መፈተሽና በዚሁ ሂደት መሻሻል እንዳለባቸው የተረጋገጡትን በቀጣይነት የማሻሻል ጉዳይ ነው፡፡



የአሰራር ለውጡ ብቃት ካለው የሰው ሃይል ውጭ ሊፈፀም እንደማይችል እሙን ነው፡፡ በመሆኑም በስራው ላይ ያሉ ሰራተኞች በአዲሱ አሰራር ላይ የተሟላ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ ሰፊ ስልጠና መካሄድ ነበረበት፡፡ ስራውን በአግባቡ ለመፈፀም በስራ ላይ ያሉ ሰራተኞችን በአጫጭር ስልጠናዎች ለማሻሻል በሚደረግ ስራ ብቻ የሚቻል አይደለም፡፡ ሰፊ የሂሳብ ሰራተኛ የሰው ሃይልን በመደበኛ ፕሮግራሞች በብቃት ማሰልጠን የሚጠይቅ ነው፡፡ በስራው ላይ ያሉ ሰራተኞችን በስራ ላይ ስልጠና አቅማቸውን ለማሻሻል ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡ ይሁንና ይህ ጥረት ከፍተኛ የሙያተኛ እጥረት ባለባቸው መስሪያ ቤቶች ውስጥ የተካሄደ ስልጠና በመሆኑ የሰራተኛውን ብቃት ከማሻሻል አኳያ ሊያስገኝ የሚችለው ለውጥ የራሱ ውሱንነት የነበረው ነው፡፡ እንደዋነኛ ችግር ሊቀመጥ የሚችል ባይሆንም የስልጠናው ውጤታማነትና ጥራትም የሚሻሻል ነገር የሌለው የተዋጣለት ነበር ለማለት አይቻልም፡፡ ከሁሉም በላይ ግን በሂሳብ ስራና የሚፈለገውን ከፍተኛ፣ መካከለኛና ዝቅተኛ ሙያተኛ በሚፈለገው መጠንና አይነት ለማሰልጠን የሚያስችል የትምህርትና ስልጠና ስርአት ባልተዘረጋበት ወቅት የሚካሄድ ለውጥ በመሆኑ መሰረታዊ የሰው ሃይል ችግር ቀስፎ የያዘው ፕሮግራም ነበር ማለት ይቻላል፡፡

የወጭ አስተዳደር ስርአቱን ለማሻሻል በስርአቱ ውስጥ ያሉት አደረጃጀቶች፣ የውጭና የውስጥ ኦዲት አደረጃጀቶችንም ጨምሮ የተቀየሰውን የተሻሻለ አሰራር ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችል አኳኋን መስተካከል ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ አኳያ

የተሻሻሉ አደረጃጀቶች ምን መምሰል እንዳለባቸው በውል ለይቶ ለማስቀመጥ ሰፊ ስራ ተሰርቷል፡፡ ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግም የተለያዩ ሙከራዎች ተደርገዋል፡፡ ይሁንና አደረጃጀቶች ዞሮ ዞሮ ብቃት ባለው የሰው ሃይል ዙሪያ የሚፈጠሩ ነገሮች መሆናቸው አልቀረም፡፡ ከላይ እንደተገለፀው ፕሮግራሙ ከፍተኛ ብቃት ያለው የሰው ሃይል ችግር ያጋጠመው ፕሮግራም ነው፡፡ በመሆኑም አደረጃጀቱም ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተሟላ አኳኋን ተግባራዊ ሊሆን የቻለ አይደለም፡፡

ይህ ንኡስ ፕሮግራም ከሁሉም ንኡስ ፕሮግራሞች አስቀድሞ የተጀመረና በከፊልም ተግባራዊ መሆን የጀመረ ፕሮግራም ነው፡፡ በተለይም የተሻሻሉ አሰራሮችን ከመንደፍ አኳያ ረጅም ርቀት የተሄደበትና አጥጋቢ ስራ የተሰራበት ፕሮግራምም ነው፡፡ በዚሁ መልኩ ሲታይም ጥሩ ውጤት የተገኘበት ፕሮግራም ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ይሁንና ይህ ፕሮግራም እስካሁን የሲቪል ሰርቪስ ፕሮግራሙ በርካታ ችግሮች የተጠናወቱት እንደነበረ ግልፅ ነው፡፡ የፕሮግራሙን የቴክኒካዊ ገፅታ ብቻ በምናይበት ወቅት ስራው ከሰፊ የሰው ሃይል ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ጋር በቀጥታ ተያይዞ የተፈፀመ ስላልነበረ ሶስቱን የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራዎች አሟልቶና አቀናጅቶ ለመፈፀም የተቻለ አልነበረም፡፡ ስለሆነም በሚፈለገው መልክ የማስፈፀም አቅምን ለመፍጠር አልቻለም፡፡ ከዚሁ በተጨማሪ ሌሎች የሲቪል ሰርቪሱን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉ ስራዎች አብረውና በተቀናጀ አኳኋን ሊፈፀሙ ባልቻሉበት ሁኔታ ተግባራዊ መሆን የጀመረ ስለነበረ በተናጠል ሊያስገኝ ይችል የነበረው ውጤት የራሱ



ውሱንነት እንደነበረው የሚካድ አይደለም፡፡ ስለሆነም ምንም እንኳ የማይናቁ መሻሻሎች ያመጣና በተለይም ለቀጣዩ ስራችን የሚበጁ በርካታ ልምዶች ለመቅሰም ያስቻለን ጠቃሚ ፕሮግራም የነበረ ቢሆንም አፈፃፀሙን ቀይደው የያዙ ከላይ የተጠቀሱት መሰረታዊ ቴክኒካዊ ችግሮችም የነበሩት ንኡስ ፕሮግራም ነው፡፡

### 3.2. የሰው ሃይል አስተዳደር ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራም፣

ሲቪል ሰርቪሳችን ዞሮ ዞሮ ባለው የሰው ሃይል ጥራትና መጠን የሚወሰን አቅም ነው የሚኖረው፡፡ በመሆኑም የሲቪል ሰርቪሳችን የሰው ሃይል አስተዳደር ዘመናዊ እንዲሆንና ካስቀመጥነው የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታና የልማት እቅዳችን ጋር አብሮ እንዲሄድ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህን ለማድረግ ሲቪል ሰርቪሱ የሚተዳደርባቸው አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎች የሲቪል ሰርቪሱን መብትና ጥቅም ለማስከበር የስራ ተነሳሽነቱን ለማሻሻል በሚያስችል አኳኋን መሻሻል ነበረባቸው፡፡ የሰው ሃይሉ ምልመላና እድገት ፍትሃዊ በሆነ አኳኋንና የስራ ውጤትን በብቃት በመለካት ላይ የተመሰረተ መሆን ነበረበት፡፡ ሲቪል ሰርቪሱ የሚያስፈልገውን የሰው ሃይል በእቅድ ለመመልመል፣ ለማሰልጠንና ለማስተዳደር የሚያስችለው አሰራር መቀየስ ነበረበት፡፡ የሰው ሃይሉን በዚሁ መልኩ ለማስተዳደር ብቃት ያላቸው የሰው ሃይል አስተዳደር ሙያተኞችና አደረጃጀቶችም ማግኘት ነበረበት፡፡ የሰው ሃይል አስተዳደር ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራም እነዚህን ጉዳዮች ለማሟላት ይችላሉ ተብለው የተገመቱ ፕሮጀክቶችን የያዘ ንኡስ ፕሮግራም ነው የነበረው፡፡

በዚህ ንኡስ ፕሮግራም በተለይ አሰራሮችን ከማስተካከል አኳያ የሀገር ውስጥና የውጭ ሙያተኞችን ባሳተፈ አኳኋን ሰፊ የቅድመ ዝግጅት ስራ ሰርቷል፡፡ የሲቪል ሰርቪሱን መተዳደሪያ አዋጅ ለማሻሻል የሚያስችል ጥናት ተካሂዶ አዋጁ ተሻሽሏል፡፡ ሰራተኛውን ለማትጋት ያስችላሉ ተብለው የተገመቱ የደሞዝ ጭማሪን ጨምሮ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፣ በመሰራትም ላይ ናቸው፡፡ የሰራተኛው ምልመላና እድገት በብቃቱና በስራ ውጤቱ ላይ ብቻ የተመሰረተ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችሉ የተለያዩ አሰራሮችም ተቀምጠዋል፡፡ የስራ ውጤት መመዘኛ ስርአቱን ለማሻሻል የሚያስችሉ የአሰራር ለውጦችም ተነድፈዋል፡፡ በዚህም ለቀጣዩ ስራችን መነሻ የሚሆን በርካታ ስራ ተሰርቷል ማለት ይቻላል፡፡

ይሁንና በዚህ ፕሮግራምም ላይ ለቀጣዩ እንቅስቃሴያችን ማነቆ የሚሆኑ በርካታ ችግሮች መኖራቸው አልቀረም፡፡ ስራው ከሰው ሃይል ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ጋር በቅርብና በቀጥታ በተቀናጀ አኳኋን በመካሄድ ላይ ያልነበረ በመሆኑ በቀጣዩ የአፈፃፀም እንቅስቃሴ የራሱ ተፅእኖ ማሳረፉ የማይቀር ነው፡፡ ሲቪል ሰርቪሱን የማሻሻል ስራ የሰራተኛውን አመለካከትና እምነት ከማስተካከል ጋር ካልተያያዘ በስተቀር በቴክኒካዊ ማሻሻያዎች ብቻ የሚፈለገው አይነት የሲቪል ሰርቪስ ሰራተኛ ማግኘት የሚቻል አይሆንም፡፡ ንኡስ ፕሮግራሙም ሆነ ሲቪል ሰርቪሱ በአጠቃላይ ለለውጡ ፖለቲካዊ ገፅታና በዚህ ደረጃ መሰራት ላለበት ስራ በቂ ትኩረት የሰጠ አልነበረም፣ ስለሆነም



ለአፈፃፀሙ የተሟላ ዝግጅት ተደርጎ ነበር ሊባል አይችልም፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የስራ ውጤት መመዘኛን ለማሻሻል የተደረገው ጥረት እያንዳንዱ ሰራተኛ በስራ ውጤቱ በትክክል መመዘን እንዳለበት ተገንዝቦ ይህንን በጥብቅ ተግባራዊ ለማድረግ ቆርጦ ከተነሳ ሰራተኛና ሃላፊ መፍጠር ውጭ ብዙም ውጤት እንደማይኖረው መገመት የሚያዳግት አይሆንም፡፡

### 3.3. የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራም፣

የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራም ሲቪል ሰርቪሱ ለተጠቃሚው ቀልጣፋ በግልፅነትና በተጠያቂነት መርህ ላይ የተመሰረተ አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ የሚያስችሉ አሰራሮችና አደረጃጀቶችን ለመቅረፅ የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የሲቪል ሰርቪሱ የአገልግሎት አሰጣጥ መርሆዎችን የሚዘረዝሩ፣ ተጠቃሚው ምን አይነት አገልግሎት ከማን የማግኘት መብት እንዳለው የሚጠቁሙ፣ አገልግሎት የተጓደለበት ወይም የዘገየበት ተጠቃሚ አቤቱታ ስለሚያቀርብበት ሁኔታ ዝርዝር ፖሊሲዎችና መመሪያዎች የማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል፡፡ ይህ አሰራርን የመለወጥ ስራ በአገር ውስጥና በውጭ ሙያተኞች በአብዛኛው ከውጭ አገሮች ልምድ በመነሳት የተፈፀመ ቢሆንም በአገራችንም ሻል ያለ አገልግሎት ይሰጣሉ ተብለው የተገመቱ መስሪያ ቤቶች ልምድ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ በአፈፃፀም ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን ለይቶ ለማወቅ እንዲረዳም ንኡስ ፕሮግራሙ በተወሰኑ መስሪያ ቤቶች እንዲሞከር ተደርጎ የተገኘው ልምድ ተቀምሯል፡፡

የአገልግሎት አሰጣጡን ስርአት ለማሻሻል ለሰራተኛው ስለተሻሻለው አሰራር በቂ ስልጠና መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ጥራት ያለው ቀልጣፋ አገልግሎት የመስጠት እምነትና አመለካከት በሰራተኛው እንዲያድር ማድረግም ያስፈልጋል፡፡ ስለተሻሻለው ስርአት ሰራተኛው በቂ እውቀት እንዲኖረው ለማድረግ ያስችላሉ ተብለው የተገመቱ የማሰልጠኛ ፅሁፎች ተዘጋጅተዋል፡፡ በዚህ በኩል ሰራተኛው ሊይዘው የሚገባውን እምነትና አመለካከት መቅረፅን በተመለከተ ግን በአብዛኛው በሲቪል ሰርቪሱና በህብረተሰቡ ውስጥ በሚሰራ የፖለቲካ ስራ የሚሸፈንና መሸፈንም የሚገባው ነው፡፡

በሲቪል ሰርቪሱ የሚሰጠውን አገልግሎት ለማሻሻል፣ አሰራሩን ከማስተካከልና ሰራተኛውን ከማሰልጠን በተጨማሪ አደረጃጀቱን ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል አኳኋን ማስተካከል እንደሚያስፈልግም ይታመናል፡፡ ከዚህ አኳያ ጠቀሜታ አላቸው ተብለው የሚታመንባቸው የአደረጃጀት መርሆዎች ያሉ ቢሆንም ዝርዝሩ ከየመስሪያ ቤቱ ባህሪና ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር ተያይዞ የሚቀየስ እንጂ ሲቪል ሰርቪሱን በአጠቃላይ የሚሸፍን ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም አጠቃላይ መርሆዎች የተቀመጡ ቢሆኑም የአደረጃጀት ለውጦች ንኡስ ፕሮግራሙ ተግባራዊ በሚሆንበት ወቅት በዝርዝር መመለስ ያለባቸው ሆነው ይገኛሉ፡፡ ይህ ስራ ከፍተኛ ሙያና የስራ ልምድ የሚጠይቅ በመሆኑና በዚህ ረገድ በአገራችን ከፍተኛ የሙያተኛ እጥረት ያለ በመሆኑ፣ እንዲሁም አደረጃጀቶች ቅልጥፍናን ለማረጋገጥ



በሚያስችል አኳኋን ባልተስተካከሉበት ወቅት በሚሰጠው አገልግሎት ላይ መሰረታዊ ማሻሻያ ለማድረግ አስቸጋሪ በመሆኑ የንኡስ ፕሮግራሙን አፈፃፀም ሊጎዳ የሚችል ከፍተኛ ችግር ሆኖ ይታያል፡፡

የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራም እስከዛሬ ድረስ ቅድመ ዝግጅቶችን ከማጠናቀቅ አልፎ ተግባራዊ መሆን ያልጀመረ ፕሮግራም ነው፡፡ ይህ ንኡስ ፕሮግራም በአንድ መልኩ ሲታይ የአጠቃላይ የሲቪል ሰርቪሱ ንኡስ ፕሮግራም እምብርት ነው ሊባል ይችላል፡፡ የሲቪል ሰርቪሱ ማሻሻያ ፕሮግራም ዞሮ ዞሮ አላማው ለተጠቃሚው ቀልጣፋ ፍትሃዊና የግልፅነትና የተጠያቂነት መርህን የተከተለ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ ነው፡፡ ሌሎቹ ንኡስ ፕሮግራሞች ይህንን የሚደግፉና የሚያጠናክሩ ናቸው፡፡ በመሆኑም የአጠቃላይ ፕሮግራሙን ስኬታማነት ከሚወስኑት ንኡስ ፕሮግራሞች ውስጥ በዋነኛነት ሊጠቀስ የሚችል ይኸው ንኡስ ፕሮግራም ነው፡፡

ንኡስ ፕሮግራሙን ተግባራዊ የማድረግ ስራ በሚሰራበት ወቅት በሌሎች ንኡስ ፕሮግራሞችም ያጋጥማሉ ተብለው የተጠቀሱት ችግሮች በዚህኛውም ፕሮግራም ላይ ማጋጠማቸው የማይቀር ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዚህ ንኡስ ፕሮግራም ሊያጋጥም የሚችል ለየት ያለ ቴክኒካዊ ችግር ይኖራል፡፡ ንኡስ ፕሮግራሙን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ከአሰራር ለውጦችና ሰራተኛውን ከማሰልጠንና አመለካከቱን ከፕሮግራሞቹ አላማዎች አኳያ ከማስተካከል በተጨማሪ መስሪያ ቤቶችን ቀልጣፋ

አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል አኳኋን ማደራጀት ይጠይቃል። ይህንን ለመፈፀም የሚረዱ አጠቃላይ የአደረጃጀት መርሆች የተቀመጡ ቢሆኑም ስራው ከየመስሪያ ቤቱ አገልግሎት ጋር ተያይዞ መሰራት ያለበትና ከፍተኛ እውቀትና ልምድ የሚጠይቅ ስራ ነው። በአገራችን በዚህ ረገድ ልምድና ሙያው ያለው በቂ የሰው ሃይል የሌለ በመሆኑ ስራውን ለማስፈፀም ጠንካራ የውጭ ሙያተኛ ድጋፍ ያስፈልጋል። የውጭ ሙያተኛ በሚፈለገው መጠንና ጊዜ ለማግኘት የተለያዩ ችግሮች ስለሚኖሩና የውጭ ሙያተኞች የየመስሪያ ቤቱን የስራ ባህሪ ለመገንዘብ የሚወስድባቸው ጊዜ መኖሩ ስለማይቀር ይህም አፈፃፀሙን ሊያጓትት እንደሚችል መገመት ይቻላል። ስለዚህም የመስሪያ ቤቶች ቅደም-ተከተል አውጥቶ በዋናዎቹ ላይ አትኩሮ በመረባረብና በአፈፃፀሙ ሂደት የአገራችን ሙያተኞች እውቀቱንና ልምዱን እንዲያገኙ በመጣር ችግሩን ማቃለል ካልተቻለም በአጠቃላይ በፕሮግራሙ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያሳድር ይችላል።

**3.4. የከፍተኛ አመራር ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራም፣**

የሲቪል ሰርቪሳችን ብቃት ወደሚፈለገው ደረጃ ሊደርስ የሚችለው ከላይ ከተዘረዘሩት ስራዎች በተጨማሪ ብቃት ያለው ከፍተኛ አመራር ሲያገኝ፣ ከፍተኛው አመራር ስራው ስትራተጂያዊ አመራር መስጠት መሆኑን ተገንዝቦ በዚህ ተግባር ላይ ሲያተኩርና ይህንኑ ለማድረግ የሚያስችል ብቃት ሲኖረው ነው። በዚህ ደረጃ ላይ ያለው አመራር የመስሪያ ቤቱን አላማ፣



ራዕይና ግብ በትክክል አስቀምጦ፣ መስሪያ ቤቱ የሚሰራበትን የውስጥና የውጭ ሁኔታ በአግባቡ ተንትኖ፣ ተልእኮውን ለመፈፀም የሚያስፈልገውን የሰው ሃይልና ማቴሪያል ለይቶ የመንግስትን ፖሊሲ ውጤታማ፣ ቀልጣፋና ወጭን ቆጣቢ በሆነ መንገድ ለመፈፀም የሚያስችል እቅድ ማውጣት መቻል አለበት። የእቅዱን የአፈፃፀም ጉድለቶች ለማስተካከል፣ ጠንካራ ጎኖችን ለማዳበር በሚያስችል አኳኋን በተከታታይ የሚገመገም በግምገማው ላይ ተመስርቶ የማስተካከያ ርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስችል መሆን አለበት። ሰራተኛውን በነዚህ ዙሪያ በብቃት የሚያንቀሳቅስ፣ የሚያተጋና የሚቆጣጠር መሆን አለበት። በሲቪል ሰርቪሱና በፖለቲካው አመራር መካከል ያለው ድንበር ተለይቶ በሚገባ ተቀናጅተው የሚሰሩበትን ሁኔታ መፍጠር የሚችል መሆን አለበት። በመጨረሻም ይህን ስራ ለመስራት የጥናትና የምክር አገልግሎትን የሚፈጥርና በአግባቡ የሚጠቀም መሆን አለበት።

የከፍተኛ አመራር ማሻሻያ ፕሮግራምን ተግባራዊ ለማድረግ መነሻ ሊሆን ይችላል ተብሎ የተገመተና አሰራሩን በተወሰኑ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ከፍተኛ አመራር አካላት ተግባራዊ ለማድረግ የተደረገ ጥረት አለ። ከዚህ ጥረት ከፍተኛ ልምድ ተገኝቷል። በፖለቲካ አመራሩና በሲቪል ሰርቪሱ መካከል ያለውን ዳር ድንበር በውል ለይቶ ለማስቀመጥም የተለያዩ ርምጃዎች ተወስደዋል፣ በመወሰድም ላይ ናቸው። ይሁንና ንኡስ ፕሮግራሙ በአጠቃላይ ሲታይ በተሟላ አኳኋን ተግባራዊ መሆን ያልጀመረ ብቻ ሳይሆን ቅድመ-ዝግጅቶች ከማከናወንም አንፃር ገና ብዙ ርቀት ያልሄደ ሆኖ ይገኛል።

ከዚህ በፊት የተለመዱ የእቅድ ዝግጅትና ክትትል አሰራሮችን ፈትሾ፣ በ-ይለት ደረጃ በተወሰኑ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች የተሞከረውን ስራ ገምግሞ የእቅድ ዝግጅት፣ አፈፃፀምና ክትትል አሰራሩን ወጥነት ባለው አኳኋን ለማስተካከል የሚያስችል የአሰራር ለውጥ ስራ ገና ለወደፊቱ መካሄድ ያለበት ስራ ነው:: በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ ሁሉም ሰው የተመደበለትን ስራ ራሱን ችሎ በብቃት የሚፈፅምበት፣ ይህ ከተጠያቂነት መርህ ጋር ተያይዞ የሚከናወንበት የአሰራርና አደረጃጀት መስተካከል ገና ለወደፊቱ መሰራት የሚኖርበት ስራ ነው::

ከፍተኛ አመራሩን ለማሻሻል የሰው ሃይል ስልጠናና የምርምርና ጥናት አቅም ግንባታ ስራዎች ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ:: በዚህ ደረጃ በጣም ተፈላጊ የሚሆነው በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነና ልምድ ያለው ሰራተኛ ነው:: የዩኒቨርሲቲዎች መስፋፋትና ከዚህም ጋር ተያይዞ የድህረ-ምረቃ ትምህርት መስፋፋት የሚፈለገውን ሙያተኛ በማፍራት ረገድ ያለብንን ችግር በከፍተኛ ደረጃ እንደሚቀርፍ ይገመታል:: ይሁንና ይህ ስራ በመደበኛ ዩኒቨርሲቲዎች ብቻ ሊሸፈን የሚችል አይደለም:: በሲቪል ሰርቪሱ ብቻ የሚፈለጉ ለየት ያሉና ከፍተኛ ሙያ የሚጠይቁ የትምህርትና ስልጠና መስኮች መኖራቸው አይቀርም:: በዚሁ ክልል የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደርና የግብር አሰባሰብ ሙያን በምሳሌነት መጥቀስ ይችላል:: ሌሎችም በተመሳሳይ መልክ የሚታዩ የትምህርትና ስልጠና መስኮች ይኖራሉ:: ከዚህ በተጨማሪ የሲቪል ሰርቪሱን የአቅም ችግሮች በየጊዜው



እየገመገሙ አጫጭር ስልጠናዎችን በመስጠት መፈታት ያለባቸው ጉዳዮች ይኖራሉ:: እነዚህን አገልግሎቶች መስጠትን እንደዋነኛ ስራው የወሰደ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ማደራጀት በጣም ጠቃሚና አስፈላጊ ነው:: መንግስት ይህንኑ በመገንዘብና ከሌሎች አገሮች ልምድም በመማር የሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅን አቋቁሟል::

በአገራችን የተቋቋመው የሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በአንድ በኩል የክልሎችን ከፍተኛ የሰው ሃይል እጥረት በፍጥነት ለመፍታት የሚረዱ የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞችን እንዲፈፅም፣ በሌላ በኩል ደግሞ በሌሎች የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የማይሰጡ የድህረ-ምረቃ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት፣ የሲቪል ሰርቪሱን ፍላጎቶች እያጠኑ አጫጭርና ተከታታይ የስልጠና ፕሮግራሞችን በማዘጋጀትና የምርምርና ጥናት ስራዎችን በማከናወን ሲቪል ሰርቪሱን እንዲያጠናክር የተቋቋመ ድርጅት ነው:: የክልሎችን ፍላጎት ከማርካትም አኳያ ሰፊ ስራ ለመስራት ችሏል:: የሚሰጠው ትምህርት የጥራት ችግር ያለበት ቢሆንም የሙያተኛ እጥረት በየክልሉ እንዲቃለል ከማድረግ አኳያ የተጫወተው ሚና ግን በጣም ጠቃሚና ከፍተኛ እንደነበረ ግልፅ ነው:: አንዳንድ የድህረ-ምረቃ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀትና በማስፈፀም ረገድም ቀላል ግምት የማይሰጠው ስራ ሰርቷል:: ይሁንና በሲቪል ሰርቪሱ ስትራተጅካዊ አመራር መስጠት ላይ ተሳታፊ የሚሆኑ ሰዎችን በማስተማርና በተከታታይ ስልጠና በማሻሻል ረገድ ሊጫወት የሚገባውን ሚና ተጫውቷል ማለት አይቻልም:: በመጀመሪያ ዲግሪና ዲፕሎማ ደረጃ የሚሰጠው

ስልጠና ከዩኒቨርሲቲዎች መስፋፋት ጋር ተያይዞ አላስፈላጊ እየሆነ በመሄድ ላይ በመሆኑ፣ በዚህ ረገድ በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች በማይሰጡ ውሱን የትምህርት መስኮች ላይ ካልሆነ በስተቀር ሌላውን ደረጃ በደረጃ እየተወ የሚሄድበትን መንገድ መቀየስ አስፈላጊ ሆኖ ይታያል። ዋናው ትኩረት በሌላ ተቋም በማይሰጡ ትምህርቶች በተለይም የድህረ-ምረቃ ትምህርቶች ላይ እንዲሆን፣ ከዚህ ጎን ለጎን አጫጭርና ተከታታይ የማጠናከሪያ ስልጠናዎችን የማዘጋጀትና የመስጠት አቅም እንዲያዳብር፣ የምርምርና ጥናት ስራዎችንም እንዲሰራ ማድረግ ላይ ማትኮር ያስፈልጋል። ተቋሙን በሰው ሃይልና በቁሳቁስ ይህንን ስራ ለመፈፀም በሚያስችል መልኩ ማጠናከርም ያስፈልጋል። ይህን ስራ የሲቪል ሰርቪሱን ከፍተኛ አመራር ከማሻሻል ስራ ጋር በቅርብ የማስተሳሰሩ አስፈላጊነትም ጎልቶ የሚታይ ነው። በዚህ ደረጃ ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ስራ ካልተሰራ በስተቀር የሲቪል ሰርቪሱን ከፍተኛ አመራር በረጅምና መካከለኛ ጊዜም በሚፈለገው ደረጃ ለማጠናከር አስቸጋሪ ይሆናል።

የሲቪል ሰርቪሱን ከፍተኛ አመራር ለማሻሻል ከስራው ጋር የሚመጥን የምርምርና ጥናት አቅም መፈጠር አለበት። የመንግስት ፖሊሲዎችን ለማሻሻል የሚረዳ ጥናትና ምርምር፣ የፖሊሲ አፈፃፀምን ለማሻሻል የሚረዳ ጥናትና ምርምር፣ ሲቪል ሰርቪሱን በቀጣይነት ለማሻሻል የሚያስፈልግ ጥናትና ምርምር ወዘተ. መካሄድ አለበት።

እንደዚህ አይነት የጥናትና ምርምር አቅሞች በሲቪል



ሰርቪሱ ውስጥ ብቻ የሚቋቋሙ ሊሆኑ አይችሉም። ቀደም ብሎ እንደተገለፀው የሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅን ጨምሮ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አንዱ መሰረታዊ ተልእኳቸው እንደዚህ አይነቱን የጥናትና ምርምር ስራ መስራት ነው። ከዚህ በተጨማሪ በተወሰኑ የስራ መስኮች ላይ አትኩረው የጥናትና ምርምር ስራ የሚያካሂዱ የመንግስት ተቋሞች መፈጠር ይኖርባቸዋል። በዚህ መሰረት የግብርና ምርምር አቅማችንን ለማሻሻል፣ የህግ ጥናትና ምርምር ተቋምንና፣ የኢኮኖሚ ልማት ምርምር ተቋምን ለማደራጀትና ለማጠናከር የተሰሩ ስራዎች በምሳሌነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው። በነዚህ ላይ ተጨማሪ የሚሆኑ በየመንግስት መስሪያ ቤቱ የጥናትና ምርምር ስራ የሚሰሩ ተቋሞች ያስፈልጋሉ። እንደዚህ አይነቱን ሰፊ የጥናትና ምርምር አቅም ለመፍጠርና ለማጠናከር ከፍተኛ ጥረት ቢደረግም ገና ብዙ ስራ እንደሚቀረን ግልፅ ነው። በዚህ ደረጃ ያለው ዋነኛው ማነቆ ብቃት ያለው ተመራማሪ የሰው ሃይል እጥረት ስለሆነ ይህንኑ ከተያዘው የከፍተኛ ትምህርት ማስፋፋት እቅድ ጋር በተቀናጀ አኳኋን መፍታት ያስፈልጋል። ይህ ስራ በአጥጋቢ ሁኔታ ባልተሰራበት ወቅት የሲቪል ሰርቪሱን ከፍተኛ አመራር በሚፈለገው ደረጃ ማሻሻል አይቻልምና።

### 3.5. የስነ-ምግባር ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራም፣

ሙስና እጅግ ውስን የሆነውን የመንግስት ሃብት ለግለሰቦች ያለአግባብ መጠቀሚያ እንዲሆን በማድረግ

ልማታችንን ክፉኛ የሚፈታተነን፣ በግልፅነትና በተጠያቂነት መርህ እየተመራ ህዝብን የሚያገለግል ሲቪል ሰርቪስ እንዳይኖርና ሲቪል ሰርቪሱ ክፉኛ እንዲበላሽ የሚያደርግ፣ በልማት በጎ አስተዋፅኦ ካላቸው ባለሃብቶች ይልቅ ለጥገኞች የተመቻቸ ሁኔታ የሚፈጥርና በአጠቃላይም የስርአቱን የጥገኛ ዝቅጠት አደጋን የሚያቀላጥፍና የዚሁ አደጋ መገለጫም ስለሆነ መወገድና በቁጥጥር ስር መግባት ያለበት ጉዳይ እንደሆነ ግልፅ ነው:: በመሆኑም በሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራማችን ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት ለበርካታ አመታት ሲሰራበት የነበረ ጉዳይ ነው:: ይህንኑ አላማ ከዳር ለማድረስ የስነ-ምግባር ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራምና የዚሁ ማስፈፀሚያ የሆኑ የተለያዩ ፕሮጄክቶች ተቀርፀው ተግባራዊ ሆነዋል፣ በመሆንም ላይ ይገኛሉ::

ሙስናን በብቃት ለመዋጋት በዚሁ ተግባር ላይ የተሰማሩ ሰዎችን የዴሞክራሲ ስርአት በሚፈቅደው ህጋዊ አኳኋን ለፍርድ ማቅረብና የተጠያቂነት መንፈስን ማንገስ ይጠይቃል:: በዚሁ ተግባር ላይ የተሰማሩትን ሰዎች በህጋዊ መንገድ በብቃት ለመከታተልና ለመቅጣት በማይቻልበት ሁኔታ ሙስና ከቁጥጥር ውጭ መሆኑ በፍፁም የማይቀር ጉዳይ ነው:: በመሆኑም በንኡስ ፕሮግራሙ ውስጥ ትኩረት ከተሰጣቸው ዋነኛ ጉዳዮች አንዱ ሙስናን በህጋዊ መንገድ በብቃት የመዋጋት አቅማችንን የማሻሻል ስራ ነው::

ይህንኑ ለማድረግ በአገራችን ሙስና የሚበራከትባቸውን ስራዎችና የሚፈፀምባቸውን መልኮች ለማጥናት፣ ሙስናን በህጋዊ



መንገድ ለመዋጋት ዕንቅፋት የሚሆኑ የህግና የአደረጃጀት ችግሮችን ለመለየት ተሞክሯል:: በዚህ ረገድ ጥሩ ውጤት አስገኝተዋል ተብለው የሚታወቁት ሆንግ ኮንግና ሲንጋፖር በመሆናቸው ከነዚህ አገሮች ልምድ ለመማር ተከታታይና ውጤታማ ስራ ተሰርቷል:: ሙስናን በመዋጋት ግንባር ቀደም ሚና በመጫወት ላይ ካሉ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የልምድ ልውውጥና የሰው ሃይል ስልጠና ስራም ተሰርቷል:: በዚህ ሰፊ ጥናት ላይ በመመስረት ሙስናን በብቃት በመዋጋት በዚህ ስራ ላይ የሚያተኩር አንድ ጠንካራ ማዕከላዊ አካልን ማቋቋምና የህግ ማሻሻያ ስራዎችን መስራት እንደሚያስፈልግ ታምኖበት ይህንኑ ለመስራት የሚያስችል ስራ ተሰርቷል:: የውጭ ሙያተኞችንና የሌሎች አገሮች ልምድን በሰፊው በመጠቀም የማዕከላዊ አካል ማቋቋሚያ አዋጅና የህግ ማሻሻያ አዋጆች ተዘጋጅተው በተወካዮች ምክር ቤት እንዲፀድቁ ተደርጓል::

በተሻሻሉት አዋጆች መሰረት ተቋሙ ከተደራጀ በኋላ በቅድሚያ በፖለቲካ አመራር ቦታ ላይ የነበሩ በሙስና የተጨማለቁ ሰዎችን ለፍርድ ማቅረብ እንደሚያስፈልግ፣ ተጠያቂነት በመጀመሪያ ደረጃ በበላይ አካላት መጀመር እንዳለበት፣ በዚሁ ተግባር ላይ ለመሰማራታቸው መረጃ የተገኘባቸው ሰዎች ለፍርድ እንዲቀርቡ ተደርጓል:: ከዚሁ በማከታተልም ዋነኛ የሙስና ማዕከላት ተብለው በተገመቱ መስሪያ ቤቶች ላይ ያተኮረ የማጥራትና ተጠርጣሪዎችን ለፍርድ የማቅረብ ስራ በመካሄድ ላይ ይገኛል:: በዚህ መልኩም በሲቪል

ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራሞች ውስጥ ቀድመው ተግባራዊ መሆን ከጀመሩትና አጥጋቢ ውጤት ካስገኙት ንኡስ ፕሮግራሞች አንዱ የስነ-ምግባር ማሻሻያ ፕሮግራም ሊሆን በቅቷል። በሙስና ተግባር ላይ የተሰማሩ ሰዎችን ለህግ በማቅረብ የተጠያቂነት መንፈስን በማዳበርና ሙስናን በመዋጋት ረገድ ከእንግዲህ የሚቀር ነገር ቢኖር በተግባር የሚገኙትን ተሞክሮዎች እየቀመሩ ፀረ-ሙስና ኮሚሽኑን ማጠናከርና ተፈላጊ ሆነው የሚገኙትን የህግና ሌሎች ማሻሻያዎችን ማድረግ ነው።

ሙስናን በዚሁ ተግባር ላይ የተዘፈቁ ሰዎችን ለፍርድ በማቅረብ ብቻ በብቃት መዋጋት አይቻልም። በህዝቡ ውስጥ ሙስናን አጥብቆ የሚቃወምና በህጋዊ መንገድ ለመዋጋት ዝግጁ የመሆን እምነትና አመለካከት መቀረፅ አለበት። ሚዲያና ሌሎችም አካላት በተጨባጭ መረጃ ላይ ተመስርተው ሙስናን የሚዋጉበትና የሚያጋልጡበት ሁኔታ መፈጠር ይኖርበታል። ይህ ስራ በስነ-ምግባር ማሻሻያ ፕሮግራም ውስጥ የተካተተ ቢሆንም በአብዛኛው በትምህርትና ስልጠና ተቋሞች ውስጥ በሚካሄድ የስነ-ዜጋና የስነ-ምግባር ትምህርት መፈፀም ያለበት ነው። ሚዲያ በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ መጫወት የሚገባውን ገንቢ ሚና እንዲጫወት ለማድረግ በተያዘው ሰፊ የፖለቲካ ስራ ዕቅድ ውስጥ ተካቶ የሚፈፀም ነው። ከዚህ አኳያ የስነ-ምግባር ማሻሻያ ፕሮግራምን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበርና የስነ-ምግባር ትምህርቱና ስነ-ምግባርን በሚመለከት በሚዲያ ሊሰራ የሚገባው ስራ በቂ ትኩረት እንዲሰጠው የማድረግን ስራ ነው ሊሰራ የሚችለው።



ስነ-ምግባርን ለማሻሻል የሲቪል ሰርቪስ የስነ-ምግባር ኮድ ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ፣ ሃላፊዎች ንብረትና ገቢያቸውን እንዲያሳውቁ የማድረግ ስራ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት ከዚህ አኳያም መደረግ የሚገባው ቅድመ ዝግጅት በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል። እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ የግልፅነትን አሰራር በመንግስት ብቻ ሳይሆን በህብረተሰቡም ውስጥ መስፈኑ ሙስናን ለመከላከል ልዩ ፋይዳ ያለው መሆኑ ነው።

መንግስት የሚሰጠው አገልግሎት ምን እንደሆነ፣ ለማን? መቼ? እንዴት? እንደሚሰጥ በዝርዝር መመሪያ መልክ ተቀምጦ የመንግስት ሰራተኛውም ህዝቡም እንዲያውቀው ከተደረገ፣ በዚህ ረገድ የሚታዩ ጉድለቶችን ለማስተካከል የሚቻልበት የአቤቱታ አቀራረብ ስርአት ከተነደፈ ከዚህ በግልፅ ከተቀመጠ መመሪያ ውጭ ለመሄድና በሙስና ለመዘፈቅ ያለው ከፍተኛ ዕድል ይጠባል። መላው ህዝብ ገቢውና ንብረቱ ከታወቀ፣ አዲስ ገቢና ንብረት ሲያገኝ ግልፅነት በተላበሰ አኳኋን የሚታወቅ እንዲሆን ከተደረገ በሙስና ለመክበርና ለመጠቀም የሚደረግ ሙከራ ሁሉ በከፍተኛ ደረጃ እንደሚቀንስ እሙን ነው።

ሙስና በምስጢርና በድብቅ የሚፈፀም ወንጀል ነው። ከሌላው ወንጀልም በባሰ በተግባሩ ላይ የተሰማሩ ወገኖች ጉቦ ሰጪውና ጉቦ ተቀባዩ ወዘተ. መመካከርና መተማመን መቻል አለባቸው። በሙስና ያካበቱትን ሃብት የሚደብቅላቸውና እንዲጠቀሙበት የሚያስችላቸው ጫካ መኖር አለበት። በሰጪውና

በተቀባዩ መካከል መተማመን እንዳይፈጠር ለማድረግ የሚያስችል ሁኔታ ከተፈጠረ፣ ሙሰኛው ያካበተውን ሃብት ያለጠያቂ ሊጠቀምበት የሚያስችለው መደበቂያ ጫካ ከተመነጠረና ግልፅነት ከተስፋፋ ሙስና አብሮ የሚከስምበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ የሙስናን ጨለማ ማጥፋት የሚቻለው በላዩ ላይ የግልፅነት ብርሃን ደምቆ እንዲበራ በማድረግ ነው፡፡ ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የግልፅነት አሰራር በሁሉም መስኮች እንዲሰፍን ለማድረግ የሚያስችሉ አማራጮችን እያጠና ሊያቀርብ ይችላል፣ ይገባዋልም፡፡ ነገር ግን ስራው መላውን የኢኮኖሚ አሰራራችንንና የመንግስት አሰራርን የሚመለከት ስለሆነ ሁሉም የየበኩሉን አስተዋፅኦ ካላበረከተና ተቀናጅቶ በሙስና ላይ ካልዘመተ በስተቀር የሚፈለገው ውጤት ሊገኝ የሚችል አይሆንም፡፡ ይህ ጉዳይ ምን ያህል መሰረታዊ እንደሆነ የግብር ስርአቱን ለማሻሻል ከሚደረገው ጥረት ጋር ተያይዞ ከሚቀርበው ትንተና መረዳት ይቻላል፡፡ ቀጥለው ባሉ የፅሁፉ ክፍሎችም የሚዘረዘር ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ የስነ-ምግባር ማሻሻያ ፕሮግራሙ በራሱ ሊፈፅማቸው የሚችላቸው ዋና ዋና ተግባራት በአጥጋቢ ሁኔታ የተፈፀሙበት፣ የቀሩት ደግሞ ከሌሎች አካላት ጋር በመተባበርና በሌሎች መስኮች ከሚካሄዱ የለውጥ ርምጃዎች ጋር በመቀናጀት መፈፀም ያለባቸው ናቸው፡፡ የተሳካ ስራ የተሰራበትና በመሰራትም ላይ ያለበት ነው ሊባል ይችላል፡፡

## 4. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ቀጣይ ስራዎቻችን፣



በሚቀጥሉት ጊዜያት የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራምን በተሻለ ጥራትና ውጤታማነት ለመፈፀም እስካሁን የተሰሩ ስራዎችና በአፈፃፀም ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን መነሻ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተለይም በቀጣይ እንቅስቃሴያችን ማነቆ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የተለዩትን ነገሮች በአጭሩ ማስቀመጥና እነዚህን ለማስወገድ ልንከተላቸው የሚገቡትን አቅጣጫዎች ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡

### 4.1. ሲቪል ሰርቪሱን ማሻሻል መሰረታዊ ፖለቲካዊ ስራ መሆኑን መገንዘብ፣

ሲቪል ሰርቪሳችን ያስቀመጥነውን የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ አላማ ለማስፈፀምና ህዝቡን በአግባቡ ለማገልገል የሚችል እንዲሆን ለማድረግ ሰፊ የፖለቲካ ስራ እንደሚጠይቅ ተቀምጧል፡፡ የሲቪል ሰርቪሱን እምነትና አመለካከት ማስተካከል እንደሚያስፈልግ፣ ይህ ስራ በህብረተሰቡ ውስጥ በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ አንድ የጋራ አገራዊ አመለካከት ከመፍጠር ጋር ተያይዞ መፈፀም እንዳለበት፣ ይህ የፖለቲካ ስራ በመንግስት የሚካሄድና አመለካከትና እምነትን ከማስተካከል አልፎ የሚሄድ የድርጅት ስራ መስራትን የማያካትትና ማካተትም የሌለበት እንደሆነ ተቀምጧል፡፡ ባለፈው ጊዜ ሲሰራ የነበረው የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም በመሰረቱ ቴክኒካዊ ጉዳይ እንደሆነ በማየት ሊፈፀም የተሞከረና ይህም በመሆኑ መሰረታዊና ዘላቂ ለውጥ ለማምጣት የማይችል እንደነበር ተሰምሮበታል፡፡ ቀጣይ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራማችን እነዚህን ጉድለቶች በብቃት

የሚያስተካክል መሆን አለበት።

ከዚህ አኳያ በመጀመሪያ ደረጃ መሰራት ያለበት ስራ የሲቪል ሰርቪሱ ማሻሻያ ፕሮግራም፣ በአገራችን ልማትንና ዴሞክራሲን ለማረጋገጥ የተያዘው የመሰረታዊ ፖለቲካዊ ለውጥ እንቅስቃሴ አካል የሆነ፣ ከፍተኛ ቴክኒካዊ ገፅታ ቢኖረውም በመሰረታዊ ይዘቱ ፖለቲካዊ የሆነ ፕሮግራም እንደሆነ፣ ፕሮግራሙ በመሰረታዊ ይዘቱ ፖለቲካዊ ነው ሲባል ምን ማለት እንደሆነና ምንስ ማለት እንዳልሆነ ህዝቡና የሲቪል ሰርቪሱ አባላት በሚገባ እንዲገነዘቡ ማድረግ ነው። በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ከፍ ብሎ የቀረበው ትንተና ይህንን ለማድረግ ያስችላል ተብሎ ይገመታል።

ቀጥሎ ሊተኮርበት የሚገባው ጉዳይ ይኸው የፖለቲካ ስራ እንዴትና መቼ መሰራት እንዳለበት በውል ለይቶ ማስቀመጥና በተከታታይ ተግባራዊ ማድረግ ነው። ከረጅም ጊዜ አኳያ ሲታይ በየትምህርት ቤቱና በየስልጠና ተቋሙ የሚሰጠው የስነ-ዜጋና የስራ አመለካከትና ስነ-ምግባር ትምህርት ዋናው መሳሪያ እንደሚሆን መገመት ይቻላል። በዚህ መልኩ በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ አንድ አገራዊ የጋራ አመለካከት ይፈጠራል ብሎ መገመት ይቻላል። በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራው ሰው ወደፊት በዚሁ የትምህርትና ስልጠና ስርአት ያለፈ ስለሚሆን ከመቀጠሩ በፊት በሲቪል ሰርቪስ አባልነቱ ሊይዛቸው የሚገቡ እምነቶችና አመለካከቶችን ይይዛል ብሎ መገመት ይቻላል። ህብረተሰቡ በአጠቃላይ በትምህርትና ስልጠና ስርአቱ አማካኝነት



በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ አንድ የጋራ አመለካከትና እምነት ሲይዝ በሲቪል ሰርቪሱ አባላት ላይ ተፅዕኖውን በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ ማሳረፉ አይቀርም። የመንግስት አገልግሎት ተጠቃሚ ሆኖ ከሲቪል ሰርቪሱ ጋር በሚገናኝበት ወቅትም ሆነ በተለያዩ ማህበራዊ ግንኙነቶቹ አማካኝነት ህዝቡ ተፅእኖውን እያሳረፈ የሲቪል ሰርቪሱን እምነትና አመለካከት በመቅረፅ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያደርግ እሙን ነው። በመሆኑም ከረጅም ጊዜ አኳያ ዋናው መፍትሄ በትምህርትና ስልጠና ስርአቱ ውስጥ የሚካሄደውን የስነ-ዜጋና የስራ አመለካከትና ስነ-ምግባር ትምህርትን ማጠናከር ነው።

ከላይ የተጠቀሰው የረጅም ጊዜና ዘላቂ መፍትሄ ከማስገኘት አኳያ ወሳኝ ቢሆንም አሁን ለተጀመረው ስራ ይህን ያህል አስተዋፅኦ የሚኖረው ጉዳይ አይደለም። ስለሆነም በአሁኑ ወቅት በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ ሰፊ የፖለቲካ ስራ መሰራት አለበት። ይህ የፖለቲካ ስራ የአንድን ድርጅት አላማ ለማስረፅ የሚደረግ መሆን የለበትም። ይህ የድርጅቶች የራሳቸው ስራ እንጂ የመንግስት ተልዕኮ ሊሆን አይገባውም። ከዚህም አኳያ የሚካሄደው ስራ አገሪቱ የምትመራባቸውን ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች የማስረዳትና ህገ-መንግስቱንም የማስጨበጥ ስራን ማዕከል ያደረገ፣ መልካም የስራ ስነ-ምግባርን ለመፍጠር የሚያስችል መሆን አለበት። ሲቪል ሰርቪሱ የፖሊሲ አስፈፃሚ አካል እንደመሆኑ መጠን የሚያስፈፅመውን ፖሊሲ አብጠርጥሮ ሳያውቅ ስራውን በፍፁም ሊሰራ አይችልም። አገሪቱ የምትመራበትን ህገ-መንግስት በሚገባ ሳይጨብጥ ስራውን ሊሰራ

አይችልም። ስለሆነም ፖሊሲዎችንና ህገ-መንግስቱን ለማስረዳት ለማስጨበጥ፣ በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ የሲቪል ሰርቪስን ሚናና ሃላፊነት እንዲገነዘብ ለማድረግ የሚሰራው ስራ አመለካከቱንና እምነቱን ለማስተካከል ብቻ ተብሎ የሚሰራ ስራ ሳይሆን ከዚህ ውጭ ሲቪል ሰርቪሱ ሃላፊነቱን ሊወጣ የሚችልበት ምንም አይነት ሌላ አማራጭ ስለሌለም መሰራት ያለበት ነው።

በዚህ መሰረት በቅርቡ እንደተጀመረው የመንግስትን መሰረታዊ ፖሊሲዎች የሚያስረዱ ፅሁፎች እየተዘጋጁ መላው የሲቪል ሰርቪሱ አባል በሰፊውና በነፃ እንዲወያይባቸውና እንዲከራከርባቸው ማድረግ ያስፈልጋል። በተለያዩ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ሴሚናሮች አወደ-ጥናቶች ወዘተ. እየተዘጋጁ የሲቪል ሰርቪሱ አባል እውቀት እንዲዳብር መደረግ አለበት። ይህ በዘመቻ መልክ ተከናውኖ የሚያበቃ ሳይሆን ቀጣይነት ያለው መሆን ስላለበት ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የተለያዩ ስልቶች ተነድፈው ተግባራዊ መሆን አለባቸው በዚህ መሰረት ለምሳሌ አዳዲስ ሰራተኞች በሚቀጠሩበት ወቅት በፖሊሲ ጉዳዮች ላይ፣ በሲቪል ሰርቪሱ አሰራርና ስነ-ምግባር ላይ ወዘተ. ግልፅነት እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያስችል የትውውቅ ስልጠና ፕሮግራም ተዘጋጅቶ በቀጣይነት የሚሰጥበት ስርአት ሊፈጠር ይችላል፣ ይገባልም። ሰራተኞች የመንግስት መሰረታዊ አቅጣጫዎችና ፖሊሲዎች በአግባቡ ተቀናጅተውና ተጠርዘው ተዘጋጅተውላቸው በየጊዜው እነዚህን እየፈተሹና እያነበቡ ስራቸውን የሚሰሩበት ስርአትም ሊዘጋጅ ይገባል። ሌሎች አማራጮችም ሊቀርቡና በየጊዜው ሊዳብሩ ይችላሉ። ዋናው



ጉዳይ ይህ የመንግስት ፖሊሲዎችንና መሰረታዊ አቅጣጫዎችን የማስጨበጥ ስራ ቀጣይነት ያለው ስራ እንጅ የአንድ ጊዜ የዘመቻ ስራ ብቻ እንዳይሆን ማድረግ ነው።

የአንድን ሰው አመለካከትና እምነት ከመቅረፅ አኳያ የዕለት-ተዕለት ተግባርና ከዚህ የሚገኝ ልምድ ወሳኝነት እንዳለው ይታወቃል። የሲቪል ሰርቪሱን እምነትና አመለካከት የመቅረፁም ጉዳይ ከዚህ ተለይቶ የሚታይ አይሆንም። ሲቪል ሰርቪሱ የስራ እቅዱን ሲያወጣ የተቀመጡትን ፖሊሲዎችና አቅጣጫዎች መሰረት በማድረግና እነሱን ለማስፈፀም በሚያስችል አኳኋን ያወጣው መሆኑ መፈተሽ አለበት። የስራ አፈፃፀሙም ሲገመገም ከተቀመጠው ፖሊሲና አቅጣጫ አኳያ መፈተሽ ይኖርበታል። ሲቪል ሰርቪሱ በዴሞክራሲያዊ ስርአት የሚጠበቅበትን ስራ እየሰራ መሆኑ መገምገም ይኖርበታል። የእቅድ አወጣጥ፣ አፈፃፀምና ግምገማ በተቀመጡት ፖሊሲዎችና አቅጣጫዎች መሰረት መካሄዳቸውን በጥብቅ መቆጣጠር ሲቻልና በዚሁ መልክ ጥሩ የስራ ውጤት ሲገኝ ይኸው ተጨባጭ ተግባራዊ እንቅስቃሴ የሲቪል ሰርቪሱን አመለካከትና እምነት ከመቅረፅ አኳያ የላቀ ሚና ሊጫወት ይችላል። በመሆኑም ይህ ስራ በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ የሚሰራው ፖለቲካ ስራ ቁልፍ አካል ተደርጎ መወሰድ ይኖርበታል።

እነኚህ ስራዎች ሁሉ ባለቤት ሊኖራቸው ይገባል። በህብረተሰቡ በአጠቃላይ በሚዲያና በሌላም መልክ የሚካሄደው ስራ የራሱ ባለቤት ያለውና በተዘዋዋሪ መንገድ በሲቪል ሰርቪሱ

ላይ የበኩሉን በጎ ተፅእኖ የሚያሳርፍ ነው፡፡ በራሱ በሲቪል ሰርቪሱ ላይ በቀጥታ የሚሰራው የፖለቲካ ስራ መሰራት ያለበት በየመስሪያ ቤቱ ባሉ ሃላፊዎችና የፖለቲካ ተሿሚዎች ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ስራቸው ሲቪል ሰርቪሱ የመንግስትን ፖሊሲ የሚያስፈፀም እቅድ እንዲያወጣ በአግባቡ እንዲፈፅምና እንዲገመግም ማድረግ ነው፡፡ ይህ ስራ በአግባቡ ከተሰራ እዚያው ሳለም ቁልፍ የፖለቲካ ስራ አካል ነው ሊባል ይችላል፡፡ እነዚህ ሰዎች ስራቸው ሲቪል ሰርቪሱ የመንግስትን ፖሊሲ እንዲያስፈፅም በፖለቲካ ላይ የጠራ ግንዛቤ እንዲኖረው ተፈላጊው የስራ ስነ-ምግባርና ተነሳሽነት እንዲኖረው ማድረግ ነው፡፡ ይህም እዚያው ሳለ በሲቪል ሰርቪሱ የሚሰራው ዋነኛ የፖለቲካ ስራ ገፅታ ነው፡፡ በመሆኑም የፖለቲካ ስራው በፖለቲካ ተሿሚዎችና ከፍተኛ ሃላፊዎች መሰራት እንዳለበት ግልፅ ሊሆን ይችላል፡፡ ይልቁንም የነዚህ ሰዎች ስራ ከፍ ሲል እንደተጠቀመው በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ፖለቲካዊ ነው፡፡ ሌላ ስራ የላቸውም፡፡ የፖለቲካ ተሿሚዎች ይህንኑ ተገንዝበው በየመስሪያ ቤታቸው ይህንን ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ማድረግና መቆጣጠር የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራሙ አንድ መሰረታዊ ኣካል ተደርጎ መወሰድ አለበት፡፡

### 4.2. የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ስራ እንዲሰራ ማድረግ፣

ቅንጅትን በተመለከተ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ሶስት መሰረታዊ ችግሮች እንዳሉበት ተገልጿል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ በሶስቱ የአቅም ግንባታ ገፅታዎች ማለትም በሰው ሃይል፣



በአሰራርና አደረጃጀት ለውጦች መካከል፣ በተለይም የሰው ሃይል ስልጠናው ወደኋላ መቅረቱና አለመቀናጀቱ ያስከተለው ችግር አለ፡፡ የተለያዩ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ንኡስ ፕሮግራሞች በመካከላቸው እርስ በርስ የመመጋገብ ባህሪ ያላቸው ቢሆንም በአፈፃፀም ላይ ተቀናጅተው አለመሄዳቸው ያስከተለው ችግርም አለ፡፡ በመጨረሻም የአገራችን የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ስራ ሁለቱን ሲቪል ሰርቪሶች ማለትም የፌዴራልና የየክልሉን ሲቪል ሰርቪሶች መሸፈን፣ የሚገባውና ሁለቱን አቀናጅቶ መፈፀም የሚገባው ሆኖ ሳለ በአብዛኛው በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ላይ የታጠረ ፕሮግራም መሆኑ ፕሮግራሙን ክፉኛ ሊጎዳ የሚችል ነው፡፡

የማስፈፀም አቅም ግንባታን ሶስት ገፅታዎች አቀናጅቶ ከማስፈፀምና ከነዚህ ውስጥ ወደኋላ የቀረውን የሰው ሃይል የማሟላት ስራ አብሮ እንዲራመድ የማድረግ ስራ በሁለት ደረጃ ተከፍሎ ሊታይ የሚችል ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ አሁን በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ ያለውን የሰው ሃይል አመዳደብ የማስተካከልና በአጫጭር ስልጠናዎች ብቃቱን የማሻሻል ጉዳይ ነው፡፡ ከሲቪል ሰርቪሱ ውጭ ብቃት ያለው የሰው ሃይል የማፈላለግና ከትምህርት ስልጠና ፕሮግራም መመልመል ረጅም ጊዜ ሊወስድ የሚችል ነገር ነው፡፡ እንደአሰራር ተገቢ የሚሆነውም በመጀመሪያ ደረጃ በእጅ ያለውን የሰው ሃይል በላቀ ደረጃ መጠቀም ነው፡፡ በመሆኑም ቅድሚያ የሚሰጣቸው የሲቪል ሰርቪስ መደቦች ተለይተው ያለውን የሰው ሃይል በማሸጋሸግ ማሟላት፣ ያለቦታቸውና ከሙያቸው ውጭ የተመደቡ ሰዎች ካሉ ምደባቸውን ማስተካከል፣

በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ ላሉ ሰራተኞች በአግባቡ የተደራጀና ብቃቱ የተረጋገጠ ተከታታይ የአጫጭር የስራ ላይ ስልጠና ፕሮግራሞችን እያዘጋጁ ማሰልጠን፣ ብቃቱን ማሻሻል በቅድሚያ ሊሰራ የሚገባው ስራ ነው:: የሚመለከተው መስሪያ ቤትና የማስፈፀም አቅም ግንባታ ሃላፊዎች ይህንኑ ስራ በክልልም በፌዴራልም ደረጃ በሰፊው መስራት እንዳለባቸው ሊገነዘቡ ይገባል:: ይህ የምደባና የስልጠና ስራ ከሚካሄደው የአሰራርና አደረጃጀት ማስተካከያ እንቅስቃሴ ጋር በቀጥታ የተያያዘ፣ የሰው ሃይሉ ይህንኑ ለውጥ እንዲያውቀውና ለውጡን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችለው ብቃት እንዲያገኝ ለማድረግ የታቀደ መሆን አለበት::

በአሁኑ ወቅት በእጅ ያለውን የሰው ሃይል በላቀ ደረጃ ለመጠቀም መሞከር ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ቢሆንም በዚሁ አማካኝነት የሲቪል ሰርቪሱን የሰው ሃይል ችግር መፍታት እንደማይቻል በጣም ግልፅ ነው:: በተለይም በክልሎችና ከዚያ በታች ባሉ ዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች እጅግ ሰፊ የሰው ሃይል ክፍተት ስላለ ያለውን በማሸጋሸግ ብቻ ረጅም ርቀት መሄድ አይቻልም:: ከትምህርትና ስልጠና ስርአቱ በተለይም ከቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋሞችና ከዩኒቨርሲቲዎች የሚመለመል የሰው ሃይል ከፍተኛ ግምት ሊሰጠው ይገባል:: እነዚህ ተቋሞች ከአጭር ጊዜ አኳያ የመንግስትን የሰው ሃይል ፍላጎት ለማሟላት ስራ ቅድሚያ መስጠት እንዳለባቸው ተቀምጧል:: ይህንን መሰረት በማድረግ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚያስፈልጋቸውን የሰው ሃይል በመጠንና በአይነት



ለይተው በማስቀመጥ ይህንኑ ፍላጎታቸውን በትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሙ በተቻለ ፍጥነት እንዲያሟሉ ማድረግ መቻል አለባቸው:: ይህ ስራም በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ በመካሄድ ላይ ካለው የአሰራርና የአደረጃጀት ለውጥና ከአጠቃላዩ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ጋር በቅርብ የተቀናጀና ይህንን ለማስፈፀም የሚችል ብቃት ያለው የሰው ሃይል ለማፍራት እንዲያስችል ተደርጎ የተቀረፀ መሆን አለበት::

እስከአሁን ድረስ በሲቪል ሰርቪሱ ማሻሻያ ፕሮግራም ውስጥ ሲሰራ የነበረው ስራ በዋነኛነት የቅድመ ዝግጅት ስራ ነው:: እስካሁን የተሰሩ የአፈፃፀም ስራዎች ቢኖሩም ፕሮግራሙ በሰፊው ወደ ተግባር ተሸጋግሯል ሊባል የሚችል አይደለም:: አብዛኞዎቹ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች በአሁኑ ወቅት በመጠናቀቅ ላይ ያሉ በመሆናቸው ዋና ዋናዎቹን ንኡስ ፕሮግራምች አቀናጅቶ ተግባራዊ ለማድረግ ይቻላል:: ከዚህም አኳያ በፕሮግራሞቹ መካከል ያለውን ተመጋጋቢነት ዘርዝረንና ለይተን በማስቀመጥ በምን አይነት ቅደም ተከተልና ትስስር መፈፀጸም እንዳለባቸው የሚያሳይ፣ ጊዜንና ገንዘብን በሚቆጥብ አኳኋን የተሻለ ውጤት ለማስገኘት የሚያስችል የተቀናጀ የአፈፃፀም እቅድ ማዘጋጀት አለብን:: አፈፃፀሙም እንደዚሁ የተቀናጀ መሆን አለበት:: የማስፈፀም አቅም ግንባታ ሃላፊዎች በየደረጃው የተቀናጀ እቅድ መዘጋጀቱንና አፈፃፀሙም መቀናጀቱን ማረጋገጥ አለባቸው::

የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም በክልልና በፌዴራል ደረጃ በተቀናጀ አኳኋን እንዲፈፀም ለማድረግ በቅድሚያ ወደኋላ

የቀረው የክልሎች ፕሮግራም መቀላጠፍ አለበት። በፌዴራል ደረጃ የተሰራው ቅድመ ዝግጅት በአብዛኛው በክልሎችም የሚሰራ በመሆኑ ተፈላጊ የሆኑ አንዳንድ ማስተካከያዎች ታክለውበት የክልሎች የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም እቅድ መዘጋጀት አለበት። በዚህ ረገድ የፌዴራል አካላት የላቀ ሚና መጫወትና ክልሎችን ማገዝ ይኖርባቸዋል። በየክልሉ ፕሮግራሙን ለማስፈፀም የሚያስፈልገው የሰው ሃይል በአግባቡ ተደራጅቶ ስራውን መጀመር አለበት። አፈፃፀሙን በክልልና በፌዴራል ደራጃ ለማቀናጀት በየአካባቢው ከሚገኙ ልምዶች ለመማር የፌዴራልና የክልል የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም አስፈፃሚ አካላት በቅርብ እየተደጋገፉ የሚሰሩበት ስርአት መፈጠር ይኖርበታል።

**4.3. ፕሮግራሙን አሳታፊ በሆነ መንገድ መፈፀም፣**

ተደጋግሞ እንደተብራራው የሲቪል ሰርቪሱ ማሻሻያ ፕሮግራም ያስቀመጥናቸውን መሰረታዊ የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ አላማዎች ለማስፈፀም የሚያስችል አቅም የመገንባት ጉዳይ ነው። መላውን ህዝብ የሚመለከትና የሚነካ ጉዳይ ነው። ፕሮግራሙ በርካታ ቴክኒካዊ ገፅታዎች ያለውና ሊኖረውም የሚገባ ቢሆንም በመሰረታዊ ይዘቱ ፖለቲካዊ ነው። በፖለቲካዊ ይዘቱ መላውን ህዝብ የሚነካና የሚመለከት ጉዳይ ነው። ይህን ያህል መሰረታዊ ትርጉም ያለው ስራ በሚፈለገው መጠን ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው ሁሉም አስተዋፅኦ ማድረግ የሚችል ወገን ሚናውን ሲጫወት ብቻ ነው። በመሆኑም ፕሮግራሙ የተወሰኑ ሙያተኞች ስራ ተደርጎ መወሰድ የለበትም።



ሰፊ ተሳትፎን የሚጠይቅና በእንደዚህ አይነቱ ተሳትፎ ላይ በመመስረት ብቻ መፈፀም ያለበት ነው። አሳታፊ በሆነ መንገድ መፈፀም ያለበትም ነው።

መሳተፍ የሚገባቸው ሁሉ እንዲሳተፉበት ለማድረግ የመጀመሪያው ጉዳይ መላው ህዝብ በፕሮግራሙ መሰረታዊ አለማና ይዘት ላይ ግልፅነት እንዲኖረው የማድረግ ጉዳይ ነው፡ ማንኛውም ወገን በማያውቀው ጉዳይ ላይ ሊሳተፍ ስለማይችል ቀድሞ መምጣት ያለበት ጉዳይ የማሳወቅ ጉዳይ ነውና። በርግጥ እያንዳንዱ ዜጋ የፕሮግራሙን ዝርዝር ቴክኒካዊ ገፅታ ማወቅ አለበት ማለት አይደለም። ይህ የሚቻልም አይደለም፣ የህዝቡን ተሳትፎ ለማረጋገጥም አስፈላጊ አይደለም። የፕሮግራሙ መሰረታዊ አላማና ግቦች፣ ፕሮግራሙ ለልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስራችን ያለው ፋይዳ፣ የፕሮግራሙ መሰረታዊ ይዘቶች ከተገለፁ ለአብዛኛው ሰው በቂ ነው። በመሆኑም በዚህ ፅሁፍ ላይ የሰፈሩትን ነገሮች ህዝቡ እንዲያውቃቸው ማድረግን በመነሻነት በመጠቀም በጉዳዩ ላይ ህብረተሰቡ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረውና ለፕሮግራሙ ተፈፃሚነት የየበኩሉን ድርሻ እንዲያበረክት ማነሳሳት ያስፈልጋል። በየደረጃው ያሉ የመንግስት ሃላፊዎች ይህንን ስራ መስራት ይኖርባቸዋል።

ከህዝቡ አጠቃላይ ተሳትፎ በተጨማሪ በየደረጃው ያሉ የመንግስት ሃላፊዎችና የፖለቲካ ተሿሚዎች ፕሮግራሙን በማስፈፀም ረገድ ቁልፍ የአመራር ሚና መጫወት አለባቸው በየደረጃው ያሉ የማስፈፀም አቅም ግንባታው ሃላፊዎች

ፕሮግራሙን የመምራትና የማስተባበር ሃላፊነት ሲኖርባቸው፣ ሌሎች የመንግስት ሃላፊዎች ደግሞ ፕሮግራሙ በየመስሪያ ቤታቸው ሲፈፀም አመራር የመስጠት ሃላፊነት አለባቸው:: ከዚህ በመነሳት በዚህ ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎች ስለፕሮግራሙ ይዘትና አላማ ጠለቅ ያለ እውቀት ማግኘት አለባቸው:: እንደየሁኔታው ከፕሮግራሙ ቴክኒካዊ ገፅታዎችም ቢያንስ የተወሰኑትን በሚገባ መጨበጥ አለባቸው:: አጠቃላይ ህዝቡ ከሚኖረው ግንዘቤ የላቀና የጠለቀ እውቀት ያስፈልጋቸዋል::

የፖለቲካ ተሿሚዎቹ ራሳቸው ስለፕሮግራሙ በቂ ግንዛቤ ከያዙ በኋላ ህዝቡን የማሳወቅና በፕሮግራሙ አፈፃፀም ላይ በየደረጃው ተሳታፊና ደጋፊ እንዲሆን የማድረግ ስራ መስራት ይኖርባቸዋል:: የመንግስት ሰራተኞች ስለፕሮግራሙ የጠለቀ እውቀት እንዲኖራቸው፣ ይህን እንደሁኔታው የፕሮግራሙ ቴክኒካዊ ገፅታም የሚጨምር እንዲሆን የማድረግ ስራ መስራት አለባቸው:: በዚህ ላይ ተመስርተው በየስራ መስካቸው የተሟላ የአፈፃፀም እቅድ መውጣቱን፣ መፈፀሙንና በየጊዜው እየተገመገመ መስተካከሉን የማረጋገጥ ስራ መስራት ይጠበቅባቸዋል:: በአጠቃላይ በየደረጃው ያሉ የፖለቲካ ተሿሚዎች ፕሮግራሙን የመምራት ሃላፊነት እንዳለባቸው ተገንዝበው የተሟላ የፖለቲካ አመራር መስጠት መቻል አለባቸው::

ህዝቡ በየደረጃው ያሉ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ፕሮግራም ሃላፊዎችና ሌሎችም የፖለቲካ ተሿሚዎች ከላይ እንደተገለፀው የየራሳቸው ሚና አላቸው፣ ሚናቸውን ይጫወታሉ ተብሎም ይገመታል:: ዞሮ ዞሮ ግን ፕሮግራሙን የሚያስፈፅመውና



የሚፈፅመው ሲቪል ሰርቪሱ፣ በዚህ ውስጥ የታቀፈው የመንግስት ሰራተኛ ነው:: ይህ ሰራተኛ ስለፕሮግራሙ ጥልቅና የተሟላ ግንዛቤ እንዲይዝ፣ ለፕሮግራሙ መሳካት ቆርጦ እንዲነሳ ከማድረግ ውጭ የተሳካ አፈፃፀም ሊኖር አይችልም:: ስለሆነም በፕሮግራሙ አላማና ግቦች እንዲሁም በይዘቱ ላይ ጠለቅ ያለ እውቀት እንዲኖረው ማድረግ ያስፈልጋል:: ከዚህም አልፎ በሚፈፅማቸው የፕሮግራሙ ክፍሎች ላይ ዝርዝር ቴክኒካዊ ገፅታዎችን በሚጨምር መልኩ እንዲያውቃቸው መደረግ ይኖርበታል:: በዚህ ላይ ሰፊ የማብራራትና የማሳመን ስራ ከተሰራ በኋላ እቅዱ ተዘጋጅቶ ሰራተኛውም ስለእቅዱና እቅዱን ለመፈፀም ከእያንዳንዱ ሰው ስለሚጠበቀው ነገር በቂ እውቀት እንዲኖረው መደረግ አለበት:: በእቅዱ አፈፃፀም ሂደት ከሚገኘው ልምድ በበቂው እንዲማር የሚያስችሉት መድረኮችም ሊፈጠሩለት ይገባል:: የፕሮግራሙ አፈፃፀም የሰራተኛውን ሰፊና ሁለገብ ተሳትፎ በማረጋገጥ ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት::

### 4.4. ፕሮግራሙ ረጅም ጊዜ የሚጠይቅ ፕሮግራም መሆኑን የተገነዘበ አፈፃፀም እንዲኖር ማድረግ፣

የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራሙ የረጅም ጊዜ ተከታታይ ስራ የሚጠይቅ ፕሮግራም ነው:: ለዘመናት የቆየ አሰራርና አመለካከትን በአዲስ አመለካከትና አሰራር ለመቀየር የሚካሄድ ትግል በመሆኑ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሁሉም ነገር ተስተካክሎ ሊያልቅ አይችልም:: ለረጅም ጊዜ የማያቋርጥ ጠንካራ ስራ በመስራት ነው እንደዚህ አይነቱ መሰረታዊ የባህልና የአመለካከት ለውጥ ሊመጣ የሚችለው:: ፕሮግራሙን በተሳካ

ሁኔታ ለመፈፀም ሰፊ የሰው ሃይል ስልጠና ስራ መጠየቁ አይቀርም። ይህን በተሟላ መልኩ ለመፈፀም የራሱ ጊዜ መጠየቁ የማይቀር ነው። ከዚህም ባሻገር የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስራችን እየተሳካ ሲሄድ በዚያው መጠን በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ ለውጥ ማምጣትን የሚጠይቅ መሆኑ አይቀርም። ከሁኔታዎች እድገት ጋር አብሮ የሚሄድ ለውጥ መጠየቁ አንዱ ጉዳይ ሆኖ ይህንኑ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ሁኔታም በእድገቱ በራሱ መፈጠሩ የማይቀር ነው። ይህ ለውጡ የረጅም ጊዜ ለውጥ እንዲሆን የሚያደርግ አንድ ምክንያት ነው። ለውጡን ለማምጣት ከፍተኛ ልምድና ሙያ የሚጠይቁ ስራዎችን መስራት የሚያስፈልግ መሆኑና በዚህ ደረጃ ከፍተኛ እጥረት ያለብን መሆኑ ለሂደቱ መርዘም ተጨማሪ ምክንያት ይሆናል።

ፕሮግራሙ የረጅም ጊዜ ተከታታይ ጥረትን የሚጠይቅ ፕሮግራም መሆኑን መገንዘብ በአፈፃፀሙ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ የሚያሳድር ጉዳይ ነው። ለውጡ በአጭር ጊዜ ውስጥ መጥቶ ሁሉም ነገር ተመቻችቶ የሚሰራበት ሁኔታ ይፈጠራል በሚል እምነት ህዝቡና አስፈፃሚ አካላት በዚህ ፕሮግራም ላይ እንዲሳተፉ ከተደረገ በተጨባጭ ሊሆን የማይችል ነገርን በመጠበቅ የሚሰሩት ስራ ስለሚሆን በአንድ መልኩ ነገሮች በይድረስ ይድረስ ተሰርተው ታጥቦ ጭቃ መሆንን ያስከትላል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለውጡ በአጭር ጊዜ ሳይመጣ ሲቀር ተስፋ የመቁረጥ ነገር ሊከሰትና መካሄድ የሚገባውን ተከታታይ ጥረት ሊያስተጓጉል ይችላል። የረጅም ጊዜ ተከታታይ ጥረት የሚጠይቅ ስራ መሆኑ አስቀድሞ ተሰምሮበት የሚካሄድ ሲሆን ግን ከላይ የተዘረዘሩትን ችግሮች



አስወግዶ ፕሮግራሙን በተሳካ ሁኔታ ለመፈፀም ይቻላል።

ስራው የረጅም ጊዜ ተከታታይ ጥረት የሚጠይቅ ስራ መሆኑ ሲሰመርበት በአጭር ጊዜ ላይደርስልን ምን አላላጠን የሚል ስሜት መፈጠር ያለበት አይደለም። ይልቁንም ሊያመልክት የሚገባው ይህንኑ ረጅም ጊዜ መጠየቁ የማይቀር ስራ በተሳካ ሁኔታ ለመፈፀምና መሆን ከሚገባው በላይ ጊዜ እንዳይወስድ ከወዲሁ ባለን አቅም ሁሉ መረባረብ እንዳለብን፣ ይህንኑ ርብርብ ግባችንን እስክንመታ ድረስ ባለሚቋረጥ መቀጠል እንዳለብን ነው። የአጭር ርቀት ሩጫ ሳይሆን የማራቶን ሩጫ መሆኑን ተገንዝበን ከወዲሁ ባለን አቅም መረባረብ መጀመርንና ይህ ርብርብ የረጅም ጊዜ ርብርብ መሆኑን ታሳቢ ያደረገ ስልት ተነድፎለት እንዲፈፀም ማድረግን የግድ የሚል ነው።

በዚሁ መሰረት ፕሮግራሙ በአጠቃላይ ተቀናጅቶ መከናወኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በእያንዳንዱ ምዕራፍ የላቀ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ነገሮች የትኞቹ እንደሆኑ ለይተን መስራት የሚጠበቅብን ይሆናል። በአሁኑ ወቅት በብቃት ሊሰራ የሚችለው በመሰራቱ ምክንያት ለፕሮግራሙ በአጠቃላይ መሳካት ለረጅም ጊዜ ጥረታችን ዋስትና መሆን የተሻለ አስተዋፅኦ የሚኖረውን ስራ ለይተን በዚሁ ላይ አተኩረን መረባረብ፣ በዚህ መልኩ በአንድ ምዕራፍ ያገኘነው ጥሩ ውጤት ለሚቀጥለው ምዕራፍ መረማመጃ እንዲሆን በማድረግ በተከታታይ ስራዎች ድምር ውጤት የምንፈልገው ደረጃ ላይ የምንደርስበትን አካሄድ መከተል አለብን። በመሆኑም ቁልፍ ተግባርን ለይቶ የመረባረብና የአንዱ

ምዕራፍ ስራ ለሌላው መነሻ እንዲሆን አድርጎ መቀየስ ልዩ ግምት የሚሰጠው የእቅድ አወጣጥና አፈፃፀም አቅጣጫ ይሆናል፡፡

የሙያተኛ እጥረት ፕሮግራማችንን በማጓተት ረገድ ሊያስከትል የሚችለውን ችግር የመቅረፉም ጉዳይ ከዚሁ ከረጅሙ ጊዜ እይታ አኳያ መፍትሄ ሊበጅለት ይገባል፡፡ በዚሁ መሰረት ከአጭር ጊዜ አኳያ የተቻለውን ያህል የውጭ ሙያተኛ በስፋትና በብቃት መጠቀም ይኖርብናል፡፡ ሙያተኞቹ ቁልፍ ሚና ስላላቸው ልዩ ግምት ሊሰጣቸው ይገባል ተብለው በተለዩ የፕሮግራሙ ክፍሎች ላይ አተኩረው ስራቸውን እንዲሰሩ መደረግ አለበት፡፡ በራሳችን አቅም መስራት መልመድ ዋናው ነገር ቢሆንም ከሁሉም በላይ የሚታየው ግን የላቀ ጥራት ያለው ስራ ሰርተን አላማችንን ከዳር ለማድረስ የሚያስችል ዘመናዊ ሲቪል ሰርቪስ መፍጠር ነው፡፡ በመሆኑም ጥራቱ የተጠበቀ ስራ ለመስራት ተፈላጊ ሆኖ የተገኘ ሙያተኛ አስፈላጊ ሆኖ እስከተገኘበት ጊዜ ድረስ የውጭ ሙያተኛ መጠቀምን እንደ አንድ መሰረታዊ አቅጣጫ መውሰድ ይኖርብናል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን የራሳችንን የሙያተኛ አቅም ለመፍጠር ሰፊ ስራ መስራት ይኖርብናል፡፡ የውጭ ሙያተኞችም ስራቸውን በሚያካሂዱበት ጊዜ ተተኪ ኢትዮጵያውያን ሙያተኞች የማፍራትን ጉዳይ እንደ አንድ መሰረታዊ ግብ ወስደው እንዲሰሩበት መደረግ ይኖርበታል፡፡ የውጭ ሙያተኞቹ የአጭሩን ጊዜ ስራ በብቃት ሰርተው ለቀጣዩ ምዕራፍ የተመቻቸ ሁኔታ ከመፍጠር ባሻገር በዚሁ ሂደት ተተኪ ኢትዮጵያውያን ሙያተኞችን አፍርተው በቀጣዮቹ ምዕራፎች ስራውን በራሳችን ሙያተኞች በሰፊው የምንሰራበት ሁኔታ እንዲፈጥሩልን መደረግ



አለበት፡፡

በአሁኑ ወቅት በንኡስ ፕሮግራም ደረጃ ተቀርፀው በመፈፀም ላይ ያሉት ከላይ የተዘረዘሩት አምስት ንኡስ ፕሮግራሞች መሆናቸው በሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ውስጥ ሊታቀፉ የሚችሉት እነዚህ ብቻ ናቸው ማለት አይደለም፡፡ ራሳቸውን ችለው በመፈፀም ላይ ያሉ እንደ መንግስት ግብር አሰባሰብ ማሻሻያ ፕሮግራም ያሉት ፕሮግራሞች በባህሪያቸው የሲቪል ሰርቪሱ ማሻሻያ ስራ አካል ተደርገው ሊወሰዱ የሚችሉ ናቸው፡፡ ለወደፊቱም የተለያዩ ፕሮግራሞች ተቀርፀው እንደሚፈፀሙ አያጠራጥርም፡፡ በአምስቱ ንኡስ ፕሮግራሞች ላይ የታጠረ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ መቀረፁ ዋና ዋናዎቹን ለመለየትና አፈፃፀሙንም የቀለለ ለማድረግ እንጂ የፕሮግራሙን ዳር ድንበር ለመከለል እንዳልሆነ ሊሰመርበት የሚገባ ነው፡፡

**5. የመንግስት የግብር አሰባሰብ ማሻሻያ ፕሮግራም፣**

**5.1. የመንግስት የግብር አሰባሰብ ማሻሻያ ፕሮግራም አላማዎች፣**

ማንኛውም መንግስት አላማውን ለማስፈፀም የሚያስፈልገውን ወጭ ለመሸፈን ግብር ያስከፍላል፣ ይሰበስባል፡፡ አስቀድሞ የተገነባ የበለፀገ ኢኮኖሚና የዳበረ ዴሞክራሲ ያላቸው አገሮችም ቢሆኑ ሰፊ የግንባታ ተልዕኮ ባይኖራቸውም የተለያዩ መንግስታዊ አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚያስፈልጋቸውን ወጭ ለመሸፈን ከፍተኛ ግብር ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡ እኛ የተለመዱትን መንግስታዊ አገልግሎቶችን ከመስጠት ባሻገር ሰፊ የልማትና

የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ተልእኮም ስላለን ይህንኑ ለማስፈፀም የሚያስችል ገቢ መሰብሰብ ይኖርብናል:: ከዚህ ውጭ ያስቀመጥነው አላማ ሊሳካ አይችልም:: መንግስታት ግብር የመጣልና የመሰብሰብ ብቃታቸው ይለያያል:: የመንግስታት ብቃት አንዱ መሰረታዊ መመዘኛ ተደርጎ የሚወሰደውም ይኸው የመንግስትን ግብር የመሰብሰብ ብቃት ነው:: በዚሁ ረገድ የመንግስታችን ብቃት እጅግ በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የሚካድ አይደለም::

እንደ ስዊድን ባሉ የበለፀጉ አገሮች መንግስታት በአገራቸው ከሚመረተው ጠቅላላ ገቢ ውስጥ እስከ ስድሳ በመቶ የሚሆነውን በተለያዩ የመንግስት ግብሮች ለመንግስት ገቢ እንዲሆን በማድረግ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋሉ:: ይህ መጠን በሁሉም አገሮች በአለፉት አስር አመታት እየቀነሰ የመጣ ቢሆንም በአውሮ- የበለፀጉ አገሮች ከጠቅላላ ገቢያቸው ከአርባ እስከ ሃምሳ በመቶ የሚሆነው በግብር መልክ ለመንግሰት ገቢ የሚደረግ ነው:: ደካማ መንግስታት ባሉበት በአፍሪካም ቢሆን መንግስታት ከጠቅላላ አገራዊ ገቢያቸው ከሃያ አምስት በመቶ የማያንሰውን በግብር መልክ ለመንግስት ገቢ ያደርጋሉ:: በአገራችን የሚሰበሰበው ግን በአፍሪካ በአማካይ ከሚሰበሰበው ከግማሽ በታች ነው:: ከአገራችን ጠቅላላ ገቢ ውስጥ በግብር መልክ ፈሰስ እየተደረገ ያለው ከአስራ ሁለት በመቶ የሚበልጥ አይደለም:: በመንግስት ግብር አሰባሰብ ብቃት ረገድ በአለም የመጨረሻ ከሚባሉት ውስጥ ሆነን እንገኛለን::



በእንደዚህ አይነቱ ከመጠን በላይ ዝቅተኛ በሆነ የመንግስት የገቢ መሬት ላይ የሚገነባ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት ሊታሰብ አይችልም። እስካሁን ድረስ በዚህ ችግር ምክንያት መንግስት እንደትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ማስፋፋት፣ የመሰረተ-ልማት አውታሮችን መዘርጋት የመሳሰሉ በጣም መሰረታዊ የመንግስት ስራዎችን በሚፈለገው ፍጥነት ለመስራት ሳይችል ቀርቷል:: ይህ የአሁኑ ብቻ ሳይሆን የወደፊት እድገታችንን ከማቀጨጭ አንፃር ምን ያህል ከፍተኛ ተፅእኖ አንዳሳደረ መገመት አያስቸግርም:: የልማት ስራዎቻችን ሁሉ በከፍተኛ የፋይናንስ እጥረት ተተብትበው በሚፈለገው ፍጥነት መራመድ ሳይችሉ ከመቅረታቸውም ባሻገር የተሰራውም ስራ በከፍተኛ ደረጃ በውጭ ብድርና ርዳታ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ስለሆነም አስተማማኝነቱ አጠያያቂ እንዲሆን አድርጎታል። በሂደት በገቢ አሰባሰብ ረገድ ቢያንስ ሌሎቹ የአፍሪካ አገሮች ወደደረሱበት ደረጃ ካልደረስን የፋይናንስ ችግሩ እየተባባሰ ሄዶ አገሪቱን ለከፋ ቀውስ ሊዳርጋት እንደሚችል መገመት አያስቸግርም::

የምንሰበስበው የግብር ገቢ ይህን ያህል በጣም ዝቅተኛ የሆነው የተጣለው ግብር ከመጠን በላይ ዝቅ ያለ በመሆኑ አይደለም:: የተጣለው ግብር ከሌሎች ብዙ አገሮች የግብር መጠን ጋር ተመሳሳይ ነው:: ከዚህ አኳያ በአንዳንድ መስኮች የተጣለው ግብር ይቀንስ እንደሆነ እንጅ መጨመር ያለበት አይደለም:: ዋናው ችግራችን የግብሩ መጠን መቀነስ ሳይሆን ግብር ከፋዩ ግብሩን አለመክፈሉ ነው:: መንግስት ከሚሰበሰበው ግብር ወደ ሰማንያ በመቶ የሚሆነውን የሚከፍሉት የተለያዩ

የመንግስት አካላትና ሰራተኞች ናቸው:: ሌላው እጅግ የሚበዛው ግብር ከፋይ አንድም ጠቅላላውን ግብር አይከፍልም፣ አለያም የሚከፍለው ግብር መክፈል የሚገባውን ያህል አይደለም:: በመሆኑም በአንዳንድ መስኮች የግብሩን መጠን ቀንሰን መክፈል የሚገባው ሁሉ እንዲከፍል ብናደርግ የምናሰባስበው ገቢ በከፍተኛ ደረጃ ሊያድግና ሌሎች የአፍሪካ አገሮች ወደደረሱበት ደረጃ በሂደት መድረስ ይቻላል:: ስለሆነም ምንም እንኳ በተወሰኑ መስኮች የተወሰነ የግብር ቅናሽ ማድረግ ሊታሰብ የሚገባው ጉዳይ ቢሆንም ዋናው ትኩረት የግብር አሰባሰቡን በማሻሻል ላይ መሆን አለበት:: የመንግስት ግብር አሰባሰብ ማሻሻያ ፕሮግራም የሚያስፈልግበት አንዱ መሰረታዊ ምክንያትና የፕሮግራሙ አንዱ መሰረታዊ አላማ መንግስት ስራውን እንዲሰራ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ገቢ ለማስገኘት ይሆናል::

ግብር የመጣልና የመሰብሰብ ስራ አስፈላጊ የሚሆነው የመንግስትን ገቢ ለማሳደግ ብቻ አይደለም:: መንግስታት ኢኮኖሚውን ለመምራትና ለመቆጣጠር የሚጠቀሙበት አንድ ቁልፍ መሳሪያ በመሆኑም ጭምር ነው:: መንግስታት የግብር መጠንን በመጨመር ወይም በመቀነስ፣ ከዚህ ጋር ተያይዞ የመንግስትን ወጪ በተለይም የመንግስት ብድርን በመጨመርና በመቀነስ የኢኮኖሚውን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠርና ለመምራት ይችላሉ:: በመሆኑም ፊስካል ፖሊሲ እየተባለ የሚታወቀው ይህ አሰራር መንግስታት ከሚጠቀሙባቸው ሁለት ዋነኛ የኢኮኖሚ መሳሪያዎች አንዱ ሆኖ ይገኛል:: መንግስታት ከዚህም አልፈው ግብርን የህብረተሰቡን ገቢ ለማመጣጠን ይጠቀሙበታል:: ለአንዱ



ግብር ጨምረው ለሌላው ግብር በመቀነስ የተሻለና ፍትሃዊ የገቢ ክፍፍል እንዲኖር ያደርጋሉ:: መንግስት ሊያደፋፍራቸው ለሚፈልጋቸው የስራ መስኮች ግብርን መቀነስ፣ ሊያደፋፍራቸው በማይፈልጋቸው የስራ መስኮች ላይ ግብር በመጨመር እድገቱን አቅጣጫ ለማስያዝም ይጠቀምበታል::

ከላይ በተጠቀሰው አኳኋን ፊስካል ፖሊሲን እንደ አንድ ትልቅ የኢኮኖሚያዊ አመራር መሳሪያ ለመጠቀም የሚቻለው ብቃት ያለው የግብር አሰባሰብ ስርአት ሲኖር ነው:: ግብር ከፋዩ ምንም አይነት ግብር ቢጣል በሚፈለገው መጠን ግብር የማይከፍል ከሆነ ግብር በመጨመርና በመቀነስ ኢኮኖሚውን ለመምራት የሚቻልበት ዕድል እጅግ በጣም አነስተኛ ይሆናል:: ፊሲካል ፖሊሲው ብቃት ያለው ጥርስ የሌለው ፖሊሲ ሆኖ ይቀራል:: በጣም ግርድፍና በጣም ውሱን ውጤት ያለው ፊስካል ፖሊሲ ብቻ ሆኖ ይቀራል:: በመሆኑም የመንግስት ግብር አሰባሰብ ማሻሻያ ፕሮግራማችን አንዱ መሰረታዊ አላማ ብቃት ያለው ውጤታማ የፊስካል ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሁኔታን መፍጠር ይሆናል::

የልማት አላማችን ልማታዊ ባለሃብቶችን በማደፋፈር ላይ የተመሰረተ ነው:: በልማት ተግባር ላይ አንዳች አይነት በጎ አስተዋፅኦ የሌላቸውን ባለሃብቶችና ጥገኝነትን በማስቀረት ላይ የተመሰረተ ነው:: የመንግስት ግብር አሰባሰብን ማሻሻል ጥገኝነትን ከማዳከምም አኳያ ከፍተኛ ፋይዳ ሊኖረው ይችላል:: የተለያዩ ተቋሞችና ፋብሪካዎች ያቋቋሙ ባለሀብቶች ንብረታቸውን

መደበቅ ስለማይችሉ ይብዛም ይነስም ግብር ለመክፈል ይገደዳሉ፡፡ አየር በአየር ነጋዴው ግን ገቢውንና ንብረቱን በቀላሉ መደበቅ ስለሚችል ግብር ሳይከፍል ይቀራል፡፡ ይህ አሰራር በተጨባጭ ልማታዊ ባለሃብቱን ጎድቶ የአየር በአየር ነጋዴውን የሚጠቅም ነው፡፡ ሁሉም ግብር እንዲከፍል ለማድረግ የሚያስችል ሁኔታ ከተፈጠረ ሚዛኑን ማስተካከል ጥገኝነትንም ማዳከም ይቻላል፡፡ ከታች እንደሚዘረዘረው ጠንካራ የግብር አሰባሰብ ስርአት በሚኖርበት ወቅት ግልፅነትን በማስፈን ጥገኝነትን ለማዳከም የኢኮኖሚውን አጠቃላይ ቅልጥፍና ለማሻሻል ይረዳል፡፡ በመሆኑም የመንግስት ግብር አሰባሰብ ማሻሻያ ፕሮግራማችን ሌላው አላማ ፀረ-ጥገኝነት ትግላችንን ማገዝ ይሆናል፡፡

### 5.2. የመንግስት ግብር ስርዓትና የንብረትና ገቢ ማሳወቅ ስርአት፣

የገበያ ኢኮኖሚ በወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚ ነው፡፡ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ለኢኮኖሚው ተዋናዮች ሁሉ በዝቅተኛ ወጭና በቀላሉ የሚዳረስበት ሁኔታ ሲፈጠር መረጃ በሰፊው እየፈሰሰ የኢኮኖሚው ቅልጥፍና በከፍተኛ ደረጃ ይሻሻላል፣ እድገቱም የተፋጠነ ይሆናል፡፡ እንደዚህ አይነቱ የመረጃ ፍሰት በሌለበትና ግልፅነት ባልሰፈነበት ሁኔታ ግን የኢኮኖሚው ቅልጥፍናና እድገት በዚሁ ምክንያት ተተብትቦ መያዙ የማይቀር ይሆናል፡፡ የብዙዎቹ የበለፀጉ አገሮች የኢኮኖሚ እድገት ዋነኛ አንቀሳቃሽ ሞተር ዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጅ ሆኖ የሚገኝበት አንዱ መሰረታዊ ምክንያትም ይኸው ነው፡፡



በአገራችን የታክስ ስርአትን ለማሻሻል ወሳኝ ሚና ከሚጫወቱት ጉዳዮች አንዱ የእያንዳንዱን ዜጋ ገቢና ንብረት የሚመለከት ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡ እንደዚህ አይነቱ መረጃ በሚኖርበት ወቅት ማን ምን ያህል ግብር መክፈል እንዳለበት በአስተማማኝነት ሊታወቅ ይችላል፡፡ በግብር አከፋፈል ረገድ የሚታየውን ሙስና በወሳኝ መልኩ ማስቀረት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ገቢና ንብረቱ የተከፈለውም ግብር፣ በይፋ የሚታወቁ ስለሚሆኑ በዚህ ረገድ የሚደረግ የማጭበርበር ስራ በቀላሉ የሚታወቅና የሚስተካከል ይሆናልና፡፡ መክፈል የሚገባውን ግብር ሳይከፍል የቀረ ሰውም በይፋና በግልፅ ስለሚታወቅ ተከታትሎ ለማስከፈል እጅግ የቀለለ ይሆናል፡፡

የእያንዳንዱ ሰው ንብረትና ገቢ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ በይፋ የሚታወቅ በሚሆንበት ወቅት ሙስናን ለመዋጋትም እጅግ በጣም የተሻለ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ በአሁኑ ወቅት የማንም ሰው ንብረትና ገቢ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ አለ ማለት አይቻልም፡፡ በዚህ ረገድ ግልፅነት ሳይሆን ጥቅጥቅ ጫካና ጨለማ ነው ያለው ማለትም ይቻላል፡፡ ሙሰኞች የዘረፉትን ዘርፈው እዚህ ጫካ ውስጥ ነው የሚደበቁት፡፡ ዘርፈው ያገኙትን ንብረት በህጋዊ መንገድ ከተገኘው ከሌላው ንብረት ለመለየትም ሆነ፣ ማን ምን አይነት ገቢና ንብረት እንዳለው በማይታወቅበት ሁኔታ ውስጥ ተዝናንተው ሊጠቀሙ የሚችሉበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ የእያንዳንዱ ሰው ገቢና ንብረት ውቅታዊና ትክክለኛ መረጃ የሚገኝና በይፋ የሚታወቅ ቢሆን ግን በሙሰኞች ለተዘረፈ ንብረትና ገቢ መደበቅያ የሚሆን ነገር አይኖርም፡፡ ህጋዊ ምንጭ

የሌለው ገቢና ንብረት ተጎልጉሎ የሚወጣበትና አስፈላጊው ርምጃ ሊወሰድ የሚችልበት የተመቻቸ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

የእያንዳንዱ ሰው ገቢና ንብረት ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ ቢኖር ለፋይናንስ ስርአታችን መጠናከር በጣም ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ እያንዳንዱ ሰው በህግ እውቅና ያገኘ ትክክለኛና ወቅታዊ የንብረትና ገቢ መረጃ ስላለው፣ ለዚሁ ተጨማሪ ማረጋገጫ ሳያስፈልገው ይህንኑ በዋስትና አስይዞ ተበድሮ ስራውን ለማስፋፋት በጣም የቀለለ ይሆንለታል፡፡ ባንኮችም ማን ምን ገቢና ንብረት እንዳለው በይፋና በአስተማማኝ መንገድ ስለሚያውቁ በዚሁ አስተማማኝ መረጃ ላይ ተመስርተው በቂ ብድር ለመስጠት፣ በብድር አሰጣጥና አሰባሰብ ላይ የሚያጋጥመውን በጣም ከፍተኛ ውጣ ውረድና የሚፈፀመውን ሙስና ለማስቀረት ይችላሉ፡፡ የፋይናንስ ስርአታችንን ቀልጣፋነት ውጤታማነትና ጤንነት ከማረጋገጥ አኳያ ከእንደዚህ አይነቱ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ አቅርቦት የማረጋገጥ ስራ የላቀ አስተዋፅኦ ማድረግ የሚችል አንዳችም ሌላ ነገር አይኖርም፡፡ የፋይናንስ ስርአቱ በዚህ መልክ በከፍተኛ ደረጃ ሲሻሻል ለኢኮኖሚያዊ እድገታችን የሚኖረው አስተዋፅኦ በጣም ከፍተኛ እንደሚሆን ግልፅ ነው፡፡ እንደዚህ አይነቱ መረጃ በሌሎች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችም ላይ ተመሳሳይ በጎ ተፅእኖ ይኖረዋል፡፡

የእያንዳንዱ ዜጋ ንብረትና ገቢ ትክክለኛ ወቅታዊ መረጃ መኖሩና ይህም በይፋ የሚገኝ መረጃ መሆኑ ለግብር አሰባሰብ፣ ሙስናን ለመዋጋትና፣ የኢኮኖሚውን ቅልፍናና እድገት ለማሻሻል



ይህን ያህል ቁልፍ ሚና የመጫወት ቢሆንም የእንደዚህ አይነቱ መረጃ አቅርቦት ማረጋገጥ ጉዳይ በቀላሉ የሚፈፀም አይደለም፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ በአገራችን ባህልና ልምድ ብዙው ሰው ገቢውንና ንብረቱን መደበቅ እንጂ ማሳወቅ አይፈልግም፡፡ ይፋ የሆነ የገቢና ንብረት መረጃ መኖሩ ለንብረቱና ገቢው መንግስታዊ እውቅናና ዋስትና በመስጠትም ሆነ ከዚህ ጋር ተያይዘው በሚገኙ ጥቅሞች ግለሰቡ እንደሚረዳ አይገነዘብም፡፡ ስለሆነም እያንዳንዱ ዜጋ እንደዚህ አይነቱን መረጃ ማቅረብን የሚፈልግበትንና ይህንኑ ተግባራዊ የሚያደርግበትን ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ከዚሁ በተጨማሪ ለዜጎች ገቢና ንብረት ህጋዊ እውቅና መስጠትና መመዝገብ፣ ይህም ቀጣይ በሆነ ሁኔታ ወቅታዊነቱን የጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል ስርአት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡

በጣም የሚበዛው ዜጋ ስለንብረቱና ገቢው ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ መስጠት በማይፈልግበት አገር ዜጋው ራሱን ይህንን መረጃ ስራዬ ብሎ ወደሚያቀርብበት ደረጃ ለመሸጋገር የሚያስችለንን አማራጭ ለመሻት ሙስናን ለመዋጋት ከሌሎች አገሮች ልምድ በመማር ያደርግናቸውን የህግ ለውጦች በመነሻነት መውሰድ ያስፈልጋል፡፡ ከተደረጉት ቁልፍ የህግ ለውጦች አንዱ በሙስና የተጠረጠረው ሰው ገቢውንና ንብረቱን በህጋዊ መንገድ ያገኘው መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ የመንግስት ሳይሆን የግለሰቡ እንዲሆን መደረጉ ነው፡፡ መንግስት ምንጩ ያልታወቀ ንብረት በሙስና የተገኘ መሆኑን ለማረጋገጥ በተለይ በኛ አገር ሁኔታ እጅግ በጣም አስቸጋሪ እንደሚሆንና ሙስናን በህጋዊ መንገድ ለመታገል ያለውን ዕድል በጣም እንደሚያጠበው ገሃድ ነው፡፡

ምንጩ ያልታወቀን ገቢና ንብረት በህጋዊ መንገድ የተገኘ መሆኑን የማረጋገጥ ሃላፊነት የባለንብረቱ ሲሆን ግን በዚሁ መልክ ባለንብረቱ ማረጋገጫ ያላቀረበለትን ገቢና ንብረት በህገ-ወጥ መንገድ የተገኘ እንደሆነ አድርጎ ስለሚወስድ ሙስናን ለመዋጋት የተሻለ ዕድል ይፈጥራል፡፡

ግብር ያልተከፈለበት ንብረትና ገቢም በተመሳሳይ መልኩ እንዲታይ ሊደረግ ይችላል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ማንም ዜጋ ግብር የመክፈል ህጋዊ ግዴታ እንዳለበት ሊሰመርበት ይገባል፡፡ ይህን ህጋዊ ግዴታ ለመፈፀም የገቢውንና የንብረቱን ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ መስጠት አለበት፡፡ እንደዚህ አይነቱን መረጃ ካላቀረበ ግብር የመክፈሉን ግዴታ ሊወጣ አይችልም፡፡ ስለሆነም ይህንን መረጃ በህጋዊ የምስክርነት ቃል መልክ ለመንግስት እንዲሰጥ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ትክክለኛ መረጃ የሌለው ሰው የሃሰት የምስክርነት ቃል እንደሰጠ ወንጀለኛ የሚቆጠርበትና በዚሁም ምክንያት ከፍተኛ ቅጣት የሚከተልበት ሁኔታ እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ ግለሰብ ንብረቱንና ገቢውን በትክክለኛ መንገድ እንዲያሳውቅና እንዲያስመዘግብ፣ በዚህም ላይ ተመስርቶ ግብር እንዲከፍል በህግ ሲጠየቅ፣ ከዚህ ውጭ ሆኖ የተገኘ ገቢና ንብረት ምን ይሆናል የሚለውም ጥያቄ ሊመለስ ይገባዋል፡፡ ህጋዊ እውቅና ያልተሰጠውና ህጋዊ ግብር ያልተከፈለበት ንብረትና ገቢ ህገ ወጥ ገቢ እንደሆነ ተቆጥሮ ሊወረስ ይገባዋል፡፡ እንደዚህ አይነቱ ንብረትና ገቢ የተገኘበት ሰውም በሙስና ተጠያቂ መሆን ይኖርበታል፡፡ እንደዚህ አይነቱ ህጋዊ አሰራር ቢቀረፅ፣ ሁሉም



ዜጋ ለገቢውና ለንብረቱ ህጋዊ እውቅና ለማስገኘት፣ ከመወረስና በሙስና ከመጠየቅ ለመዳን ሲል በራስ ተነሳሽነት ትክክለኛ መረጃ የሚሰጥበት የተመቻቸ ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡

እንደዚህ አይነቱ ስርአት ተግባራዊ መሆን በሚጀምርበት ወቅት ለዘመናት በህጋዊም ሆነ በህገ-ወጥ መንገድ የተከማቸን ንብረት ለማጣራት ወደተወሳሰበና ከፍተኛ ችግር ወደሚፈጥር ሁኔታ መግባት ሊኖር ይችላል፡፡ ሆኖም ግን እዚህ ላይ የመንግስት ዋነኛ ፍላጎት ያለፈውን ሂሳብ የማወራረድ ወይም ባለፉት ጊዜያት ያልተከፈለውን ግብር ማስከፈል መሆን የለበትም፡፡ ዋነኛው አላማ በቀጣይ ጊዜያት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ገቢና ንብረቱ በህግ የታወቀ፣ ግብር የሚከፍልበትና በህጋዊ መንገድ የሚገኝ ብቻ እንዲሆን ማድረግ ነው መሆን ያለበት፡፡ ከዚህ በመነሳት ዜጎች ንብረታቸውንና ገቢያቸውን በትክክል እስካሳወቁና እስካስመዘገቡ ድረስ ንብረቱንና ገቢውን በህጋዊ መንገድ ስለማግኘታቸው እንዳይጠቁ ማድረግ ይቻላል፡፡ ይህ ጥያቄ ንብረትና ገቢ በህጋዊ መንገድ ከተመዘገበ በኋላ ለሚገኘው ገቢና ንብረት ብቻ የሚያገለግል እንዲሆን ማድረግ ይቻላል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ያልተከፈሉ ውዝፍ ግብሮችን በተወሰነ ደረጃ በምህረት በመሰረዝና ከዚህ በፊት በውዝፍነት ያልተመዘገቡ ግብሮች በለውጡ ምክንያት በውዝፍነት የሚታሰቡበት ሁኔታ እንዳይፈጠር ማድረግ ይቻላል፡፡

ይህ የለውጥ ርምጃ ቀደም ሲል የተዘረዘሩ እጅግ በጣም መሰረታዊ ጥቅሞች ያሉት በመሆኑ መፈፀም የሚገባው ሲሆን አፈፃፀሙ የዜጎችን ንብረት የመያዝ ፍላጎትና መብት በማይጎዳ

መልኩ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከዚህም አኳያ ከላይ ከተቀመጡት የመፍትሄ አቅጣጫዎች በተጨማሪ ህጋዊ አሰራሩን በተመለከተ ገፅታው በሚገባ ተጠንቶ መፈፀም ያለበት ይሆናል፡፡ ዜጎች በአንድ መልኩ ንብረት የማፍራትና ለንብረታቸው ጥበቃ የማግኘት መብት እንዳላቸው፣ በሌላ በኩል ደግሞ ግብር የመክፈል፣ ንብረታቸውንና ገቢያቸውን በህጋዊ መንገድ ብቻ የማፍራት፣ የሌለውን የንብረት መብት (የመንግስት ንብረት በመዝረፍም ሆነ ግብር ባለመክፈል) በማይጋፋ መልኩ የመስራት ግዴታ እንዳለባቸው ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት፡፡ ቀደም ሲል የወጣውንና ዜጎች ንብረታቸው በህጋዊ መንገድ የተገኘ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ እንዳለባቸው የሚደነግገውን ህግ ታሳቢ ያደረገና ይህንኑ ግብር ያልተከፈለበት ንብረት ህገ-ወጥ ንብረት ነው ከሚለው መርህ ጋር የሚያስተሳስር መሆን ይኖርበታል፡፡

ከላይ በተጠቀሰው መልክ እያንዳንዱ ዜጋ ስለንብረቱና ገቢው ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ እንዲሰጥ የሚያስገድድ፣ ይህ ሳይሆን ሲቀር ግብር ያልተከፈለበትን ንብረትና ገቢ ለመውረስና ከዚሁ በተጨማሪ ግለሰቡን የሃሰት ምስክርነት ቃል በመስጠትና በሙስና ለመጠየቅ የሚያስችል ህጋዊ ሁኔታ ሲፈጠር የመረጃው አቅርቦት በከፍተኛ ደረጃ እንደሚሻሻል እሙን ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ሲፈጠር ክፉኛ የሚጎዱ ጥገኞችና ሙሰኞች ሲሆኑ እጅግ የሚበዛው ሰው ግን ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በሙስና የሚጎዳ እንጂ የማይጠቀም በመሆኑ ሙስና የሚደበቅበትን ጫካ በመመንጠር ሙስናን ለመቆጣጠር ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያደርገው ይህ ስራ ሲሰራ በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡



ቀልጣፋ የመረጃ ፍሰት ተረጋግጦ ልማት ሲፋጠን ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ ለንብረቱና ገቢው አስተማማኝ ህጋዊ እውቅና በማግኘት ከዚህ የሚመነጩ በርካታ መሰረታዊ ጥቅሞችን ያገኛል፡፡ ይህ በጣም ስር ነቀልና መሰረታዊ ርምጃ ያለውን ጠቀሜታ ህዝቡ እንዲገነዘብና በሙሉ ልብ እንዲደግፈው፣ ከዚህ አኳያ ጥቅማቸው የሚነካባቸው ወገኖች ማራገባቸው የማይቀረውን ውዥንብር ማምከን ለአጠቃላይ ስራው ስኬታማነት ወሳኝ ነው፡፡

ይህ ስር ነቀል ርምጃ በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆን ከዚሁ በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ የሚሆነውን ምልአተ-ህዝቡን ማስረዳትና ማሳመን ዋናው ጉዳይ ቢሆንም ከዚሁ ጋር ተያይዘው መፈፀም ያለባቸው ተጨማሪ ርምጃዎች አሉ፡፡ ከላይ ከተጠቆሙት መፍትሄዎች በተጨማሪ የንብረትና የገቢ ምዝገባ ስርአቱ ከላይ አስከታች ተፈትሾ ቀልጣፋና ዘመናዊ እንዲሆን መደረግ አለበት፡፡ ስርአቱም ግልፅ ቅደም ተከተል ወጥቶለት ለባለንብረቶችና ከፍተኛ ገቢ ላላቸው ቅድሚያ ሰጥቶ ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል፡፡ በዚህ መሰረት እጅግ የሚበዛው የአገራችን ህዝብ አርሶ አደር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አርሶ አደሩን በዚሁ ስርአት የማካተት ስራ የሌላው ስራ እንዳበቃ ሊደረግ የሚችልና የማያጣድፍ መሆኑ እንዲሰመርበት ይገባል፡፡ ለንብረትና ገቢ ህጋዊ እውቅና መስጠት የሚያስገኘውን ጠቀሜታ አሟጦ ለመጠቀም ይቻል ዘንድ መረጃውን ለሚፈልግ ባለጉዳይ መረጃው በሚፈለገው ፍጥነትና ያለውጣ ውረድ የሚቀርብበት ስርአት አብሮ መቀየስ አለበት፡፡ የመረጃውን ወቅታዊነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ባህሪም ሊኖር ይገባል፡፡ ከዚህ አኳያ የዳበሩት አገሮች በዘመናት ልምድ ያዳበሩት

ቀልጣፋ የንብረትና ገቢ አመዘጋገብ ስርአት ስላለ ከዚሁ በስፋት ተምረን በተፋጠነ አኳኋን በአገራችን ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል፣ ይገባልም።

## 5.3. የመንግስት ግብር ስርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ይዘት፣

ይህ ፕሮግራም እንደሌሎቹ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ሁሉ ሶስት ገፅታዎች ይኖሩታል። አሰራርና አደረጃጀትን ማስተካካልንና የሰው ሃይሉን ማብቃትን ያካተተ ሶስቱንም በማጣመር የሚፈፀም ፕሮግራም ነው።

አሰራር ማስተካከልን በሚመለከት እጅግ በጣም በርካታ ስራዎች መሰራት እንዳለባቸው ግልፅ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ከላይ የተገለፀው የንብረትና ገቢ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ማረጋገጫ ስርአት መፈጠሩ ለታክስ አሰባሰቡ ስራ መሻሻል ስር-ነቀል በሆነ አኳኋን ድጋፍ የሚሰጥ በመሆኑ በቅደም ተከተሉ መሰረት በተቻለ ፍጥነት መስተካከል ያለበት ይሆናል። በአሁኑ ሰአት በመንግስት ተጥለው የሚገኙ ግብሮች ለአሰባሰብ የማይመቹ ብዙዎቹ ዘመናዊነት የሚጎድላቸውና አንዳንዶቹም መቀነስ የሚገባቸው ስለሆኑ ይህንን ለማድረግ የሚያስችሉ ህጎች ደንቦችና መመሪያዎች መዘጋጀት ይኖርባቸዋል።

ከተለያዩ ገቢዎች የሚሰበሰበው ግብር ወጥነት ያለው፣ ለአሰባሰብ የሚመችና በመጠኑም አሁን ካለው ዝቅ ያለ እንዲሆን መደረግ ይገባዋል። ይህንን ለማድረግና ረቂቅ አዋጅ ለማዘጋጀት



የሚያስፈልገው ቅድመ ዝግጅት በመጠናቀቅ ላይ ያለ በመሆኑ ይኸው ተፋጥኖ በያዝነው አመት በምክር ቤት እንዲፀድቅ መደረግ ይኖርበታል። በተመሳሳይ መልኩ የሽያጭ ግብራችን አምራቹን ለተደራራቢ ክፍያ የሚዳርግ በመሆኑ በዘመናዊ የተጨማሪ እሴት ግብር መተካት አለበት። ይህን በተመለከተም ረቂቅ አዋጁ የተዘጋጀ በመሆኑ ለአፈፃፀሙ የሚያስፈልጉ ቅድመ-ዝግጅቶች ተፋጥነው በተያዘው እቅድ መሰረት ተፋጥኖ ተግባራዊ እንዲሆን መደረግ አለበት። ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውና የሂሳብ መዝገብ ለመያዝ የማይችሉትን ግብር ከፋዮች በደረጃ በደረጃ መድቦ ለደረጃቸው የተወሰነውን ግብር የሚከፍሉበት ለግብር አሰባሰብ የቀለለውን የቁርጥ ግብር ስርአት ተግባራዊ ለማድረግ እየተሰራ ያለው ቅድመ-ዝግጅትም መፋጠን አለበት።

የግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶች ግብር እንዲከፈል የማስገደድ በቂ ስልጣን ሊኖራቸው ይገባል። ከዚህ አኳያ የኛ የታክስ ስርአት ከዘመናዊው አሰራርና በዳበሩት አገሮች ካለው በተለየ ሁኔታ ግብር እንዲከፈል የማስገደድ ስልጣኑ እጅግ ደካማ ነው። መስሪያ ቤቶቹ ከግብር ከፋዮች ጋር በየፍርድ ቤቱ ሲካሰሱ ግብሩ ሳይከፈል ለአመታት የሚቆይበት ሁኔታም ይታያል። ስለሆነም መስሪያ ቤቶቹ ግብር እንዲከፈል የማስገድድ ስልጣን እንዲኖራቸውና በዚህ ዙሪያ የሚነሳ ክርክር ካለ ግብሩ ከተከፈለ በኋላ የሚካሄድ እንጂ የተጣለው ግብር ሳይከፈል የሚከናወን እንዳይሆን ማድረግ፣ በሌሎች አገሮች በዚህ ረገድ ያለውን ውጤታማና ዘመናዊ አሰራር በአገራችንም ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል። ከዚሁ ጎን ለጎን ሁሉም ግብር

ከፋይ የመለያ ቁጥር እንዲሰጠው የሚያደርጉ በሌሎች አገሮች በተግባር ከፍተኛ ውጤት ያስገኘው አሰራር በአገራችንም ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግና ግብር የከፈለውንና ያልከፈለውን ሰው ቀልጣፋ በሆነ አኳኋን መከታተል የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡ ይህንን በተመለከተ መደረግ የነበረባቸው ቅድመ-ዝግጅቶች በወሳኝ መልካቸው የተጠናቀቁ ስለሆኑ በአፋጣኝ ወደተግባር እንዲሸጋገሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ፕሮግራሙ ከፍተኛ የሰው ሃይል ስልጠና ስራ የሚጠይቅ ነው፡፡ በመንግስት ገቢ አሰባሰብ ተቋሞች ውስጥ ያሉት ሰራተኞች ስለአዲሱ የግብር አሰባሰብ ስርአትና ስለሚስተካከሉት አሰራሮች የተሟላ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ከዚህም ባሻገር በተለያዩ መስኮች በተለይም በሂሳብ ስራና በኮምፒዩተር ሳይንስ የሰለጠኑ ሰዎችን መቅጠርና ማሰልጠን ይጠይቃል፡፡ የመንግስት ግብር በፌዴራል መንግስት ብቻ ሳይሆን በክልሎችም የሚሰበሰብ በመሆኑ ተቋሞችን በሰለጠነ የሰው ሃይል የማሟላቱ ስራ በክልሎችም መካሄድ ይኖርበታል፡፡ በግብር አሰባሰቡ ስራ ውስጥ በቀጥታ ከሚሳተፉት ሰዎች በተጨማሪ የዜጎች የንብረትና ገቢ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ ስርአትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ፣ የንብረትና ገቢ ምዝገባ ስርአት አካላትን የሚያንቀሳቅሱ በስራው ተገቢ የሆነ ስልጠና የተሰጣቸው ሰዎች መመደብ ይኖርባቸዋል፡፡

የስርአቱ ለውጥና መሻሻል በግብር ከፋዮች፣ በተለይም



በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ዘንድ ብቃት ያለው የሰው ሃይል ፍላጎትን እንደሚጨምር ለመገመት ይቻላል፡፡ እነዚህ ድርጅቶች የተስተካከለ ሂሳብ መያዝ፣ በሂሳብ መርማሪዎች በየወቅቱ እንዲመረመር ማድረግ የሚጠበቅባቸው ይሆናል፡፡ በመሆኑም ብቃቱ ያለው የሂሳብ ሰራተኛና የሂሳብ ምርመራ ድርጅቶች በሚፈለገው መጠን መሰልጠንና መፈጠር ይኖርባቸዋል፡፡ የትምህርትና ስልጠና ስርአታችን ይህንን ታሳቢ ያደረገ እቅድ ሊኖረው ይገባል፡፡

አዲሱን የግብር አሰባሰብ ስርአት ተግባራዊ ለማድረግ የአደረጃጀት ለውጦችንም መጠየቁ አይቀርም፡፡ በርግጥ በአዲሱ አሰራር እያንዳንዱ ግብር ከፋይ ስለንብረቱና ገቢው ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ከመስጠት በተጨማሪ በዚሁ ላይ ተመስርቶ መክፈል የሚገባውን ግብር አስልቶ ለግብር ሰብሳቢ ድርጅቶች መክፈል ይጠበቅበታል፡፡ ግብር ሰብሳቢ ድርጅቶች በዚሁ መልኩ ተሰልቶ የቀረበላቸው የግብር ክፍያ ትክክለኛ መሆኑን በተመረጠ አኳኋን የማረጋገጥ ሃላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ስራቸውን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያቃልልላቸው ይታመናል፡፡ ይሁንና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንደመስጠትና ይህንኑ መከታተልን የመሳሰሉ አዳዲስ አሰራሮች ከዚሁ ጋር አብሮ የሚሄድ የአደረጃጀት ለውጥ የሚጠይቁ መሆናቸው አይቀርም፡፡ ሌሎችም የአሰራር ለውጦች ተመጣጣኝ የአደረጃጀት ለውጥ ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም ከአሰራሩ ለውጥ ጎን ለጎን ሰፊ የመልሶ ማዋቀርና ማደራጀት ስራ የሚጠይቅ ይሆናል፡፡

## 5.4. በመንግስት ግብር ስርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም አፈፃፀም ላይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፣

የመንግስት ግብር ስርዓትን ለማሻሻል የተዘጋጀው ፕሮግራም የመንግስትን ገቢ በማሳደግ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት በማምጣት ያለብንን ከፍተኛ የፋይናንስ ችግር በማቃለል ረገድ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ ሌሎች የአፍሪካ አገሮች ወደደረሱበት ደረጃ በሂደት መድረስ ቢቻል የመንግስት የግብር ገቢ በእጥፍ ሊጨምር እንደሚችልና ይህም የግብር መጠኑን በመቀነስና መክፈል የሚገባው ሁሉ እንዲከፍል በማድረግ ብቻ ሊፈፀም እንደሚችል እሙን ነው፡፡ ፕሮግራሙ የፊስካል ፖሊሲያችን ጥርስ እንዲኖረውና ኢኮኖሚውን በተሻለ ብቃት ለመምራት የሚያስችል መሳሪያ እንዲሆን የሚያደርግ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የእያንዳንዱ ግብር ከፋይ ንብረትና ገቢ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ እንዲኖር ለማድረግ የተቀየሰው ስርአት የኢኮኖሚያችንን ቅልጥፍናና እድገት በማፋጠን፣ በሙስና የተገኘ ንብረት የሚደበቅበትን ጫካ በመመንጠር፣ ሁሉም ግብር ከፋይ የሚጠበቅበትን ግብር እንዲከፍል የሚያስገድድ ሁኔታ ለመፍጠር የላቀ ሚና ይጫወታል፡፡ ፕሮግራሙ በህብረተሰባችን የወደፊት ጉዞ ላይ ስር ነቀል ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ነው፡፡ በመሆኑም ከተያዙት የማስፈፀም አቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ውስጥ የላቀ ትኩረት ከሚሰጣቸው ውሱን ፕሮግራሞች አንዱ ይሆናል፡፡ በግብር አሰባሰብ ስራችንና በህዝቡ የግብር አከፋፈል ባህል ላይ ስር ነቀል ለውጥ የሚያመጣ ጉዳይ በመሆኑ በአፈፃፀሙ ሂደት የተለያዩ ውስብስብ ችግሮች ሊከሰቱ እንደሚችሉ



መገመትና እነዚህን ለማስወገድ በሚያስችሉ የመፍትሄ አቅጣጫዎች ላይ በቂ ትኩረት ማድረግ የሚጠይቅ ይሆናል፡፡

እንደዚህ አይነቱን ስር-ነቀል ለውጥ ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሴ በሚደረግበት ወቅት የሚያጋጥመው ዋነኛ ችግር የአመለካከት ችግር ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ በእንደዚህ አይነት ለውጥ በከፍተኛ ደረጃ ሊጎዱ የሚችሉት ወገኖች አደጋውን ቶሎ ብለው ይገነዘቡታል፡፡ ለውጡን ለማሰናከል ሰፊ የቅስቀሳና የሃሰት መረጃና ትንተና የማሰራጨት ስራ ይሰራሉ፡፡ ከለውጡ ተጠቃሚ የሚሆኑት ወይም ለውጡ ትርጉም ባለው ደረጃ የሚጎዳቸው ወገኖች፣ የለውጡ ይዘት ምን እንደሆነና ይህም በምን መልኩ እንደሚጠቅማቸው ወዘተ. ዝርዝርና ተጨባጭ ማብራሪያና መረጃ ስለማይሰጣቸው ብዙውን ጊዜ ተቃዋሚ ይሆናሉ፣ ግፋ ቢል ገለልተኛ ይሆናሉ፡፡ በመሆኑም ፕሮግራሙ ተቃዋሚና ገለልተኛ እንጂ ደጋፊ የሌለው ሆኖ ተሰናክሎ ይቀራል፡፡ እንደዚህ አይነቱን ከፍተኛ አደጋ ለማስወገድ መወሰድ ያለባቸው ርምጃዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

የመጀመሪያውና ትልቁ ርምጃ ስለለውጡ ለህዝቡና ለአስፈፃሚ አካላት ተጨባጭና ዝርዝር ማብራሪያ፣ መረጃ የመስጠት ጉዳይ ነው፡፡ ከላይ የቀረበውን የለውጡን አላማና ይዘት መነሻ በማድረግ በለውጡ አጠቃላይ ጉዳዮች ላይ ለህብረተሰቡ ሰፊ ማብራሪያ መስጠትና በጉዳዩ ላይ ሰፊ ውይይት እንዲካሄድ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በዚሁ ሂደት ህብረተሰቡ ስለፕሮግራሙ መሰረታዊ ግንዛቤ እንዲኖው ማድረግ ይቻላል፡፡

የፕሮግራሙ ተቃዋሚዎች ፕሮግራሙን ለማሰናከል የሚያቀርቧቸው ሃሳቦች ምን እንደሚሆኑም ተለይተው ይወጣሉ፡፡ በዚህ ላይ ተመስርቶ የፕሮግራሙ ዝርዝር ይዘት፣ ፕሮግራሙ በእያንዳንዱ የህብረተሰብ ክፍል ላይ ምን አይነት ጥቅምና ጉዳይ እንደሚያስከትል፣ በፊት ከነበረው ስርአት እንዴት እንደሚለይ ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡ ይህንኑ ነጥብ በትክክል ለመረዳት የአርሶ አደሩን ሁኔታ በምሳሌነት እንውሰድ፡፡

እያንዳንዱ ግብር ከፋይ ገቢውንና ንብረቱን የሚመለከት ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ እንዲያቀርብ የሚለው አሰራር በአርሶ አደሩ ላይ ከጥቅም በስተቀር አንዳችም አይነት ጉዳት አያደርስም፡፡ አርሶ አደሩ የሚደበቅ ንብረት የለውም፡፡ መሬቱ፣ ቤቱ፣ ከብቶቹ ሁሉም የሚታወቁና ሊደበቁ የማይችሉ ናቸው፡፡ ይልቁንም እነዚህ ተመዝግበው የመንግስት እውቅና ቢያገኙ አርሶ አደሩ በመሬት የመጠቀም መብቱ የተሻለ ዋስትና ያገኛል፡፡ የሚጠቀምባት መሬት ተለይታ ተመዝግባ የሱ መሆኗን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ቢሰጠው በጣም ከፍተኛ ጥቅም ያገኛል፡፡ ይህን ስራ ለመስራት ሰፊ ዝግጅት የሚጠይቅ ይሆናል፡፡ ስለሆነም ከምዝገባ አኳያ ሌሎች የምዝገባ ስራዎች ቅድሚያ የሚሰጣቸው ይሆናሉ፡፡ የግብር ክፍያም ቢሆን አርሶ አደሩ በአብዛኛው የተጣለበትን ግብር ይከፍላል፡፡ በሂደት ከእድገቱ ጋር ተያይዞ የሚከፈለው መጠን እንደሚጨምር ቢገመትም ከአጭር ጊዜ አኳያ ግብር ሲከፍል በነበረው አርሶ አደር ላይ የሚጨመር ነገር አይኖርም፡፡ ፕሮግራሙ ተግባራዊ ሲሆን አርሶ አደሩ ይህንን ጉዳይ በትክክል እንዲገነዘብ ካልተደረገ የግብር ዕዳ ይጨመርብሃል፣ ቤት ንብረት



ይመዝገብ ተብሏል ወዘተ. በሚል ብቻ ለማስበርገግ ሰፊ ጥረት እንደሚደረግ መገመት ይገባል፡፡ ስለሆነም ፕሮግራሙ ለእያንዳንዱ የህብረተሰብ ክፍል ያለውን ፋይዳ በዝርዝር ማስቀመጥና ማስረዳት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ይሆናል፡፡

የመንግስት ግብር አሰባሰብ ማሻሻያ ፕሮግራሙ በሙሉና በተቀናጀ አኳኋን መፈፀም ያለበት ቢሆንም ሁሉም የፕሮግራሙ ክፍሎች እኩል ክብደት የሚሰጣቸው አይደሉም፡፡ በዚህ መሰረት ለምሳሌ ለእያንዳንዱ ግብር ከፋይ የመለያ ቁጥር የመስጠቱና ይህንኑን በጥብቅ ተግባራዊ የማድረጉ ስራና፣ ግብር ከፋዮች ስለገቢያቸውና ንብረታቸው ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ እንዲያቀርብ የማድረጉ ስራ ከሌሎቹ የላቀ አስተዋፅኦ ያላቸው ናቸው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የመንግስት ሰራተኞች ከማንም በላይ የተጣለባቸውን ግብር ሲከፍሉ የነበሩ ናቸው፣ አርሶ አደሩም በተመሳሳይ መልኩ የሚታይ ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን በንግድና አገልግሎት ዘርፍ ከተሰማሩት ባለሃብቶች ውስጥ የተጣለባቸውን ግብር በአግባቡ የማይከፍሉ በርካታ እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ ለሁሉም ግብር ከፋዮች እኩል ክብደት ከመስጠት ይልቅ የከፋ ችግር ባለባቸውና ዋነኛ ግብር ከፋይ በሆኑት ላይ ማትኮር ያስፈልጋል፡፡ ሁሉን አቀፍ ፕሮግራምነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ግልፅ ቅደም ተከተል ወጥቶለት በዋነኛ ስራዎችና ግብር ከፋዮች ላይ ያተኮረ እንዲሆን ማድረግ ለአፈፃፀሙ መሳካት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

ይህ ፕሮግራም እንደሌሎቹ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ሁሉ በርካታ አመታት የሚጠይቅ መሆኑ ግልፅ

ነው፡፡ የአፈፃፀም እቅዱም በዚሁ መሰረት በየጊዜው እየተዘረዘረና ከሚገኘው ልምድ በመማር እየተሻሻለ መሄድ ያለበት ይሆናል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ስራው ወደተግባር ከመሸጋገሩ በፊት ቢያንስ በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ መደረግ የሚገባቸው ቅድመ-ዝግጅቶች ተጠናቀው፣ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች አስቀድመው ተለይተውና የመፍትሄ አቅጣጫ ተቀምጦላቸው፣ መሰረታዊ የአፈፃፀም እቅድ ሊዘጋጅላቸው ይገባል፡፡ እንደዚህ አይቱን ስር-ነቀል ለውጥ ተግባራዊ ለማድረግ በሚጣርበት ወቅት በአግባቡ የተዘጋጀና የጠራ የአፈፃፀም እቅድ ከሌለ አፈፃፀሙ ይበልጥ የተወሳሰበ ሊሆንና ለውጡን ሊደግፉ ይችሉ የነበሩ ሃይሎችን ለውዥንብር የሚዳርግ ይሆናል፡፡ ስለሆነም የጠራ የአፈፃፀም እቅድና የተሟላ ቅድመ-ዝግጅት ይዞ ስራውን መጀመር እጅግ በጣም አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ስራዎች ሁሉ በክልሎችም በፌዴራል መንግስት ደረጃም መሰራት ያለባቸው ይሆናሉ፡፡

## 6. የፍትህ አስተዳደር ስርአት የማሻሻያ ፕሮግራም፣

### 6.1. የፍትህ አሰተዳደር ስርአት ማሻሻያ ፕሮግራም አላማዎች፣

መንግስት ያቀደውን የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስራ ለማስፈፀም እያንዳንዱን የአስተዳደርና የልማት ስራ የሚመሩ ህጎችና መመሪያዎች መውጣት አለባቸው፡፡ እነዚህ ህጎችና መመሪያዎች አላማዎቹን ለማሳካት በሚያስችል አኳኋን መፈፀምና መተርጎም አለባቸው፡፡ የፍትህ አስተዳደር ስርአት ማሻሻያ ፕሮግራም በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ አላማው



ያስቀመጥነውን የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ለማሳካት የሚያስፈልግ የተሟላ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖር ማድረግ፣ ህጎች የተነሱበትን አላማ በሚያሳካ አኳኋን እንዲፈፀሙና እንዲተረጎሙ ማድረግ ነው ሊባል ይችላል፡፡ ይህ አጠቃላይ አላማው እንደተጠበቀ ሆኖ ዝርዝር አላማዎቹን እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

ከዴሞክራሲያዊ ስርአት መለያዎች አንዱ በመንግስትና በዜጎች መካከል የሚኖር ግንኙነት በዝርዝር ህጎች ላይ የተመሰረተ እንዲሆንና በህጉ መሰረት የሚፈፀም እንዲሆን የማድረጉ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም በአንድ በኩል የዜጎችን የዴሞክራሲና ሰብአዊ መብቶች ለማስከበር፣ በሌላ በኩል የህብረሰተቡን ሰላምና የተረጋጋ ኑሮ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የተሟሉ ህጎች መኖር ይገባቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ ምንም አይነት የህግ ክፍተት እንዳይኖር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የተሟላ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖር ማድረጉ ህጎች በጥብቅ ተግባራዊ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት ለምሳሌ ህጎቹ ሲቀረፁ ግልፅ አላማና ግብ ያላቸው፣ ለአፈፃፀም የሚያመቹና በተቻለ መጠን ቀላልና ግልፅ አቀራረብ ያላቸው በመሆኑም ለአፈፃፀም የተመቹ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ የመንግስት የዕለት-ተዕለት ተግባራት እነዚህን ህጎች በትክክልና አላማቸውን ለማሳካት በሚያስችል አኳኋን በመፈፀም ላይ የተመሰረተ፣ የህግ የበላይነትን መርህ በትክክል ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል መሆን አለበት፡፡ የህግ አተረጓጎም የዜጎችን መብት ለማስጠበቅ፣ ህጎቹን ከተቀመጠላቸው መሰረታዊ አላማና ግብ ጋር በማስተሳሰር የግለሰቡን መብትና የህብረተሰቡን

መሰረታዊ አላማና ጥቅም ባጣጣመ መልኩ መሆን ይኖርበታል፡፡

በመሆኑም የፍትህ አስተዳደሩ ስርአት ማሻሻያ ፕሮግራም እንደ መሰረታዊ አላማ ዴሞክራሲያዊ አመራርን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የተሟላ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖር፣ ህጎቹ ይህንኑ አላማ ለማሳካት በሚያስችል አኳኋን እንዲፈፀሙና በተግባር እንዲተረጎሙ በማድረግ በአገራችን የህግ የበላይነትን ማስፈን ነው፡፡ በዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ሂደት ህጎችና የፍትህ አስተዳደር ስርአት መጫወት የሚገባቸውን ከፍተኛ ሚና እንዲጫወቱ ማስቻል ነው፡፡

የአገራችንን ኢኮኖሚ ቀልጣፋነት በማሻሻል እድገቱን ለማቀላጠፍ ይህንኑ ለማድረግ የሚያስችሉ ህጎች መኖርና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴው በነዚህ ህጎች በመመራት የሚፈፀም እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የህግ ሽፋን ማግኘት የሚገባቸውን ስራዎች የሚገዙ ህጎች ከሌሉ አንድም ስራዎች ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ መፈፀም ይጀምራሉ፣ አለበለዚያም ስራዎቹ ሳይሰሩ ቀርተው ኢኮኖሚያዊ እድገታችን ይጎተታል፡፡ ስለሆነም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን በሙሉ በህጋዊ አኳኋን ለማካሄድ የሚያስችሉ የተሟሉ ህጎች መኖራቸው በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ህጎች መኖራቸው ብቻውን ግን በቂ አይደለም፡፡ ህጎቹ ራሳቸው የተቀመጠውን የፈጣን እድገት አላማ ለማሳካት የሚያስችል ይዘት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የልማት እንቅስቃሴን ቀስፈው የሚይዙ፣ ከተቀመጡት አላማዎች ጋር አብረው የማይሄዱ፣ የህጎችን አፈፃፀምና አተረጓጎሙም የተወሳሰበ እንዲሆን የሚያደርጉ ህጎች በላይ በላይ



ቢነባበሩ አላማዎቻችንን ከማሳካት አኳያ የሚፈይዱት ነገር አይኖርም፡፡ ስለሆነም አላማችንን ለማሳካት የሚያገለግሉ፣ የተሟሉ፣ ግልፅና ለአፈፃፀም የሚያመቹ ህጎችን በማዘጋጀት የልማት አላማችንን ማሳካት የለውጡ አንድ መሰረታዊ አላማ ነው፡፡

እንደዚህ አይነቱ የተሟላና ለአፈፃፀም የቀለለ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖር ማድረግ ትልቅ አላማ ቢሆንም ትክክለኛና ቀልጣፋ አፈፃፀም ከሌለ ልማታችን መስተጓጎሉ አይቀርም፡፡ የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ህጎችን ቀልጣፋና ትክክለኛ በሆነ መንገድ ማስከበር አለባቸው፡፡ ፍርድ ቤቶችም ቀልጣፋና ዘመናዊ አገልግሎት መስጠት አለባቸው፡፡ በዚህ ረገድ የኮንትራት አፈፃፀም ጉዳይ በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችል ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ኮንትራት ለማስፈፀም ወደፍርድ ቤት መሄድ ከሞላ ጎደል ፋይዳ ቢስ ተደርጎ የሚታየበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ በኮንትራት ማስከበር ዙሪያ ያለው ውጣ ውረድና ክርክር የሚወስደው ጊዜ በጣም ከፍተኛ ሆኖ ይታያል፡፡ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ኮንትራታዊና ኮንትራት ነክ ግንኙነቶችን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ኮንትራቶች በጣም ፈጣንና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ እንዲከበሩ ካልተደረገ በስተቀር ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማረጋገጥ እጅግ በጣም አዳጋች እንደሚሆን እሙን ነው፡፡ ስለሆነም የተሟላ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖር ከማድረግ በተጨማሪ ለልማታችን በጣም አስፈላጊ የሆነውን ቀልጣፋና ፍትሃዊ ዳኝነት የማረጋገጥ ጉዳይም አንድ የለውጡ መሰረታዊ አላማ ነው፡፡

### 6.2. የፍትህ አስተዳደር ስርአት ማሻሻያ ፕሮግራም ይዘት፣

ይህ ፕሮግራም እንደሌሎቹ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ፕሮግራሞች የአሰራር፣ የአደረጃጀትና የሰው ሃይል ለውጦችን ያካተተ ነው፡፡ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታና የልማት አላማዎቻችንን ለማሳካት የሚያስችል ይዘት ያላቸው፣ ለእንቅስቃሴዎቻችን ሁሉ የተሟላ የህግ ማዕቀፍ ለማድረግ የሚያስችሉ ለአፈፃፀም የተመቹ ህጎችን ለማውጣት ሰፊ የቅድመ ዝግጅት ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚሁ መሰረት ዋናዎቹ የህግ ኮዶቻችን በዝርዝር እንደገና እንዲፈተሹ ተደርጓል፡፡ ካስቀመጥነው የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታና የልማት አላማ አኳያ ህጎቹን ለማስተካከል ተጥሯል፡፡ በቂ የህግ ሽፋን ያልነበራቸው ጉዳዮች በቂ ሽፋን እንዲያገኙ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ ይህ ስራ የራሳችንን ሙያተኞችና የህግ ምርምር ተቋማችንን በሰፊው በመጠቀም የተፈፀመ ስራ ቢሆንም የውጭ ሙያተኞችም እንዲሳተፉበት ተደርጓል፣ እየተሳተፉበትም ነው፡፡ በዚህ ረገድ ገና መጠናቀቅ ያለባቸው የተወሰኑ የቅድመ-ዝግጅት ስራዎች ቢኖሩም ዋናው የቅድመ ዝግጅት ሰራ ተጠናቋል ሊባል ይችላል፡፡ ከዚህ አኳያ የሚቀረው ዋናው ነገር ለተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ እንዲፀድቁ የማድረጉ ጉዳይ ነው፡፡

እነዚህን መሰረታዊ የህግ ለውጦች የማፅደቅ ጉዳይ ሰፊ ስራና ተሳትፎ የሚጠይቅ እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ህብረተሰቡ ስለህግ ለውጡ መሰረታዊ አላማና



ይዘት አጠቃላይ ማብራሪያዎች ማግኘትና ጥሩ ግንዛቤ እንዲኖረው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የህግ ለውጡን በቅርብ ለመከታተልና በጉዳዩ ላይ የበሰለ አስተያየት ለመስጠት ፍላጎቱና አቅሙ ያላቸው ዜጎችና የተደራጁ የህብረተሰብ ክፍሎች አስተያየታቸውን በግንባር እየቀረቡም ሆነ በፅሁፍ ሊያቀርቡ የሚችሉበት በቂ ጊዜና ሰፊ ዕድል ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ምክር ቤቱ እያንዳንዱን አንቀፅ ከዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ፣ ከልማት አላማችንና በዚሁ ዙሪያ ከተቀመጡት መሰረታዊ አቅጣጫዎች አኳያ እየመዘነ ተፈላጊ የሆኑ ማስተካከያዎችን ለማድረግ መቻል አለበት፡፡ ህብረተሰቡ ከዚህ አኳያ የሚያቀርባቸው ጠቃሚና ገንቢ ሃሳቦችም እንዲካተቱ መደረግ አለበት፡፡ በአጭሩ ለምክር ቤቱ የሚቀርቡት የተሻሻሉ የህግ ረቂቆች የህዝብ ሰፊ ተሳትፎን በሚያረጋግጥ አኳኋን ህጎቹ በርግጥም የተቀመጠላቸውን አላማ ሊያሳኩ የሚችሉ መሆናቸው በዝርዝር እየተፈተሸ መፅደቅ የሚገባቸው እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል፡፡

ከአሰራር ለውጡ ጋር አብሮ የሚታየው የዳኝነት ስርአቱን ዘመናዊና ቀልጣፋ ለማድረግ መከናወን ያለባቸው ለውጦች ናቸው፡፡ የዳኝነት ስርአቱ ዘመናዊና ቀልጣፋ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችሉ የአሰራር ለውጦችን ለማምጣት ሰፋ ያለ የቅድመ-ዝግጅት ስራ ሲካሄድ ቆይቷል፡፡ የችግሮቹ ይዘትና ምንጭ ምን እንደሆነ በጥናት ለመለየት ተሞክሯል፡፡ እነዚህን ለማስወገድ የሚያስችል የመፍትሄ አቅጣጫ ምን መሆን እንዳለበት ለማስቀመጥም ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህ ረገድ ጥሩ ልምድ አላቸው ከሚባሉ አገሮች ልምድ ለመማር ሰፊ ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህ

ላይ በመመስረት አዲሱን አሰራር በተግባር ለመፈተሽ በተወሰኑ ፍርድ ቤቶች የሙከራ ስራ ተካሂዷል፡፡ ከዚሁ የተገኘው ትምህርትም ተቀምሯል፡፡ በአሁኑ ወቅት ይህንኑ በተሟላ ሁኔታ በሰፊው ተግባራዊ ወደማድረጉ ለመሸጋገር ዝግጅት በመደረግ ላይ ነው፡፡

ይህንን ቀልጣፋና ዘመናዊ አሰራር ለማምጣት እየተከናወነ ያለውን ስራ በተመለከተ ሊቀመጡ የሚገባቸው መሰረታዊ ነጥቦች አሉ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ቅድመ-ዝግጅቶቹ ከሞላ ጎደል የተጠናቀቁ በመሆናቸው በአፋጣኝ ወደተግባር የመሸጋገሩ ጉዳይ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም የፕሮግራሙ አፈፃፀም አድማስ ሁሉንም የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ብቻ ሳይሆን የክልል ፍርድ ቤቶችንም የሚሸፍን እንዲሆን መደረግ አለበት፡፡ የእስካሁኑ ዝግጅት የተወሰኑ የክልል ፍርድ ቤቶችን ያቀፈ በመሆኑ በዚህ ደረጃ መስተካከል ይገባዋል፡፡ የአፈፃፀም ስራውን ቶሎ መጀመር ብቻ ሳይሆን የፕሮግራሙ ማስፈፀሚያ ጊዜ ተብሎ የተቀመጠውንም ለማሳጠር ጥረት መደረግ አለበት፡፡ ከዚህም በላይ ህብረተሰቡ ስለፕሮግራሙ ምንም አይነት ግንዛቤ የሌለው በመሆኑ ይህ መስተካከል አለበት፡፡ በርግጥ ፕሮግራሙ ሰፊ ቴክኒካዊ ገፅታ ስላለው ሰፊው ህዝብ ነገሩን በዝርዝር እንዲያውቀው ለማድረግ ያስቸግራል፡፡ ይሁንና የለውጡን መሰረታዊ አላማና ይዘት በሚመለከት ለህብረተሰቡ አጠቃላይ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ መሰራት አለበት፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን በዳኝነት ስርአቱ ውስጥ ያሉ ሰዎች ስለለውጡ ዝርዝርና የተሟላ እውቀት እንዲኖራቸው፣ ተወያይተው እንዲያምኑበትና



ለተግባራዊነቱ ቆርጠው እንዲነሱ ለማድረግ ስፊ የማብራሪያና የውይይት ስራ መሰራት አለበት፡፡

የህግ ለውጦቹ አንዳንድ የአደረጃጀት ለውጦችን ማስከተላቸው አይቀርም፡፡ በዚህ መሰረት ለምሳሌ የግብር ከፋዮችን ንብረትና ገቢ ምዝገባ ስርአት በተሟላ ሁኔታ ለመተግበር ለዚሁ የሚበጅ አደረጃጀት መኖሩ የማይቀር ነው፡፡ የኮንትራት አስተዳደርን ለማሻሻል የሚደረጉ የህግ ለውጦችም የአደረጃጀት ለውጥ ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ ከተለወጡት ህጎች የሚመነጩ የአደረጃጀትና የአወቃቀር ለውጦችን ዘርዝሮ በማስቀመጥ ከሌሎቹ የለውጡ ፕሮግራሞች ጋር በቅንጅት እንዲፈፀሙ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

ከዳኝነት ነፃነት ጋር የተያያዙ የአመለካከትና የአደረጃጀት ችግሮችም ስላሉ በዚህ ረገድም ለውጥና ማሻሻያ መደረግ ይኖርበታል፡፡ የምንገነባው ዴሞክራሲያዊ ስርአት በተለያዩ አካላት መካከል ግልፅ የሆነ የስልጣን ክፍፍልና የርስ-በርስ ቁጥጥር እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ከዚህ በመነሳት በህዝብ የተመረጠው ምክር ቤት ሌሎች የመንግስት አካላት የሚመሩባቸውን ህጎችና እነዚህን ለማስፈፀም የሚያስፈልገውን በጀት የማፅደቅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ የህግ አስፈፃሚው አካል በምክር ቤቱ የፀደቁ ህጎችን ይዘትና አላማ በትክክል ተገንዝቦ አላማቸውን ለማሳካት በሚያስችል አኳኋን በትክክል የማስፈፀም ግዴታ አለበት፡፡ የምክር ቤቱን ህግ በመሰለው መንገድ ለማውገርገርም ሆነ ከተቀመጠለት በጀት ውጭ መሄድ አይችልም፡፡ የዳኝነቱ ስርአትም በተመሳሳይ

መልኩ ህግ አውጭው ያወጣውን ህግ ከህጉ አላማ ጋር አስተሳስሮ በትክክል ከመተርጎም ውጭ ህግ በመተርጎም ሽፋን የራሱን ህግ ሊያወጣ ወይም እንዳሻው ሊሄድ አይችልም፡፡

ምክር ቤቱ ያወጣቸው ህጎችና ያፀደቀው በጀት በትክክል መፈፀሙን ለማረጋገጥ ህግ አስፈፃሚውንና ዳኞችን የመቆጣጠር ስልጣንም አለው፡፡ የህግ አስፈፃሚው ከፍተኛ ሃላፊዎችና የዳኞች ሹመት በምክር ቤት እንዲፀድቅ የሚደረግበት አንዱ ምክንያትም ይህንኑ የቁጥጥር ስራ ለማስፈፀም ነው፡፡ የዳኝነት ነፃነት በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ የሚረጋገጥ እንጅ ይህንን የሚፃረር መሆን የለበትም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ዳኞች የቀረበላቸውን ጉዳይ በህጉ መሰረት በራሳቸው ነፃ ህሊና መዳኘት ካልቻሉ፣ በህግ-አስፈፃሚውም ሆነ በሌላ አካል በዳኝነት ጉዳይ ላይ ጣልቃ መግባት ከመጣ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ አላማችን የሚጠይቀው የዳኝነት ነፃነት ሊኖር አይችልም፡፡ ስለሆነም በአንድ በኩል ነፃነቱ በሌላ በኩል ደግሞ ቁጥጥሩ ተቀናጅተውና ተጣጥመው የሚሄዱበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት፡፡ ይህንኑ ከማድረግ አኳያ ችግር በመፍጠር ላይ ያሉ አመለካከቶችን ማስተካከል ዋናው ጉዳይ ቢሆንም አደረጃጀቶችንም መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መሰረት ለምሳሌ ከሌሎች አገሮች ልምድ በመማር የዳኝነት አስተዳደር ጉባኤን አሰራርና አደረጃጀት መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡ የተቋሙ አሰራርና አደረጃጀት የዳኝነት ነፃነትን የሚያጠናክር፣ አልፎ አልፎ በዳኞች የሚታየውን የችሎታ



ማነስና የማን አለብኝነት አዝማሚያ ለመቅረፍ የሚያስችል እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ህዝቡ በስርአቱ ላይ ያለውን ቅሬታ ለማሰማት የሚችልበት ዕድልም ሊከፈት ይገባል፡፡

የዳኝነት ስርአቱን አሰራር ዘመናዊና ቀልጣፋ ለማድረግ የተያዘው እቅድ በፍርድ ቤቶች የውስጥ አወቃቀርና አደረጃጀትም ላይ ለውጥ ማምጣትን የሚጠይቅ ሊሆን ይችላል፡፡ የለውጥ እቅዱ የአደረጃጀት ለውጡንም በሚያካትት አኳኋንና ከሌሎች ርምጃዎች ጋር በማቀናጀት እንዲፈፀም ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

አሰራርና አደረጃጀትን ለማስተካከል የሚሰራው ስራ የሚፈለገውን ጥራቱ የተጠበቀ የሰው ሃይል በሚፈለገው መጠን ከማቅረብ ጋር ተያይዞ መከናወን ይኖርበታል፡፡ ከረጅም ጊዜ አኳያ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚከናወነው የህግ ትምህርት በመጠንና በአይነት ከፍተኛ መሻሻል እንዲያሳይ መደረግ ይኖርበታል፡፡ የከፍተኛ ትምህርትን ለማስፋፋት የተያዘው እቅድ የህግ ትምህርትን ለማስፋፋት በሚያስችል አኳኋን መፈፀም ይኖርበታል፡፡ በህግ ትምህርት ረገድ የድህረ-ምረቃ ፕሮግራሞችን ለማስፋፋትና ለማጠናከርም ጥረት መደረግ ይኖርበታል፡፡ መጠኑን ከመጨመር ያላነሰ ምናልባትም ከዚሁ የላቀ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ለሚሰጠው ትምህርት ጥራት ነው፡፡ በዚህ ረገድ የህግ ሙያተኞች በኢኮኖሚ እንቅስቃሴው ውስጥ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ሚና ያላቸው በመሆኑ ስልጠናቸው ህጉን በተናጠል ሳይሆን ከበስተጀርባው ካሉ የኢኮኖሚ ልማት መርሆችና

አላማዎች ጋር አስተሳስረው እንዲመለከቱት ለማድረግ የሚያስችል ሊሆን ይገባል፡፡

የአንድ አገር ህጎች ከአገሪቱ የልማትና የአስተዳደር አላማዎችና ግቦች ተነጥለው የሚታዩ አይደሉም፡፡ እነዚህን አላማዎች ለማሳካት ተብለው የሚቀረፁና ከነዚህ አላማዎች ውጭ ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ናቸው፡፡ ህጎች ይህንኑ አላማ ለማሳካት በሚያስችል አኳኋን እንዲቀረፁና በትክክልም ተግባር ላይ እንዲውሉ በማድረግ ረገድ የህግ ሙያተኞች ከፍተኛ ሚናና ሃላፊነት አላቸው፡፡ ለአገሪቱ ህገ-መንግስትና ለህብረተሰቡ መሰረታዊ አላማዎች ታማኝ የሆኑ ሙያተኞች በሌሉበት ጤናማ የፍትህ አስተዳደር ስርአት ሊኖር አይችልም፡፡ በዳበሩት አገሮች ከሚሰለጥኑት የህግ ሙያተኞች እጅግ በጣም የሚበዙቱ ከማንኛውም ሌላ ሙያተኛ በላቀ ደረጃ እንደዚህ አይነት ታማኝነት እንዳላቸው በገሀድ የሚታወቅ ጉዳይ ነው፡፡ በኛ አገር ሁኔታ ግን ነገሩ የተገላቢጦሽ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ለዚሁም ዋነኛው ምክንያት በዚህ መስክ የሚሰጠው ስልጠና ጥራት የጎደለው፣ በቂ የስነ-ዜጋና የስነ-ምግባር ትምህርት ያላካተተ መሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም የፍትህ አስተዳደር ስርአቱን ከማሻሻል ፕሮግራም ጋር ተሳስሮ በከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች የሚሰጠው የህግ ትምህርት ስፋቱ እንዲጨምርና አይነቱም በከፍተኛ ደረጃ እንዲሻሻል መደረግ ይኖርበታል፡፡

ከአጭር ጊዜ አኳያ በስራው ላይ ያሉ ሙያተኞችን በተከታታይ ስልጠና ማሻሻል ዋናው ስራ ሊሆን ይገባል፡፡ በዚህም



መሰረት የዳኝነት ስርአቱን አሰራር ዘመናዊና ቀልጣፋ ለማድረግ የተያዘውን እቅድ በማስፈፀም ዙሪያ ሰፊ ስልጠና መሰጠት አለበት፡፡ በአንድ በኩል የፕሮግራሙን አላማና ዝርዝር ይዘት በሚገባ እንዲጨብጡት ለማድረግ በሌላ በኩል ደግሞ አሰራሮቹን ለመተግበር የሚያስችላቸው ብቃት እንዲኖራቸው ተከታታይና አጫጭር ስልጠናዎችን ማግኘት አለባቸው፡፡ ከዚህም ባሻገር በስራ አፈፃፀም ላይ የሚያጋጥሟቸው ችግሮች እየተጠኑ እነዚህን ለመፍታት የሚያስችል ስልጠና እንዲያገኙ መደረግ ይኖርበታል፡፡ የተደራጀ፣ ጥራቱ የተጠበቀና በእቅድ የሚመራ ሰፊ የስራ ላይ ስልጠና መከናወን ይኖርበታል፡፡

የፍትህ አስተዳደር ስርአቱ ፍርድ ቤቶችን ብቻ የሚመለከት አይደለም፡፡ ለምሳሌ የፖሊስና የአቃቤ ህግ ስራም አብሮ መታየትና መስተካከል ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም ምንም እንኳ እስካሁንም እንዳለው የለውጡ ማዕከል ፍርድ ቤቶች ሆነው መቀጠላቸው ተገቢ ቢሆንም፣ የስራው አድማስ ሁሉንም የፍትህ አስተዳደር አካላት ተዋናዮች የሚሸፍን መሆን አለበት ፡፡ የለውጡ እምብርት ፍርድ ቤቶች በመሆናቸው የዳኝነት ስርአቱ መሪዎች ለውጡን በማቀድና በማስፈፀም ረገድ ግንባር ቀድም ሚና ሊጫወቱ ይገባል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ስራው የህግ አፈፃፀም አካሉን በሰፊው የሚመለከት ስራ ነው፡፡ ሁለቱ ክፍሎች የየራሳቸው ነፃነት እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚሁ የጋራ አላማ በጋራና በቅንጅት መስራታቸው ተገቢና በጣም አስፈላጊም ነው፡፡ እስካሁን ድረስ በፌዴራል ደረጃ በዚህ መልክ እየተሰራ ያለ በመሆኑ ይህ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ይህ አሰራር

በክልሎችም ተግባራዊ መሆን ይገባዋል፡፡

## 7. ማጠቃለያ፣

የአቅም ግንባታ ስራችን የሁሉም የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስራዎቻችን እምብርት በመሆኑ ልዩ ትኩረት ሰጥተን መረባረብ እንዳለብን ይህንኑ ለማስፈፀም ልንከተላቸው የሚገቡን አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡ ስራውን በዋነኛነት ተቋሞች በመፍጠርና በማጠናከር ዙሪያ ለመፈፀም እንዲቻልም የተለያዩ ፕሮግራሞች ተቀርፀዋል፡፡ ፕሮግራሞቹ የመንግስትን፣ የግል ባለሃብቶችን፣ የህዝብ ድርጅቶችንና ማህበራትን ለማጠናከር በሚያስችል አኳኋን የተቀረፁና በመቀረፅ ላይ ያሉ ናቸው፡፡



በዚህ ፅሁፍ ውስጥ የመንግስትን አቅም ለመገንባት ከተቀረፁት ፕሮግራሞች ውስጥ ሶስቱን በምሳሌነት ወስደን ዘርዝረናል፡፡ የግል ባለሃብቱን ለማጠናከር የሚሰሩት ፕሮግራሞችና የህዝብ ማህበራትንና ድርጅቶችን ለማጠናከር የሚሰሩትንም በቀጣይ ፅሁፎች የምንመለስባቸው ይሆናሉ፡፡ ህዝቡና አስፈፃሚ አካላት በዚህ ፅሁፍ ላይ የሰፈሩትን ሃሳቦች መነሻ በማድረግ ያለፈ ስራቸውን ገምግመው ቀጣይ ስራቸውን በዚሁ ቅኝት አጠናክረው እንደሚፈፅሙ ይጠበቃል፡፡